# አምስተኛው የትምህርት ዘርፍ

# ልማት መርሃ-ግብር

2008-2012 ዓ.ም

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት

## የትምህርት ሚኒስቴር

**ማውጫ**


1. **ብሔራዊ የልማት ገጽታ** ........ 12

**መልክዓ- ምድር እና ህዝብ** ........ 12

የፖለቲካ፤ የጤና፤ የግብርናና የኢኮኖሚ ገጽታዎች ........ 12

በትምህርት ዘርፉ ላይ ያሉ ተጽእኖዎች ........ 16

2. **የትምህርት ልማት ገጽታ** ........ 19

**አጠቃላይ ትምህርት** ........ 19

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት (አማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን ጨምሮ) ተደራሽነትና ፍትሃዊነት ........ 20

የጐልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ተደራሽነትና ፍትሃዊነት ........ 25

የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ........ 26

ብሔራዊ የትምህርት ቅበላ ጥናት ........ 28

አራተኛና ስምንተኛ ክፍሎች ........ 28

አስረኛና አስራ ሁለተኛ ክፍሎች ........ 30

የህፃናት እንክብካቤና የትምህርት ጥራት ........ 31

የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥራት (አማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን) ........ 32

ስርዓተ ትምህርት የመማሪያ መፃህፍት እና ምዘናን በተመለከተ ........ 34

የኢንፎርሜሽን ኰምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በተመለከተ ........ 35

የትምህርት ቤቶች መሠረተ ልማት እና ፋሲሊቲዎች ጥራትን በተመለከተ ........ 36

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ........ 37

ተደራሽነትና ፍትሃዊነት ........ 37

ጥራት ........ 39

ምርምር ........ 40

የሥራ ደረጃዎች (OS) ........ 40

ምዘና ........ 41

የተቀናጀ ስልጠና ........................................................................................................................ 41

የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና የቴክኖሎጂ ሽግግር አገልግሎቶች ................................................................ 42

ከፍተኛ ትምህርት ...................................................................................................................... 42

ጥራት .......................................................................................................................................... 44

ምርምር ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የማህበረሰብ አገልግሎት .............................................................. 45

ዖታና ትምህርት ........................................................................................................................ 46

የልዩ ፍላጐትና አካቶ ትምህርት ................................................................................................. 48

ቅድሚያ የተሰጣቸው ፐሮግራሞች መርሃ ግብሮች ...................................................................... 76

መግቢያ ....................................................................................................................................... 77

ንኡስ ተግባር 1፡- የትምህርት ዘርፉን መዋቅር ማሻሻል ................................................................. 79

ንኡስ ተግባር 2፡- በሁሉም አካላት ትኩረት ጉዳዮች (Cross-cutting issues) መርሃ ግብሮችን ትግበራ መምራት ........................................................................................................................................ 79

ንዑስ ተግባር 2፡- የፋይናንስ መረጃ የመሰብሰብና የመተንተን ሂደት ................................................ 84

ንዑስ ተግባር 3፡- በመረጃ የተደገፈ ውሣኔ መስጠት ...................................................................... 84

ንኡስ ተግባር 2፡- የመረጃ አያያዝ ማዕከላትንና የመረጃ ልውውጥ አጠቃቀም ማሻሻል ....................... 89

ንኡስ ተግባር 1፡ የተቀጣሪዎች መረጃና ቅጥር ............................................................................... 91

ንኡስ ተግባር 2፡ የሙያ ላይ እድገት ምክር ስልጠናና የሥራ ላይ እገዛ .......................................... 92

6. ቅድሚያ የተሰጠው ፕሮግራም፡- አጠቃላይ የትምህርት ጥራት ..................................................... 95

መግቢያ ....................................................................................................................................... 95

ቅድመ ሥራ ስልጠና .................................................................................................................. 102

ንኡስ ተግባር 3. የአመራሮች ስልጠናና ሙያዊ ልማት ................................................................ 107

ንኡስ ተግባር 1፡ የስርዓተ -ትምህርት ቀረፃ ................................................................................ 114

ንኡስ ተግባር 2፡ የመማር ማስተማር ቁሳቁስ አቅርቦት ................................................................. 116

ንኡስ ተግባር 1፡ የማህበረሰብ ተሳትፎ ......................................................................................... 120

ንኡስ ተግባር 2፡- የትምህርት ቤት አካባቢ ................................................................................... 122

ንኡስ ተግባር 3፡ መማር ማስተማር ........ 123

ንኡስ ተግባር 4፡ የትምህርት ቤት አመራር ........ 125

ንኡስ ተግባር 1፡ የአይሲቲ መሠረተ ልማት ለመማር ማስተማር ........ 129

ንኡስ ተግባር 2፡ ለአይሲቲ የሚሆን የትምህርት ይዘት ዝግጅት ........ 130

ንኡስ ተግባር 1፡ የትምህርት ቤት ክትትል/ ቁጥጥር ........ 132

ንኡስ ተግባር 2፡ የመምህርና የትምህርት አመራር ሙያ ፈቃድ ........ 134

ንኡስ ተግባር 3፡ ምዘናዎችና ፈተናዎች ........ 135

7. ቅድሚያ የተሰጠው ፕሮግራም፡- የጠቅላላ ትምህርት ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት ፣ ውስጣዊ ውጤታማነት ........ 139

መግቢያ ........ 139

8. ቅድሚያ የተሰጠው መርሃግብር፡- የጎልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት ........ 157

መግቢያ ........ 157

ንኡስ ተግባር 1. ውጤታማ የሴቶችና ጎልማሶች ትምህርት መንደፍና መተግበር ........ 161

ንኡስ ተግባር 2፡ ከማህበረሰቡ ጋር በመሆን የድህረ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራሞችን መቅረጽና መተግበር ........ 162

ንኡስ ተግባር 1፡ የዘርፎችን የባለቤትነት መንፈስ ማሳደግ ........ 180

ንኡስ ተግባር 2፡- ተደራሽ የሆነ ፣ ጥራት ያለው ምዘና የማረጋገጥ አገልግሎት አሰጣጥን በመፍጠር የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥን ማሻሻል ........ 181

ንኡስ ተግባር 1፡- አቅማቸው የጎለበተ የኢንዱስትና የተቋማት አሰልጣኞች፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና አመራሮችና የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ........ 185

ንኡስ ተግባር 2፡- የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማትን በወረዳዎች በማስፋፋት ተደራሽነታቸውን ማሳደግ ........ 188

ንኡስ ተግባር 3፡-ብቃት ያላቸው የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ምሩቃንን ማፍራት ........ 189

ንኡስ ተግባር 4፡- የማኑፋክቸሪንግ ምርታማነትና ጥራት ለማሳደግ የብረታ ብረት ስራ አቅምን መገንባት ........ 191

10. ቅድሚያ የተሰጠው መርሃግብር፡- የከፍተኛ ትምህርት ........ 197

መግቢያ ........ 197

ንዑስ ተግባር 1፡ ተቋማዊ ትብብር ........ 212
ንኡስ ተግባር 2፡ አመራርና አስተዳደር ........ 213
11. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን /cross-cutting issues/ በተመለከተ የቀረበ ማጠቃለያ ........ 216
ሥርዓተ ጾታ ........ 216
የልዩ ፍላጎትና አካቶ ትምህርት ........ 216
ኤችአይቪ ኤድስ ........ 217
ተግባር 4፡ የመረጃና የግንኙነት ቴክኖሎጂ ........ 217
ጎልማሶች ........ 217
ተግባር 2፡ በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት የሴቶችን ተሳትፎ ማሻሻል ........ 217
የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ........ 217
ተግባር 2፡ የሰልጣኞች ዕድገትና ተቋማዊ አቅም ግንባታ ........ 217
ከፍተኛ ትምህርት ........ 218
ተግባር 5፡ ተቋማዊ ትብብር፣አመራርና አስተዳደር ........ 218
ትምህርት በአደጋ ጊዜ ........ 218
ተግባር 1፡ የመምህራንና የአመራሮች ልማት ........ 218
ተግባር 2፡ ሥርዓተ ትምህርት፣የመማሪያና ማስተማሪያ ቁሳቁሶች ........ 218
የአጠቃላይ ትምህርት ተደራሽነት ........ 218
ተግባር 2፤ አንደኛ ደረጃ ........ 218
ተግባር 3፡ ሁለተኛ ደረጃ ........ 219
የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ........ 219
የተመጣጠነ ምግብ በትምህርት ቤት ........ 219
ተግባር 3፡ የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ ግብር ........ 219
ተግባር 4፡ የመረጃና የግንኙነት ቴክኖሎጂ ........ 219
የአጠቃላይ ትምህርት አቅርቦት ........ 219
ተግባር 1፡ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ........ 219

ተግባር 2፡ አንደኛ ደረጃ......220

ጎልማሶች......220

ተግባር 2፡ በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርትና በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት መርሃ ግብር የሴቶችን ተሳትፎ ማሻሻል፣......220

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና......220

ተግባር 5፡ ተቋማዊ ትብብር፣ አመራርና አስተዳደር......220

ከፍተኛ ትምህርት......220

ተግባር 5፡ ተቋማዊ ትብብር፣ አመራርና አስተዳደር......220

የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት......221

ተግባር 3፡ የትምህርት ጥራት ማሻሻል መርሃ ግብር......221

ተግባር 4፡ የመረጃና የግንኙነት ቴክኖሎጂ......221

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና......221

ከፍተኛ ትምህርት......222

ተግባር 5 ተቋማዊ ትብብር፣ አመራርና አስተዳደር......222

ውሃ፣ ንጽህናና ጤና......222

ተግባር 2፡ ሥርዓተ ትምህርት፣ የመማርና ማስተማር መሣሪያዎች......222

ተግባር 3፡ የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ ግብር......222

ተግባር 4፡ የመረጃና የግንኙነት ቴክኖሎጂ......222

የአጠቃላይ ትምህርት ተደራሽነት......222

ተግባር 1፡ ቅድመ መደበኛ......222

ተግባር 2፡ አንደኛ ደረጃ......223

ተግባር 3፡ ሁለተኛ ደረጃ......223

12. ትግበራ ፣ ክትትልና ግምገማ......225

ጠቅለላ የአሰራር ማእቀፍ......225

የትግበራ መዋቅሮችና ሂደቶች......226

የክልል አመራር ቡድኖች ........ 229

የየክፍሉ የስራ ስትራቴጂክ እቅዶች፣ አመታዊ የአፈፃፀም እቅዶችና ቢ.ኤስ.ሲ(BSC) ........ 229

የክትትል፣ ዳሰሳና ግምገማ ሂደት ........ 230

በማእከልና በየደረጃው የሚከናወኑ የየእለት ክትትሎች ........ 233

የጣምራ ምልከታ ተልዕኮና  የአመታዊ ምልከታ ስብሰባዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር ........ 236

የአጋማሽ ወቅትና የመጨረሻ ግምገማ ........ 236

ዋና ዋና የአፈፃፀም አመላካቾች (key performance Indicators) ........ 238

የትምህርት ፋይናንስ ዳሰሳ ........ 248

ዋጋን ለመተመን የወጡ መስፈርቶች ........ 250

ለቅበላና ውስጣዊ ብቃት ........ 250

**በሀብት አጠቃቀም ታሳቢ የተደረጉ መለኪያዎች** ........ 251

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር የሚኖሩት ቀጣይ የትምህርት ማስፋፊያና ማሻሻያ ሥራዎች ወጪ በቀጣይነት በሥራ ላይ የምናውለው የሰው ሀብትና የቁሳቁስ ሀብት ደረጃን መሠረት ያደረገ ሲሆን ዋና ዋናዎቹም ከዚህ በታች ተመልክተዋል፡፡ ........ 251

**ሠንጠረዥ 21፡ ወጭን ለማቀድ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ልኬታዎች** ........ 252

**ደረጃ** ........ 252

**ልኬታ** ........ 252

የቅድመ መጀመሪያ ትምህርት ........ 252

የተማሪዎች ብዛት (በየክፍሉ) ........ 252

50 ........ 252

**የአንደኛ ደረጃ ትምህርት** ........ 252

**የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት** ........ 252

**የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት** ........ 253

**ቴክኒክና ሙያ ትምህርት** ........ 253

**ለወጭ ታሣቢ የተደረጉ** ........ 254

የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር ጠቅላላ ወጭ ........ 254

የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር ፋይናንስ ........ 258

የመንግሥት በጀትና የፋይናንስ ክፍተት ........ 258

ሠንጠረዥ 1፡ አህጽሮተ ቃላትና አቻ የአማርኛ ትርጉሞች

ሠንጠረዥ 2፡  የኢትዮጵያ ትምህርትና ስልጠና ስርዓት አወቃቀር[1]

ሠንጠረዥ 3፡ የክልሎች ቅድመ አንደኛ ደረጃና /ኪንደርጋርተን ጥቅል የቅበላ ድርሻ -2006 በመቶኛ
ሠንጠረዥ 4፡ ንጥር የአንደኛ ክፍል ቅበላ ( በፆታ በመቶኛ (2006)

ሠንጠረዥ 5፡ በ2006 ዓ.ም የነበረው ንጥር እና ጥቅል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቅበላ

ሠንጠረዥ 6፡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዘጠነኛና አስረኛ ክፍል ጥቅል የተማሪዎቹ ቅበላ፣ ከ2002-2006 (በመቶኛ)

ሠንጠረዥ 7፡ በሰባት ቋንቋዎች የአቀላጥፎ ማንበብ ደረጃዎች ፣ ሁለተኛ ክፍል (በመቶኛ)

ሠንጠረዥ 8፡ የብሄራዊ የመማር ዳሰሳ ውጤት ከአራተኛው የትምህርት ልማት እቅድ አንፃር (በመቶኛ)

ሠንጠረዥ 9፡ በአራተኛ ክፍል ብሄራዊ የትምህርት ዳሰሳ በትምህርት ዓይነቶች የታዩ  አቀላጥፎ 2000 እና 2004 ሲነፃፀሩ (በመቶኛ)

ሠንጠረዥ 10፡  በስምንተኛ ክፍል ትምህርት ዳሰሳ በትምህርት ዓይነቶች የታዩ  አቀላጥፎ 2000 ዓ.ም እና 2004 ዓ.ም ሲነጻጸሩ (በመቶኛ)

ሠንጠረዥ 11፡ የትምህርት ቤቶች የሚገኙበት ደረጃ

ሠንጠረዥ 12፡ ለ5ኛው የትምህርት ዘርፍ የልማት መርሀ ግብር ቁልፍ የትግበራ አመልካቾች (በአስፈላጊው ቦታ ግቦች ሴት/ወንድ በሚል ተገልጸዋል፣ ሁሉም በመቶኛ ተገልጸዋል ካልተብራሩ በቀር)

ሠንጠረዥ 13 ፡ የ5ኛው የትምህርት ዘርፍ የልማት መርሃ ግብር የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ቅንጅት

ሠንጠረዥ14፡- ለአጠቃላይ ትምህርት ጥራት መሻሻል አስተዋጽኦ ያላቸው ዘርፎች መዋቅር

ሠንጠረዥ 16፡- በልዩ የድጋፍ ፕሮግራም የተለዩ ሦስቱ የአቅም ግንባታ ትኩረቶች

ሠንጠረዥ 18፡ አምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብርን የየወሩ የሥራ ዕቅድ ኃላፊ ድረስ ማውረድ
ሠንጠረዥ 19፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር የክትትልና ትግበራ መርሐግብር
ሠንጠረዥ 20፡ የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር የዋና ዋና አፈፃፀም አመልካቾች (KPI) (እንደአስፈላጊነቱ በፆታ ተለይተዋል)
ሠንጠረዥ 21፡ ወጭን ለማቀድ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ልኬታዎች

ሠንጠረዥ 22፡ የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር አጠቃላይ ወጭ (በሚሊዮን ብር)
ሠንጠረዥ 23፡ የ5ኛ የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር አጠቃላይ ወጭ በንዑስ ሴክተር በአመት እና በፕሮግራሙ ቆይታ (በሚልዮን ብር)
ሠንጠረዥ 24፡ በ5ኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር የየንዑስ ሴክተር ድርሻ (በዓመት)
በሠንጠረዥ 25፡ የየአመቱ የአጠቃላይ ትምህርት ድርሻና የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃግብር ድርሻ
ሠንጠረዥ 26፡ በዕቅድ ዘመን የካፒታልና መደበኛ በጀት (በየደረጃው በመቶኛ)
ሠንጠረዥ 27፡ በእያንዳንዱ የፕሮግራም አመት ሊኖር የሚችለው የፋይናንስ ክፍተት (በሚሊዮን )
ሠንጠረዥ 28፡ የአምስተኛው ትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር ፋይናንስ ክፍተት (በሚሊዮን ብር እና በመቶኛ)

*ሠንጠረዥ 1፡ አህጽሮተ ቃላትና አቻ የአማርኛ ትርጉሞች*

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ABE** | Alternative Basic Education<br>አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት | **IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት)** | Integrated Functional Adult Education<br>የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጐልማሶች ትምህርት |
| **ANFE** | Adult and Non-Formal Education<br>የጐልማሶች እና ኢ-መደበኛ ትምህርት | **IFMIS** | Integrated Financial Management Information System<br>የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደርና መረጃ ስርዓት |
| **BPR** | Business Process Reengineering<br>የሥራ ሂደት ለውጥ | **KG** | Kindergarten<br>መዋዕለ ህፃናት |
| **BSC** | Balanced Scorecard<br>ባላንስድ ስኰር ካርድ | **KPI** | Key Performance Indicator<br>ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካች |
| **CEICT** | Centre for Educational Information and Communication Technology<br>የትምህርት መረጃና ኰሚዩኒኬሽን ማዕከል | **MoE** | Ministry of Education<br>ትምህርት ሚኒስቴር |
| **CLC** | Community Learning Centre<br>የማህበረሰብ ትምህርት ማዕከል | **MoFED** | Ministry of Finance and Economic Development<br>የገንዘብና ኢኰኖሚ ልማት ሚኒስቴር |
| **CPD** | Continuous Professional Development<br>ተከታታይ የሙያ እድገት | **MSE** | Micro and Small Enterprises<br>መካከለኛና ዝቅተኛ ኢንተርፕራይዞች |
| **CTE** | College of Teacher Education<br>የመምህራን ትምህርት ኰሌጅ | **NEAEA** | National Educational Assessment and Examinations Agency<br>ብሔራዊ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ |
| **DSA** | Drug and Substance Abuse<br>አደገኛ መድሃኒቶችና እጾች | **NER** | Net Enrolment Rate<br>ንጥር የቅበላ ብዛት |
| **ECCE** | Early Childhood Care and Education<br>የህፃናት እንክብካቤና ትምህርት | **NGO** | Non-Governmental Organisation<br>መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት |
| **EGMA** | Early Grade Mathematics Assessment<br>የዝቅተኛ ክፍሎች የሂሣብ ትምህርት ዳሰሳ | **NIR** | Net Intake Ratio<br>ንጥር የቅበላ ድርሻ |
| **EGRA** | Early Grade Reading Assessment<br>የዝቅተኛ ክፍሎች የንባብ ክህሎት ዳሰሳ | **NLA** | National Learning Assessment<br>ብሔራዊ የትምህርት ቅበላ ጥናት |
| **EMIS** | Education Management Information System<br>የትምህርት አስተዳደር መረጃ ስርዓት | **OS** | Occupational Standards<br>የሥራ ደረጃዎች |
| **ESDP** | Education Sector Development Programme<br>የትምህርት ዘርፍ የልማት ፕሮግራም | **PSTA** | Parent, Student and Teacher Association<br>የወላጆች ተማሪዎችና መምህራን ህብረት |
| **ETWG** | Education Technical Working Group<br>የትምህርት ቴክኒካል የሥራ ቡድን | **REB** | Regional Education Bureau<br>የክልል ትምህርት ቢሮ |
| **GDP** | Gross Domestic Product<br>አጠቃለይ የምርት መጠን | **SIP** | School Improvement Programme<br>የትምህርት ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራም |
| **GEQIP** | General Education Quality Improvement Programme<br>የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም | **SMIS** | School Management Information System<br>የትምህርት ቤቶች አስተዳደር መረጃ ስርዓት |
| **GER** | Gross Enrolment Rate<br>ጥቅል የቅበላ ብዛት | **SNE** | Special Needs Education<br>የልዩ ፍላጐት ትምህርት |
| **GIS** | Geographical Information System<br>ጂኦግራፊያዊ የመረጃ ስርዓት | **TMIS** | Teacher Management Information System<br>የመምህራን አስተዳደር መረጃ ስርዓት |
| **GPI** | Gender Parity Index<br>የፃታ እኩልነት መለኪያ | **TVET** | Technical and Vocational Education and Training<br>የቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና |
| **HIV/AIDS** | Human Immunodeficiency Virus infection and Acquired Immune Deficiency Syndrome<br>ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ | **WASH** | Water, Sanitation and Hygiene<br>ውሃ፣ የአካባቢ ንጽህናና ጤና አጠባበቅ |
| **ICT** | Information and Communications Technology<br>ኢንፎርሜሽንና ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ | **WHO** | World Health Organisation<br>የአለም ጤና ድርጅት |

# የልማት

# ገጽታዎች

## 1. ብሔራዊ የልማት ገጽታ

### መልክዓ- ምድር እና ህዝብ

ኢትዮጵያ ከ95 ሚሊየን በላይ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችና የቋንቋ ተናጋሪዎች የሚኖሩባት ትልቅና ብዝሃነት ያላት ሀገር ነች፡፡ የሃገሪቱ አጠቃላይ የመሬት ስፋት 1.1 ሚሊዮን ስኩየር ኪ.ሜ ሲሆን፣ በአማካይ በአንድ ስኩየር ኪ.ሜ 86 ሰው ይኖራል፡፡ ከጠቅላላው ህዝብ አራት አምስተኛው በተራራማ ቦታዎችና በወይና ደጋና በደጋማ አካባቢዎች የሰፈረ ነው፡፡ ቀሪው አንድ አምስተኛ ህዝብ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ሲሆን ከአገሪቱ ጠቅላላ ስፋት 60 በመቶ በሚሸፍነው ቆላማ አካባቢ የሰፈረ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም ዝቅተኛ የከተማ እድገት ካላቸው አገሮች አንዷ ስትሆን በከተማ የሚኖረው ህዝቧ 19 በመቶ ይሆናል ተብሎ ይገመታል፡፡ የከተማ እድገት ደረጃቸው ከ20 በመቶ በታች ከሆኑት ከዓለም አስራ ስድስቱ አገራት አንዷ ስትሆን ከነዚህ አገሮች ሲነፃፀር የህዝቧ ብዛት በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ አጠቃላይ የህዝብ እድገቱ በየዓመቱ 2.6 በመቶ እየጨመረ በመሄድ ላይ ሲሆን የከተማ ህዝብ ብዛትም በዓመት 4.4 በመቶ በማደግ ላይ ይገኛል፡፡ ስለሆነም በ2050 በከተማ የሚኖረው የህዝብ ብዛት እጥፍ ይሆናል ተብሎ ይገመታል፡፡ (ይህም ከ190 ሚሊየን ጠቅላላ የህዝብ ብዛት፣ 70 ሚሊዩኑ የከተማ ነዋሪ ይሆናል ማለት ነው)፡፡

የህዝብ ብዛትና የከተሞች እድገት በፍጥነት መጨመር፣ ከጠቅላላ የህዝቡ ብዛት 44 በመቶ ከ14 ዓመት ዕድሜ በታች መሆን 53 ከመቶው ደግሞ በ15 እና 65 ዓመት ዕድሜ መካከል መሆኑ በኢትዮጵያ ሊመጣ የሚችለው የማህበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥና እድገት አመላካች ነው፡፡

### የፖለቲካ፤ የጤና፤ የግብርናና የኢኮኖሚ ገጽታዎች

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ የመንግሥት አወቃቀር ስርአት የምትከተል ሲሆን ዘጠኝ የክልላዊ ብሄራዊ መንግሥታት (አፋር፣ አማራ፣ ቤንሻንጉል -ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ሃረሪ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሊያ፣ ደቡብ ብሄር

ብሄረሰቦችና ህዝቦች እና ትግራይ) እና ሁለት የከተማ አስተዳደሮች (አዲስ አበባ እና ድሬዳዋ) ይገኙባታል፡፡ ሃገሪቱ በጣም ከተማከለና ዲሞክራሲያዊ ካልሆነ የመንግሥት አስተዳደር በመላቀቅ ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) አመራር ዲሞክራሲያዊ ወደሆነ ስር- ነቀል ስርዓት ተሸጋግራለች፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሃገሪቱ አምስት ምርጫዎች የተካሄዱ ሲሆን፣ ያልተማከለ አስተዳደር በመፍጠር በበጀትና በተለያዩ ጉዳዩች ላይ የመወሰን ስልጣን ለክልሎች እንዲተላለፉ ተደርገዋል፡፡

ኢትዮጵያ በ2017 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ያላት ሀገር የመሆን ራዕይ ይዛ በመስራት ላይ ትገኛለች፡፡ ይህን ራዕይ ለማሳካት የሚያስችል የማክሮ-ኢኮኖሚ ፓሊሲ በማውጣት መሰረተ ልማት ለማስፋፋት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ተመድቧል፡፡ ከ1996 እስከ 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በተከታታይ በአማካይ 10 በመቶ የኢኮኖሚ እድገት ያስመዘገበች ሲሆን  በወቅቱ በአካባቢው ሀገሮች የነበረው እድገት 5 በመቶ ብቻ ነበር፡፡

አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ኑሮው የተመሰረተው በግብርና ሲሆን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን፤ አገልግሎት ሰጪዎችና ኢንዱስትሪዎች በኢኮኖሚው ያላቸው ድርሻ እየጨመረ  በመሄድ ላይ ይገኛል፡፡ ለምሣሌ፣ በ2005 ዓ.ም በነበረው እድገት የኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ዘርፍ 46 በመቶ፤ግብርና 40 በመቶ፤ ኢንዱስትሪ  ደግሞ 16 በመቶ ድርሻ የነበራቸው ሲሆን ቀደም ባለው አመት የነበራቸው ድርሻ ግን በአንጻሩ  45 በመቶ፤ 43 በመቶ እና 12 በመቶ ነበር፡፡ በኢንዱስትሪው ሴክተር የነበረው ዓመታዊ እድገት ከፍተኛ ሲሆን (21በመቶ) ለዚህ ዋናው ምክንያቱ የኮንስትራክሽን ዘርፉ እንቅስቃሴ ማደግ ነበር፡፡

በኢኮኖሚው ዘርፍ  እየታየ ያለው አድገት በትምህርትና ሥልጠና ላይ የራሱ የሆነ ግልጽ ተጽእኖ የነበረው ቢሆንም ለግብርና የተሰጠው ትኩረት ይቀንስዋል ማለት አይደለም፡፡  የኢንዱስትሪውና የአገልግሎት ዘርፎች በኢኮኖሚው ላይ ያላቸው ድርሻ እያደገ መሄድም ሆነ እነዚሁ ዘርፎች በአዲስ የአመራረት  ዘዴ የበለጠ ድርሻ እንዲኖራቸው ያለው ፍላጐት እንዳለ ሆኖ ፣ ለህብረተሰቡ ህልውና

ካለው አስተዋጽኦ አንፃር ግብርና በሁለተኛው የአድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ቅድሚያ ትኩረት እንደያዘ ይቆያል፡፡

በተከታታይ  የተካሄደው የኢኮኖሚ እድገት በከተሞችና በገጠር ድህነትን የመቀነሱ ሂደት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በ1997 ዓ.ም በብሔራዊ ደረጃ 39 በመቶ የነበረው ድህነት በ5 ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ 30 በመቶ ዝቅ እንዲል ተደርጓል፡፡ ይህ ስኬት ሊመዘገብ የቻለው የኤክስቴንሽን፤ የሴፍቲኔትና ሌሎች ደሀ-ተኮር ፕሮግራሞችን በመንደፍ ዝቅተኛው ገበሬ ተጠቃሚ እንዲሆን በመደረጉ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የህፃናትን ሞት በመቀነስ የሚሊኒየሙ የልማት ግብ /MDG/ እንዲሳካ አድርጋለች፡፡ የውሃ አቅርቦት የውሃ አቅርቦት ከሚያስፈልገው ህዝብ ግማሹ ያህል ውሃ እንዲያገኝ ተደርጓል፡፡ በነዚህና በሌሎች የሚሊነየሙ የልማት ግቦች መሻሻል ምክንያት በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያውያን በህይወት የሚቆይበት አማካይ እድሜ 65 ዓመት ይሆናል ተብሎ የሚገመት ሲሆን፣ ይህም በ2001 ዓ.ም ከነበረው 60 ዓመትና በፈረንጆቹ የሚሊኒየም መጀመርያ ከነበረው 52 ዓመት ጋር ሲነፃፀር ልዩነቱ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ሌሎች በርካታ አገሮች በተሻለ ፣ በተለይም በማህበራዊ እድገት፣ በትምህርትና በጤና ረገድ የተሻለ ውጤት አስመዝግባለች፡፡

**ብሄራዊ የልማት ፖሊሲ**

ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ኢትዮጵያ የድህነት ቅነሳን ለማፋጠን የሚያስችሉ የተለያዩ የማክሮ-ኢኮኖሚ ልማት ፕሮግራሞች ያከናወነች ሲሆን፡፡ አሁንም አራተኛውን ምዕራፍ ለማካሄድ ዝግጅት አድርጋለች፡፡ የነዚህ ፕሮግራሞችና ብሔራዊ ስትራቴጂዎች ዋና ዋና ዓላማ ያደረጉት ለልማት ተፈላጊ የሰው ኃይል ልማት እንዲኖር ማድረግ፣ የሚሊኒየሙን ልማት ግቦችን በተቀናጀ መንገድ በቀጣይነት እንዲካሄዱ በማድረግ ኢትዮጵያ በ2017 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ያላት አገር እንድትሆን ማስቻል ናቸው፡፡ ብሄራዊ የልማት እቅዶቹ በአጭሩ ከታች ቀርበዋል፡፡

| ዓመት | የተካሄደው የአቅድ ዓይነት | ጭብጦች |
|---|---|---|
| 1988 እስከ 1998 | ዘለቄታዊ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም | ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥታትን እና መዋቅራቸውን መመስረትና ማጠናከር |
| | | ማዕከላዊ መንግሥትን ወደ ክልሎች ማስፋፋት |
| | | የነፃ ኢኮኖሚ ስርዓት መመስረትና ማስፋፋት |
| | | ማህበራዊ ዘርፎችን ማሳደግ |
| 1998 እስከ 2003 | ድህነትን ለማጥፋት የተፋጠነና ቀጣይነት ያለው የልማት እቅድ | ድሃ ተኮር እድገት እንዲኖር ማድረግ |
| | | ድህነት ቅነሳ |
| | | መንግሥትንና አስተዳደር የሚጠናከር ስራ |
| | | እርዳታን በአግባብ ማስተዳደር |
| 2003-2007 | የመጀመርያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ | የኢኮኖሚ እድገት |
| | | የኢንዱስትሪ ልማት |
| | | መሠረተ ልማትን ማስፋፋት |
| | | የሚሊኒየም ዴቨሎፕመንት ግቦችን ማሳካት |
| 2007-2012 | ሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ | የኢኮኖሚ ማሳደግና የኢኮኖሚ ዘርፍ አማራጮችን ማስፋፋት |
| | | ኢንዱስትሪና ሜካናይዘሽን እንዲስፋፋ ማድረግ |
| | | የተሻሻለ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት እንዲኖር ማድረግ |
| | | ተከታታይ የልማት ግቦችን ማሳካት |

**በትምህርት ዘርፉ ላይ ያሉ ተጽእኖዎች**


አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ በተበታተነ ሁኔታ በገጠር መኖሩ በትምህርት ዘርፉ ላይ አንዳንድ ተግዳሮቶችን ፈጥሯል። ይህ አኗኗር ከአገሪቱ መልክዐ- ምድራዊ አቀማመጥ ጋር ተደምሮ ትምህርትን ለማስፋፋት እና ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ የሚደረጉትን እንቅስቃሴዎች አስቸጋሪ ያደርጋቸዋል። በተጨማሪ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች በተበታተነ ሁኔታ የመኖራቸው ሁኔታ የትምህርት ቤቶችን አደረጃጀትና የሥርዓተ ትምህርቱ አግባብነት አስቸጋሪ ያደርገዋል። በአገሪቱ ያለው የህዝብ ብዛትና ተያይዘው የሚመጡት የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ሌሎች ጫናዎች በተለይ ጥራት ላለው የትምህርት አቅርቦት ያለውን ፍላጐት ያሳድጉታል። መንግሥት የተመጣጠነ የትምህርት አቅርቦት ስርጭት ላይ አስፈላጊውን ትኩረት ካደረገ የህዝብ ብዛት መጨመር ለልማት የተመቻቸ ሁኔታን ይፈጥራል።

ኢትዮጵያ መካከለኛ ገቢ ያላት አገር የተያዘው ረጅም ራዕይ እውን መሠረታዊ የሃብት መፍጠርያ ስልቶች ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና የፈጠራ ችሎታ ሆነው ተወስደዋል። እያደር የኢንዱስትሪውና የማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች በኢኮኖሚው ላይ ያላቸው ድርሻ እየጨመረ ሲሄድ መካከለኛና ከፍተኛ ክህሎት ያለው የሰው ሃይል እንዲኖር ያስፈልጋል።

ከዚህ በተጨማሪ ይህን ራዕይ ለማሳካት ይቻል ዘንድ ጥራት ያለው መሠረታዊ ትምህርትን ማስፋፋትና በአጠቃላይ የህብረተሰቡን የማንበብና የመፃፍ ለማሻሻል ልዩ ጥረት መደረግ አለበት። በየወቅቱ ስልጠና በመስጠትና የዳበረ የሰው ኃይል እንዲኖር የትምህርትና የስልጠና ፕሮግራሞችን በየጊዜው በማሻሻል በተለያዩ የምርት ሥራዎች ሊሰማራ የሚችል የሰው ኃይል እንዲኖር ጥረት መደረግ ይኖርበታል።

የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት እቅድ የተዘጋጀው በዚህ ራዕይ በመመስረት ነው ማለትም፣ አጠቃላይ ትምህርትን ፍትሀዊ በሆነ መልኩ በጥራት የማዳረሱ ሂደት በተጀመረው ፍጥነት ማስቀጠል፤ በሁሉም ወረዳዎች የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ማሠልጠኛ (TVET) ተቋማትን መክፈት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ማጠናከርና በማንኛውም የአድሜ ደረጃ ውስጥ ያለ ኢትዮጵያዊ እንዲማር እድል መፍጠር። እነዚህን ግቦች ለማሳካት መንግሥት ለትምህርትና ስልጠና ባለው ቁርጠኝነት በመታገዝና፣ የትምህርት ዘርፍ ግቦቹ የተሳኩ እንዲሆኑ የሚያስችለውን አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ከፍተኛ ርብርብ የሚያስፈልገው አምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት እቅድ ተዘጋጅቷል።

## ሠንጠረዥ 2፡ የኢትዮጵያ ትምህርትና ስልጠና ስርዓት አወቃቀር[2]




ማስታወሻ፡በአቻ ግመታ መመርያ ከጐልማሶች ኢ-መደበኛ ትምህርት ወደ መደበኛ ትምህርት ቴክኒክና ሙያ መወዘዋወር

[1]ቴክ/ሙ/ማ ማለት ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማለት ነው፡፡

ይቻላል፡፡

## 2. የትምህርት ልማት ገጽታ

### አጠቃላይ ትምህርት

በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ሁለት ዋና ግቦች ተለይተው ነበር፡፡ የመጀመሪያው ግብ፣ ጥራት ያለው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነትን በማሻሻል ህፃናት ወጣቶችና ጐልማሶች በኢትዮጵያ ልማት ሙሉ ለሙሉ ተሳታፊ ሊሆኑ የሚያስችላቸውን ብቃት፣ ክህሎትና ሥነ-ምግባር እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡ ሁለተኛው ግብ ጥራት ያለው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፍትሃዊ ተደራሽነትን በማስቀጠል ኢኮኖሚው የሚፈልገው በመካከለኛና ከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡

በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር እያንዳንዱ ንዑስ ዘርፍ የራሱ የሆኑ የቅድሚያ የትኩረት አቅጣጫዎችና ግቦች ነበሩት፡፡ በእቅዱ ዘመን የነበሩት ክንውኖች እንደሚከተለው ተገልጸዋል፡፡[2]

### የአጠቃላይ ትምህርት ተደራሽነትና ፍትሃዊነት

### የህፃናት አንክብካቤና ትምህርት ተደራሽነትና ፍትሃዊነት


በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር የመጀመሪያው ዓመት መንግሥት ስትራቴጂካዊ የሆኑ የትግበራ ዕቅድና መመሪያዎችን አወጣ፡፡ ስትራተጂው የግል ኢንቨስተሮች፣ የእምነት ተቋማትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በህፃናት እንክብካቤና ትምህርት መስክ አንዲሰማሩ ያበረታታ ነበር፡፡ በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም የመጨረሻ ዓመታት መንግሥት ለህፃናት እንክብካቤና ትምህርት ቅድሚያ በመስጠት በብሄራዊ ደረጃ የአመራር ኮሚቴ፣ በክልሎች ደረጃ ቡድኖችን እንደዚሁም በወረዳ ደረጃ የቴክኒክ ኰሚቴዎችን በማቋቋም ህፃናት አንደኛ ክፍል ከመግባታቸው በፊት መዘጋጃ እንዲሆን የ0(ኦ) ክላሶችን በማስፋፋት ፈጣን የተደራሽነት ሁኔታ አንዲፈጠር አድርጓል፡፡ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለ ድርሻዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ አወቃቀሩ ከሌሎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ጋር በመተባበርና በመረዳዳት የተከናወነ ነው፡፡ በዚህም የህፃናት እንክብካቤና ትምህርት በአፋጣኝ እንዲስፋፋ መሠረት ተጥሏል፡፡

*[2]ክንውኖች በሌላ ጊዜ የተፈፀሙ ከሆነ፣ ይሄው ይገለፃል፡፡ ካልሆነ ግን ሁሉም ክንውኖች በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት እቅድ*

እነዚህ ጥረቶች በ2005 ዓ.ም የቅድመ አንደኛ ደረጃ አጠቃላይ የቅበላ አሃዝ 34 በመቶ እንዲደርስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ሲሆን ፣ ከነዚህ ውስጥ ሦስት አራተኛው በሦስት ዓመት የአፀደ ህፃናት ትምህርት ቀሪዎቹ ደግሞ በ1 ዓመት የ0 (ኦ) ክላስ የእርስ በእርስ የህፃናት መማማር የተከናወኑ ናቸው። ይሄ አፈፃፀም በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት በእቅድ ተይዞ ከነበረው 20 በመቶ በላይ ነው (ፕላኑ ሲጀምር የነበረው መነሻ 6.9 በመቶ ነበር)።

ህፃናት አንደኛ ክፍል የመግባት እድላቸው እንዲሰፋ የተደረገው እንቅስቃሴ ጥሩ ተሞክሮ የተገኘበት ነው። የህፃናት የ0 ክፍል የርስ-በርስ መማማር ፕሮግራም በየጊዜው ጥራቱ እየተሸሻለ በፈጣን ሁኔታ በመካሄድ ላይ ቢሆንም፣ በከተሞች አካባቢ የአጸደ-ህፃናት ትምህርት የሚከታተሉት ህፃናት የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል።

**ሠንጠረዥ 3፡ የክልሎች ቅድመ አንደኛ ደረጃና /ኪንደርጋርተን ጥቅል የቅበላ ድርሻ -2006 በመቶኛ**





### የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት (አማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን ጨምሮ) ተደራሽነትና ፍትሃዊነት

"ትምህርት ለሁሉም" የሚለውን ግብ ለማሳካት መንግሥት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ተደራሽ ለማድረግ በስፋት እየሠራ ይገኛል። በትምህርት ቤቶችና በተማሪ መኖሪያዎች ያለውን ርቀት ለመቀነስ የትምህርት ቤቶች ግንባታ በጥሩ ሁኔታ ተካሂዷል። በ1999 ዓ.ም በወጣው የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ብሄራዊ ስትራተጂ በመመስረትአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ማዕከላት እንዲስፋፉና ወደ

መደበኛ ትምህርት ቤቶች እንዲሸጋገሩ የተደረጉ ሲሆን ተጨማሪ ማዕከላት እንዲመሠረቱም ተደርጓል፡፡ አማራጭ የመሰረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የተለያዩ ፍላጐቶችን ያሳካ ሲሆን፣ ለታዳጊ ክልሎች ከሚደረገው የአቅም ግንባታ ፕሮግራም ጋር ተዳምሮ ቀደም ሲል እድሉ ያልነበራቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በትምህርት እንዲሳተፉ የተሻለ እድል ፈጥሮላቸዋል፡፡

ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ በተደረገው ከፍተኛ ጥረት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቁጥር (የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ማዕከላትን ጨምሮ) ከ11000 ወደ 32048 ያደገ ሲሆን፣ በዚሁ ወቅት 3 ሚሊዮን ይጠጋ የነበረው የተማሪ ቁጥርም ወደ 18 ሚሊዮን አድጓል፡፡ ይህ በጣም ጥሩ የሆነ ስኬት ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ያሉት የትምህርት ቤቶች እድሜአቸው ሰባት ዓመት የሆናቸውን ህፃናት ሙሉ በሙሉ ለማስተናገድ ይችላሉ፡፡ በ2006 ዓ.ም ዕቅድ የነበረው የተጣራ የቅበላ አማካይ አቅም (Net Intake Ratio) 100 ከመቶ ሲሆን አፈጻጸሙ ግን 106 ከመቶ (ማለፍያ 102 በመቶ ለሴቶች 109 በመቶ ለወንዶች ) ነበር፡፡ በእርግጥ ከ100 በመቶ በላይ የሚለው ቅበላ በስሌት ትርጉም የለሽ ቢሆንም፣ ችግሩ የሚሰተው አስቸጋሪ ከሆኑ የህዝብ ብዛት ትመናዎች እንዲሁም የተለያዩ የተማሪዎችና ትምህርት ቤት መግቢያ እድሜዎች ሊሆኑ ይችላል ተብሎ ይገመታል፡፡ (ለምሣሌ ፣ በአንድ ደረጃ ወጥ የሆነ የልደት ምዝገባ አለመኖር)፡፡


**ሠንጠረዥ 4፡ ንጥር የአንደኛ ክፍል ቅበላ ( በፆታ በመቶኛ (2006)**



በትክክለኛ እድሜ (ማለትም በሰባት ዓመት) ተማሪዎች መቀበልን በተመለከተ በክልሎች መካከል ከፍተኛ ልዩነቶች የታዩ ሲሆን፣ ይህም ልዩነት በአማካዩ የተጣራ ቅበላ ከ50-120 በመቶ መካከል ባለው ቁጥር ይገለፃል፡፡

ይህ እመርታዊ የተደራሽነት ስኬት እንዳለ ሆኖ፣ ከፍ ወዳሉ የትምህርት እርከኖች የመዘዋወሩ ሁኔታ ግን የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ትምህርታቸውን ያቋርጣሉ፣ ለዚህም 8ኛ ክፍልን የሚያጠናቅቁ ተማሪዎች ቁጥር 47 በመቶ ብቻ መሆኑ ጥሩ አመላካች ነው፡፡ የመጀመሪያውን ሳይክል (ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል) አጠቃላይ ቅበላ እቅድ 125 በመቶ የነበረ ሲሆን ክንውኑ በወንዶች በኩል ከእቅድ በላይ በሴቶችም ቢሆን ከእቅዱ ብዙ የራቀ አልነበረም፡፡ የተጣራ ብሔራዊ የቅበላ አሃዙ (NER) የጨመረ ከመሆኑ አንፃር ፣ በአሁኑ ወቅት ህፃናት በትክክለኛ እድሜያቸው ትክክለኛ የክፍል ደረጃ መግባታቸውና ከክፍል ክፍል መሸጋገራቸውን የሚያመላክት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ አንደኛ ደረጃ ሁለተኛው ሳይክል ላይ ሲደርስ ግን ለየት ያለ ሁኔታ እናገኛለን፡፡ በ2006 ዓ.ም በሁለተኛው ሳይክል አጠቃላይ ቅበላ 64 በመቶ (63 በመቶ ሴቶች፣ 65 በመቶ ወንዶች) የተጣራ ቅበላ ደግሞ 50 በመቶ (50 በመቶ ሴቶች ፣ 49 በመቶ ወንዶች) ነበር፡፡ ታቅዶ የነበረው ግን አጠቃላይ ቅበላ 100 በመቶ የተጣራ ቅበላ ደግሞ 80 በመቶ ነበር፡፡

**ሠንጠረዥ 5፡ በ2006 ዓ.ም የነበረው ንጥር እና ጥቅል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቅበላ (በ2002 ከነበረው መነሻ አንፃር በመቶ)**




በአንደኛ ደረጃ ትምህርት የሁለተኛው ሳይክል ቅበላ አነስተኛ መሆን ትምህርት የማቋረጥና ክፍል የመድገምን ተግዳሮቶች መሃራቸውን ያመላክታል፡፡ በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት እቅድ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት በሁለቱም ሳይክሎች ተይዞ የነበረው አንድ በመቶ ትምህርት የማቋረጥና አንድ በመቶ ክፍል የመድገም ግቦች ከአቅም በላይ የነበሩ መሆናቸውን ያሳያል የማይቻሉ ነበሩ፡፡

አምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ሲጀምር ክፍል የሚደግሙ ተማሪዎች ቁጥር 8 በመቶ፣ ትምህርት የሚያቋርጡ ደግሞ (ምንም እንኳ በ2006 መሻሻል የታዬ ቢሆንም) አንደኛ ክፍል ላይ 22 በመቶ ከዚያ በላይ ባሉት ክፍሎች ደግሞ 11 በመቶ ነው፡፡ ትምህርት በማቋረጡና ክፍል በመድገሙ አንጻር ቀመር በወንዶችና በሴቶች መካከል ልዩነት አይታይም፡፡

### የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነትና ፍትሃዊነት

ባለፉት 20 ዓመታት ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቅበላ ፈጣን እድገት በማሳዬት በ1986 ዓ.ም የነበረው 371,000 የተማሪዎች ቁጥር በ2006 ዓ.ም አምስት እጥፍ በመጨመር ወደ ሁለት ሚሊዬን ያህል ተጠግቷል፡፡ በዚህ ወቅት የታየ ችግር ቢኖር ተደራሽነቱ በገጠርና በከተማ ተመሣሣይ አለመሆኑና በአብዛኛው በከተሞች ላይ ያተኮረ መሆኑ ነው፡፡ 32,048 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለ 2,333 የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚያሸጋግሩት የተማሪ ቁጥር ከፍ ያለ በመሆኑ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ ተጽእኖ እንዲፈጠር ካደረጉት ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ  ድህነት ፣ የትራንስፖርት ችግር፣ ሥራ ላይ የመሠማራት ፍላጐት (በጊዜ እጥረትና በኢኮኖሚ ችግር ምክንያት)፣ ያለ ዕድሜ ጋብቻ (ያታዊ ተጽእኖ) በትምህርት ቤት አካባቢ መኖሪያ ማጣት (የፋይናንስ ችግር፣ ባህላዊ ተጽእኖና ማህበራዊ ተጽእኖ) እና የአካል ጉዳተኝነት፡፡ እነዚህ የአቅርቦትና የፍላጐት ልዩነቶች በክልሎች መካከል የተለያየ ቅበላ እንዲኖር ተጽእኖ አሳድሯል፡፡ ለምሣሌ ፣ በአፋር ክልል ልዩነቱ ከ10 በመቶ በታች ሲሆን በአዲስ አበባ ከ100 በመቶ በላይ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 6፡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዘጠነኛና አስረኛ ክፍል ጥቅል የተማሪዎቹ ቅበላ፣ ከ2002-2006 (በመቶኛ)




በተለይ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን የሚያጠናቅቁ ተማሪዎች ብዛት ከተጠበቀው በታች መሆኑ (በሲስተሙ ሂደት ምክንያት) የዘጠነኛና አስረኛ ክፍል አጠቃላይ የተማሪዎች ቅበላ ብዙም ሳይቀየር ከነበረበት 39% ተነስቶ 39.3 በመቶ የደረሰ ሲሆን በእቅድ ተይዞ የነበረው ግን 62 በመቶ ነው፡፡ በአንጻሩ በሁለተኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል (11ኛና 12ኛ ክፍል) የታየው የተሻለ ቅበላ ሊኖር የቻለው የዩኒቨርስቲዎች የመቀበል አቅም በመጨመሩ ምክንያት ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ከአስረኛ ወደ አስራ አንደኛ ክፍል በሚሸጋገሩ ተማሪዎች ላየ መነቃቃትን በመፍጠሩ በፖሊሲው ታቅዶ የነበረው 20 በመቶ የቅበላ እድገት (በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም የመጨረሻ ዓመታት) ወደ 30.35 በመቶ ሊያድግ ችሏል፡፡

ጥቅል ቅበላው እንደሚያሳየው ከተመዘገቡት 20 በመቶ የመጀመሪያ ሳይክልና6 በመቶ የሁለተኛ ሳይክል ተማሪዎች መካከል ግማሾቹ የእድሜ ጣሪያቸው ከሚማሩበት የክፍል ደረጃ በላይ ነው፡፡ በፆታ አንጻር ያለው ፍትሃዊነት በከፍተኛ ደረጃ መሻሻልን ያሳዩ ሲሆን፣ በ2002 የነበረው 0.80 ፡ 0.45 የወንድ/ሴት ጥመርታ በ2006 ወደ 0.94 ፡0.85 በማደጉ ሴቶች ተሳታፊነት ጨምሯል፡፡

### የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ተደራሽነትና ፍትሃዊነት

ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ጎልማሶች ማንበብና መፃፍ ስለማይችሉ በተለይም በ2017 ዓ.ም ልንደርስበት ላሰብነው የመካከለኛ ገቢ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ ለመድረስ የአለምነውን ጉዞ ያደናቅፋል። ጎልማሶች ትምህርት ባገኙ ቁጥር ልጆቻቸው ትምህርት የመቀበል ፍላጎታቸው እንዲያድግ ያግዛል፤ ልማትንም ያፋጥናል። እያንዳንዷ እናት አንድ ተጨማሪ ዓመት በተማረች ቁጥር የህፃናት ሞት ይቀንሳል፣ ጤንነታችሁም ይሻሻላል።

በአራተኛው የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም የተተገበረው ብሄራዊ የጎልማሶች ትምህርት ስትራተጂ በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት (IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት)) ላይ ልዩ ትኩረት ያደረገ ነበር ። ይህ ሁለት ዓመት የሚፈጀው የተቀናጀ ፕሮግራም ከ15-60 ዓመት እድሜ ያላቸው ሰዎች በአፍ-መፍቻ ቋንቋቸው ንባብና ጽሑፍ እንዲማሩ እንዲሁም የሂሣብ ስሌት ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ ከተግባራዊ እውቀትና ክሂል ጋር በማቀናጀት ይሰጣል። ትምህርቱ ከልማት ሠራተኞች (የግብርና፣ የጤና፣ ወዘተ) በሚገኝ እውቀትና በአገር በቀል አውቀት ላይ የተመሠረተ ነው። የሂሣብና የንባብ /ጽሁፍ ክህሎቶችን ከግብርና (ከእርሻ ውጭ ያሉትን ሥራዎች ጨምሮ) ፣ ከጤና ፣ ከሲቪክስና ባህል ጋር በማስተሳሰር ትምህርቱ የሚሰጥ ሲሆን የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አገልግሎት ሰጪዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ ይደረጋል።

በአራተኛው የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ፕሮግራም 36.4 ሚሊዮን ጎልማሶችን በሁለት ዓመቱ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ለማሳተፍ ታቅዶ ነበር። ሆኖም የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በ2004 ዓ.ም ባቀረበው ሪፖርት መሠረት ያልተማሩ ጎልማሶች ቁጥር 20.4 ሚሊዮን ሆኖ በመገኘቱ ፣ በ2005 ዓ.ም የተሳታፊዎች ቁጥር ወደ 19.4 ሚሊዮን ዝቅ እንዲል ማስተካከያ ተደርጓል።[3] ከነዚህ ውስጥ 10.2 ሚሊዮን የሚደርሱ ጎልማሶች ( በድምር 53 በመቶ

[3]*በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃግብር ወቅት ብሄራዊ የህዝብ ቆጠራ ይካሄዳል። ይህን ከሌሎች ሪፖርቶች ጋር በማጣጣም ያልተማሩ ጎልማሶች ብዛት እንዲስተካከል ይደረጋል።*

ከነዚህ ውስጥ 42 በመቶ ሴቶች ናቸው በተቀናጀው ኮርስ የመጀመሪያ ዓመት ተሳታፊ ሲሆኑ ሁለተኛውን ዓመት አጠናቀው የጨረሱ ጐልማሶች 7.2 ሚሊዮን (35 በመቶ) ናቸው፡፡ በአራቱ ታዳጊ ክልሎች ፕሮግራሙ ያለው ተደራሽነት እጅግ አነስተኛ በተለይ ደግሞ መፃፍና ማንበብ የማይችሉ ሴቶች ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ ይበልጥ ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ 13.4 ሚሊዮን (9.3 ሚሊዮን ሴቶችና 4.1 ሚሊዮን ወንዶች) ጎልማሶች በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ የተቀናጀ የሁለት ዓመቱ የተግባር ፕሮግራም ተሳታፊ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

## የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት

### የትምህርት ውጤቶች

#### የዝቅተኛ ክፍል ደረጃ የንባብ ዳሰሳ (EGRA)

በ2002 ዓ.ም በሁለተኛና ሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የዝቅተኛ ክፍል ደረጃ የንባብ ደሰሳ ጥናት ተካሂዶ ነበር፡፡ ጥናቱ በመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በቀጣይ ክፍሎች በአግባቡ ለመማር የሚያስችሉዋቸውን መሠረታዊ ክህሎቶች ያላዳበሩ መሆናቸውን አሳይቷል፡፡ ለምሣሌ፣ ሁለተኛ ክፍል ከሚማሩት ተማሪዎች 34 በመቶ ለደረጃው ከተዘጋጀው ምንባብ ውስጥ አንድም ቃል ማንበብ ሳይችሉ ቀርተዋል፤ ከተማሪዎቹ 48 በመቶው ከተዘጋጀው አንብቦ የመረዳት ፈተና አንዱንም መመለስ አልቻሉም፣ በተጨማሪ ከተማሪዎቹ መካከል በደቂቃ 60 ቃላትን አቀላጥፈው ማንበብ (ተማሪዎች በደቂቃ 60 ቃላት እንዲያነቡ ይጠበቅ ነበር) የቻሉት 5 በመቶ ብቻ ናቸው፡፡

በዝቅተኛ የትምህርት ደረጃዎች መሠረታዊ ክህሎቶች ካለዳበሩ፣ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው፣ በአማርኛና በእንግሊዝኛ አቀላጥፈው እንዳይማሩ ከማድረጉ በተጨማሪ፣ በተከታታይ ደረጃዎች ባሉት ክፍሎች በሚማሩዋቸው የትምህርት አይነቶች ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ የዝቅተኛ ክፍል ደረጃ የንባብ ዳሰሳ /EGRA/ ውጤትን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሰባት የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች አዲስ ሥርዓተ ትምህርት የተነደፈ ሲሆን በዚሁ ስርዓተ ትምህርት መምህራን እንዲሰለጥኑና የመማርያ ቁሳቁሶች ተመርተው እንዲከፋፈሉ ተደርጓል፡፡

ሰባቱ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች ያሉበትን ደረጃ በየጊዜው ለመገምገም የሚያስችል የመነሻ መስፈርት በ2006 ዓ.ም ተዘጋጅቷል። (ይሄ ለሌሎች አፍ መፍቻ ቋንቋዎችም ያገለግላል)። ይህ መስፈርት አቀላጥፎ የማንበብ ችሎታን በአራት የብቃት ደረጃዎች የከፋፈለ ሲሆን እነዚህ ደረጃዎች የማያነብ፣ ከመደበኛ በታች (ዝግተኛ ንባብና ውሱን አንብቦ መረዳት)፣ መደበኛ (መጠነኛ የተቀላጠፈ ንባብና አንብቦ መረዳት) እና ፈጣን አንባቢ (አቀላጥፎ የሚያነብና ሙሉ ለሙሉ አንብቦ የሚረዳ) በመባል ተከፍለዋል።

**ሠንጠረዥ 7፡ በሰባት ቋንቋዎች የአቀላጥፎ ማንበብ ደረጃዎች ፣ ሁለተኛ ክፍል (በመቶኛ)**

| ቋንቋ | አቀላጥፎ የሚያነብና የሚረዳ ፈጣን አንባቢ | መጠነኛ አቀላጥፎና አንብቦ መረዳት | ዝግተኛ ንባብና ውሱን መረዳት | የማያነብ |
|---|---|---|---|---|
| የብቃት ደረጃ | ፈጣን አንባቢ | መደበኛ | ከመደበኛ በታች | የማያነብ |
| አፋን ኦሮሞ | 5 | 20 | 21 | 54 |
| ኣፍ- ሶማሊ | 34 | 27 | 13 | 26 |
| አማርኛ | 6 | 21 | 48 | 25 |
| ሃዲይሳ | 4 | 7 | 13 | 76 |
| ሲዳሞ አፋ | 3 | 13 | 15 | 69 |
| ትግርኛ | 2 | 33 | 34 | 31 |
| ወላይታቶ | 12 | 20 | 18 | 50 |

**ብሔራዊ የትምህርት ቅበላ ጥናት**

በየአራት ዓመቱ አራተኛ፣ ስምንተኛ፣ አስረኛና አስራ ሁለተኛ ክፍሎች ብሄራዊ የመማር ዳሲሳ ጥናት ይካሄዳል። በአራተኛው የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ወቅት የተማሪዎች ነጥብ ቢያንስ 50 በመቶ እና 75 በመቶ እንዲሆን በግብነት ተይዞ ነበር። በአጠቃላይ በታቀደውና በተፈፀመው መካከል በሁሉም ደረጃዎች ሰፊ ልዩነት የታዬ ሲሆን፣ ሻል ያለ ውጤት ሊታይ የቻለው አስረኛ ክፍል ላይ ነው።

**ሠንጠረዥ 8፡ የብሔራዊ የትምህርት ቅበላ ጥናት ውጤት ከአራተኛው የትምህርት ልማት እቅድ አንፃር (በመቶኛ)**


| ክፍል (የዳሰሰ ጊዜ) | 4 (2004) | | 8 (2004) | | 10 (2006) | | 12 (2006) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| *የታቀደ ውጤት* | ግብ | ውጤት | ግብ | ውጤት | ግብ | ውጤት | ግብ | ውጤት |
| ዝቅተኛ መነሻ 50 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ | 75 | 25 | 70 | 7.5 | 70 | 23 | 70 | 34 |
| 75 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ | 25 | 2.3 | 25 | 0.1 | 25 | 3 | 25 | 4 |

**አራተኛና ስምንተኛ ክፍሎች**

የ2000 ዓ.ም እና የ2004 ዓ.ም ውጤት በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች "ከመደበኛ" ወደ "ከመደበኛ በታች" ወርዶ ተገኝቷል። በነዚህ ዓመታት አማካይ የሁሉም ትምህርት

አይነቶች ውጤት ከ41 በመቶወደ 40 በመቶ ዝቅ ያለ ሲሆን፣ እስካሁንም ከአዲስ አበባ በስተቀር በሁሉም ክልሎች ውጤቱ ከ50 በመቶ በታች ነው፡፡

**ሠንጠረዥ 9፡ በአራተኛ ክፍል ብሄራዊ የትምህርት ቅበላ ጥናት በትምህርት ዓይነቶች የታዩ አቀላጥፎ 2000 እና 2004 ሲነፃፀሩ (በመቶኛ)**





ስምንተኛ ክፍልን በተመለከተ በ2004 ዓ.ም የታየው ብቃት በ2000 ዓ.ም ከነበረው ብቃት ሻል ያለ ሆኖ ታይቷል (14 በመቶ የነበረው አማካይ ውጤት ወደ 16 በመቶ አድጓል)፡፡ ከአራተኛ ክፍል ጋር ሲነፃፀር ፣ የስምንተኛ ክፍሉ ዳሰሳ በአጠቃላይ ብቃት እድገት የታየበት ሲሆን “ከዝቅተኛ በታች” የነበረው ነጥብ በ6 በመቶ ቀንሶ ታይቷል፡፡

ከመደበኛ በታች    መደበኛ 2001    ብቁ    ከመደበኛ በታች    መደበኛ 2004    ብቁ

ንባብ    እንግሊዝኛ    ሒሣብ    አካባቢ ሳይንስ    ጭማቂ

**ሠንጠረዥ 10፡ በስምንተኛ ክፍል ብሄራዊ የትምህርት ቅበላ ጥናት በትምህርት ዓይነቶች የታዩ አቀላጥፎ 2000 ዓ.ም እና 2004 ዓ.ም ሲነጻጸሩ (በመቶኛ)**




## አስረኛና አስራ ሁለተኛ ክፍሎች

በ2006 ዓ.ም በተደረገው ዳሰሳ በአምስቱ ዋና ዋና የትምህርት ዓይነቶች (ሂሣብ፣ እንግሊዝኛ፣ ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪና ባዮሎጂ) አማካይ ውጤታቸው 50 በመቶ የደረሰ አስረኛ ክፍል ተማሪዎች ቁጥር 23 በመቶ ነው፡፡ በዚሁ ዳሰሳ 75 በመቶ እና ከዚያ በላይ ነጥብ ማግኘት የቻሉት 3 በመቶ ብቻ ናቸው፡፡ ከትምህርት ዓይነቶቹ የተሻለ ውጤት የተገኝበት ባዮሎጂ ሲሆን፣ 40 በመቶ ተማሪዎች 50 በመቶ እና ከዚያ በላይ 11 በመቶደግሞ 75 በመቶና ከዚያ በላይ ውጤት አግኝተዋል፡፡ ይህ ውጤት በፊዚክስ ትምህርት ከተገኘው ውጤት (14 በመቶ ተማሪዎች 50 በመቶ ያገኙ፣ 2 በመቶ ደግሞ 75 በመቶ በጣም የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በአጠቃላይ ውጤቶቹ ዝቅ ያሉ መሆናቸው እንዳለ ሆኖ በ2006 የታየው ውጤት በ2002 ዓ.ም ከታየው ውጤት (14 በመቶ ተማሪዎች 50 በመቶ አማካይ ውጤት ሲያገኙ፣ 75 በመቶ አማካይ ውጤት ያገኙት 1 በመቶ ብቻ ነበሩ) የተሻለ እንደነበር ይታያል (በሁለቱ ዓመታት የተሰጠው ፈተና አንድ ዓይነት ነበር)፡፡

አስራ ሁለተኛ ክፍል ላይ የተሻለ ውጤት ታይቷል፣ ይህ የሚጠበቅ ነበር፡፡ ምክንያቱም አስረኛ ክፍል ላይ ይማሩ ከነበሩት ተማሪዎች የተሻለ ውጤት በማስመዝገብ ወደሚቀጥለው ክፍል ስለሚሸጋገሩ ነው፡፡ በ2006 ዓ.ም በተደረገው ዳሰሳ 34 በመቶ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች አምስት ዋና ዋና

ትምህርቶች (ሂሣብ፣ እንግሊዝኛ፣ ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪና ባዮሎጂ) ጭማቂ ውጤታቸው 50 በመቶ ሲሆን፣ ከተማሪዎቹ 4 በመቶ ደግሞ ውጤታቸው 75 በመቶ ነበር። ይህ ውጤት ከ2002 ዓ.ም የብቃት ውጤት ጋር ሲነፃፀር ትንሽ ዝቅ ያለ ሆኖ ታይቷል። ውጤቱ ምንም እንኳን በከፍተኛ ትምህርት ጥራት ላይ ተጽእኖ ያለው ቢሆንም ፣የመሰናዶ ትምህርት ከሚቀላቀሉ ተማሪዎች ቁጥር መጨመር አንፃር ሲታይ የሚያስደንቅ አይሆንም።

## የህፃናት እንክብካቤና የትምህርት ጥራት

የቅድመ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት፣ በተለይም የ(0) ኦ ክፍል በአፋጣኝ መስፋፋት በትምህርት ጥራት ላይ ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችል ጉዳይ ነው። በአሁኑ ጊዜ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ነፃ በሚሆኑበት ክፍለ ጊዜ የ(0)ኦ ክፍልን ትምህርት እየሰጡ ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ ማህበረሰቡ አስተማሪዎችን ክፍያ በመስጠት የ(0) ኦ ክፍል እንዲያስተምሩለት እያደረገ ይገኛል። እነዚህ አዳዲስ ዘዴዎች የሚመሰገኑ ቢሆንም፣ ከአፀደ ህፃናት ትምህርት አንፃር ሲታይ ቀጣይነታቸውና አግባብነታቸው አጠያያቂ ይሆናል።

እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ እርምጃዎች ተወስደዋል። በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም የመጨረሻው ዓመት ካሉት 36 የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ሰባቱ፣ በተለይ በቅድመ መደበኛ ትምህርት የመምህራንን በዲፕሎማ ፕሮግራም ማሰልጠን ጀምረዋል። ካሉት ኮሌጆች መካከል አንዱ በህፃናት እንክብካቤና ትምህርት ክህሎት የሰለጠኑ መምህራን ያሉት ሲሆን፣ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ጊዜ በሁሉም ኮሌጆች በህፃናት እንክብካቤና ትምህርት በቂ እውቀት፣ ክህሎት እና ልምድ ያላቸው መምህራን እንዲኖሩ ይደረጋል። በተጨማሪ፣ ለ(0) ኦ ክፍል የተለየ ሥርዓተ ትምህርትና የመማርያ ቁሳቁስ በመዘጋጀት ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ በመስኩ በሠርተፊኬት ደረጃ የአንድ ዓመት የስልጠና መርሃ ግብር ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል። እነዚህ እርምጃዎች በሙከራ ደረጃ ከሚካሄዱት የተፋጠኑ የህፃናት ዝግጁነት ፕሮግራሞች፣ የህፃናት የእርስ በርስ መማማር ፕሮግራም ግምገማና የ(0) ኦ ክፍል ትምህርት አሰጣጥ ግምገማ ጋር ተዳምረው በአምስተኛው

የአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ለሚኖረው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የጥራት ግብአት በመሆን ያገለግላሉ፡፡

## የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥራት (አማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን)

ከላይ የተዘረዘሩት ዝቅተኛ ውጤቶች ትምህርት የማቋረጥና ክፍል የመድገም ችግሮች የትምህርት ግብአቱ ጥራት እንደሌለው ያሳያል፤ በምሣሌነትም በቂ ክህሎት ያላቸው መምህራን አለመኖር፣ የመማር ማስተማር ቁሳቁስ የተገቢነት ችግሮችና የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ትምህርት ቤት ከሚገቡት 1000 ህፃናት ውስጥ ያለማቋረጥ አምስተኛ ክፍል የሚደርሱት ግማሽ ያህሉ ሲሆኑ ስምንተኛ ክፍልን የሚያጠናቅቁት አንድ አምስተኛ ብቻ ናቸው፡፡ የትምህርት ስርዓቱ ተማሪዎች መሠረታዊ የሆኑ የንባብና የሂሣብ ክህሎቶች እንዲኖሩዋቸው ማረጋገጥ አለመቻሉ ለታየው ዝቅተኛ አፈፃፀም እና ውጤት አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

### መምህራንና አመራርን በተመለከተ

በመምህራን ልማት ፖሊሲው መሠረት በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃግብር በአጠቃላይ ትምህርት በሁሉም ደረጃዎች የሚያስተምሩ መምህራን ተገቢውን የትምህርት ደረጃ ያሚሉ፣ ሙሉ ፍላጐት እና ብቁ ሥነ ምግባር ያላቸው እንዲሆኑ ታቀዶ ነበር፡፡ በዚህም መሠረት እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ ዲፕሎማ ያላቸው የአንደኛ ደረጃ መምህራን ቁጥር ከ38 በመቶ ወደ 100 በመቶ ለማሳደግ ተጠብቆ ነበር፡፡ እስከ 2006 ዓ.ም ድረስ በነበረው ጊዜ 70 በመቶ የአንደኛ ደረጃ መምህራን ተፈላጊው የትምህርት ደረጃ ነበራቸው (55 በመቶ በመጀመሪያው ሳይክል፣ 92 በመቶ በሁለተኛው ሳይክል)፡፡ ምንም እንኳ የታቀደው ባይሟላ፣ ይህ ቁጥር ቀደም ሲል ከነበረው በእጥፍ ስለጨመረ ሂደቱ በቀላል የሚታይ አይደለም፡፡ በዚህን ጊዜ የመምህራኑ ቁጥር በ 30 በመቶ የጨመረ ሲሆን፣ የተማሪ መምህር ጥመርታውም ከ 51 ወደ 47 ወርዷል፡፡ ከዚህ ሌላ፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከሚያስተምሩት መምህራን 93 በመቶ ተፈላጊው የትምህርት ደረጃ ያላቸው ናቸው (የመጀመሪያ ወይም ሁለተኛ ዲግሪ)፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ መምህርነት መስፈርቱን የሚያሟሉ መምህራን ቁጥር ከክልል ክልል ይለያያል፡፡ ህዝብ በሚበዛባቸው በሃረሪና አዲስ አበባ ከተሞች መስፈርቱን የሚያሟሉ መምህራን በያንዳንዳቸው 82 በመቶ እና 91 በመቶ ሲሆን፣ በሶማሌ እና በአፋር ክልሎች ግን 35 በመቶ እና 42 በመቶ ብቻ ነው፡፡ በሶማሌ ክልል በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ተገቢው ደረጃ ያላቸው መምህራንን ለመሳብ ጥቅማ ጥቅም በመስጠት ጥሩ ውጤት ለማግኘት ተችሏል፡፡ ቢሆንም ግን በክልሎች መካከል የሚታየው የመምህራን የብቃት ደረጃ ልዩነት ፖሊሲውን በተለይም በመምህራን ጥቅማ ጥቅምና አመዳደብ ላይ ሙሉ ለሙሉ ሊተገበር አለመቻሉ ነው፡፡ ከአጠቃላይ የመጀመሪያ ደረጃ መምህራን ቁጥር 63 በመቶ ወንዶች ሲሆኑ 37 በመቶ ሴቶች ናቸው፡፡ ከወንዶቹ መካከል 68 በመቶ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሲሆኑ፣ ሴቶች ደግሞ 73 በመቶውን ያሟላሉ፡፡

በ2007 ዓ.ም ሁሉም መምህራን የብቃት ማስረጃ እንዲኖራቸው በእቅድ ተይዞ ነበር፡፡ ይህ ግን የሥራውን ብዛት ያላገናዘበ እና ሂደቱን የሚከታተል ተቋም ከመቋቋሙ በፊት የታቀደ ነበር፡፡ በ2003 ዓ.ም የብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ተቋቁሞ ሥራ የጀመረ ሲሆን፣ አግባብነት ያለው ደረጃና ብቃት ያላቸው መምህራንን ለመለየት ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ በየጊዜው በማደግ ላይ ያለው የብቃት ማረጋገጫና የዳግም ብቃት ማረጋገጫ ስርዓት በቅድሚያ በሚወጡ መስፈርቶች አንፃር የሙያ ብቃትን ይገመግማል፡፡

የስልጠና አግባብነትንና ጥራትን በተመለከተ ፣ ሁለተኛ ዓመቱን የያዘው አዲሱ የአንደኛ ደረጃ መምህራን የሦስት ዓመት የዲፕሎማ መርሀ ግብር በሁሉም የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል የሚሰጠው ሊኒያር (Linear) ስርዓተ ትምህርት እንዳለ የሚቀጥል ሲሆን፣ በአንደኛው ሳይክል በክላስተር (Cluster) የሚካሄደው ሥርዓተ ትምህርት መምህራን የተለያዩ ተዛማጅነት ያላቸው የትምህርት አይነቶች አንድ ላይ ለማስተማር ዝግጁ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው፡፡

በመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሚያስተምሩ መምህራን የተግባር ልምድ እጥረት የሚታይባቸው ሲሆን፣ ሰልጣኞችደግሞ በየትምህርት መስኩ ያላቸው እውቀት አነስተኛ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ

የፔዳጐጂ ክህሎት ትምህርት (ለምሣሌ ተማሪ ተኰር የማስተማር ዘዴ) የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ ነው። እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ አስረኛ ክፍልን አጠናቀው የሚገቡ አዳዲስ ሰልጣኝ መምህራን ተገቢው የትምህርት መስክ እውቀት ይኖራቸው ዘንድ የመሸጋገሪያ ኰርሶች እንዲሰጡ ተደርጓል። መምህራን በተግባር የተደገፈ ልምድ ይኖራቸው ዘንድ፣ የመምህራን ትምህርት ኰሌጆችና መምህራንን የሚያስለጥኑ ዩኒቨርስቲዎች በአካባቢው ከሚገኙ አፀደ ህፃናት፣ አንደኛና ሁለተኛ ትምህርት ቤቶች ጋር በትብብር እንዲሰሩ ይበረታታሉ። እነዚህ ትስስሮች በአምስኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት እቅድ እንዲጠናከሩ ይደረጋል።

በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ እቅድ ወቅት አዲስ የአመራርና አስተዳደር ፕሮግራም ተቀርፆ 25,000 ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች  ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል። ከሁለት ዓመታት በፊት በተጀመረው አዲሱ ፕሮግራም በሱፐርቪዥን በማኔጅመንትና በትምህርት አመራር የቲዎሪና የተግባር ሥልጠና እየተሰጠ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የትምህርት አመራሮች የመማር ማስተማሩን ሂደት ለመደገፍ ይችሉ ዘንድ በስልጠናው እንዲካተት ይደረጋል (ለምሣሌ የክፍል ምልከታ ክህሎት ስልጠና ይሰጣል)።

**ስርዓተ ትምህርት የመማሪያ መፃህፍት እና ምዘናን በተመለከተ**

አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ወቅት ሲተገበር ቆይቷል። ሥርዓተ ትምህርቱ በሁሉም ትምህርት ቤቶች የተሰራጨ ሲሆን በአንደኛ ደረጃ ትውውቁ ት/ቤቶች ግን ዘግየት ያለ ነበር። እድሜያቸው ከፍ ላለ ተማሪዎችም የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ለትግበራውም በቂ ስልጠና ተሰጥቷል።

በአጠቃላይ ትምህርት የጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም (GEQIP) በመመራት በሁለሙ የትምህርት እርከኖች የመማርያ መፃሕፍትና የተማሪዎች ጥምረትን 1:1 ለማድረስ ከፍተኛ የህትመትና የስርጭት ሥራ የተከናወነ ሲሆን፣ አንዳንድ ዳሰሳዎች እንዳመለከቱት ግን መፃህፍቱ በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ሲጠቀሙባቸው አይታይም። ልዩ የትምህርት ፍላጐት የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን በተመለከተ ግን ስርዓተ ትምህርቱ መሟላት የሚገባቸው የቁሳቁስ አቅርቦት ችግሮች ይታያሉ። ከዚህ ሌላ ብቃት

ያላቸው የማተሚያ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ አለመኖራቸው የህትመት ጥራት ችግርና የዋጋ መናር ሁኔታዎች ይታያሉ፡፡

አዲስ የስርዓተ ትምህርት ክለሳ ጥሩ ተቀባይነት የነበረው ቢሆንም፣ ተማሪዎች፣ መምህራንና ከፍተኛ ባለስልጣናት ፣ በሚሰጡ ፈተናዎችና በስርዓተ ትምህርቱ መካከል ያለመጣጣም ችግር መኖሩን ይገልፃሉ፡፡ ትምህርት ሚኒስቴር ከብሔራዊ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ጋር በመተባበር ብሔራዊ ፈተናዎች ከሥርዓተ ትምህርቱ ጋር ያላቸውን መጣጣም ለማረጋገጥ በሂደት ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ በክልል ደረጃ ለሚሰጡ ፈተናዎች ክልሎች ተመሳሳይ ክትትል ያደርጋሉ፡፡

**የኢንፎርሜሽን ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በተመለከተ**

በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም በሁሉም የሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የሳተላይት ቴሌቭዥን ትምህርትና ኢ-ለርኒንግ ፕሮግራሞችን ለመከታተል የሚያስችሉ የተደራጁ የኮምፒዩተር ላቦራቶሪዎች እንዲኖሩ ታቅዶ ነበር፡፡ እስካሁን ድረስ ባለው ጊዜ 69 በመቶ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሳተላይት ቴሌቭዥን ትምህርት ፕሮግራም ተጠቃሚ ለመሆን ችለዋል፡፡ በትምህርት ቤቶች የሚፈጠር የኃይል እጥረት ለመቋቋም ዲጂታል የቴሌብዥን ትምህርት ፕሮግራሞች በዲ.ቪ.ዲ ተቀርፀው ለሁሉም የክልል ትምህርት ቢሮዎች ተሠራጭተዋል፡፡

የኢንተርኔት አገልግሎት የሚያገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 28 በመቶ ብቻ ሲሆን፣ ከነዚህ ውስጥ 6 በመቶ ብቻ ከፍተኛ አቅም ያለው ሰርቨር አላቸው፡፡ ከኃይል እና ከኔትወርክ ችግሮች ጋር በተገናኘ በአይ.ሲ.ቲ አጠቃቀም ላይ በክልሎች መካከል ልዩነት ይታያል፡፡

እንግሊዝኛ ቋንቋን በሬዲዮ የማስተማር ፕሮግራም በትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት መረጃና ግንኙነት ቴክኖሎጂ ማዕከል ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት አገልግሎት እንዲውል ተደርጓል፡፡ በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ወቅት እነዚህና ሌሎች የትምህርት ዓይነቶች በድምጽ ተቀርጸው ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሠራጩ ተደርገዋል፡፡

**የትምህርት ቤቶች መሠረተ ልማት እና ፋሲሊቲዎች ጥራትን በተመለከተ**

የትምህርት ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራም (SIP) የተቋቋመው የትምህርት ቤቶችን ፍላጐት በቅደም ተከተል በማስቀመጥ በማሻሻያው ፕሮግራም መሠረት አቅማቸውን ማሳደግ ነው፡፡ ትምህርት ቤቶች (እንደየተማሪዎቻቸው ብዛት) በእቅድ የተያዙ ፕሮግራሞችን ለማከናወን የገንዘብ ድጐማ ይደረግላቸዋል፡፡ በአብዛኛዎቹ ትምህርት ቤቶች የመሠረተ ልማቱና የፋሲሊቲው አቅርቦት በተፈለገው ደረጃ ላይ ደርሷል ለማለት አይቻልም፡፡ ለምሣሌ፣ ከ92 በመቶ በላይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መፀዳጃ ቤት እንዳላቸው የገለፁ ሲሆን 60 በመቶ ያህሉ ግን የውሃ አቅርቦት የላቸውም በተጨማሪ 20 በመቶ ብቻ ክሊኒክ ሲኖራቸው፣ የፔዳጐጂ ማዕከል ያላቸው ግማሾቹ ብቻ ናቸው፡፡ አካቶ ትምህርትን ለማገዝ በሙከራ ደረጃ በ 113 ክላስተር ትምህርት ቤቶች የማበልፀጊያ ማዕከላት ተቋቁመዋል፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሁኔታ ከአንደኛ ደረጃዎቹ የተሻለ ነው፡፡ ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መፀዳጃ አላቸው ለማለት ይቻላል፣ ከአምስቱ አራት እጅ ውሃ እና የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት አላቸው፣ 72% ትምህርት ቤቶች የቤተመፃህፍት አገልግሎት ያገኛሉ፡፡

ትምህርት ቤቶች የሚገኙበት ሁኔታ በ2004 ዓ.ም በተቋቋመው ፣ የትምህርት ቤት የውስጥ ኢንስፔክተሮችና ሌሎች ነፃ ኢንስፔክተሮች በሚገኙባቸው የትምህርት ኢንስፔክሽን ቡድኖች አሰራራቸው እንዲገመገም ይደረጋል፡፡ በስምንት ክልሎች ለመጀመሪያ ጊዜ በ2006 ዓ.ም የተካሄዱት የውስጥ ኢንስፔክሽኖች እንደሚያሳዩት የሁኔታዎች መሻሻል የታዩ ቢሆንም በአጠቃላይ ግን ትምህርት ቤቶቹ ያሉበት ሁኔታ ከሚጠበቀው በታች ነው፡፡

ሠንጠረዥ 11፡ የትምህርት ቤቶች የሚገኙበት ደረጃ 2006 ዓ.ም

| ደረጃ | ከደረጃ በላይ የሆኑ (ደረጃ 4) | ደረጃውን የሚያሟሉ (ደረጃ 3) | መሻሻል የሚጠበቅባቸው (ደረጃ 2) | ከደረጃ በታች የወረዱ (ደረጃ 1) | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| *መጀመሪያ* | 855 (3 በመቶ) | 5,197 (18 በመቶ) | 15,043 (53 በመቶ) | 7,117 (26 በመቶ) | 28,212 (100 በመቶ) |
| *ሁለተኛ* | 59 (3 በመቶ) | 466 (27 በመቶ) | 1,054 (60 በመቶ) | 184 (10 በመቶ) | 1,763 (100 በመቶ) |

**የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና**

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዋና ዓላማ፣ በዝቅተኛና መካከለኛ ደረጃ ብቁ የሆነ፣ ሙሉ ፍላጐት ያለው፣ ራሱን ከሁኔታዎች አንፃር የሚያስተካክልና የፈጠራ ችሎታ ያለው የሰው ኃይል ማፍራት ነው፡፡ አላማው በፍላጐት ላይ በመመስረትና ጥራት ባለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና በመሰልጠን ተፈላጊ የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማምጣት የሚችል ፣ ድህነትን ለመቀነስና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦ ለማበርከት የሚችል የሰው ኃይል መፍጠር ነው፡፡

**ተደራሽነትና ፍትሃዊነት**

በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ወቅት የአስረኛ ክፍል ፈተና ከሚወስዱት ተማሪዎች መካከል 80 በመቶዎቹ መደበኛ የሆነ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ይሰጣቸዋል ተብሎ ይጠበቅ ነበር፡፡ ሆኖም ግን አስረኛ ክፍል ጨርሰው ወደ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሚገቡት ተማሪዎች ቁጥር በመቀነሱ በተያያዥነት አጠቃላዩ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቅበላ ቁጥር

አነስተኛ  ሊሆን ችሏል፡፡ በ2006 ዓ.ም አስረኛ ክፍል ካጠናቀቁት ተማሪዎች መካከል 45 በመቶ፣ ማለትም 276,106 ተማሪዎች ቴክኒክና ሙያ ትምህርትን ተቀላቅለዋል (በመጀመሪያው የአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም የገቡት 80 በመቶ ማለትም ከ 340,000 ተማሪዎች በላይ ነበሩ)፡፡ የቴክኒክና ሞያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሙን የተሳተፉት  ሴቶች ቁጥር 51 በመቶ በመሆን ከግብ በላይ ፍትሃዊነት የተመዘገበ ቢሆንም፣ በስልጠና መስኰች ግን በወንዶችና በሴቶች መካከል ልዩነቶች ይታያሉ፡፡

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የመካፈል እድሎች በሁሉም ክልሎች የነበሩ ቢሆንም፣ አንዳንድ ክልሎች በጂኦግራፊያዊ አቀማመጥና ህዝብ ብዘት ምክንያቶች በቂ ሠልጣኞች አልነበሩዋቸውም፡፡ በተለይ በአፋር፣ ጋምቤላ ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ሶማሌና ሃረሪ ክልሎች የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶች ቅበላ አንሰተኛ ነበር፡፡

በታሳቢነት ተይዞ የነበረው 80 በመቶ የቅበላ እቅድ ሊሟላ ያልቻለበትና በዚህም ምክንያት የተፈጠረው የአቅርቦትና የፍላጐት አለመጣጣም ችግር ምክንያቶቹ አምስት ናቸው፡፡ በመጀመሪያ፣ አስረኛ ክፍል የተከታተሉና ያጠናቀቁ ተማሪዎች ቁጥር በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ እቅድ ታቅዶ ከነበረው ያነሰ ስለነበር ከምንጩ በቂ አቅርቦት አልነበረም፡፡ ሁለተኛ፣ በፖሊሲው መሠረት 20 በመቶ ተማሪዎች ወደ 11ኛ ክፍል ይዘዋወራሉ ቀሪዎቹ 80 በመቶ ደግሞ ቴክኒክና ሙያ ይገባሉ ተብሎ የታቀደው ቢሆንም፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቅበላ አቅም በማደጉ ወደ 11ኛ ክፍል የሚገቡት ተማሪዎች ቁጥር ወደ 30 እና 35 በመቶ ሊያድግ ችሏል፡፡

ሦስተኛ፣ አስረኛ ክፍልን ካጠናቀቁት ተማሪዎች 15 በመቶ ያክሉ በመምህራን ማሰልጠኛዎች፣ እንደዚሁም በፖሊስና ወታደራዊ አካዳሚ ፕሮግራሞች ተመዝግበዋል፡፡ አራተኛው ምክንያት የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛዎች በሁሉም ወረዳዎች አለመገኘታቸው ነው፡፡ በ2006 ዓ.ም 1,348 የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛዎች (የታቀደው 1074 ነበር) የነበሩ ቢሆንም፣ በሙሉ አቅም (እስከ ከፍተኛው ደረጃ 5) የሚያሰለጥኑት 334 የመንግሥትና 282 የግል/መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ብቻ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 732 (325 የመንግስት፣ 407 የግል) ተቋማት አጫጭር ስልጠናዎችን ብቻ የሚሰጡ ናቸው (አንዳንዶቹ

ብቻ እስከ ደረጃ 2 ስልጠናን ይሰጣሉ)። አምስተኛና የመጨረሻ ምክንያቱ፣ ባለፉት ዓመታት የተካሄደው ዘለቄታዊ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ስርዓት ህዝቡ እንዲያውቀውና እንዲገነዘበው በቂ መረጃ ባለመስጠቱ የተጠበቀው ያህል ቅበላ ሊኖር አልቻለም።

ሊታወቅ የሚገባው ግን በ2005 እና 2006 ዓ.ም በተሰጡት የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች የተካፈሉት ሰልጣኞች ቁጥር በመደበኛነት ከተካፈሉት ጋር አብሮ አልተደመረም፣ ምክንያቱም ሰልጣኞቹ ከአስረኛ ክፍልና ከሌሎች የተለያየ የክፍል ደረጃዎች የመጡ በመሆናቸው ነው። ለምሣሌ በ2006 ዓ.ም የአጭር ጊዜ ስልጠና የወሰዱ ተማሪዎች ቁጥር 1,955,826 የነበረ ሲሆን ይህ የሚያመለክተው አጠቃላዩ የቴክኒክና ሙያ የሰልጣኞች ቁጥር እንዳልቀነሰ ነው። በእቅዱ መሠረት 40 በመቶ ሰልጣኞች በግል ዘርፍ ሥራ ይሰማራሉ ተብሎ የተያዘ ቢሆንም ስኬቱ ግን 20 በመቶ ብቻ ከመሆኑ ሌላ ድርሻው ቀስ በቀስ እየቀነሰ በመሄድ ላይ ይገኛል። የግል ዘርፉ የተገመተውን ያህል በስልጠና ባለመሳተፉ ተደራሽነቱ ውሱን ሊሆን ችሏል።

### ጥራት

የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ፕሮግራሞችን የጥራት ደረጃ ለማሻሻል በተወሰደው እርምጃ የአሰልጣኞች ብቃት ተጠንቶ አስፈላጊ የሆኑ የሥራ ላይ ሰልጠናዎች ተሰጥተዋል። የስልጠናዎቹ ርዕሶች በታየው የቴክኒካል ጉድለት ላይ ብቻ ያተኮሩ ሳይሆኑ፣ የሥራ ፈጠራ ስልጠና፣ሥራ ተኮር ስርዓተ ትምህርት ቀረጻ፣ ስልጠና የመስጠት ዘዴዎች፣ እንደዚሁም ተቋማዊ ግምገማ ጥራትና ምርት ማሻሻያዎችን ያካተቱ ነበሩ። ሰልጣኞች መሠረታዊ ክህሎቶችን ለማሻሻል እንዲችሉ 30 በመቶ ጊዜያቸውን በተቋሙ ቀሪውን 70 በመቶ ደግሞ የተግባር ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ በኢንዱስትሪ እንዲያሳልፉ የተቀናጀ የስልጠና ዘዴ እንዲካሄድ ተደርጓል።

ግብአትን እና የሥራ ሂደትን ለማሻሻል የተወሰዱት እርምጃዎች በ2001 ዓ.ም የነበረውን 20 በመቶ ዓመታዊ ብቃት በ2006 ዓ.ም 60በመቶ እንዲደርስ አስተዋጽኦ ያደረገ ሲሆን፣ ወደ አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች የተደረገው የቴክኖሎጂ ሽግግር ቁጥርም ከፍ እንዲል አስችሏል። አጠቃላይ

የአሰልጣኞች ቁጥር በ2002 ዓ.ም 11,153 የነበረ ሲሆን በ2006 ዓ.ም ወደ 17,322 አድርጓል፡፡ በእቅድ ተይዞ የበረው የአሰልጣኞች 1:3 ፡ 24 ወይም ሀ፣ለ፣ሐ ስብጥር (ሀ- ከፍተኛ ክህሎት፣ ሐ- ዝቅተኛ ክህሎት) [4] ሊሟላ ችሎአል፡፡ ሆኖም ግን ሴት አሰልጣኞች ከጠቅላላው 17 በመቶ ብቻ ሲሆኑ፣ በአመራር ደረጃም ከአጠቃላዩ 2,604 የሴቶች ድርሻ 3 በመቶ ብቻ ነው፡፡

### ምርምር

በቴክኒክና ሙያ ስልጠና የሚካሄዱ የምርምር ሥራዎች ደካማ ከመሆናቸው ሌላ በስርዓት የታቀዱ አይደሉም፡፡ የፌዴራሉ ቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ፣ በአግባቡ የተዋቀረ ባይሆንም፣ በውጭ ሃገር ኤክስፐርቶች እገዛ በሥራ ደረጃዎች፣ በምዘና፣ በስርዓተ - ትምህርት ቀረፃና በጥራት ጉዳዮች መለስተኛ የሆኑ ጥናቶች እንዲካሄዱ አድርጓል፡፡ የምርምር አጀንዳዎችን መለየትና የፕሮጀክት ዲዛይኖች ምርጫ ወደፊት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ናቸው፡፡ የሚካሄደው ምርምር በትምህርትና ሙያ ስልጠና ተቋማዊ አሰራርና በገበያ ፍላጐት መካከል ባለው ግንኙነት ላይ በማተኮር የሙያ ትምህርቱና ስልጠናው ወደፊት የሚሻሻልበትን መንገድ ተንትኖ ማሳዬት ይኖርበታል፡፡

### የሥራ ደረጃዎች (OS)

የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ንዑስ ዘርፍ OSን (የሥራ ደረጃ) በመነሻነትና በማጣቀሻነት የሚጠቀም ውጤት ተኮር አሰራርን ይተገብራል፡፡ የሥራ ደረጃዎች (OS) በሥራ ቦታ ያለውን ኡነታና ፍላጐት የሚያመላክቱ በየእንዱስትሪው ባሉ በኤክስፐርቶች የሚጠኑ እንደመሆናቸው የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛዎች በፍላጐት ላይ በመመስረት ውጤት ተኮር ሆነው የመደራጀታቸው ጉዳይ እንደ ማዕዘን ድንጋይ ተደርጐ ይወሰዳል፡፡ የዚህ ዓይነት አደረጃጀት የመማር ማስተማር ሂደቱ እንደአስፈላጊነቱ እንዲስተካከል ስለሚፈቅድና በጊዜና በቦታ ስለማይወሰን፣ የብቃት እውቅና ችግር የለበትም፡፡ ስለሆነም መደበኛና መደበኛ ያልሆነ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናን በማዋሃድ ሃገሪቱን ያላትን ሰፊ የስልጠና አቅም በጥቅም ላይ ማዋል ያስችላታል፡፡  በሥራ ላይ የተሰማራው የሰው ኃይልም የክህሎት ብቃቱን በማጥናትና ክፍተቶቹን በመለየት ፣ በልዩ ትኩረት ፕሮግራሞችን አዘጋጅቶ በማሰልጠን የኢንዱስትሪ ውጤታማነት እና ጥራት እንዲጨምር ያደርጋል፡፡

በ2001 እና 2006 ዓ.ም መካከል በነበረው ጊዜ ውስጥ 613 ተጨማሪ የሥራ ደረጃዎች (OS) እንዲጸድቁ ተደርጓል፡፡ ከነዚህ ደረጃዎች አብዛኛዎቹ ከሌሎች አገሮች በቀጥታ የተወሰዱ ቢሆንም ፣ በተቻለ መጠን የኢንዱስትሪ ኤክስፐርቶች ደረጃዎቹን በመፈተሽና በማጽደቅ ሂደቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

**ምዘና**

ሥራዎች በየደረጃው ማሟላት የሚገባቸው ነገሮች የተዘረዘሩ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ሥራም የራሱ የሆነ ደረጃ (OS) እንዲሰጠው ተደርጓል፡፡ ደረጃ የተሰጣቸው ሥራዎ ከብሄራዊው የቴክኒክና ሙያ የደረጃ መስፈርቶች ጋር እንዲተሳሰሩ በማድረግ በአምስት ተከፍለው በምዘና ይሰጣሉ፡፡ ስልጠናውን የማካሄድና ምዘናውን የማስፈፀም ኃላፊነቶች የተሰጡት ለሁለት የተለያዩ አካላት ነው፡፡ ደረጃዎቹ የሚዘረዘሩትና የምዘና መስፈርቶቹ የሚወጡት በፌዴራል ደረጃ ሲሆን፣ ምዘናውን የማካሄድ ኃላፊነት ግን ስምምነት በተደረገባቸው የፌዴራል ደንቦች በመመስረት ሙሉ በሙሉ ለክልል ብቃት ማዕከላት የተሰጠ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ፣ የምዘና እቅድ፣ አደረጃጀትና አመዘጋገብ በክልሎች የሚካሄድ ሲሆን ፣ ማስረጃዎችን የመሰብሰብና መረጃዎችን የመስጠት ሥራ በፌዴራል ደረጃ ይከናወናል፡፡

**የተቀናጀ ስልጠና**

የተቀናጀ ስልጠና ማለት በቴክኒክና ሙያ ተቋማትና በኢንዱስትሪ የሥራ ቦታዎች በጋራ ስልጠና በመስጠት ላይ የሚያተኩር የትብብር ሞዴል ነው፡፡ ይህ አሰለጣጠን ሰልጣኞች ሙሉ በሙሉ በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ከሚሰጠው ስልጠና ይለያል፡፡ የተቀናጀ ስልጠና የሥራ ቦታ ሁኔታን በቅርበት እንዲያውቁ ከማድረግ በተጨማሪ ስልጠናው አግባብነቱ የተረጋገጠ የተሟላና ዘላቂነት ያለው እንዲሆን ያደርጋል፡፡ አሁን ባለው መስፈርት ሰልጣኞች 70 በመቶ ስልጠናቸውን በኢንዱስትሪ ማግኘት ቢኖርባቸውም ይህ በስፋት ተግባር ላይ አልዋለም (ትክክለኛ የሆነ መረጃም አልተገኘም)፡፡ ለዚህ አንዱ ምክንያት ፣ ተቋማቱ በኢንዱስትሪው በቂ የስልጠና ቦታ ማግኘት አለመቻላቸው ነው፡፡ በቂ የስልጠና ቦታ ለማግኘት ይችሉ ዘንድ ተቋማቱ ፊታቸውን ወደ መካከለኛ ሴክተር ኢንተርፕራይዞች ማዞር

ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህ ኢንተርፕራይዞች ብዙ ሰልጣኞች ሊፈጥሩ የሚችሉ ከመሆናቸው በተጨማሪ ወደፊት ብዛት ያላቸው የቴክኒክና ሙያ ምሩቆች የሚሰሩባቸው ቦታዎች ይሆናሉ፡፡

**የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና የቴክኖሎጂ ሽግግር አገልግሎቶች**

የመካከለኛ ሴክተር ኢንተርፕራይዞች በኢኮኖሚ ልማት፣ በስራ ፈጠራና ድህነትን በመቀነስ ሊኖራቸው የሚችለው ሚና በብሄራዊ የልማት ሰነዱ ተዘርዝሯል፡፡ በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ፕሮግራም ላይ የተዘረዘረ ቀጥተኛ እገዛ ባይኖርም፣ ኢንተርፕራይዞቹ እንዲፈጠሩና እንዲያድጉ ስትራተጂዎች ተነድፈዋል፡፡ ከነዚህ ስትራቴጂዎች አንዱ ነሃሴ 2003 ዓ.ም የተጀመረው በቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚገኙ አሰልጣኞች ለኢንዱስትሪዎች የሚሰጡት የኤክስቴንሽን አገልግሎት ነው፡፡ ይህ አገልግሎት መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን በጥራትና በምርታማነት ለመርዳት የተዘጋጁ አራት ፓኬጆች ያሉት ሲሆን እነርሱም የቴክኖሎጂ አቅም መገንባት፣ የቴክኒክ ክህሎት ማሳደግ፣ ኢንተርፕረነርሺፕ አቅም ግንባታ እና የካይዘን አቅምን ማሳደግ ናቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት የኢንዱስትሪው ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለ214,743 ኢንተርፕራይዞች የሚሰጥ ሲሆን የአገልግሎቱ ጥራት ግን ከታለመው ደረጃ ላይ ገና አልደረሰም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በ2006 ዓ.ም 2627 የቴክኖሎጂ ሽግግሮች ተደርገዋል (በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ፕሮግራም በ2007 ዓ.ም 3000 ሽግግሮች ለማድረስ በእቅድ ተይዞ ነበር)፡፡

## ከፍተኛ ትምህርት

በኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት የተጀመረው በ1950ዎቹ ነው፡፡ ሆኖም ግን መንግሥትና የልማት አጋሮች ለሴክተሩ የቅድሚያ ትኩረት የሰጡትና ተደራሽነቱ ሊጨምር የቻለው ባለፉት አስራ አምስት አመታት ነው፡፡

**ተደራሽነትና ፍትሃዊነት**

ባለፉት አስር አመታት መንግሥት ጥራትና አግባብነት ያለው የከፍተኛ ትምህርት በፍትሃዊነት ተደራሽ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቁጠር ከ8 ወደ 36 (ሰላሣ ሦስቱ ተማሪዎችን በቀጥታ ከ12ኛ ክፈል ይቀበላሉ) ያደገ ሲሆን እነዚህም በሁሉም ክልሎች የተቋቋሙ ናቸው፡፡ የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም በቁጥር 98 ሲሆኑ እስከ አራተኛው የትምህርት ልማት ዘርፍ መጨረሻ ድረስ የቅበላ አቅማቸው ከአጠቃላይ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቁጥር 15በመቶ ያህል ደርሷል፡፡

የተፈጠረው  ተጨማሪ አቅም የቅበላ ቁጥሩ በፍጥነት እንዲያድግ አድርጓል፡፡በ2002 ዓ.ም የነበረው 447,693የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ቅበላ (በመንግሥትና በግል) በ2006 ወደ 593,571 አድጓል፡፡ አስራ ሁለተኛ ክፍል ከሚያጠናቅቁት ተማሪዎች 90 በመቶ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ይገባሉ ተብሎ ቢታቀድም ክንውኑ 84 በመቶ ነው፡፡ ከጠቅላላ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች 57 በመቶ በመደበኛ ፕሮግራም ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ሲሆኑ ቀሪዎቹ 43 በመቶ በርቀት፣ በክረምትና በተከታታይ ትምህርት (extension) ፕሮግራሞች የሚሳተፉ ናቸው፡፡ በመንግሥት ተቋማት በማስተርስ ዲግሪ ደረጃ የሚማሩ ተማሪዎች ቁጥር በ1999 ዓ.ም ከነበረው 7211 በ2006 ዓ.ም ወደ 27,643 አድጓል፡፡ የግል ተቋማት በማስተርስ ዲግሪ ማስተማር በቅርቡ የጀመሩ ሲሆን የተማሪዎቻቸው ቁጥርም 3,000 ደርሷል፡፡ ስለዚህም በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ፕሮግራም መጨረሻ አጠቃላይ ቅበላው 30,643 ደርሷል፡፡ በዶክትሬት ዲግሪ ደረጃ ጠቅላላ ቅበላው በ1999 ከነበረው 258 በ2006 ዓ.ም 3,169 ደርሷል፡፡ ከአንድ የግል ተቋም በቀር ሁሉም የሦስተኛ (ዶክትሬት) ዲግሪዎች የሚሰጡት በመንግሥት ተቋማት ነው፡፡ በክልሎች በተለያዩ አካባቢዎች ፍትሃዊ የሆነ በከፍተኛ ትምህርት የመማር እድል ለመስጠትና አካባቢያው የኢኮኖሚ እድገት እንዲኖር ለማድረግ አዳዲስ ዩኒቨርስቲዎች በመቋቋም ላይ ይገኛሉ፡፡

በከፍተኛ ትምህርት የሴቶች ያለው ተሳትፎ መጨመር ይገባዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በቅድመ ምረቃ ትምህርት ያለው የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከጠቅላላው 32 በመቶ የደረሰ ሲሆን በ2007 ዓ.ም የነበረው የሴቶች ቅበላ ከጠቅላላው 38 በመቶ ነበር፡፡ በከፍተኛ ትምህርት ያለው የሴት ተማሪዎች ቁጥር ማነስ

ምክንያቱ አስራ ሁለተኛ ክፍል የሚያጠናቅቁት በቁጥር አነስተኛ መሆናቸው ነው። ከዚህ በተጨማሪ ስርዓተ ትምህርቱና አጠቃላይ የማስተማር ሂደቱ በስርአተ ፆታ ላይ በሚያሳድረው ተጽእኖ ምክንያት የአስራ ሁለተኛ ክፍል ፈተና የሚወስዱ ሴት ተማሪዎች ውጤት ዝቅ እንዲል አድርጎታል። (በ2007 ዓ.ም 34 በመቶ ሴቶች 350 ነጥብ እና በላይ ሲያገኙ የወንዶች ድርሻ 45 በመቶ ነው)።

### ጥራት

የከፍተኛ ትምህርትን የተቀላቀሉ ብዛት ያላቸው ተማሪዎች ከመግቢያ ፈተናው ዝቅተኛው የመግቢያ ነጥብ (50 በመቶ) በታች ያገኙ ናቸው። በተጨማሪ ለኢንጅነሪንግ ትምህርት መሠረት በሆነው በፊዚክስ ትምህርት የተማሪዎች ውጤት በጣም ዝቅተኛ ነው። ከዚህ ሌላ ትምህርታቸውን አጠናቀሙ የሚመረቁ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ብዛት ካጠቃላይ 79 በመቶ ነው። ይህ አነስተኛ አፈፃፀም የሚያመለክተው ምናልባት ጥራቱ ዝቅ ያለ የትምህርት አሰጣጥ መኖር ወይንም የሚሰጡት ኮርሶች አግባብነት አጠያያቂ ሲሆን ነው። በሌላ በኩል የማስተማር ጥራቱ ቢኖርም፣ ከፍተኛ ትምህርትን የሚቀላቀሉት የሚገቡት ተማሪዎች በዚህ ደረጃ ለመማር ዝግጅት የሌላቸው መሆናቸውን አመላካች ሊሆን ይችላል።

የትምህርት ጥራቱንና የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማሻሻል ከተወሰዱት በርካታ እርምጃዎች መካከል ወጥ የሆነ የቅድመ ምረቃ መርሃ ግብር ማዘጋጀት፣ አሳታፊ ትምህርት (active learning) ይኖር ዘንድ ሞድዩላር የማስተማር ዘዴ መጠቀም፣ በየዩኒቨርስቲው የጥራት ማረጋገጫ ጽ/ቤቶችን መክፈት እና ቤተመፃህፍትና ቤተሙከራዎች እንዲሟሉ የማድረግ ስራዎች ይገኙባቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ፣ የኢትዮጵያ የትምህርት ደረጃ ማእቀፍ (qualification framework) የማዘጋጀቱ ሂደት ከፍፃሜ ደረጃ ላይ የደረሰ ሲሆን፣ በ2 ቢሊዩን ብር በጀት በመካሄድ ላይ ያለው "የኢትዮጵያ የትምህርትና ጥናት ኔትወርክ" ፕሮጀክት በ2008 ዓ.ም ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል። ለዩኒቨርስቲዎች የሚደረገው ግብአት እጅግ ከፍተኛ ቢሆንም አሁንም ቢሆን የመፃህፍት፣ የማጣቀሻ መፃህፍት ፣ የላቦራቶሪና የወርክሾፕ ቁሳቁሶችና የኢንፎርሜሽን ኰምዩኒኬሽን ፋሲሊቲዎች ችግር እንዳለ ይነገራል።

በ2006 ዓ.ም በመደበኛ ትምህርት የመምህር ተማሪ ጥመርታውን 1:16 በማድረስ ከፍተኛ መሻሻል ታይቷል፡፡ (መደበኛና ኢ-መደበኛ ትምህርትን በድምር ስንመለከት ጥመርታው ወደ 1:23 ከፍ ያለ ነው)፡፡ ከኢንተርናሽናል ስታንዳርዱ (1:19) እና ከተመሳሳይ አገሮች ጋር ሲነፃፀር የመምህር ተማሪ ጥመርታው ጥሩ ደረጃ ላይ መሆኑን እናያለን፡፡ የመምህራኑን (21,109) የትምህርት ደረጃ ስንመለከት ግን በማስተማር ጥራት ላይ የሚኖረውን ተጽእኖ እንመለከታለን፡፡

ስብጥሩ (የባችለር፣ ማስተርስ እና የዶክትሬት ዲግሪ) 0:70:30 ይሆናል ተብሎ የታቀደ ቢሆንም አሁን ያለው ግን 27:58 :15 ደርሷል፡፡ እየታየ ያለው የተማሪዎች ቅበላ መጨመርና የድህረ ምረቃ ዲግሪ ያላቸው መምህራን አቅርቦት ሊጣጣሙ አልቻሉም፡፡ በዚህ ምክንያት ብዛት ያላቸው የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች የመጀመሪያ ዲግሪ ብቻ ያላቸው መምህራን እያስተማሩዋቸው ይገኛሉ፡፡ የዩኒቨርስቲዎች የቅበላ አቅም አሁን ባለው ፍጥነት የሚቀጥል ከሆነ፣ ተመጣጣኝ የእውቀትና ክህሎት ስብጥር ያላቸው በቂ መምህራን  መኖራቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

### ምርምር ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የማህበረሰብ አገልግሎት

ለምርምር የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ አነስተኛ ነው፡፡ በ2003 ዓ.ም ለምርምር የተመደበው በጀት ለዩኒቨርሲቲዎች ሁሉ ከተመደበው አጠቃላይ በጀት 1 በመቶ ብቻ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከፍተኛ ጥራት ያለው ምርምር ለማካሃድ ብቃት የለው የሰው ኃይል አነስተኛ ሲሆን፣ አብዛኛዎቹ ጥናቶች የሚካሄዱት በድህረ - ምረቃ ተማሪዎች ነው፡፡ የምርምር አግባብነትን ለማሻሻልና የቴክኖሎጂን እድገት ለማህበሪዊና አገራዊ ፍላጐት ለማዋል ይቻል ዘንድ፣ ተቋማት በመምህሮቻቸው አቅምና በአካባቢ ፍላጐት በመመስረት የምርምርና የምጥቀት ርዕሶቻቸውን ለይተዋል፡፡ ብሔራዊ የምርምር ሥራዎች ማእቀፍ (National Research Undertaking Framework) ከተጠናቀቀና የቅድሚያ የምርምር ርዕሶች ከተለዩ በኂላ በውድድር የበጀት ምደባ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እና የትምህርት ሚኒስቴር በጥምረት የሚመሩት ብሄራዊ ፎረም በማቋቋም ተቋማት ከኢንዱስትሪዎችና ከታላላቅ ፕሮጀክቶች ጋር በትብብር እንዲሰሩ የሚያስችል ሁኔታ እየተፈጠረ ነው፡፡ በቴክኖሎጂ

ተቋማትና በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲዎች የቢዝነስ ኢንክዩቤሽን ማእከላት የማቋቋም ጥረቶች በጥሩ ሁኔታ እየተካሄዱ ሲሆን፤ እነዚህም ጥሩ የገቢ ማስገኛ ምንጮች በመሆን ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

**ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዩች** (Cross cutting issues)

***ፆታና ትምህርት***

በትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የፆታ እኩልነትን በመፍጠር ሁሉም ህፃናትና ወጣቶች አቅማቸውን ሙሉ በሙሉ መጠቀማቸውን ለማረጋገጥ በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ግቦችና የድርጊት ፕሮግራሞች ታቅደው ነበር፡፡ በክልል ትምህርት ቢሮዎችና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የፆታ ቢሮዎችና ፎረሞች፣ የሴት ተማሪ ክለቦችና የሴት ማህበራት እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪ፣ ፆታ ነክ መመሪያዎች እንዲጠናከሩ ተደርገዋል፣ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የህይወት ክህሎት ስልጠና ማኑዋል ተዘጋጅተዋለ፣ ፆታ ነክ ትንኰሳዎችን ለመቀነስ የሚያስችል የስነ ባህርይ ደንብ ወጥቷል፡፡ ቀደም ሲል የነበረው የሴት ተማሪዎች ስትራተጂና የድርጊት እቅድ ወቅታዊ እንዲሆን ተደርጐ ለአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ዝግጁ ሆኗል፡፡ እነዚህ ጥረቶች በትምህርት መስክ የሴት ተማሪዎች ቅበላና ተሳትፎ እንዲጨምር በማሰብ የተከናወኑ ናቸው፡፡ የሁለቱም ፆታዎች ቅድመ መጀመሪያ ደረጃ ቅበላ በፍጥነት የጨመረ ቢሆንም የፆታ እኩልነት አመልካቹ (Gender parity Index) እንደሚያሳየው ግን በ2001 ዓ.ም የነበረው 0.98 በ2006 ዓ.ም ወደ 0.95 ወርዷል፡፡ በመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የፆታ እኩልነት እመርታ አሳይቷል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል የፆታ እኩልነት አመልካቹ በ2001 ዓ.ም ከነበረው 0.93 በ2006 ዓ.ም ወደ 0.91 ቢወርድም፣ በነዚህ ጊዜያት በሁለተኛው ሳይክል በብሄራዊ ደረጃ ከ0.94 ወደ 0.97 ሊያድግ ችሏል፡፡

ባለፉት አራት አመታት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አጠቃላይ ሴት ተማሪዎች ቅበላ በእጅጉ ከፍ ያለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ ደረጃ አንደኛ ሳይክል (9ኛ እና 10ኛ ክፍል) በ2001 ዓ.ም የነበረው 0.80 የፆታ እኩልነት አመልካች በ2006 ዓ.ም ወደ 0.94 ከፍ ሲል፣ በሁለተኛው ሳይክል (11ኛና 12 ኛ ክፍል) በተመሣሣይ ወቅት ከ0.46 ወደ 0.85 አድጓል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ በመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች

በፆታ እኩልነት አንፃር አሁንም ክፍተቶች አሉ። በተለይም የአንደኛ ክፍል የሴት ተማሪዎች ቅበላ ባለፉት ዓመታት እያደገ ቢሆንም፣ ከወንዶች ቅበላ አንፃር ሲታይ ግን በጣም ዝቅ ያለ ነው።

የፆታ ልዩነት ሲባል፣ በቅበላ ቁጥርና ክፍልን በማጠናቀቅ አንፃር ብቻ የሚወሰን ጉዳይ ሳይሆን፣ በትምህርት  ውጤታማ መሆንንም ይመለከታል። አስረኛ ክፍልን አጠናቀው አጠቃላይ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቅያ ፈተና በመውሰድ 2.00 እና ከዚያ በላይ ነጥብ የሚያገኙ ሴት ተማሪዎች ብዛት ከወንዶቹ ያነሰ ነው(የሴቶች 64 በመቶ ሲሆን የወንዶች 76 በመቶ ነው)። አስራ ሁለተኛ ክፍል በሚሰጠው የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተናም የመግቢያውን ዝቅተኛ ነጥብ (350 ነጥብ) እና ከዚያ በላይ ያገኙት ወንዶች ቁጥር 45 በመቶ ሲሆን የሴቶቹ 34 በመቶ ብቻ ነው።

በአንደኛ ደረጃ መምህርነት የሚሰለጥኑ ሴት ተማሪዎች ቁጥርም ከወንዶቹ በታች ነው (41 በመቶ ሴቶች ሲሆኑ 59 በመቶ ወንዶች ናቸው)። ቢሆንም ግን ከ2001 ዓ.ም እስከ 2006 ዓ.ም በነበረው ጊዜ የሴት ሰልጣኞች ቁጥር በዓመት 3.8 በመቶ እድገት ያሳዩ ሲሆን የወንዶች ደግሞ 3.4 በመቶ ነው። በሌላ በኩል በ2006 ዓ.ም የነበሩት አሰልጣኝ መምህራን ቁጥር 1974 ወንዶችና 182 ሴቶች ነበር።

ማንበብና መፃፍ ከማይችሉ አጠቃላይ ጐልማች 66 በመቶ ሴቶች ናቸው። የክልሎችን ሁኔታ ስናይ፣ ከወንዶች ይልቅ ያልተማሩ ሴቶች የሚበዙበት ክልል አፋር (ያልተማሩ ሴቶች 69 በመቶ ሲሆኑ ወንዶች 53 በመቶ ነው)  ሲሆን፣ ሶማሌ ክልል ይከተላል (68 በመቶ ሴቶች አልተማሩም)። በገጠር ከአስር ሴቶች መካከል ሰባት (71 በመቶ) ያልተማሩ ሲሆኑ፣ በከተማ ከአስሩ ሦስቱ (31 በመቶ) ያልተማሩ ናቸው። በወቅቱ በመካሄድ ላይ የሚገኘው የጐልማሶች ትምህርት ቅበላ፣ በሴቶች ቅበላ ላይ የተለየ ትኩረት በማድረግ ማንበብና መፃፍን 100 በመቶ ለማሳካት የተያዘውን አካሄድ የሚያመላክት አይደለም።

በቴክኒክና ሙያ ትምህርት የሚሰለጠኑ ሴቶች በ2001 ዓ.ም 46 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2004 ዓ.ም 51 በመቶ መድረስ ችሏል። ይህም በ2003 ዓ.ም ይደረስበታል ከተባለው ግብ ትንሽ ከፍ ያለ ነው። በክልሎች መካከል ልዩነቶች የሚታዩ ቢሆንም፣ በብሄራዊ ደረጃ ያለው መረጃ እንደሚያመለክተው

በአጭር ጊዜ ፕሮግራሞች (ደረጃ አንድና ሁለት) የሚሰለጥኑ ሴት ተማሪዎች ቁጥር በረዥም ጊዜ (ከደረጃ ሦስት እስከ አምስት ) ከሚሰለጥኑ በጣም የበዛ ነው። ለዚህ ምክንያቱ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት የሚሰጡት ስልጠናዎች አጫጭር በልምድ የሴቶች ናቸው በሚባሉት በቢዝነስ፣ ኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ እና በፀጉር ውበት እና በመሳሰሉት ፕሮግራሞች ስለሚያተኩሩ ነው።

በርካታ ዩኒቨርስቲዎች የሴት ተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል ቱቶርያል በመስጠት፣ የዩኒቨርሲቲ ፕረዚዳንቶች ተካፋይ የሚሆኑባቸው መደበኛ የትምህርት ፎረሞች በማዘጋጀት ፣በአገር አቀፍ ደረጃ የፆታ ትንኰሳን ለማስወገድ የሥነ ምግባር ደንብ በማውጣትና የህይወት ክህሎት ሞድየሎችን በማዘጋጀት ተጨባጭ የሆኑ እርምጃዎች ወስደዋል። እነዚህ ሁሉ ጥረቶች የተደረጉ ቢሆንም የሴቶች ውክልና በከፍተኛ ትምህርት ቅድመ ምረቃ ፕሮግራም 32 በመቶ በድህረ ምረቃ 19 በመቶ በመምህርነት ሙያ 12 በመቶ ብቻ የተወሰነ ሲሆን፣ በከፍተኛ የስልጣን ደረጃ የምትገኝ አንድ ሴት ብቻ ናት። (በእቅድ በዚህ ደረጃ ተይዞ የነበረው ቁጥር 16 ነበር)።

### የልዩ ፍላጐትና አካቶ ትምህርት

በኢትዮጵያ የሚገኙ የአካል ጉዳተኞች ህፃናት ቁጥር በትክክል አይታወቅም። የአለም ጤና ጥበቃ ድርጅት (WHO) የሚያወጣው የአካል ጉዳተኞች ግምታዊ ቁጥር ለእቅድ ማስፈፀሚያ አገልግሎት እየዋለ ይገኛል። በድርጅቱ የ2003 ዓ.ም ግምት መሠረት በማንኛውም ህብረተሰብ ከአጠቃላዩ ህዝብ 15 በመቶ ጉዳተኛ ተደርጐ ይታሰባል። በ4 እና 18 ዓመት እድሜ መካከል የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር ከ 33.5 ሚሊዩን በላይ ስለሆነ በዚህ ስሌት መሠረት በግምት 5 ሚሊዩን የሚሆኑ ተማሪዎች የልዩ ፍላጐት ትምህርት ተጠቃሚ መሆን ይገባቸዋል። በ2006 ዓ.ም ከአንደኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል በልዩ ፈላጐት ትምህርት የተመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር 77,850 (42 በመቶ ሴቶች ፣ 58 በመቶ ወንዶች) ነበር። በአሁኑ ጊዜ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ተመዝግበው የሚገኙ የልዩ ፍላጐት ትምህርት የሚያስፈልጋቸው ህፃናትን የሚመለከት መረጃ የሌለ ሲሆን በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ እቅድ የመጀመሪያው ዓመት መረጃውን ለማጠናቀር ታቅዷል። በአንደኛ ደረጃ ትምህርት የልዩ ፍላጐት

ትምህርት ያስፈልጋቸዋል ተብለው ከሚገመቱት ህፃናት 4 በመቶ ብቻ በመማር ላይ የሚገኙ ሲሆን ይህ ሁኔታ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም የማዳረሱን ጥረት የሚገድብ ነው፡፡

በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያለው የልዩ ፍላጐት ትምህርት ተሳትፎ በ2001 ዓ.ም ከነበረው 398 የመነሻ አሃዝ በአራተኛው የትምህርት ልማት ዘርፍ ፕሮግራም መጨረሻ በእያንዳንዳቸው ከ1000 በላይ መድረስ ችሏል፡፡ ከፍተኛ ትምህርት የሚገቡ የልዩ ፍላጐት ትምህርት ተማሪዎች ቁጥር ሊገደብ ከቻለባቸው ምክንያቶች አንዱ፣ አስራ ሁለተኛ ክፍልን የሚያጠናቅቁት አነስተኛ በመሆናቸው ነው፡፡ ወደ ከፍተኛ ትምህርት የሚገቡ የልዩ ፍላጐት ትምህርት የሚያሻቸው ተማሪዎች ቁጥር ለማሳደግ ይቻል ዘንድ መምህራን አግባብነት ያለው ክህሎት እንዲኖራቸውና የማስተማርያ ቁሳቁሶች በልዩ ሁኔታ ከማዘጋጀት በተጨማሪ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ የልዩ ፍላጐት ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት መስኮች የመካፈል እድል ስለማያገኙ፣ አብዛኛውን ጊዜ በልዩ ፍላጐት ትምህርት (Special Needs Education)ብቻ ሲመደቡ ይታያል፡፡

በአራተኛው የትምህርት ልማት ዘርፍ መርሃግብር ወቅት ልዩ ፍላጐት ያላቸውን ተማሪዎች በመርዳት አንፃር ለታየው ዝቅተኛ አፈፃፀም ምክንያት ከሆኑት ውስጥ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፣

- የንቃት ማነስ
- ከፌዴራል ጀምሮ እስከ ትምህርት ቤት ድረስ የልዩ ትምህርት ፍላጐትን ለማገዝ የሚያስፈልግ እውቀት፣ ክህሎትና ቆራጥነት አለመኖር
- የልዩ ፍላጐት ተማሪዎች ያሉበትን ሁኔታ በመረዳት ተገቢ መፍትሄ ለመስጠት ያለው መረጃ በቂ አለመሆን
- ከፌዴራል ጀምሮ እስከ ወረዳና ትምህርት ቤት ድረስ የልዩ ፍላጐት ትምህርትን ለማስተባበርና ለማስተዳደር የሚያስችል መዋቅር አለመዘርጋት
- የልዩ ፍላጐትና የአካቶ ትምህርት በፋይናንስ ሊደገፉ የሚችሉበት መንገድ አለመነደፉ

- የትምህርት ቤቶች መሠረተ ልማት ዝቅተኛ መሆን፣ ለልዩ ትምህርት የተዘጋጁ ማስተማሪያ መፃህፍት አለመኖርና ልዩ ፍላጐትን የሚመለከቱ የአሰራር ደንቦችና መመሪያዎች አለመኖር
- የልዩ ትምህርት ፍላጐት መምህራን የማስተማር ክህሎት ዝቅተኛ መሆን
- በአካቶ ትምህርት ማእከላትና በአካባቢ በሚገኙ የሳተላይት ትምህርት ቤቶች በመዘዋወር እንዲያስተምሩ የሚጠበቁ ተዘዋዋሪ መምህራንን ለማበረታታት ልዩ መዋቅር (career structure) አለመኖር።

## የሰው ልጅ የተፈጥሮ መከላከያ በኤች አይቪ ኤድስ መጠቃት

### ኤች አይቪ ኤድስና ትምህርት

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ኤች አይቪ ኤድስን ስርጭት ዝቅ ብሏል በ1993 ዓ/ም ከነበረበት 7.3 በመቶ 2004 ወደ 1.5 በመቶ ቀንሷል። ኤች አይ ቪ ኤድስ ከትምህርት ጋር የሚዛመደው በዋናነት በመከላከልና ስርጭቱን በመግታት ላይ ያለው ነው። ይህም ማለት ግንዛቤ መፍጠር ላይ ያተኮሩ ተግባራት ላይ ማቀድና መተግበር ነው።

በትምህርት ቤቶች የሚገኙ ወጣቶች የኤች አይቪ ኤድስ አጠቃላይ እውቀት መኖርና አለመኖር ለመፈተሽ የተደረጉ ጥናቶች ጥቂት ናቸው። በምስራቅ ኢትዮጵያ የተደረገ ጥናት እንደሚያለመክተው በትምህርት ቤት ውስጥ ከሚገኙ ወጣቶች አንድ አራተኛው ወይም ዕሩብ ያህሉ ወጣቶች ናቸው፡ አጠቃላይ የሆነ የኤች አይቪ ኤድስ አጠቃላይ እውቀት ያላቸው። ከወንድ ተማሪዎች ይልቅ ሴቶች ለኤች አይቪ የተጋለጡ ሆነው እያለ በተፃራሪው ስለኤች አይቪ ኤድስ ያላቸው የዕውቀት ደረጃ ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ነው። ሴት ተማሪዎች ከወር አበባ ጋር ተያይዞ እርግዝና ስለሚከስትባቸው ቀናት ተገቢው እውቀት ቢኖራቸውም ስለ እርግዝና አጠቃላይ የሆነ እውቀት የላቸውም። ከዚህ በተጨማሪ ሁለቱም ፆታዎች ስለኤች አይቪ ኤድስ መተላለፊያ መንገድ አጠቃላይ ግንዛቤ ወይም እውቀት ቢኖራቸውም በሽታው በተለያዩ መንገዶች ሊተላለፍ እንደሚችል የጠለቀ እውቀት የላቸውም።

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተደረገ ጥናት እንደሚያመለክተው በትምህርት ቤቶች የሚገኙ ወጣቶች በእድሜያቸው ምክንያት በሚኖረው ለአደጋ አጋላጭ የወሲብ ሁኔታዎች በኤች አይቪ ኤድስ የመያዛቸው ዕድል ሰፊ ነው። ከተገቢው ዕድሜ ቀድሞ ለወሲብ መነሳሳት፣ ከተለያዩ

ሰዎች ጋር ወሲብ በተደጋጋሚ መፈፀም፣ ዝቅተኛ የኮንዶም አጠቃቀምና ሁሌ ጊዜ ኮንዶምን አለመጠቀም፣ አደንዛዥ እጾች መጠቀም፣ በትምህርት ቤት የሚገኙ ወጣቶችን ለኤች አይቪ ኤድስ ተጋለጭ እንዳደረጋቸው ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ በዚህ የእድሜ ክልል በሚገኙ ወጣቶች በተደጋጋሚ በሚከሰቱ ያልተፈለገ እርግዝናና በውርጃና በወሲብ በሚተላለፉ በሽዎች ምክንያት የበሽታውን ስርጭት የከፋ ያደርገዋል፡፡

ትምህርት ቤቶችና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የፀረ- ኤች አይቪ ኤድስ ክበባትን እንዲመሰርቱ መደገፍ ይኖርባቸዋል፡፡ ኤች አይቪ ኤድስ በስርዓተ ትምህርቱ እንዲካተት፣ የት/ቤት ማህበረሰብ ውይይቶች፣ ወዘተ አጠቃላይ የወሲብ ትምህርት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም ባለፉት አራት አመታት የማህበረሰብ ውይይቶች በሁሉም ክልሎች በሚገኙ ት/ቤቶች እንዲተገበር ተደርጓል፡፡ በ2000/1 3,255 ት/ቤቶች የት/ቤት ማህበረሰብ ውይይቶችን መስርተዋል፡፡ በ2003/4 የት/ቤቶች ማህበረሰብ ውይይት ያቋቋሙ ትምህርት ቤቶች ቁጥር በአራት እጥፍ አድጓል፡፡

## ለተሻሻለ አስተዳደር አቅምን ማጎልበት

የአቅም ውስንነት ውጤታማ የሆነ የእቅድ ትግበራና አስተዳደር እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ በ2003 የአስተዳደርና እቅድ ጥናት ተካሂዷል፡፡ ይህ ጥናት የአቅም ግንባታ መርሃ -ግብር በፌደራልና ባልተማከለ ስርዓት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያለውን አስተዳደር ለማሻሻል ያቀደ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ ጥናቱ በክልል ደረጃ አጠቃላይ ስልታዊ እቅድ የማዘጋጀት ክህሎት እንደሚጎድል ለይቷል፡፡ የተለየው የክህሎት ክፍተት ሪፖርት በሴክተሩ ፓሊሲን ለመደገፍና በቂ በጀት ለመመደብ የሚረዳ የበጀት ትንተና፣ ትወራ ስልታዊ አማራጮችን ማመንጨት የሚያስችል እንዳልሆነ ተለይቷል፡፡

በጥር 2007 በፌደራል ደረጃ 2ኛው የአቅም ማጎልበት ጥናት ተካሂዷል፡፡ ይህ ጥናት የተለያዩ ጉዳዮችን ለይቷል፡፡ እነዚህም የሰው ሀብት አስተዳደርና አመራር አጠቃላይ ድክመቶች፣ የትምህርት ሚኒስቴርን ግብ/አላማ ከእስፔሽያላዜሽን ጋር ለማያያዝ የተለያዩ ዳይሬክቶሬቶችን መዋቅር ማሻሻል፣ የመረጃ ጥራት ፣ ተገቢነትና ወቅታዊነት መጓደል የአመራሩን አቅም ውጤታማ እንዳይሆን፣ የቁልፍ ተግባሮች አተገባበር ዝቅ እንዲል፣ የአመራሮችና የባለሙያዎች በተሎ መቀያየር፣ በቂ ያልሆነ ተግባራትን የመቀባበል ሁኔታ፣ በቂ ያልሆነ የልምድ ልውውጥ የተቋሙን አሰራር በእጅጉ እንደጎዱት ናቸው፡፡

የትምህርት ሚኒሰቴር የሰው ሃብት ልማት የስራ ሂደት አጫጭር ስልጠናዎችን፣ በዲግሪና በማስተርስ፣ በቁልፍ መደቦች/የስራ ዘርፎች ላይ እየሰሩ ላሉ የስራ ባልደረቦች ስልጠናዎችን በመስጠት አቅም ማጎልበቱን ደግፏል፡፡ የተጠናከረ መረጃ ባይቀርብም በክልል ደረጃም ተመሳሳይ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ለምሳሌ ባለፉት 3 ዓመታት የክልል አቅም ግንባታ የሚከተሉትን ተግባራት በማከናውን አቅም ግንባታውን ደግፎታል፡ 1) በእቅድ፣መረጃን መሰረት ባደርገ ክትትልና ሪፖርት አቀራረብ 10,074 ባለሙያዎች፣ ሱፐርቫይዘሮችና ር/መምህራን ስልጥነዋል፡፡ 2) በሁለት ክልሎች ለሚገኙ ት/ጽ/ቤቶችና የጉድኝት ማዕከላት 1,000 ኮምፒውተሮች አሰራጭተዋል፡፡ 3) የትምህርት የመረጃ ስርዓት ዩኒቶችን በኮምፒውተር በጂኦግራፊያዊ የመረጃ ስርዓት መሳሪያዎችና በዲጂታል ካሜራዎች አሟልተዋል፡፡ ሌሎች የአቅም ግንባታ ተግባራት የሚከተሉትን ያካትታል፡- በት/ሚ ለሚገኙ 7 ከፍተኛ የትምህርት ኦፊሰሮች በዓለም አቀፍ የትምህርት ሳይንስና ባህል ድርጅትና በአለም አቀፍ የትምህርት እቅድ ተቋም የተዘጋጀ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም ለ60 የት/ቢሮ ከፍተኛ የትምህርት ባሙያዎች፣ ከት/ሚኒስተርና ከዩኒቨርሲቲዎች ለተመለመሉ ሰዎች ለሁለት ሳምንታት በአመራርና በአስተዳደር ጥበብ ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎች፡- በችግር ፈች ጥበብ፣ በአይሲቲ፣ በግብ አጣጣልና በተግባር እቅድ፣ በግንኙነት፣ በግጭቶች አፈታትና በቡድን አመሰራረት ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡

የሚከተሉት ዋና ዋና ተግዳሮቶች ግን በዚያው ቀጠሉ፡፡ ለዚህም ዋን ምክንያት በሚከተሉት ጉዳዮች በቂ መረጃ አለመኖር ነው፡፡ ሀ) በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ በቅርብ ዓመታት የተሰጡ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች በቂ መረጃ አለመኖር  ለ) ከእነዚህ ስልጠናዎች ሁሉ በኋላ ያልተወገዱ ክፍተቶችን አለመገንዘብ፣ ቀሪ ተግባራትን በት/ሚኒስተር በሚገኙ ዳይሬክተሮቶች፣ በጥልቀት አለመገንዘብ፡፡  በት/ሚኒስተር  በክልል ት/ቢሮዎችና ከዚያም በታች ባሉ መዋቅሮች ያለ ደካማ የግንኙነት አግባብ፤ ከዚያም በተጨማሪ በወረዳዎችና በት/ቤቶች ደረጃ ያለ አጥጋቢ ያልሆነ የትምህርት የመረጃ ስርዓትና (በአቅም ውስንነት ምክንያት) የመረጃ ትንተና የስታፍ አባላት ውስን ክህሎትና ደካማ የሆነ የመረጃ ግንኙነት ቴክኖሎጂ መዋቅር ናቸው፡፡

## የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ትምህርት

በአከባቢ እንክብካቤና  በእድገት መካከል ያለውን ግንኙነት ግንዛቤ ለመፍጠር የአከባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ትምህርት ከዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ጋር ተያይዟል፡፡ ውጤታማ የሆነ የተፈጥሮ/ የአካባቢ እንክብካቤ አያያዝ፣ አስተዳደር ቀጣይ የሆነ የማህበራዊ  እድገትን ያመጣል፡፡ የስርዓተ

ትምህርት  ክለሳ በተደረገበት ጊዜ የአከባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ጉዳዮች በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ተካቷል፡፡ (የአካባቢ  ሳይንስ ትምህርት ከአንደኛ ክፍል እስከ 4ኛ ክፍል ወደ ሞጁሎች ማለትም በማህበራዊ ሳይንስ፣ በስነ-ዜጋና ስነ-ምግባር ትምህርቶች ስነ-ህይወት፣ ጂኦግራፊና ከሌሎች ጋር የተቀናጀ ሳይንስ)

ከዚህ በተጨማሪ መማር ማስተማሩን ለማጎልበት የመምህሩ መመሪያዎች ለሁሉም ት/ቤቶች ተሰራጭቷል፡፡ የመምህሩ መመሪያንም እንዴት እንደሚጠቀሙ ለብዙ ክልሎች ስልጠና ተሰቷል፡፡ (ለደ/ብ/ብ/ሕ፣ ለአማራ፣ ለኦሮሚያ፣ ለትግራይ፣ ለቤንሻንጉል ጉምዝና ለአዲስ አበባ) ተማሪዎችና መምህራን የትምህርቱን ይዘት ይበልጥ እንዲረዱትና የአካባቢያቸውን የማገገም ችሎታ እንዲያሻሽሉ ለማድረግ ቀጣይ ስልጠናዎች ይሰጣሉ፡፡

## ትምህርት በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች/በአደጋ ጊዜ ሁኔታዎች

ለሰብዓዊ ጥሪዎች የሚደረግን ስልታዊ ምላሽ አሰጣጥ ለማጠናከር በጥቅምት 2001 ከረጅ ድርጅቶች ጋር የትምህርት አስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች ተመስርቷል፡፡ በዚህም መስረት የዚህ የት/ት ጉድኝት ዋና አላማ በት/ሚ፣ በረጅ ድርጅቶችና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር የተሻለ ግንኙነት በመፍጠር ትክክለኛ ትንበያ፣ ተጠያቂነትና አጋርነት ተነሳሽነት ያለው ደረጃውን የጠበቀ ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል ነው፡፡ እንዲሁም ይበልጥ ስልታዊ ተግባራትን ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸው ተግባራት ካለ ሀብት ጋር ማቀናጀትና መጠቀም፡፡ ከጉድኝቱ ከፊል ስራዎች አንዱ በ2006 የታተመው «የኢትዮጵያ የአስቸኳይ ጊዜ የትምህርት ዝቅተኛ ስኬት» ይጠቀሳል፡፡ ይህ ጽሑፍ /ልኬት ዝቅተኛ የትምህርት ተደራሽነትና ጥራትን ያብራራል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው በኤጀንሲዎች በአስቸኳይ ጊዜ ዝቅተኛውን የትምህርት ልኬት የግንኙነት አግባብ ነው፡፡

ከ2003 እስከ 2007 በተደረገው ጥናት  በአስቸኳይ  ጊዜ/ በአደጋ ጊዜ  የተጠቁ ሕፃናትና የተሰጠው ምላሽ በዓመት በአማካይ የህፃናቱ ቁጥር ከ250,000 ወደ 385,000 ከፍ ብሎ እንደገና ወደ 181,000 ዝቅ ብሏል፡፡ በዚህ ወቅት 42% የሚሆኑት ህፃናት የገንዘብ ድጋፍ አግኝተዋል፡፡ ይህ ማለት በማንኛውም ዓመት ወደ 60% ለችግር የተጋለጡ ህፃናት ትምህርታቸውን መቀጠል የሚያስችል ድጋፍ አያገኙም ማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከዚህ አሐዝ ውጭ የኢትዮጵያ በአፍሪካ ከሚገኙ ስደተኞች ከፍተኛውን ቁጥር ይይዛል፡፡ በተለያዩ

የት/ት ደረጃዎች በተቻለው ሁሉ ከትምህርት ስርዓቱ ጋር የተቀናጁ አጫጭር  ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡

ለዚህ አጥጋቢ ላልሆነ ምላሽ ምክንያቱ ትምህርት ቤቶች ለክልሎች ፣  ክልሎች ለፌደራል የሚሰጡት ደካማ የመረጃ ልውውጥ  መኖሩ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ የእርዳታ ቁሳቁስ ጥያቄውንና የሚሰጠውን ምላሽ ያዘገየዋል፡፡ የአደጋ ጊዜ ችግርን ለመቋቋም የድርቅ፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮችን ለመቋቋም ህፃናት፣ቤተሰብ፣ ማህበረሰብና ስርዓቱ ዝቅተኛ የሆነ ድጋፍና ስልጠና ስለሚሰጣቸው ነው፡ ችግሩ የሚባባሰው፡፡

**ጤናና ሥርዓተ ምግብ በትምህት ቤት**

ብሔራዊው የጤናና ሥርዓተ ምግብ እስትራቴጂ መመሪያ እድሜያቸው ለትምህረት የደረሱ ህፃናትን የጤናና የምግብ ተደራሽነት ለማሻሻል የታቀደ/ የተዘጋጀ ነው፡፡ ይህን ስትራቴጂ አስመልክቶ ለክልሎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ 7 ሚሊየን የሚጠጉ እድሜያቸው ለትምህርት ደረሱ ህፃናትና ወደ ሶስት ሚሊየን የሚደርሱ ከትምህርት ቤት ውጭ የሆኑ ህፃናት ምግብ አጠር በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ ናቸው፡፡ የትምህርት ቤቶች ምገባ ፕሮግራም ለ670,000 ህፃናትና 43,000 በቤታቸው የሚያድጉ/ያሉ ሕጻናት በዓለም ዓቀፍ የምገባ መርሃ ግብር ታቅፈዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሴት ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ለሚልኩ አርብቶ አደር ክልሎች ልጆች ወደ ቤታቸው የሚወሰዱት ራሽን ይሰጣል፡፡ ይህ አገራዊ ፕሮግራም የሌሎች አንዳንድ ክፍሎች ተግባራትንና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሚመጡትን አይጨምርም፡፡ በአራተኛው የትምህረት ሴክተር የልማት እቅድ መጨረሻ ዓመት አገራዊ የትምህርት ቤቶች ምገባ ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ነበር፡፡  በተለያዩ ሚኒስተር መስሪያ ቤቶች የሚዋቀር አካል የድርጅቱን የት/ቤቶችን የመመገብ አቅም ያሻሽለዋል፡፡ ከተለያዩ አካባዎች ሀብት በማሰባሰብ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ያሳድጋል፡፡ በትብብር በመስራት ውጤታማትን ያሳድጋል፡፡ በቂ ውሃና የንጽህና ቁሳቁሶችን በማቅረብ በ2007 ት/ሚኒስቴር የዋን ዋሽን ስትራቴጂ መተግበር ጀምሯል፡፡ ይህ ስትራቴጂ በተጀመረበት ወቅት 40% የሚሆኑት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች 84% የሚሆኑትን የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶችና 100% የሚሆኑት ዩኒቨርሲቲዎች የውሃ አቅርቦት ተሟልቶላቸዋል፡፡ በሁሉም የትምህርት ተቋት በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የውሃ አቅርቦትና ንጽህና እስከመሚሟላ ጥረቱ ይቀጥላል፡፡

## አደንዛዥ እፆች መጠቀምን የመከላከል ትምህርት

በተወሰኑ የሀገሪቱ ክፍሎች ጫትና አልኮልን ሰዎች ሲያመርቱና ሲጠቀሙ ምዕተ አመታት ተቆጥረዋል፡፡ ይህ ቀጣይ የሆነው ማምረትና መጠቀም ከባህላዊ ተግባራት ጋር ይያያዛል፡፡ የእጾቹ ተጠቃሚዎች ስርጭት ዓለማቀፋዊ ሁኔታን የተከተለ ነው፡፡ ለምሳሌ የወንዶች የእጾች ተጠቃሚነት የጎላ ነው እንዲሁም በትምህርት ቤት ውስጥና ከት/ቤት ውጭ የሆኑ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ድሃ ወጣቶችን ያካትታል፡፡ ከ15-24 ዓመት እድሜ ክልል የሚገኙ 24,434 ወጣቶች (በት/ቤትና ከት/ቤት ውጭ ያሉ) አደንዛዥ እጽና የአልኮል መጠጥ እንደሚጠቀሙ መረጃዎች አሉ፡፡ በት/ቤት ካሉት ከእነዚህ ወጣቶች መካከል 0.4% የሆኑት በየቀኑ አልኮል መጠጥ ይጠጣሉ፡፡ 5.8% የሚሆኑት በሳምንት ጫት ይቅማሉ፡፡ ከት/ቤት ውጭ የሆኑት ወጣቶች 2.7% የሚሆኑት አልኮል በየቀኑና 13.3% የሚሆኑት በሳምንት ጫት ይቅማሉ፡፡ ካናቢስና ፈሳሾችን እንዲሁም ኮኬንን በት/ቤትና ከት/ቤት ውጭ የሆኑ እንደሚጠቀሙ ዘገባዎች ያስረዳሉ፡፡ (0.7% እና 3.8% በቅደም ተከተላቸው መሰረት).

አደንዛዥ እጾችን ለመከላከል ለሚረዱ ጥረቶች አካል እንዲሆን ትምህርት ሚኒስቴር ስምምነት ፈርሟል፡፡ አገራዊው የአደንዛዥ እጾች መከላከል ማስተር ፕላን (መሪ እቅድ) በአራተኛው የትምህርት ሴክተር የልማት እቅድ ዓመታት ተተግብሯል፡፡ ከዚህ ጋር በሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የትብብር ኮሚቴ ተመስርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ት/ሚኒስተር በ2007 በተባበሩት መንግስታት የአደንዛዥ እጽና ወንጀል መስሪያ ቤትና በሌሎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች በተመራ ሁኔታ ተጠቃልሎ በተዘጋጀ እቅድ ፈርሟል፡፡ ለ2007/8 ተግባራቱም የሚከተሉት ናቸው፡፡ የአደንዛዥ እጽ የመከላከል ስርዓተ ትምህርትን መከለስ፣ለሚመለከታቸው ቡድኖች ስልጠና ማዘጋጀትና ወደ ክልሎች ማውረድ፣ በአራተኛው የትምህርት ሴክተር ልማት እቅድ ዘመን ዘግይተው ተጀመሩና ውስን የሆኑትን የአደንዛዥ እጽ የመከላከል ተግባራትን አሳዩ፣ ምንም እንኳ አስተማማኝ የሆነ መረጃ ባይኖርም አንደኛው ተግባር የአደንዛዥ እጾች ነፃ ክበቦች በወጣቶች በት/ቤቶች መመስረት አንድ ተግባር ነው፡፡ ይህ ክበብ ከኤች አይቪ ኤድስ ክበብ ጋር ግንኙነት አለው፡፡ በተመሳሳይ ተቋማት የህይወት ክህሎት ስልጠና ከእነዚህ ክበቦች ጋር ተመስርቷል፡፡

በ2007 አማካይ የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር ከምግብ፣መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ጋር በመተባበር ለ70 ወጣቶች (ተማሪዎችን ጨምሮ) ከአዲስ አበባ ክፍለ ከተማዎች ለተውጣጡ የ3 ቀና ስልጠና መልመጃ ተሰጥቷል፡፡ ከ3 ቀናቱ ስልጠና በኋላ

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ለተከታታይ 8 ቀናት በከተማዋ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ሰጥቷል፡፡ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ እነዚህን ተግባራት በክልሎች በሚገኙ ቅርጫፎቹ ለማውረድ በዝግጅት ላይ ነው፡፡ በወጣቶች ፎረም አማካኝነት በአዲስ አበባ የተሰጡ ስልጠናዎች በትግራይ ለ330 ወጣቶች ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለአደንዛዥ እጾች መከላከያ ስልጠና የሚያገለግል መጽሐፈ እጽ (ለአሰልጣኞች) በ2006 በባለስልጣን መስሪያ ቤቱና በተባበሩት መንግስታት የአደገኛ እጾችና ወንጀሎች መከላከል ጽ/ቤት ተዘጋጀ፡፡

# የትምህርት ፖሊሲው መዋቅር /ፍሬም ወርክ/

3. የትምህርት ፖሊሲው መዋቅር /ፍሬም ወርክ /

ይህ ምዕራፍ 5ኛው የትምህርት ሴክተር ልማት እቅድ የትምህርት ፖሊሲ መዋቅርን ያሳያል፡፡ የትምህርት ፖሊሲው እንዴት እንደተዋቀረ ያብራራል፡፡ የእቅድ ቅደም ተከተሎችን ፣ ግቦችንና የሚጠበቁ ውጤቶችን ያመለክታል፡፡

**መግቢያ**

የ1987 የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ለ4 ዓመቱ መካከለኛ የትምህርት ሴክተር ልማት እቅድ አነሳሽ ነበር፡፡ አምስተኛው የትምህርት ሴክተር የልማ እቅድ ለኢትዮጵያ ከ2007/8 እስከ 2012/13 ለተዘጋጀው 5ኛው መካከለኛ የትምህርት ልማት እቅድ መነሻ ሰነድ ሆኖ አገልግሏል፡፡ ቁልፍ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መልዕክት ሆኖ ይቀጥላል፡፡

ትምህርት የህይወት ተሞክሮዎችን፣ አዲስ ግኝቶችን ለዘመናት የካበቱ ባህልና ልምዶችን ወጎችን ወዘተ የምናስተላልፍበት ሂደት ነው፡፡ ትምህርት ግለሰቦችና ማህበረሰብ የቀሰሙትን እውቀት ችሎታ ክህሎትና አመለካከቶችን ለእድገት እንዲያወሉት ያስችላል፡፡

ገጽታቸው ይለይ እንጂ አሁንም ውስብስብ የሆኑ የትምህርት ተገቢነት፣ጥራት፣ተደራሽነትና ፍትሀዊነት አሉ፡፡ የትምህርት ሴክተር የብዙሃኑን ፍላጎቶችና ተሞክሮዎች ያከብራል፡፡ ከመደበኛ ትምህርት ጀምሮ በሁሉም የትምህርት እርከኖች ያለው የግለሰብንና የማህበረሰብን የችግር ፈችነት ችሎታ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማድረግ እንጥራለን፡፡ ትምህርት ሰብዓዊ መብትን፣ የዲሞክራሲ እሴቶችን እኩልነትን፣ መግባባትና መረዳዳት በህዝቦች መሀከል እንዲሰፍን ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ ትምህርት እነዚህን ስራዎች ለመስራት ከጥናና ምርምር፣ ከተግባርና ከእድገት ጋር ተቀናጅቶ ነው ሁለንተናው የተሟ ማህበረሰብ መፍጠር የሚችለው፡፡

ትምህርት ለሰው ልጆች እድገት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ትምህርት መንግስት ለሚያካሂዳቸው የእድገት ስራዎችና ጥራቶች የቀድሚያ ትኩረት የሚሰጠው ነው፡፡ ትምህርት በተደራጀና በተመረጡ ተቋት ከሚመራ ስልጠና ጥናና ምርምርና እድገት ጋር በብዙ አውታሮች የተያያዘ የጠበቀ ቁርኝት አለው፡፡

ከሁሉም በላይ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲው ሰብዓዊ አመለካት ያላቸው ሀገራዊ ሀላፊነታቸውን የሚወጡ፣ የዲሞክራሲን ባህል የተላበሱ፣ አምራች፣አዳዲስ ነገሮችን

የሚፈጥሩ፣ የሚያደንቁማ በህብረተሰብ ግንባታ በብቃት የሚሳተፉና አካባቢያቸውን የሚንከባከቡ ዜጎችን ማፍራት ነው ዋናው ግቡ፡፡

ከዚህ በፊት እንደነበሩት የትምህርት ሴክተር የልማት እቅዶች ሁሉ 5ኛው የትምህርት ሴክተር የልማት እቅድ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲውን መሰረት ያደረገ ነው፡፡

5ኛው የትምህርት ሴክተር የልማት እቅድ በተመረጡ ጥቂት የፖሊሲ ቅድሚያ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ ለምሳሌ የመምህራንን ጥራት ማሻሻል ዋናና መሰረታዊ ክህሎትን ማሳደግ፣ የአቋራጭና የደጋሚ ተማሪዎችን ምጣኔ መቀነስ፣ የመካከለኛና የከፍተኛ ደረጃ ስልጠናዎችን ተገቢነት ማረጋገጥ፣ ውስን የሆነውን ሀብት ብዙ በሆኑት ቅድሚያ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ላይ ከማዋል ይልቅ፡ ለኢኮኖሚና ኢንዱስትሪያላይዜሽን ትኩረት ከሚሰጠው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይህ መንግስታዊ አገር አቀፍ የፖሊሲ ሰነድ በመጭው አምስት አመታት በኢኮኖሚው መዋቀር የሚጠበቁ ለውጦችን ግልጽ አድርጓቸዋል፡፡ የዚህ አንደምታ ለትምህርትና ስልጠናው እያደገ ለሚመጣው የኢኮኖሚና የምርት ሴክተር ዋናው የሰው ሃይል ምንጭ ነው፡፡ የ5ኛው የትምህርት ሴክተር የልማት እቅድ ቅድሚያ ትኩረቶች ከአገራዊና አለምአቀፋዊ ስምምነቶች ለምሳሌ ከትምህርት ለሁሉም የህፃናት መብቶች ድንጋጌና ቀጣይነት ካለው የልማት ግቦች ጋር የተጣጣመ ነው፡፡

እያደገ ከመጣው የህዝብ ምጣኔ ጋር የሚሄዱ ወጭዎችን ማስተዳደር ቀላል አይደለም፡፡ በተለያዩ ሴክተሮችና ሚኒስተር መሰሪያ ቤቶች በሁሉም ደረጃ በሚገኙ የትምህርት መዋቅሮች ጠንካራ አመራር ፣ አቅጣጫ የግንኙነት አግባብና ትብብር ያስፈልጋል፡፡ ይህ ጥራት በጸደቀ የትምህርት ህግ ሊደገፍ ይገባል፡፡ በአሁኑ ሰዓት የትምህርት ህጉ በፌደራል ደረጃ በትምህርት ሴክተር ልማት እቅድ የትምህርት ህጉ በድራፍት ደረጃ ነው፡፡

በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በትምህርት ሴክተር የምንጠብቃቸውን የተሻሻሉ ውጤቶች ለማስመዝገብ ከዚህ በፊት ውጤታማ የሆኑ አካሄዶቻችን መለየትና መስፋት ይኖርባቸዋል፡፡ ሀገራዊ የልማት ግቦችን ለማሳካት ለህፃናት፣ ወጣቶችና ጎልማሳዎች የሚሰጡ መሰረታዊ የክህሎት ስልጠናዎች ላይ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ የሚከተሉት የቅድሚያ ትኩረቶች የእቅድ ግቦችና ውጤቶች በተለዩ ተግዳሮቶች ሊበረታቱና ቅድሚያ ትኩረት ለሚሰጣቸው መረሃ-ግብሮችና ስልቶች ጥርጊያውን ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

**የቅድሚያ ትኩረቶች**

**በኢትዮጵያ ትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ የቅድሚያ ትኩረቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡**

- ለተጎጂ ቡድኖች የተለየ ትኩረት በመስጠት ለሁሉም እኩል እድልና ተሳትፎ መስጠት
- የሁሉንም ህፃናት፣ ወጣቶችና ጎልማሶች የትምህርት ፍላጎት የሚያሟላ ጥራት ያለው ትምህርት መስጠት
- ለማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ እድገት በእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ብቁ ዜጎች ማፍራት
- ብቁ አመራርና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ሀብትን በአግባቡ በመጠቀም የትምህርት ግቦችን ለማሳካት ህፃናት፣ ወጣቶችና ጎልማሶች የጋራ እሴቶችንና ልምዶችን እንዲጋሩ ብዙሃነትን እንዲያደንቁና እንዲተገብሩ መርዳት

**የመርሃ ግብሮች የቅድሚያ ትኩረት አጠቃላይ መዋቅርና ምርጫ**

ለ5ኛው የትምህርት ሴክተር ልማት መርሃ ግብር 6 የቅድሚያ ትኩረት መርሃ-ግብሮች ተመርጠዋል፡፡ የቅድሚያ ትኩረት መርሃ ግብሮች  በትምህርት እርከኖች ይመራሉ፣ የሁሉንም የትምህር ሴክተር ግቦችና ስልቶች ያንፀባርቃሉ (ከቅድመ መደበኛ እስከ ከፍተኛ ትምህርት)፡፡ በአጠቃላይ ትምህርት ሁለት የቅድሚያ ትኩረት መርሃ-ግብሮች ተጨምረዋል፡፡ እነዚህም ጥራት፣ አቅርቦት፣ ፍትሃዊነትና ውስጣዊ ብቃት ናቸው፡፡ በሌሎቹ እርከኖች ጥራት፣ አቅርቦትና ብቃት በአንድነት ነው የሚታዩት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለእቅዱ ትግበራ ነው ትኩረት የተሰጠው፡፡ ለአስተዳደራዊ ጉዳዮችም ትኩረት ተሰጥቷል፡፡

በ5ኛው የትምህርት ሴክተር የልማት መርሃ ግብር ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው መርሃ-ግሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- አቅም ግንባታ ለተሻለ አስተዳደር
- አጠቃላይ ትምህርት ጥራት
- አጠቃላይ ትምህርት፡- አቅርቦት፣ ፍትሃዊነትና ውስጣዊ ብቃት
- የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት
- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና
- ከፍተኛ ትምህርት

**የእቅድ ግቦች**

**ለተሻለ አስተዳደር አቅም ግንባታ**

**በትምህርት ሴክተር ለተሻለ አስተዳደር አቅም ግንባታ ማለት፡-**

የትምህርት ስርዓቱን አስተዳደር ማሻሻል ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ የተቋሙ አፋጻጸምና የተማሪዎች ውጤት መሻሻል ነው፡፡ ይህ ሊመጣ የሚችለው ውሳኔዎች ሲወሰኑና ሲተገበሩ ነው፡፡

**አላማዎችና ተግባሮች**

የትምህርት አስተዳደሩ የመጨረሻ አላማ ለሁሉም ተማሪዎች ጥራት ያለው የትምህርት አገልግሎት መስጠት፣ ሁሉም ክልሎችና ወረዳዎች በሰው ሃይል፣ በገንዘብና በንብረት አስተዳደር በራሳቸው የመወሰን ስልጣን አላቸው፡፡ ወረዳዎች የት/ቤቶችን ፍላጎት መሰረት በማድረግ በጀት ይመድባሉ፡፡ የት/ቤቶች አመራርና ለማህበረሰቡ የት/ቤቱን አስተዳደር ውሳኔ ለማሻሻል የሚረዳቸውን መረጃ ይሰጣቸዋል፡፡ 5ኛው የትምህርት ሴክተር የልማት መርሃ ግብር የትምህርት የሴክተሩን አስተዳደር ብቁና ውጤታማ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ይህ የትምህርት ሴክተሩ የአስተዳደር መዋቅር እንደገና መታየት ይኖርበታል፡፡ በተለይ በሁሉም ደረጃ የሚገኙ ሰራተኞችን ሃላፊነትና ተጠያቂነትን፣ ለምሳሌ የትምህርት ሚኒስቴርንና የክልል ትምህርት ቢሮዎችን ተጠያቂነት፣ ከሀብት ጋር የተያያዙ ውጤቶችንና ግቦችን በተመለከተ በትምህርት ሚኒስቴር በክልል ትምህርት ቢሮዎች፣ በቴክኒክና ሙያ ቢሮዎችና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጠንካራ አመራርና አቅጣጫ መስጠት በጣም ወሳኝ ነው፡፡

የሰው ሃይሉ የክህሎት ደረጃና አቅም፡- ስራ አፈጻጸም፣ አስተዳደራቸውና የእቅድ መሳሪያዎቻቸው ለምሳሌ ባላንስድ ከኮር፣ ካርድ ቢኤስሲና በቅድሚያ የሚሰራው፡፡ አቀራረቡ ከ4ኛው የትምህርት ሴክተር የልማት መርሃ-ግብር ትምህርት በመውሰድ በአዲሱ የትምህርት ሴክተር የልማት መርሃ ግብርና በአዲሱ ብሔራዊ የትምህርት ስልታዊ እቅድና በትምህርት ሚኒስተር በአመታዊና ወርሃዊ እቅዶች፣ በዳይሬክቶሬቶች፣ በክልች ፣ በዞኖች፣ በዩኒቨርሲቲዎችና በወረዳዎች የተሻሻለ ተያያዥነት አለው፡፡

አስተዳደሩ በትክክል እንዲሰራ መረጃ በመሰብሰብ፣ በመተንተን ለውሳኔ ማዋል ይኖርበታል፡፡ የአስተዳደር ስርዓቱ በፍጥነት ምላሽ መስጠት እንዲችል በስራ አፈፃፀም ላይ በቂ መረጃ ሊኖር ይገባል፡፡ የትምህርትን ጥራት ለማሻሻል ለቴክኒክና ሙያ ተቋማትና ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደረጃ የበለጠ በራስ የመወሰን ስልጣን ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ይህ ከጥራትና ብቃት ተጠያቂነት ይገናኛል፡፡ የስራ አፈፃፀምን መረጃ መጋራት በፈፃሚዎች መካከል ያለውን መቀናጀት ያሻሽለዋል፡፡ የሌሎች ተግባራት መፈጸም መቀናጀቱን ያጠናክረዋል፡፡

የትምህርት የበጀት ስርዓት ብቃት ለማሻሻል ጥገና ያስፈልጋል፤ በተለይ በቴክኒክና ሙያ ተቋማትና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደረጃ ከተማሪዎች ፍላጎትና ከጥራት ማረጋገጫ ስርዓት ጋር የተያያዘ ምላሽ ሰጭ የገንዘብ ስርዓት ይፈጠራል፡፡ አዲስ የገንዘብ አስተዳደር ስርዓት፣ እቅድና የሪፖርት ስርዓት ይገነባል፡፡ ሰራተኞችም ይሰለጥናሉ፡፡

በመጨረሻም ውጤታማ አስተዳደር ተወዳዳሪ ሰራተኞችና በቂ ሀብት ያስፈልገዋል፡፡ ለሁሉም የስራ ደረጃዎች የሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብሮች ይዘረጋሉ፡፡ የሰራተኞችን የአፈፃጸም ክኂል ለማሻሻል ሁሉም ቢሮዎች አስፈላጊ የሆነው ሀብት ይሰጣቸዋል፡፡

## የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት

የአጠቃላይ ትምህርትን ጥራት ማሻሻል ግቡ፡- ህፃናትን ምርታማና ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጋ ለማድረግ፣ የመጀመሪያ ደረጃና የ2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ ማነቃቃትና እውቀት ክህሎትና እሴት መስጠት፡፡

## አላማና ተግባራት

የትምህርትን ጥራት ለማሻሻል ትልልቅ ጥረቶች እየተደረጉ ነው፡፡ ከእነዚህ ጥረቶች በኂላ ሚመጣው ትምህርት ስርዓት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ በሚችሉት ለመጀመሪያ ክፍሎች መሰረት ለሆኑት ክሂሎች ትኩረት መስጠት ይኖርበታል፡፡ ት/ቤቶች በምክርና ተገቢ በሆነ ሀብት ሊደገፉ ይገባል፡፡ መምህርነት የሚመርጡት ሙያ ይሆናል፡፡ የመምህሩንና የአመቻቹን ክህሎት የሚያሻሽሉ ብሔራዊ የመምህር ሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብሮች ይዘጋጃሉ፡፡ በሚከለሰው/እንደገና በሚታየው የሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር የፔዳጎጅ ክሂል፣ ዋናና መሰረታዊ የማንበብና የመፃፍ፣ የስሌትና የአፍ መፍቻ ቋንቋ ክሂልና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ቅድሚያ

ይሰጣቸዋል፡፡ የሙያ ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ስርዓት ሁሉም መምህራን ብቃት ያላቸው እንደሆኑ ያረጋግጣል፡፡

የት/ቤት ር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች በት/ቤት አመራርና አስተዳደር ላይ ባተኮረ የሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር ሊደገፉ ይገባል፡፡ ይህ ማለት ብቃት ያለው የትምህርት ማረጋገጫ ስርዓት አንዱ አካል ማለት ነው፡፡ ለሂሳብና ሳይንስ ትኩረት በመስጠት የት/ቤት ስርዓተ ትምህርት ክለሳና ዘመናዊ ማድረግ ይቀጥላ፡፡ ይህ የሚሆነው ኢኮኖሚው ለሚፈልገው ምላሽ ለመስጠትና በጥሩ የመማሪያ ቁሳቁሶች በማዘጋጀትና በማሰራጨት ለመደገፍ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን መጠቀም ተማሪዎችና መምህራን ክሂሉንና ቴክኖሎጂውን እንዲያጎላብቱና ወደፊት ኢትዮጵያ የምትፈልገውን የስራ ሀይል ማፍራት እንዲቻል ነው፡፡

እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የትምህርት ቤት ማሻሻያ እቅድን እንዲያዘጋጅ ይበረታታል ይደገፋል፡፡ ትምህርት ቤቱ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማሟላት እንዲችል በት/ቤት ድጎማ በጀት ይደገፋል፡፡ ት/ቤቱ ለተማሪዎች ጥራት ያለው አካባቢና ትምህርት ማሟላት እንዲቻል ስልታዊ ዕቅድ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ እያንዳንዱ የት/ቤት ማሻሻያ እቅድ ውጤታማ የት/ቤት ፋሲሊቲዎች ከማሟላትና ጥሩ የትምህርት አካባቢ ለመፍጠር ከማቀድ በዘለለ መሄድ ይኖርበታል፡፡ የት/ቤት ማሻሻያ እቅድ ዋናና መሰረታዊ ክህሎት ለተማሪዎች በብቃት መስጠቱን ማረጋግጥ አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መምህራን በደንብ የሰለጠኑና የሚዘጋጁ እንዲሁም ህብረተሰብ ት/ቤቱን መደገፍን ማረጋገጥ አለበት፡፡ የት/ቤት መሻሻል እቅዶች ለዋናና መሰረታዊ ክሂሎችና ውጤቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት የለውጥ ሞተር ሆነው ሊወሰዱና ሊተገበሩ ይገባል፡፡ የት/ቤት ኢንስፔክሽ ስርዓት ይዘረጋል፡፡ በቁሳቁስ/በሃብት ይደራጃል፡፡ የትምህርቱን ስርዓት አፈፃፀም ለመቆጣጠር ብሔራዊ የተማሪዎች ውጤት ምዘና ይካሄዳል፡፡

**አጠቃላይ ትምህርት፡- አቅርቦትና ጥራት**

የአጠቃላይ ትምህርት ግብ አቅርቦትና ጥራትን ማሻሻል ነው፡፡ የአጠቃላይ ትምህርት ዓላማ ሙሉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን (8 ዓመት) እና 2 ዓመት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ ሁሉንም ህጻናት ለቅደመ መደበኛ ትምህርት አቅርቦት ማብቃት ነው፡፡

**ለላማና ተግባራት፡-** ሁሉም ህፃናት የትምህርት አቅርቦት ይሟላላቸዋል፡፡ የተማሪዎችን ተሳትፎ የሚገድቡ ይወገዳሉ፡፡ ጥሩ የሆነ የህፃናት አያያዝ ይኖራል፡፡ ይህም ማለት ማንም

ህፃን በዝቅተኛ ገቢ፣ በፆታ፣ በዘር፣ በቦታ፣ በአካል ጉድለት አድልኦ አይፈጸምበትም፡፡ የፖሊሲው አላማ በማንኛውም ደረጃ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማንም ህፃን ከት/ቤት ውጭ አይሆንም፡፡ ከፖሊሲው ግቦች ለመድረስ የትምህርትም ሆነ ሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ኃይሎች የተግባር ዕቅድና የተግባር ስልት ጨምሮ ፣ በጀት ፣ ሊያዘጋጁ ይጋባል፡፡ ተግባርና ኃላፊነታቸውንም ሊወጡ ይገባል፡፡

ሥርዓቱ በሁሉም ክልሎች የቅድመ-መደበኛ ትምህርት አቅርቦት ያገኙ ሕፃናትን ቁጥር ለመጨመር ጥረት ያደርጋል፡፡ ከሁሉም በፊት ትኩረቱ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ለተጎጅ ቡድኖች እንዲሆን ይጥራል፡፡ በመጨረሻም የሙሉቀን ትምህርት እንዲኖር፣በተለይ ለሴቶች ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ከዚህም በላይ የተማሪዎች ትምህርት ማጠናቀቅና ተሳተትፎ የቅድሚያ ትኩረት ነዉ፡፡ በተለይ በመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክልና በሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል፡፡ ሁሉም ወጣቶች የመጀመሪያ ደረጀ ትምህርታቸዉን እንዳጠናቀቁ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ይበረታታሉ፡፡ ትምህርት ሚኒስቴር ከት/ቢሮዎች ዞኖችና አስፈላጊ ሲሆን ከወረዳ ትምህርት ጽ /ቤቶች ጋር በመሆን በቂ የሆኑ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ባሉበት ፖሊሲዎችን ያረጋግጣሉ፡፡

መንግስት ከፍተኛ ለሆነው የደጋሚ ምጣኔ ምክንያቶችን ይመረምርና የሚቀንስበትን በመጨረሻ የሚጠፋበትን ፖሊሲ ይቀይሳል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ህፃናት ትምህርት የሚያቋርጡበት ምክንያቶች ይጠኑና ህፃናት ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ የሚያግዝ ፖሊሲ ይቀመጣል፡፡ ከትምህርት ስርዓቱ እንዲያቋርጡ የሚያደርጉ ጉዳዮች ጨርሰው እንዲጠፉ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪ ድጋፍና ሀብት በተደጋጋሚ አደጋ ለሚያጋጥማቸው ትምህርት ቤቶችና መምህራን ይሰጣል፡፡ ይህ ስልት ከውጫዊ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውጭ በሆነ መንገድ ትምህርት እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡

በከተማም ይሁን በገጠር ተጎጂ አካባቢዎች ተለይተው/ተነጥለው የሚገኙ የገጠር አካባቢዎችና ዝቅተኛ ማህበራዊ ህይወት በሚኖሩ አካባቢ ያሉ ከሌሎች አካባቢዎች እኩል የሆነ የአራተኛ ክፍል የትምህርት አቅርቦት አይኖራቸውም፡፡ ማንም ወላጅ ልጁ ትምህርት ቤት እንዳይገባና ትምህርቱን እንዳይቀጥል የሚያደርግ የገንዘብም ችግር በሚያጋጥመው ሁኔታ መሆን የለበትም፡፡ በሩቅ አካባቢ ወይም ወረዳዎች ያሉ ህፃናት እንደ ጎርፍ ወዘተ በመሳሰሉ ጂኦግራፊያዊ መሰናክሎችና መልካምድራዊ ችግሮች ለምሳሌ በትራንስፖርት ምክንያት ሕጻናት

ከትምህርት ስርዓቱ እንዳይኖሩ መሆን የለበትም። ለተጎዱ አካባቢዎች ትምህርት ለመስጠት ለአካባቢው አስተዳደር ሃላፊነት መስጠት።

የስርዓተ ጾታ ጉዳይ በሁሉም የት/ት እርከኖች ችግር ያለበት ሆኖ ቀጥሏል። የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተማሪዎች ጉዳይ ችግር እንደሆነ ቀጥሏል። የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተማሪዎች እስከአሁን በበቂ ሁኔታ ትምህርት እያገኙ አይደለም። በሴቶች ትምህርት ተሳትፎ ላይ እንቅፋት የሚሆኑ ምላሽ ያገኛሉ። ስለሆነም ለወንዶችና ለሴቶች እኩል የሆነ የትምህርት ተሳትፎ ይሆራል። በትምህርት ስርዓቱ ለወንዶችና ሴቶች መምህራን እኩል እድል/አጋጣሚ ይኖራል። የልዩ ፍላት ተማሪዎች ፖሊሲ ስሚቀረጽ የልዩ ፍላት ተማሪዎች እርዳታና ድጋፍ የማግኘት እድል ይኖራቸዋል። እርዳታና ድጋፋም የገንዘብም፣ የገንዘብም ያልሆነ ስለሚሆን በትምህርታቸው እንዲበረታቱ ያደርጋል።

### ጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት

### ለጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ግቦች የሚከተሉት ናቸው፡-

ከእድሜ ልክ የትምህርት እድል ጋር የተያያዙ የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት በመስጠት የሚማር ማህበረሰብ መፍጠር፣ የብዙሀኑን የትምህርት ፍላጎት የሚመልስ የትምህርት ስርዓት መዘርጋት፤ ለግል፣ ለማህበረሰብና ለኢኮኖሚ እድገት የሚያበረክቱ፡ ህብረተሰብ መፍጠር።

**ዓላማዎችና ተግባራት፡-** ቁልፉ የፖሊሲው ዓላማ መደበኛ ያልሆነ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ተሳትፎን ማሳደግ ነው። በዚህ ዙሪያ የሚያበረታቱ መሻሻሎች ተከናውነዋል። የዚህም ውጤት ላለፉት አስር ዓመታት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በ2000 ዓ.ም ከነበረበት 34% በ2011 ወደ 52% አድጓል። ይህም ሆኖ በአፍሪካ ካሉ የሰብ ሰሃራ አገሮች ዝቅተኛው ነው። ገና ማደግ ይኖርበታል።

ቀጣይነት ያለው የንባብና የጽሑፍ አካባቢ ለመፍጠር ይበልጥ የተቀናጀ የጎልማሶች ትምህርት ለማህበረሰቡ መሰጠት ይኖርበታል። ዝቅተኛ የንባብና የጽሑፍ ልኬትም ሊወጣለት ይገባል። የጥራት ማረጋገጫ ስርዓትም ይዘረጋል።

ለአመቻቾችና ለጎልማሶች ትምህርት ቱቶሮች አንድራጎጂን ዋና ይዘቱ ያደረገ የሥልጠና መርሃ ግብር ይሰጣል። ጎልማሶችን ለማስተማር የሚረዱ ጠቃሚ የሆኑ ጥራት ያላቸው የማስተማሪያ

ቁሳቁሶች በዕዉነተኛው የሕይወት ጎዳና የሚተገበሩ ማዘጋጀት ይቀጥላል፡፡ ትምህርት ቢሮዎች ተገቢና ተማሪዎችን ማዕከል ያደረገ ስርዓተ ትምህርት በቋንቋቸው ጎልማሶቹ በሚማሩበት ቋንቋ ያዘጋጃሉ፡፡ ይህ በወረዳ ደረጃ ለተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት የመማሪያ ቁሳቁሶች ለማዘጋጀት መሪ ይሆናል፡፡ የጎልማሶች የንባብ፣ የጽሑፍና ስሌት መርሀ ግብር በትምህርት ተገቢነት ይጠናከራል፡፡ በተለይ ለሴቶች የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ተመራቂዎች በመደበኛና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና እንዲቀጥሉ ዕድል ይፈጠርላቸዋል፡፡

**የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና**

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ግብ ሚከተለው ነው፡፡ በፍላጎት የሚመራ ጥራት ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና በፍላጎት በሚመራ የቴክኖሎጂ ሽግግር፤ ለድህነት ቅነሳ፤ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ‹‹ በዝቅተኛና በመካከለኛ ደረጃ ተወዳዳሪ፣ የተነቃቃ ከአካባቢው ጋር የሚስማማና አዳዲስ ነገሮችን የሚፈጥር የሥራ ኃይል መፍጠር ››

**ዓላማና ተግባራት**፡- የዚህ ፖሊሲ ዓላማ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናን መጠን፣ ጥራት፣ ውጤታማነትና ተቀባይነትን መጨመር ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የኮርሶችንና የቴክኖሎጂዎችን ተገቢነት በማሳደግ ወደ ኢንዱስትሪ መሸጋገር ነው፡፡ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ሥርዓት የኢንዱስትሪ ባለቤትነትን በመደገፍና በማሳደግ የዚህን ፖሊሲ ዓላማዎች ማሟላት ይችላል፡፡ ዋናው የተግባር ትኩረት በተገቢው ደረጃ ጥራት ያላቸው የኢንዱስትሪ አሰልጣኖች እድገት ነው፡፡ በኢንዱስትሪና በማሰልጠኛ ተቋማት ትብብር የስራ መያዣ ልኬት (occupational standard) እድገት ይዘጋጃል፡፡ ደረጃውን የጠበቀ የመመዘኛ መሳሪያዎች ኢንዱስትሪዎችን በሚመዝኑ የእንዱስትሪ መዛኞች ይዘጋጃሉ፤ ያጋጇቸውንም መሳሪያዎችኢንዱስትሪዎችን ለመመዘን ይጠቀሙባቸዋል፡፡

የቴክኒክና ሙያ ስልጠና አሁን ያሉትንና በማስፋፋትና በማሳደግ ወደፊት አዳዲሶችን በመክፈት አቅርቦቱ ያድጋል፡፡ ስለዚህ ተገቢነት ያለው ስልጠና በወረዳዎች ይኖራል፡፡ ብዙ ሰዎች/ሰልጣኖች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና እንዲመዘገቡ በማስቻል አቅርቦቱን ማሳደግ ይቻላል፡፡ ከዚህ በፊት ያልነበረ ተገቢነት ያለው ስልጠና ይኖራል፡፡ ብዙ የማለፊያ መንገዶች ይዘጋጃሉ፡፡ ስለዚህም ብዙ የስልጠና ዓይነቶች ይኖራሉ፡፡ ለምሳሌ የአጭር ጊዜ፣ መደበኛ፣ መደበኛ ያልሆነ፣ በሥራ ቦታ የሥራ ላይ ስልጠና፣ የብዙ ውህዶች/ቅንጅቶች የሥራ

ላይ ስልጠና፣ ከሥራ ውጭ፣ ከአንድ ዓመት እስከ ሶስት ዓመታት የሚደርሱ ስልጠናዎች ይሰጣሉ። የኢንዱስትሪ ተቀጽላ አገልግሎቶች ክሂልን፣ ተቋማዊ አስተዳደርን ምርታማነትን ማሳደግ፣ ተገቢነትና ተወዳዳሪነትን ማይክሮና ትንንሽ ኢንተርፕራይዞች ይደግፋሉ። እነዚህ ተግባራት በቴክኒካዊና በሥራ ልምድ ሙከራ ክህሎት፣ ወንድ የእጅ ሙያተኛና ሴት የእጅ ሙያተኞችን ጥራት ያላቸው ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን የማምረት ሂደቱን እነዚህ ማይክሮና ትንንሽ ኢንተርፕራይዞች ይደግፋሉ ።

## ከፍተኛ ትምህርት

የከፍተኛ ትምህርት ግብ የሚከተለው ነው፡-

"በተለያዩ መስኮች ተገቢው ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ያላቸው ተወዳዳሪ፣ ተመራቂዎችን ማፍራት፣ በማህበረሰብ ፍላጎትና በሀገር ዕድገት ተመስርቶ የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማምጣት የሚችል ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ በትምህርትና ጥናትና ምርምር በምክንያት፣ በዲሞክራሲ፣ በብዙሃን ባህልና እሴቶች በመመስረት የነጻነት መርሆችን ማለትም የአመለካከትና የሀሳብ ልውውጥን ማሳደግ"

**ዓላማና ተግባራት ፡-** የፖሊሲው ዓላማ የከፍተኛ ትምህርትን መጠንና ጥራት ማሳደግ ነው። ዩኒቨርስቲዎችን በማስፋፋትና በማጠናከር ተማሪዎችን የመቀበል አቅማቸውን ማሳደግ። አዳዲስ ዩኒቨርስቲዎች ይገነባሉ፡፤ ነባሮች ይጠናከራሉ። በተጎጂዎችና በሌሎች መካከል ላለው የተሳትፎ ልዩነት ምላሽ ይሰጣል። በዩኒቨርስቲዎች የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ ማሳደግ፣ ሴት መምህራንን በማስተማር፣ በጥናትና ምርምር፣ በአመራርና በአስተዳደር፣ በከፍተኛ ትምህርት ማሳደግ ዋና የፖሊሲ ዓላማዎች ናቸው። የአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ በዩኒቨርስቲዎች እንዲያድግ ትኩረት ይሰጣል።

የመንግስት ወጭን ለመቀነስና ፍትሐዊ የሀብት ክፍልን በሴክተሩ ለማስፈን አዲስ የወጭ መመለስ ፖሊሲዎች ይፈተሻሉ፣ በዩኒቨርስቲዎችና በቀጣሪዎች ያለውን የግንኙነት አግባብ በማሻሻል በተመራቂዎችና በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ባለው የቅጥር ገበያ መመጣጠንን ይበልጥ ለማረጋገጥ፣ የዩኒቨርስቲዎች መምህራን የትምህርት ደረጃ ይሻሻላል። (ወደ ሁለተኛ ዲግሪና ሶስተኛ ዲግሪ)

የዩኒቨርስቲዎች የጥናትና ምርምር አቅም በውጤት ተኮር ሥርዓት የማህበረሰብና የሀገር ዕድገት የሚያጎለብቱ ጥናትና ምርምሮችና ተመራማሪዎችን ዕውቅና በመስጠት፣ በመሸለም ይጎለብታል፡፡ በፖሊሲዎች በተቋማት መካከል የሚደረግ የጥራት ማረጋገጫ ሥርዓት የመሰረታል፣ የመርሃ ግብሮች የግምገማ ሥርዓትና ክለሳ ይቀጥላል፡፡ በየኒዓለም አቀፍ ተቋማት መካከል ሚኖረው ትብብር ይቀጥላል፡፡

**የሚጠበቁ የእቅድ ውጤቶች**

እዚህ የተገለጹ ውጤቶች ከ5ኛው የትምህርት ሴክተር ልማት መርሀግብር ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ የውጤት አመልካቾች መጠንን፣ጥራትንና ወቅታዊነትን በእያንዳንዱ አውድ የሚጠበቁ ውጤቶችን ለመለካት የተቀረጹ ናቸው፡፡ 5ኛው የትምህርት ዘርፍ የልማት መርሀ ግብር የተቀረጸው በተዋረድ ወደ ክልሎችና ወረዳዎች ዓመታዊ ዕቅድ እንዲወርዱ ተደርጎ ነው፡፡ የእነዚህም የክልሎችና ወረዳዎች ዓመታዊ ዝርዝር ዕቅዶች ከ5ኛው የትምህርት ዘርፍ የልማት ዕቅድ ትልልቅ ግቦችና ዓላማዎች የሚቀዱ ናቸው፡፡ የዚህ የ5ዓመት ዕቅድ የመጨረሻ ዓላማ የሁሉንም ተማሪዎች የመማር ውጤት ማሻሻል ነው፡፡ የሕጻናትን፣ የወጣቶችንና የጎልማሶችን የትምህርት ዕድል የሚያሻሽሉ ስልቶች ተመርጠው ተቀርጸዋል፡፡ ሁሉም ጥረቶች ተቀናጅተው እነዚህን የሚጠበቁ ውጤቶች ያሻሽላሉ፡፡

የተቀረጹ ስትራቴጂዎች ወደሚጠበቁ ውጤቶች እየመሩ መሆኑን ለመከታተል የተማሪና የስርዓት አፈጻጸም ውጤት በቋሚነት መለካት ይኖርበታል፡፡ ይህ የሚጀምረው በክፍል ውስጥ በሚካሄደው ተከታታይ ምዘናና በትምህርት ቤት ደረጃ በሚካሄዱ የማጠቃለያ ፈተናዎች ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመለኪያ መሳሪያዎች በቋሚነትና በተወሰነ ጊዜ ለሚሰጡ የትምህርት ዕድገት ምዘናዎች ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡ እነዚህ የመመዘኛ መሳሪያዎች የአጠቃላይ ትምህርት ውጤትንና ወደ ከፍተኛ ትምህርት ውጤት የሚደረግ ዕድገትን ለማወዳደር ይረዳል፡፡ የመሻሻል ምጣኔው በአንድ የትምህርት ዕርከን ከሌላው እርከን ዝቅተኛ ከሆነ ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገበውን የትምህርት ዕርከን ለማሻሻል የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች/ቁሳቁስ የማሟላት ሥራ ይሰራል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሠንጠረዥ ለ5ኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሀግብር የተመረጡ የትምህርት ውጤቶችን፣ የሚለኩ ግቦችንና ቁልፍ የትግበራ አመልካቾች ያሳያል፡፡ ይህ ዝርዝር በትግበራ፣ በክትትልና በግምገማ ምዕራፍ ዋና ማጣቀሻ ሆኖ ይደገማል፡፡

**ሠንጠረዥ 12፡ ለ5ኛው የትምህርት ዘርፍ የልማት መርሀ ግብር ቁልፍ የትግበራ አመልካቾች (በአስፈላጊው ቦታ ግቦች ሴት/ወንድ በሚል ተገልጸዋል፤ ሁሉም በመቶኛ ተገልጸዋል ካልተብራሩ በቀር)**

| ቁልፍ የትግበራ አመልካቾች<br><br>ሁሉም ግቦችአስፈላጊ በሆነበት ሴት/ወንድ ተብለው የተገለጹት፤- ተገለጹጽ በመቶኛ ናቸው በሌላ ካልተገለጹ በቀር | መነሻ<br><br>(2006/7)<br><br>(ካልተብራራ በቀር) | 2008/9 | 2009/10 | 2010/11 | 2011/12 | 2012/13 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ገንዘብና አስተዳደር | | | | | | |
| ለትምህርትና ስልጠና የመንግስት፤የሕዝብ ወጭ | 22.3<br><br>2005/2006 | 25.0 | 25.0 | 25.0 | 25.0 | 25.0 |
| ዓመታዊ የሥራ ዕቅዶች (ሁሉም ተግባሪ አካላት) ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን በብቃት የመለሱ | N.A | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የት/ቤት ሪፖርት ካርድ የተቀበሉ ት/ቤቶች (ለዕቅድና አስተዳደር እንደ ግብዓት ለመጠቀም) | 0 | 10 | 20 | 30 | 40 | 50 |
| 5ኛውን የትምህርት ሴክተር መርሃ ግብር ተግባሪ አካላት (ፌደራል፤ዳይሬክቶሬቶች፤የቴክኒክና ሙያ ት/ት ስልጠና ኤጀንሲ፤ት/ቢሮዎች፤ ዩኒቨርስቲዎች፤) ከብዙ ዓመታት ስልታዊ ዕቅድ | መረጃ ያልተገኘለት | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| አቅርቦት | | | | | | |
| የቅድመ መደበኛ ጥቅል ቅበላ ምጣኔ | 33/35 | 48/50 | 56/58 | 64/65 | 72/73 | 80/80 |
| የአንደኛ ክፍል ንጥር ቅበላ | 102/109 | 102/107 | 101/105 | 100/103 | 99/100 | 98/98 |
| ከ1ኛ- 4ኛ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጥቅል ቅበላ | 131/143 | 122/132 | 120/129 | 118/124 | 116/120 | 115/115 |
| ከ1ኛ- 4ኛ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ንጥር ቅበላ | 104/112 | 104/110 | 103/107 | 102/105 | 101/103 | 100/100 |
| ከ5ኛ-8ኛ የጥቅል ቅበላ ምጣኔ | 63/65 | 67/70 | 74/75 | 82/83 | 90/90 | 95/95 |
| ከ5ኛ-8ኛ የንጥረ ቅበላ ምጣኔ | 50/49 | 53/52 | 56/55 | 59/59 | 62/62 | 65/65 |
| ከ1ኛ-8ኛ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ጥቅል ቅበላ | 98/105 | 93/102 | 96/103 | 99/105 | 102/106 | 106/106 |
| ከ1ኛ-8ኛ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ንጥር ቅበላ | 90/95 | 91/95 | 93/96 | 94/96 | 96/97 | 98/98 |

| ቁልፍ የትግበራ አመልካቾች<br><br>ሁሉም ግቦችአስፈላጊ በሆነበት ሴት/ወንድ ተብለው የተገለጹት፤-ተገለጹጽ በመቶኛ ናቸው በሌላ ካልተገለጹ በቀር | መነሻ<br><br>(2006/7)<br><br>(ካልተብራራ በቀር) | 2008/9 | 2009/10 | 2010/11 | 2011/12 | 2012/13 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ከ9ኛ-10ኛ የጥቅል ቅበላ ምጣኔ | 37/40 | 41/44 | 48/50 | 55/55 | 62/62 | 74/74 |
| ከ9ኛ-10ኛ የንጥር ቅበላ ምጣኔ | 21/20 | 24/20 | 28/28 | 34/34 | 41/41 | 47/47 |
| በቴክኒክና ሙያ ስልጠና በመደበኛው የተመዘገበ ቁጥር | 265745 | 280006 | 304775 | 365154 | 447248 | 564054 |
| የዲፕሎማ ፕሮግራም ጥቅል ቅበላ ምጣኔ | 6/13 | 7/13 | 8/14 | 10/15 | 12/16 | 14/17 |
| ከ15-60 ዓመት ጎልማሶች የ2 ዓመት የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ያጠናቀቁ | 0/0 | 30/55 | 47/67 | 79/87 | 98/99 | 100/100 |
| ብቃት | | | | | | |
| 1ኛ ክፍል መጠነ ማቋረጥ | 23/21 | 20/19 | 17/15 | 13/12 | 9/8 | 5/5 |
| ከ1ኛ-8ኛ መጠነ ማቋረጥ | 11/11 | 10/10 | 9/9 | 7/7 | 4/4 | 2/2 |
| ከ1ኛ-8ኛ መጠነ ደጋሚ | 8/9 | 7/7 | 6/6 | 4/5 | 3/3 | 2/2 |
| 5ኛ ክፍል የመድረስ ምጣኔ | 54/57 | 59/57 | 62/61 | 64/63 | 68/68 | 70/70 |
| 8ኛ ክፍል የማጠናቀቅ ምጣኔ | 47/47 | 50/50 | 55/55 | 61/61 | 67/67 | 74/74 |
| ማይክሮና ትንንሽ ተቋማት | 428529 | 429608 | 430864 | 437337 | 448008 | 464169 |
| 1ዓመት የዲፐሎማ መርሀግብር የማጠናቀቅ ምጣኔ | መረጃ ያልተገኘለት | 95/95 | 95/95 | 95/95 | 95/95 | 95/95 |
| ጥራት | | | | | | |
| የቅድመ መደበኛ መምህራን (የቅድመ መደበኛ ሕጻናት አያያዝና ትምህርት ዲፕሎማ ያላቸው) | 0/0 | 0/0 | 2/2 | 5/5 | 9/9 | 15/15 |
| ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ለደረጃው የሚመጥኑ መምህርን (የተመረቁ) | 63/48 | 70/58 | 77/68 | 84/79 | 92/89 | 100/100 |
| ከ1ኛ-12ኛ ክፍል የሙያ ፈቃድ ያገኙ መምህራን | 0/0 | 10/10 | 21/21 | 38/38 | 55/55 | 70/70 |
| የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደረጃ 3ና በላይ የሆኑ | 21 | 29 | 37 | 44 | 52 | 60 |
| የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደረጃ 3ና በላይ የሆኑ | 30 | 36 | 42 | 48 | 54 | 60 |
| ከ1ኛ - 12ኛ ክፍል የዲጂታልቴክኖሎጅ ትምህርት የሚሰጡ | 46 | 53 | 63 | 73 | 79 | 83 |

| ቁልፍ የትግበራ አመልካቾች<br><br>ሁሉም ግቦችአስፈላጊ በሆነበት ሴት/ወንድ ተብለው የተገለጹት፤- ተገለጹጽ በመቶኛ ናቸው በሌላ ካልተገለጹ በቀር | መነሻ<br><br>(2006/7)<br><br>(ካልተብራራ በቀር) | 2008/9 | 2009/10 | 2010/11 | 2011/12 | 2012/13 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የቴክኒክና ሙያ ስልጠና አጠናቀው የብቃት ፈተና ያለፉ | 60 | 63/63 | 66/66 | 69/69 | 72/72 | 75/75 |
| የቴክኒክና ሙያ ሥራ የመያዣ ልኬት ተረጋገጠ (በሁሉም የቅድሚያ ትኩረት ዘርፎች (በቁጥር) | 650 | 701 | 738 | 775 | 812 | 850 |
| በዩኒቨርስቲዎችየመምህራን ምጣኔ (ዲግሪ፣ ማስተር፣ዶክክትሬት) | 27:58:15 | 22:60:18 | 16:65:24 | 11:65:27 | 5:68:27 | 0:70:30 |
| ፍትሃዊነት | | | | | | |
| ጾታዊ ምጥጥን/ንጽጽር በቅድመ መደበኛ | 0:95 | 0:96 | 0:97 | 0:98 | 0:99 | 1:00 |
| ጾታዊ ምጥጥን/ንጽጽር ከ1ኛ-8ኛ | 0:93 | 0:94 | 0:95 | 0:96 | 0:98 | 1:00 |
| ጾታዊ ምጥጥን/ንጽጽር ከ9ኛ-12ኛ | 0:91 | 0:92 | 0:94 | 0:96 | 0:98 | 1:00 |
| በመደበኛው ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሴቶች ተሳትፎ | 51 | 50 | 50 | 50 | 50 | 50 |
| በዲፕሎማ መርሀ ግብርየሴቶች ተሳትፎ | 32 | 34 | 36 | 38 | 41 | 45 |
| በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት የሴቶች ተሳትፎ | | 56 | 62 | 67 | 69 | 70 |
| የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ቅበላ መጠን ከ1ኛ-8ኛ | 4 | 18 | 32 | 47 | 61 | 75 |
| የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ቅበላ መጠን ከ9ኛ-12ኛ | 7 | 15 | 22 | 30 | 37 | 45 |
| በርዕሰ መምህርነትና በሱፐርቫይዘርነት የሴቶች ድርሻ | 8 | 9 | 10 | 13 | 16 | 20 |
| ውጤቶች | | | | | | |
| የ2ኛ ክፍል ተማሪዎች ከቋንቋ ክህሎት ልኬት በታች ወይም በላይ | ሰንጠረዥ 7ን ይመልከቱ | | 60/60 | | | 95/95 |
| የ2ኛ ክፍል ተማሪዎች ከቋንቋ ክህሎት ልኬት የደረሱ ወይም በላይ | ሰንጠረዥ 7ን ይመልከቱ | | 40/40 | | | 70/70 |
| የቅድመ መደበኛ ተማሪዎች የሂሳብ ልኬት የደረሱ ወይም በላይ የደረሱ | | | | | 70/70 | |
| የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች በትምህርት ቅበላ ጥናት በአማካኝ 50%ና በላይ ውጤት ያስመዘገቡ | 25<br><br>(2005) | 35/35 | | | | 50/50 |

| ቁልፍ የትግበራ አመልካቾች<br><br>ሁሉም ግቦችአስፈላጊ በሆነበት ሴት/ወንድ ተብለው የተገለጹት፤- ተገለጹጽ በመቶኛ ናቸው በሌላ ካልተገለጹ በቀር | መነሻ<br><br>(2006/7)<br><br>(ካልተብራራ በቀር) | 2008/9 | 2009/10 | 2010/11 | 2011/12 | 2012/13 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በትምህርት ቅበላ ጥናት በአማካኝ 50%ና በላይ ውጤት ያስመዘገቡ | 8<br><br>(2005) | 30/30 | | | | 50/50 |
| የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በትምህርት ቅበላ ጥናት በአማካኝ 50%ና በላይ ውጤት ያስመዘገቡ | 23 | | | 50/50 | | |
| የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች በትምህርት ቅበላ ጥናት በአማካኝ 50%ና በላይ ውጤት ያስመዘገቡ | 34 | | | 70/70 | | |
| በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና 2.00 እና በላይ ያስመዘገቡ ተማሪዎች | 64/76<br><br>(2007/8) | 68/78 | 73/81 | 78/84 | 84/87 | 90/90 |
| በከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና 350 እና በላይ ያስመዘገቡ (የተፈጥሮ ሳይንስ) | 41/51 | 47/56 | 54/61 | 61/66 | 68/71 | 75/75 |
| በከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና 350 እና በላይ ያስመዘገቡ (የማህበራዊ ሳይንስ) | 21/32 | 28/37 | 35/42 | 42/47 | 49/52 | 56/57 |
| በጥቅም ሰጭነታቸው የተለዩና ወደ ማይክሮና ትንንሽ ኢንተርፕራይዞች የተቀየሩ ተፈላጊ ቴክኖሎጂዎች (በቁጥር) | 2627 | 3252 | 3623 | 4066 | 4635 | 5442 |
| በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቀዉ በ12 ወራት ውስጥ ሥራ የተቀጠሩ | መረጃ ያልተገኘለት | 80 | 80 | 80 | 80 | 80 |

## ምዕራፍ/ክፍል 3

## ቅድሚያ የሚሰጣቸው መርሃ ግብሮች

### የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ቅንጅት

የትምህርት ሥርዓቱ ከትምህርት ዘርፉ ጋር ብቻ ያልተያያዙ ከሌሎች ዘርፎች ጋር የሚያያዙ ብዙ ችግሮች ይገጥሙታል፡፡ እነርሱም ከዚህ በታች በቀረቡት ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ይመደባሉ፡፡

- ሥርዓተ ጾታ

- ልዩ ፍላጎትና አካቶ ትምህርት

- ኤች አይቪ ኤድስ

- ትምህርትን በአደጋ /አስቸጋሪ ጊዜ ማስቀጠል

- ጤናማ የትምህርት ቤት አካባቢና ሥርዓተ ምግብ

- አደገኛ መድሃኒቶችና እጾች ስርጭትን መከላከል

- የትምህርት ቤት ውሃ አቅርቦት፣ንፅህናና ስነ ጤና

እነዚህ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች የእያንዳንዱ ንዑስ ሴክተር ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ ጠቃሚው ነገር እነዚህን ተግዳሮቶች ለማስወገድ የሚረዱ መርሀ ግብሮችና ተግባራት በእያንዳንዱ ንዑስ ዘርፍ ውስጥ አሉ፡፡ በእያንዳንዱ ንዑስ ዘርፍ ውስጥ ያሉ ተግባሪዎችና አካላት ለሚወክሉት ንዑስ ዘርፍ ውጤታማ ለሆነ ትግበራ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ሊሰማቸው ይገባል፡፡ ሙሉ የሆነ የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ጥምረት አቀራረብ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን የሴክተሩ ዋና የተግባር አካል ማድረግን ያረጋግጣል፡፡ ይህም ማለት ሁሉም ተግባሪ አካላት የጋራ ኃላፊነት አለባቸው ማለት ነው፡፡

ይህ ዕቅድ የእነዚህን ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ጭብጥ ከንዑስ ዘርፎች ጋር ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ለማድረግ ይጥራል፡፡ ለምሳሌ የፆታ ምጥጥን ስትራቴጂ በየቦታው ይገኛል፡፡ የአደገኛ መድሃኒቶችና እፆች ጉዳይ በመምህራንና በአመራር ልማት፣ ከተቋማት ፋሲሊቲዎች፣ ከአቅርቦትና ከጥራት ጋር ተያይዞ ቀርቧል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ትምህርትን በአደጋ /አስቸጋሪ ጊዜ ማስቀጠል፣ በአቅርቦትና በፍትሀዊነት፣በመምህሩ ክህሎት፣ በሥርዓተ ትምህርት ይዘትና በመማሪያ ቁሳቁሶች ተካቷል፡፡ እነዚህ ወሳኝ ጉዳዮች ብዙውን ጊዜ ትኩረት ስለሚነፈጋቸው ነው ዋና የእቅድ አካል (mainstream) የሚደረጉት፡፡ ስለዚህ የቅድሚያ ትኩረት መርሃግብሮች ከቀረቡ በኋላ በማጠቃለያ ምዕራፍ የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ተቀናጅቶ የተካተተው፡፡ ይህ ምዕራፍ በሁለት መንገዶች ጠቃሚ ነው፡፡ 1.እነዚህ ጉዳዮች በዕቅዱ በብቃት መታየታቸውን ለማረጋገጥ፡፡ 2.ዋና ዋና መርሃ ግብሮችን በመከለስ እያንዳንዱን ጉዳይ አንባቢዎች በቀላሉ እንዲገነዘቡና እያንዳንዱ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች በዕቅዱ የት እንደሚገኙ ለመለየት ይረዳል፡፡

**ሠንጠረዥ 13 ፡ የ5ኛው የትምህርት ዘርፍ የልማት መርሃ ግብር የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ቅንጅት**

| ሥርዓተ ፆታ | ልዩ ፍላጎትና አካቶ ትምህርት | ኤች አይቪ ኤድስ | ትምህርትን በአደጋ /አስቸጋሪ ጊዜ ማስቀጠል | ጤናማ የትምህርት ቤት አካባቢ.ና ሥርዓተ ምግብ | አደገኛ መድሃኒቶችና እጾች ስርጭትን መከላከል | የትምህርት ቤት ውሃአቅርቦት፣ንፅህናና ስነ ጤና |
|---|---|---|---|---|---|---|

ይህ አቀራረብ ከ4ኛው የትምህርት ዘርፍ የልማት ዕቅድ በጣም የተለየ ነው፡፡ በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ የልማት እቅድ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች በራሳቸው የቅድሚያ ትኩረት መርሃ ግብር ሆነው ነው የተካተቱት፡፡ እንደአለመታደል ሁኖ የእነዚህ መርሃ ግብሮች መኖር በትግበራ ጊዜ ትኩረት እንዲሰጠቸው መተማመኛ ሊሆን አልቻለም፣ በተቃራኒው ሆነ እንጂ፡፡ 4ኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ትግበራ በሚተነተንበት ጊዜ የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ትግበራ ከሚጠበቀው ጋር ሲነጻጸር በጣም ደካማ ነበር ፡፡ የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች አቀራረብ በ4ኛው ትምህርት ዘርፍ የልማት መርሃ ግብር የጋራ ተግባርን የሚያነሳሳ አልነበረም፡፡ የተለያዩ መርሃ ግብሮች መኖር (ለእያንዳንዱ ጉዳይ) ሙያተኖችን እነዚህን ጉዳዮች አንደኛው ንዑስ ዘርፍ ለሌላኛው ንዑስ ዘርፍ በመተው ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ትኩረት እንዲነፈጉ አድርጓል፡፡ ምንም እንኳን የዕቅዱ ቅድሚያ የትኩረት ነጥቦች ቢሆኑም የንዑስ ዘርፎች ቅድሚያ ትኩረቶች እንዲሆኑ አልተደረገም፡፡

ይህ በጣም አስቸጋሪ የሚሆነው የተለየ ኃላፊነት የሚወስድ በሌለበት ጊዜና ለጉዳዮች የተበጀተ ገንዘብ በሌለበት ጊዜ ነው፡፡ ለስርዓተ ፃታ፣ ለልዩ ፍላጎትና ኤች አይቪ ኤድስ በፌደራል ደረጃ ዳይሮክቶሬት ወይም አስተባባሪ እንዲሁም በተዋረድ መዋቅር ካላቸው በስተቀር በሌሎች ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች አተገባበሩ ደካማ ነበር፡፡ ውጤታማ የሆነ የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች መርሃ ግብር ትግበራን ለማረጋገጥ 5ኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር የሚከተሉት ተግባራት እንዲከናወኑ ያስገድዳል፡፡ ብሄራዊ አቅዱ ወደ ዳይሬክቶሬት፣ ክልል፣ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና፣ በዩኒቨርስቲዎች እቅድ ሲመነዘር እያንዳንዱ ዘርፈ ብዙ ጉዳይ ለተለያዩ አስፈጻሚ አካላት ዋና ጉዳይ ሆኗል፡፡ ምክንያቱም የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች የንኡስ ዘርፍ መርሃ

ግብር ዋና ክፍል ሆነው የንኡስ ዘርፍ ፈጻሚዎች ኃላፊነት ነው፡፡ ከዚህ በኋላ የሌላ ክፍል ወይም አካል ኃላፊነት ተደርገው አይወሰዱም፡፡

የዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን ለሚተግብሩ አካላት ተጨማሪ ድጋፍ ለመስጠት በተሻለ የልማት አስተዳደር አቅም ግንባታ የእነዚህን የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ስትራቴጂ አተገባበር እንዴት እንደሚቀናጅና እንዴት መቆጣጠር እንደሚቻል በአቅም ግንባታው ተካቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እነዚህ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ጠንካራ የሆነ የብዙ ዘርፎች ቅንጅትና ትብብር አስፈላጊ ሲሆን ከሌሎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና ዘርፎች ጋር ግንኙነት ይመሰርታል፣ ያጠናክራል፡፡

በፌደራልና በክልል ደረጃ ትብብራቸውን ለማሳለጥ ከዕቅድ ሂደት ውጤታማ ግንኙነትና የቁጥጥር ቡድን ይቋቋማል፡፡ በእያንዳንዱ ዞን አስፈላጊ ሲሆን በወረዳ፣ በቴክኒክና ሙያ፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የዚህ ዓይነት ኃላፊነት በሌለበት ተጠሪ በማስቀመጥ የሁሉንም ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ይከታተላል፡፡ ይህ መዋቅር የሌሎችን ኃላፊነትና ተጠያቂነት ለምሳሌ የኤችአይቪ ኤድስ፣ ስርዓተ ፆታ፣ ልዩ ፍላጎት ትምህርትን ተግባርና ኃላፊነት አይደግምም፡ ነገር ግን ይደግፋቸዋል፡፡ ሁሉም ሙያተኞች በሁሉም ደረጃ የጋራ ግቦችን በመተግበር ሙሉ ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን ያረጋግጣል፡፡

እነዚህን ጉዳዮች አካቶ የመስራት ተግባር ሙሉ ለሙሉ ለማሳካትና ለማረጋገጥ አምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር የሚከተለውን አቅዷል፡፡ የብሔራዊው እቅድ ወደ ዳይሬክቶሬቶች ክልሎች ቴ/ሙ/ት/ስ ና ዩኒቨርስቲዎች እቅድ ሲወርድ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች በየአንዳንዱ ንኡስ ዘርፍ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ እነዚህ ጉዳዮች የእያንዳንዱ ግለሰብ እንጂ የሌላ አካል ጉዳዮች አይሆኑም፡፡

የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን ለማስተባበርና ለማስፈፀም የሚያስፈልገውን አቅም ለማሳደግ የሚያስፈልገው ስትራቴጂ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ሥራው ዘርፈ ብዙ በመሆኑ የሌሎች ዘርፎችን ትብብር በመጠየቅና ግንኙነት በመፍጠር እንዲጠናከር ይደረጋል፡ በፌዴራልና በክልል ደረጃ የውጤታማ ተግባቦትና የአፈፃፀም ክትትል ክፍል በእቅድ ውስጥ ተካቶ እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡ በዞን፣ በወረዳ፣ በቴ/ሙ/ት/ስ ና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደግሞ ሥራዎችን የሚከታተል ተጠሪ ይመደባል፡፡ ይህ መዋቅር ቀደም ሲል የነበሩት በኤች አይ ቪ /ኤድስ የሥርዓተ-ፆታና የልዩ ፍላጐት ትምህርት ያለውን

ሚና አይደግምም ይልቁንስ እነሱን በማገዝ የተለያዩ ኃላፊዎች ሙሉ በሙሉ ኃላፊነታቸውን በመወጣት ላይ መሆናቸውን ይከታተላል።

**ቅድሚያ የተሰጣቸው ፕሮግራሞች መርሃ ግብሮች**

**ይህ ክፍል የአምስተኛውን የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ዝርዝር ቅድሚያ የሚሰጣቸው መርሃ ግብሮችን እቅድ ይዟል።**

- እያንዳንዱ መርሃ ግብር ወደ ተለያዩ ክፍሎች ተከፋፍሎ እያንዳንዱ ክፍል ደግሞ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ማብራሪያና ስትራቴጂ ይዟል።
- በተጨማሪ ከመለከያና ከመነሻ ዓላማ ካደረገው ለውጥ በዋና ወና ስትራቴጂ ከማይዘው ለእያንዳንዱ ክፍል ሠንጠረዥ ተሰርቶለታል። የመከታተያ መረጃና አላማም ተያይዟል።
- ከዋና ዋና ስትራቴጂዎች በታች ዋና ዋና የታቀዱ ተግባራት ተለይተው ተቀምጠዋል። ለነዚህ መለኪያዎች ይሆን ዘንድ በዓመታዊ የሥራ እቅዶች ውስጥ እንዲገቡ ተደርጓል።

5. ቅድሚያ የተሰጣቸው ፕሮግራም

**ለተሻለ አመራር አቅምን ማሳደግ**

**የዚህ ቅድሚያ የተሠጠው መርሃ ግብር አላማ፡-**

"የትምህርት ስርዓቱን አስተዳደር በማሻሻል ተቋማት ውሣኔ የመስጠት አፈፃፀማቸውን በማሳደግ ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ" ነው፡፡

**መግቢያ**

የትምህርት አስተዳደር ዋናው አላማ ሁሉም ተማሪዎች ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ባለው ያልተማከለ አስተዳደር እያንዳንዱ የበላይ አመራር ክፍል በስሩ ያሉትን ክፍሎች የተሻለ ግብአት እንዲመደብላቸው ውሣኔ የመስጠትና የመደገፍ ኃላፊነት አለበት፡፡ ትምህርት ሚኒስቴር ለዩኒቨርስቲዎች የገንዘብ አቅርቦትና ድጋፍ የሚያደርግ ሲሆን የክልል ትምህርት ቢሮዎች ደግሞ ዞኖችን ወረዳዎችንና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትን በገንዘብና በተለያዩ ነገሮች ይደግፋሉ፡፡ ሁሉም ክልሎች፣ ወረዳዎች፣ የቴ/ሙ/ት/ስ/ ተቋማት የቁሳቁስ፣ የሰው ኃይሉንና በጀት አጠቃቀሙን የመምራትና የማስተዳደር ነፃነቱ አላቸው፡፡ የወረዳ መስተዳድሮች ለትምህርት ቤቶች በጀት ይመድባሉ፡፡ የበጀት አመዳደቡ በትምህርት ቤቶቹ እቅድ መሠረት ሲሆን ወረዳዎች፣ የትምህርት ቤት አስተዳደሮችና ማህበረሰቡ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሣኔ እንዲሰጡ ሊረድዋቸው ይገባል፡፡

ይህ ቅድሚያ የተሰጠው ፕሮግራም የሚያተኩረው የአስተዳደር አካላትና ግለሰቦች ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ውሣኔዎችን ለማስተላለፍ መዋቅሮች የሥራ ሂደቶችና አቅሞች በሚገነቡበትና በሚሻሻሉበትን መንገድ ላይ ነው፡፡

በዚህ አሰራር ውጤታማ መሆን ይቻል ዘንድ አምስት ተግባሮችን ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡ በመጀመሪያ በትምህርት አስተዳደር መዋቅር ውስጥ ያሉ ተዋንያን ሁሉ ኃላፊነታቸውን በግልጽ የመወጣታቸውን ጉዳይ የሚመለከት ነው፡፡ ትክክለኛ አስተዳደር እንዲኖር ከተፈለገ ውሣኔ ለመስጠት መረጃን መሰብሰብ

መተንተንና ጥቅም ላይ ማዋልን ይጠይቃል፡፡ ይህ ደግሞ በኃላፊዎች መካከል ትብብርን ለማሻሻል የሚረዳ ሲሆን ሌሎች ተጨማሪ ተግባራት ትብብሩን ይበልጥ ያጠናክራሉ፡፡ በመጨረሻ አንድ ውጤታማ አመራር ብቁ የሆኑ ሠራተኞችና ሃብት እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህም የሚከተሉት አምስት ነጥቦች ቅድሚያ የተሰጣቸውን ጉዳዮች መርሃ ግብሮች ለማስፈጸም የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

- በሁሉም ደረጃ በግልጽ የሰፈረ ኃላፊነት ከተጠያቂነት ጋር እንዲኖር ማድረግ
- ውሣኔ ለመስጠት የሚያስችል መደበኛ ስብሰባና የአፈፃፀም መረጃ እንዲኖር ማድረግ (በመረጃ የተደገፈ እቅድና አሰራር)
- ጥሩ ትብብርና ተግባቦት በውስጥም ሆነ ከሌሎችም ጋር እንዲኖር ማድረግ
- በየደረጃው በቂ የሆነ የሠራተኛ አቅርቦት እንደዚሁም የቴክኒክና የአመራር ክህሎት ያለው የሰው ኃይል እንዲኖር ማድረግ
- በቂ ሃብትና አበረታች የሥራ ሁኔታ መፍጠር

ከነዚህ መካከል በተወሰኑት በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ተጨባጭ የሚባሉ መሻሻሎች ታይተዋል፤ በሌሎቹ ግን ዝቅተኛ ናቸው፡፡ የእያንዳንዱ ተግባር ትኩረትና ሽፋን ይህን ከግምት ያስገባ ነው፡፡

### ተግባር 1፡ ተገቢ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ያለው መዋቅር በሁሉም ደረጃዎች ግልጽ በሆነ ሁኔታ መዘርጋት

| **ግብ ፡** የትምህርት ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ቴ/ሙ/ት/ስ/ኤጀንሲ የክልል ትምህርት ቢሮዎች ቴ/ሙ/ት/ስ/ኤጀንሲዎችና የዩኒቨርስቲ መዋቅሮች አምስተኛውን የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብርና ባለ ዘርፈ -ብዙ ጉዳዮችን (cross cutting issues) ለመተግበር የሚያስችል መዋቅር ይሆናል፡፡ | አራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር | **ትኩረት** |
|---|---|---|
| የተተገበረውን ትምህርት ዘርፍ መዋቅር እንደገና ለመስራት የተሰጠ የመፍትሄ ሐሳብ | የለም | በ2010 የሚተገበር |
| ከዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የመርሃ ግብር ማስፈጸሚያ /ማተባበሪያና የክትትል መረጃ በየአመቱ ይኖራል፡፡ | የለም | ዓመታዊ ሪፖርትና የተለያዩ መረጃዎች |

**ንኡስ ተግባር 1፡- የትምህርት ዘርፉን መዋቅር ማሻሻል**

በሦስተኛውና አራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር የተቋማዊ የሥራ ሂደት ለውጥ (BPR) ግልጽ የሆነ መዋቅር በመዘርጋት በተለያየ ደረጃ ያሉ ኃላፊነቶች ከተጠያቂነት ጋር በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ እንዲተገበሩ ተደርጓል፡፡ በፌዴራል በክልል ዞንና ወረዳ እንደዚሁም ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲዎችና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል ያለው ግንኙነት አሁን ግልጽ ሆኗል፡፡

ስለሆነም አጠቃላይ የሆነ ሪፎርም ማካሄድ ባያስፈልግም፣ የትምህርት ሚኒስቴር ውስጣዊ መዋቅሩንና ከትምህርት ቢሮዎችና ዩኒቨርስቲዎች ጋር ያለውን ግንኙነት እንደዚሁም ከፌዴራል ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ ውስጣዊ መዋቅርና ከቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲዎች ጋር ያለው መስተጋብር መፈተሽ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ወቅት የአንዳንድ ቁልፍ ዓላማዎች አለመሳካት የሚያያዘው ከመዋቅራዊ ግንኙነት ችግሮች ጋር ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት በአምስተኛ የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር በፌዴራልና በክልል ደረጃ ያሉትንየመዋቅር ችግሮች በመፈተሽ መፍትሄ የሚሆን ምላሽ ማስጠት ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ የመፍትሄ ሐሳቦች በሚቀጠሉት አምስት ዓመታት ይተገበራሉ፡፡

**ንኡስ ተግባር 2፡- በሁሉም አካላት ትኩረት ጉዳዮች (Cross-cutting issues) መርሃ ግብሮችን ትግበራ መምራት**

በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር ወቅት ከነበሩት ተግዳሮቶች አንዱ በሁሉም አካላት ትኩረት ለሚሹ ጉዳዮችን (cross —cutting issues) በተመለከተ እቅዱን ለማስፈጸም በቂ ክትትል አለመደረጉ ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ የተቀናጀ ሥራ ሳይሠራ ቀርቷል፡፡ ስለዚህ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ወቅት በፌዴራልና በክልል ደረጃ ሙሉ በጀትና ኃላፊነት ያላቸው የማስተባበሪያ ጽ/ቤቶችን በማቋቋም የሁሉንም ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች (cross-cutting issues) ትኩረት እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡ እነዚህ ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች ሁሉም የትኩረት ጉዳዮች (cross-cutting

issues) በሥራ ላይ እንዲውሉ ድጋፍ ከመስጠት በተጨማሪ ዞን፣ ወረዳ በቴ/ሙ/ት/ስ/ና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከሚገኙ ተጠሪዎች ጋር በመተባበር ይሠራሉ።

የሚቋቋሙት ጽ/ቤቶች በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር የሚከናወኑትን ጉዳዮች በራሳቸው የመፈፀም ግዴታ የለባቸውም፤ እቅዶቹ ቅድሚያ በተሰጣቸው ፕሮግራሞች ሥራ እንዲካተቱ የተደረገ በመሆኑ፣ ጽህፈት ቤቶቹና ተጠሪዎቹ የማስተባበር፣ መረጃ የመስጠትና መሠራት ያለባቸውን ጉዳዮች ግልጽ በማድረግ የቴክኒክ ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው። የሥርዓተ ፆታ፣ ኤች አይቪ /ኤድስና የልዩ ፍላጐት ትምህርት በመሳሰሉት ጽህፈት ቤቶች የሚገኙ ኤክስፐርቶች ፣ የቴክኒክ አገልግሎት መስጠት የሚቀጥሉ ሲሆን የልዩ ትኩረት ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች እንዲያግዙዋቸው ይደረጋል። ለምሣሌ ያህል፣ ትምህርት በአደጋ ወቅትን (Education in Emergencies) ብናይ በጥሩ ሁኔታ የተዋቀረ የመረጃ ፍሰት ስልት ባለመኖሩ ምክንያት በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ አደጋ ጊዜ ፈጣን የሆነ ምላሽ ከመስጠት ያግዳል። አሁን ያለው የትምህርት አስተዳደር ስርዓተ (EMIS) መረጃ በአደጋ ጊዜ መረጃ ለመሰብሰብና ሪፖርት ለማድረግ የማያስችል በመሆናቸው ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዩች ተጠሪዎችና ጽህፈት ቤቶች መረጃ የመሰብሰብ ስርዓቱን በማሻሻል ከወረዳ እስከ ክልልና ፌዴራል ደረጃ ድረስ መረጃ የማድረስ ኃላፊነት ይሰጣቸዋል።

ይህ አወቃቀር ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፌዴራል-ክልል-ወረዳ ወይም ሌሎች ተቋማት ጋር ያለውን ተግባቦትና ግንኙትን ከማሻሻሉ በተጨማሪ በዳይሬክቶሬቶች ይህም በመሆኑ መካከል ባለው ተግባቦት ላይም ተጽእኖ ስለሚኖረው ሥራዎች በተቀናጀ ሁኔታ እንዲካሄድ ለማድረግ ያስችላል።

| ስትራቴጂዎች | መለኪያዎች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| የትምህርት ዘርፉ መዋቅርን ማሻሻል | የትምህርት ሚኒስቴርና የፌዴራ ቴ/ሙ/ት/ስ/ኤጀንሲ የውስጥ አወቃቀር መጠናቀቁን ሪፖርት ማድረግ | አምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር ዓመታዊ ሪፖርት |
| | የትምህርት ዘርፍ ተቋማዊ ለውጥ እንደገና እንዲሠራ የተሰጠው ሐሳብ መተግበር | አምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር ዓመታዊ ሪፖርት |

<table>
<tr><td colspan="3">በትምህርት ሚኒስቴርና በፌዴራል ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲ አወቃቀር ላይ ሪፖርት ማዘጋጀት</td></tr>
<tr><td colspan="3">በሪፖርቱ በቀረቡ ሃሣቦች ተወያይቶ ማጽደቅ</td></tr>
<tr><td colspan="3">ከፌዴራል እስከ ክልል ድረስ ለተሰጡ ሪፖርቶች የማስፈፀሚያ እቅድ ማዘጋጀት</td></tr>
<tr><td colspan="3">በቀረቡት የመፍትሄ ሪፖርቶች በሁሉም ደረጃ እንዲፈፀሙ ማድረግ</td></tr>
<tr><td rowspan="2">ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን መርሃ ግብር መፈፀምና ክትትል ማድረግ</td><td>በፌዴራል ደረጃና በሁሉም ክልሎች ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶችን ማቋቋም</td><td>አምስተኛው የት/ዘ/መ/ል/ ዓመታዊ ሪፖርት</td></tr>
<tr><td>ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚተገበሩ ፕሮግራሞች የአፈፃፀም መረጃ በየዓመቱ እንዲኖር ማድረግ</td><td>አምስተኛው የት/ዘ/መ/ግ አመታዊ ሪፖርት</td></tr>
<tr><td colspan="3">ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች አስተባባሪ ጽ/ቤቶች የሚያስፈልጋቸው አወቃቀር፣ ኃለፊነት የሰው ኃይልና በጀት በግልጽ ማስፈር</td></tr>
<tr><td colspan="3">ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶችን ማቋቋም (አስፈላጊውን የሰው ኃይል መመደብ)</td></tr>
<tr><td colspan="3">ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን በተመለከተ ዓመታዊ ሪፖርት ማዘጋጀት</td></tr>
<tr><td colspan="3">ከፌዴራል አስከ ወረዳ ድረስ ትምህርት በአደጋ ወቅትን አስመልክቶ የመረጃ አሰባሰብ ሁኔታ ማሻሻል</td></tr>
</table>

### ተግባር 2፡ መደበኛ ስብሰባዎችን በማካሄድና ሃሣብ በመለዋወጥ በመረጃ የተደገፈ ውሣኔ መስጠት

| አላማ፡- ተገቢ የሆኑ ውሣኔዎችን ለማስተላለፍ ሁሉም የአስተዳደር ጽ/ቤቶችና ትምህርት ቤቶች ጠቃሚ መረጃ ይኖራቸዋል | አራተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር | ግብ |
|---|---|---|
| ኢንዴክስ በመጠቀም የተተነተኑ ስታስቲካዊ መረጃዎች (በፐርሰንት) ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያ | የለም | 100 በመቶ |
| በአመታዊው የትምህርት ስታስቲካዊ መረጃ የረኩ ናሙና የፌዴራል የክልል የቴ/ሙ/ት/ስ/ዩኒቨርስቲና የወረዳ እቅድ አውጭዎችና አመራሮች (በፐርሰንት) | የለም | 80 በመቶ |

| | | |
|---|---|---|
| በየአመቱ የሪፖርት ካርድ የሚወስዱ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (በፐርሰንት) | 0 በመቶ | 50 በመቶ |

የትምህርት አፈፃፀም ጉዳዮች እንደዚሁም ፋይናንስና መምህራንን በተመለከተ በርካታ መረጃ ይገኛል (በተለይም ከትምህርት አስተዳደር መረጃ ) ነገር ግን የዚህ መረጃ ወጥነት፣ ተአማኒነት እና ስልታዊ አተናተን ፣ በተጨማሪ ወረዳው ለሚመለከተው አካል የማሰራጨቱና በመረጃው በመደገፍ ሃብት መደልደል ሁኔታ ሊሻሻል ይገባዋል፡፡ የሚከተሉት ንዑስ ተግባሮች እነዚህን ችግሮች የሚመለከቱ ናቸው፡፡

**ንኡስ ተግባር 1፡- የትምህርት አፈፃፀም መረጃን መሰብሰብና መተንተን**

የኢትዮጵያ የትምህርት አስተዳደር መረጃ ስርዓት (EMIS) ባለፉት ሁለት የዘርፉ እቅዶች በተጠናከረ ሁኔታ የትምህርት አስተዳደር መረጃ ስርዓት ጽ/ቤቶች አሁን በሁሉም ወረዳዎች ስለሚገኙ ትምህርት ቤቶችን የሚመለከት አመታዊ መረጃ በተሟላ ሁኔታ እስከ ፌዴራል ደረጃ ድረስ እየተጠናቀቀ ይቀርባል፡፡ የትምህርት አስተዳደር የመረጃ አያያዝ ሁኔታው እየተሻሻለ በሄደ ቁጥርም አዳዲስ አሰራሮች ተፈጥረዋል፡፡ በአምስተኛ የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ወቅት ሁለት ዋና ጉዳዮች ይጨመራሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የትምህርት ቤቶች አስተዳደር መረጃ ስርዓት (EMIS) ይህ የመረጃ ስርዓት የትምህርት አመራሮች በትምህርት ቤት ደረጃ ያለውን አፈፃፀም የሚመለከቱበት ነው፡፡ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ የቁሳቁስ አቅርቦት ከመደረጉ በፊት በተመረጡ ትምህርት ቤቶችና ክልሎች ሙከራ ይደረጋል፡፡ በመጨረሻም የትምህርት ቤቶች መረጃ አያያዝ ከወረቀት ወደ ማሽን ይቀየራል፡፡

**የመምህራን አስተዳደር የመረጃ አያያዝ ስርዓት (TMIS)፡-** ይህ የመረጃ ስርዓት መምህራን በሥራ ዘመናቸው ሁሉ ባለቸው አፈፃፀም ላይ ዘርዘር ያለ መረጃ ላይ ያተኩራል፡፡ በአሁኑ ወቅት ሁሉም ክልሎች ይህ የመረጃ ስርዓት ስላላቸው ክልሎች ዞኖችና ስለመምህራን በአገር አቀፍ ደረጃ ያለውን

የመምህራን ስርጭት ማግኘት ጀምረዋል፡፡ የመምህራን አስተዳደር የመረጃ አያያዝ ስርዓት የመምህራን የትምህርት ደረጃ፣ የማስተማር የፍቃድ ደረጃ፣ የየወቅቱ የሙያ እድገታቸውና የሥራ ልምዳቸውን የሚመለከት መረጃ በመስጠት በአጠቃላይ የትምህርት አስተዳደር መረጃ አያያዝ ስርዓቱ (EMIS) አካል ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ መምህር እና የሚሰራበት ተቋም በመረጃው ስርዓት ይመዘገባል፡፡ አሁን ባለው በሁሉም ክልሎች ያለው የመረጃ ስርዓት የተጠናከረ አይደለም፡፡ ስለሆነም በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ወቅት፣

ሀ) ስርዓቱ ተአማኒ የሆኑ መረጃዎችን በመሰብሰብ ለ) የተሰበሰበው መረጃ ከትምህርት ቤቶች አስተዳደር ስርዓት (EMIS) ጋር የሚገናኝ ቢሆንም ዓመታዊ የትምህርት ቤቶች ዳሰሳ ላይ ተጽእኖ በሚያመጣ መልኩ እንዲካሄድ ጥረት ማድረት ያስፈልጋል፡፡ የሚሰበሰበው መረጃ ጥራት ከማሻሻል ባሻገር የትምህርት ቤቶች አሰተዳደር መረጃ አያያዝ ስርዓት በቀጣይ ከስነምድር መረጃ አያያዝ (GIS) ስርዓት ጋር እንዲገናኝ ይደረጋል፡፡ የስነ ምድር መረጃው ስርዓት የተጠናቀቀ በመሆኑ አምስተኛው የትምህርት ልማት ዘርፍ መርሃ ግብር የመጀመሪያ ዓመት ተቋማት መረጃውን ማግኘት ይጀምራሉ፡፡ የትምህርት ቤቶች ደረጃ መለያ (ኮድ) የመስጠት ሂደት በመከናወን ላይ ሲሆን፣ ይህም ያለፉትን አምስትና አስር አመታት ተቋማትን የሚመለከቱ ትምህርት ነክ መረጃዎች ማግኘት ያስችላል፡፡

በአሁኑ ጊዜ የትምህርት አስተዳደር መረጃ አያያዝ ስርዓቱ (EMIS) በአጠቃላይ ትምህርት (የጐልማሶች ትምህርትን ሳይጨምር) ጥሩ እየሠራ ቢሆንም በቴ/ሙ/ት/ስ እና በከፍተኛ ትምህርት የሚታየው የመረጃ አሰባሰብና ሪፖርት አቀራረብ ግን ታአማኒነቱ ዝቅተኛ ነው፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ትግበራ ወቅት የመረጃ ጥራትና አግባብነትን ለማሻሻል እንደዚሁም መረጃ የመሰብሰቢያ መጠይቆች የተንዛዙ እንዳይሆኑ የሚረዳ የማጠናከርያ ሙከራዎች ይካሄዳሉ፡፡ በክልል ደረጃ እየተካሄዱ ያሉ የአቅም ግንባታ ሥራዎች የትምህርት አስተዳደር መረጃ አያያዝ ስርአቱን (EMIS) ከሁሉም ንኡስ የትምህርት ዘርፎች መረጃ እንዲያገኝ ያስችለዋል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ዩኒቨርስቲዎችና የቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲዎች የአካባቢ መረጃ በመሰብሰብ በየአመቱ ለትምህርት አስተዳደር መረጃ ስርዓት ዳይሬክቶሬት የሚመግቡበት ዘዴ ሊኖር ይችላል፡፡

እነዚህ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች በመቶዎች በሚቆጠሩ የወረዳ ኃላፊዎች ላይ የሚፈጥሩትን ጫና ለመቀነስ የመረጃ ስርአቱን የሚያስተባብር ግልጽ መዋቅር እንዲኖር ያስፈልጋል፡፡ ይህን ስራ ለማገዝና የወቅቱ ቴክሎጂ አሠራርን ለማረጋገጥ አሁን በመስጠት ላይ ያለው አገር አቀፍ የስልጠና ፕሮግራም ለዞንና ወረዳ የትምህርት አስተዳደር መረጃ አያያዝ ባለሙያዎች በመስጠት እውቀትና ክህሎታቸውን መገንባት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሂደት ያልተማከለ ሥርዓትን እውን ለማድረግ የሚያስችል በመሆኑ የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች ኃላፊነታቸውን መወጣት ይችሉ ዘንድ ሶፍትዌሮችና ሃርድዌሮች እንዲኖሩዋቸው ይደረጋል፡፡

### ንዑስ ተግባር 2፡- የፋይናንስ መረጃ የመሰብሰብና የመተንተን ሂደት

በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር የመጨረሻው ዓመት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስተር ባካሄደው የተቀናጀ  የፋይናንስ መረጃ አያያዝ ስርዓት (IFMIS) የሙከራ ሥራ ትምህርት ሚኒስቴር ተሳታፊ ሆኗል፡፡ ይህ የወረቀት ስራን የተካው የኢንተርኔት ኦንላይን (online) ስርዓት ትምህርት ሚኒስቴርን ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጋር በእቅድ በበጀትና ፋይናንስ አሠራር በቀጥታ እንዲገናኝ አድርጊል፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ወቅት ይህ የተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ አያያዝ ስርዓት (IFMIS) በሁሉም ክልሎችና መሠረተ ልማት በተስፋፋባቸው ወረዳዎች (የኔትወርክ ግንኙነት) እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡

### ንዑስ ተግባር 3፡- በመረጃ የተደገፈ ውሣኔ መስጠት

በተለያዪ ደረጃ የሚሰጡ የአስተዳደር ውሣኔዎች በትምህርትና ፋይናንስ አፈፃፀም ላይ የተመሠረቱ ይሆናሉ፡፡ የመረጃ ፍሰት አንድ አቅጣጫ ብቻ የሚከተል አይደለም፤ ተገቢው መረጃ ለተገቢው አካል መድረሱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የትምህርት አመራር መረጃ አያያዝ ስርዓት (EMIS) ለከፍተኛ ደረጃ ፖሊሲ የማውጫ ዋና የክትትል መሣሪያ በመሆን ይቀጥላል፡፡ አሁን ያለውን የትምህርት አስተዳደር መረጃ ስርዓት በማስፋፋት ወይም በማጠናከር በማእከል ፣ በክልሎችና በወረዳዎች ያሉትን ክፍተቶች በመለየት መፍትሄ ለመስጠት ይቻል ዘንድ የሚከተሉት መንገዶች ይተገበራሉ፡፡

**የትምህርት አስተዳደር መረጃ አያያዝ ስርዓት (EMIS):-** በትክክለኛ መረጃ በተጠናቀረ ብሔራዊ ስታትስቲካዊ አብስትራክት በመመስረት የአጠቃላይ ትምህርት የቴ/ሙ/ት/ስና የከፍተኛ ትምህርት ፖሊሲዎች እንዲወጡ እንደዚሁም የስትራቴጂ ማሻሻያዎች እንዲደረጉ ይሆናል፡፡ የክልል ትምህርት ቢሮዎችና የክልል ቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲዎች የት/አ/መ/ስ (EMIS) በመጠቀም እስከ ወረዳ ድረስ ያለውን የአፈፃፀም ሁኔታቸውን ለመረዳት ይችላሉ፡፡ ይህን መረጃ በመጠቀም በየወረዳዎች የሚታየውን የአፈጻጸም ክፍተት ለመሸፈን የሚያስፈልገውን ግብአት መመደብ ይችላሉ፡፡ በወረዳ ደረጃ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር በመጀመሪያው ዓመት ጀምሮ (EMIS) የትምህርት ቤቶች ሪፖርት ካርድ ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ የወረዳ የት/አ/መ/አ/ስ ጽ/ቤቶች የአካባቢ መረጃዎችን በመተንተን ትምህርት ቤቶቹ የሚገኙበትን ወቅታዊ ሁኔታ አጠናቅረው የትምህርት አመራሮች እንዲያውቁት ያደርጋሉ፡፡ ይህ ደግሞ ትምህርት ቤቶች ፈጣን የሆነ ግብረ መልስ እንዲያገኙና በአንድ የትምህርት ዓመት ውስጥ የእቅድ ማሻሻያ እንዲያደርጉ ይረዳል፡፡ የሪፖርት ካርድ በማዘጋጀት የወረዳ ኃላፊዎች ጠንካራና ደካማ ጐኖቻቸውን በመለየት በተሻለ መንገድ ወቅታዊ እርምጃ እንዲወስዱ ይረዳቸዋል፡፡

**የትምህርት ቤት አስተዳደር መረጃ ስርዓት (SMIS):-** ይህ የመረጃ ስርዓት በትምህርት ቤት ደረጃ ይተገበራል (ሙሉ በሙሉ ሲጐለብት) በትምህርት ቤት ት/አ/መ/አ/ስ (EMIS) ያለው ሚና ሊተካ ይችላል፡፡ የትምህርት ቤት አስተዳደር መረጃ ስርዓት (SMIS) የትምህርት ቤት አመራሮች የትምህርት ቤቶቻቸውን አፈፃፀም ለመለካት መረጃ እንዲሰበስቡና እንዲተነትኑ ይረዳቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመረጃ ስርዓቱ ት/ቤቶች ራሳቸውን እንዲገመግሙና "የትምህርት ቤት ሪፖርት ካርዳቸውን" እንዲያጠናክሩ ይረዳቸዋል፡፡ በትምህርት ቤት አስተዳደር መረጃ ስርዓት (SMIS) በመደበኛነት የሚሰበሰቡ ነገር ግን ወደ ማእከል የማይተላለፉ መረጃዎች (ለምሣሌ የመምህራንና የተማሪዎች የሰዓት ቁጥጥር) ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ በማቅረብ የተለያዩ ውሣኔዎችን ለማስተላለፍ ይቻላል፡፡ በነዚህ መረጃዎች በመደገፍ የትምህርት ቤት አመራሮች እቅድ በማውጣትና የግብአት ክፍፍል በማድረግ ት/ቤቶች ውጤታማ እንዲሆኑና ቢያንስ ዝቅተኛ የተባሉትን መስፈርቶች እንዲያሟሉ ማድረግ ይችላሉ፡፡

**የመምህራን አስተዳደር መረጃ ስርዓት** (TMIS):- በዚህ የመረጃ ስርዓት አማካኝነት የወረዳና የክልል ጽ/ቤቶች የመምህራንን ክህሎት፣ የሥራ ቦታ፣ ቋንቋ እንደዚሁም በሙያቸው የሚያሳዩትን እድገት መከታተል ይችላሉ። በክልል ደረጃ ያለውን የመምህራን አቅርቦትና ፍላጐት በማጥናት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የስልጠና ቅደም ተከተሎችን መለየት ይችላሉ። የወረዳ ጽ/ቤቶች የመምህራንን ተከታታይ የሙያ ስልጠና (CPD) የሚያስፈልጋቸውን ለመለዩትና ልዩ ማበረታቻ የሚያስፈልጋቸውን መምህራን ለመምረጥ ይህን የመረጃ ስርዓት ይጠቀማሉ። በፌዴራል ደረጃ ደግሞ በተለይ ለሁለተኛ ደረጃ መምህርነት በዩኒቨርስቲ ደረጃ መሰልጠን የሚገባቸውን መምህራን ማወቅ ያስችላቸዋል። ይህን የመረጃ ስርዓት በመጠቀም በየትምህርት ዓይነቱ በክልሎች ያለውን የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ስርጭት በማጥናት አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ያስችላል።

**የጂኦግራፊያዊ መረጃ ስርዓት** (GIS): ይህ የመረጃ ስርዓት ከትምህርት አስተዳደር መረጃ ስርዓት (EMIS) ጋር በማጣመር በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች በሥራ ላይ ይውላል። የወረዳ ጽ/ቤቶች የት/ቤቶችን አፈፃፀም ሊገመግሙበት ይችላሉ። በአካባቢያቸው ያለውን የትምህርት ቤቶች ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ በማወቅ የሱፐርቪዥን ስራዎቻቸውን ለማፋጠንና የክላስተር ትምህርት ቤቶችን አመዳደብ ለመወሰን ያስችላቸዋል። በወረዳም ይሁን በክልል ደረጃ ጂኦግራፊያዊ መረጃ በት/ቤቶች መስፋፋትና ስርጭት ውሣኔዎች ላይ አስተዋጽኦ አለው። የክልል ጽ/ቤቶችም የት/ቤቶችን አፈፃፀም ለመገምገመና ወረዳዎች የሚያስፈልጋቸውን ግብአት ለመመደብ እንደዚሁም በአደጋ ጊዜ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ለማስፋፋትና በከፍተኛ ደረጃ ፍትሃዊ የሆነ የትምህርት ተደራሽነት እንዲኖር ጂኦግራፊያዊ የመረጃ ስርዓትን (GIS) መጠቀም ያስፈልጋል።

የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር መረጃ አያያዝ ስርዓት (IFMIS) ይህ የመረጃ ስርዓት በፌደራልና ክልል የፋይናንስ እቅድ አመራሮች ጥቅም ላይ ይውላል። በመንግሥት የተለያዩ አካላትና በትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ በጀትን የተመለከተ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖርና የበጀት ጥያቄ የበጀት ክፍፍል እንደዚሁም የወጭዎች ግምገማ በማድረግ ቀልጣፋ የሃብት አጠቃቀም ስርዓት እንዲኖር ያደርጋል።

| ስትራቴጂዎች | መለኪያ (መነሻንና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| የትምህርት አፈፃፀም መረጃን መሰብሰብና መተንተን | እንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ተጠቅመው መረጃ የሚሰበስቡ ትምህርት ቤቶች ብዛት በ15 በመቶ ይጨምራል | የትምህርት አስተዳደር መረጃ ስርዓት (EMIS) |
| | መምህራን የሚካተቱ በመምህራን አስተዳደር መረጃ ስርዓት (TMIS) ብዛት 65 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የመምህራን አስተዳደር መረጃ ስርዓት (TMIS) |
| የትምህርት ቤቶች አስተዳደር መረጃ ስርዓት (SMIS) ሙከራና ትውውቅ | | |
| የመምህራን አስተዳደር መረጃ ስርዓትን ማስፋፋት (ቁጥርና ዝርዝር መረጃ) | | |
| በተለይ በከፍተኛ ትምህርት በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ጎልማሶችና ኢ-መደበኛ ላይ ያተኮሩ የትምህርት አስተደደር መረጃ ስርዓት (EMIS) ጋር መገምገም | | |
| የጂኦግራፊያዊ መረጃ ስርዓትን (GIS) ከትምህርት አስተዳደር መረጃ ስርዓት (EMIS) ጋር ማቀናጀት | | |
| የመምህራን አስተዳደር መረጃ ስርዓት (TMIS) እና የት/ቤቶች አስተዳደር መረጃ ስርዓት (SMIS) ከትምህርት አስተዳደር መረጃ ስርዓት (EMIS) ማቀናጀት | | |
| የፋይናንስ መረጃ መሰብሰብና መተንተን | የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር መረጃ ስርዓትን የሚጠቀሙ የክልል ጽ/ቤቶች ቁጥር ከምንም ወደ መቶ በመቶ ማሳደግ | ተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር መረጃ ስርዓት |
| | በቂ የመሠረተ ልማት ባላቸው ወረዳ ጽ/ቤቶች ሙሉ በሙሉ የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር መረጃ ስርዓት እንዲኖራቸው ማድረግ | የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር መረጃ ስርዓት |
| የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር መረጃ ስርዓትን በሁሉም ክልል ጽ/ቤቶች እንዲሠራጭ ማድረግ | | |
| ተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር መረጃ አያያዝ ስርዓት በቂ መሠረተ ልማት ባላቸው ወረዳዎች ሁሉ እንዲሰራጭ ማድረግ | | |
| በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሣኔ ለመስጠት እንዲቻል የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ማድረግ | አመታዊ መረጃ ቀርቦ በአመታዊ ስታስትካል ትንተና ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች መቶ በመቶ ይደርሳሉ፡፡ | የስታትስቲክስ ትንታኔ |
| | ዓመታዊ የሪፖርት ካርድ የሚሰጣቸው አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ቁጥር 50 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የጠቅላላ ትምህርት የጥራት ማሻሻያ መርሃ ግብር |
| | በአምስተኛ የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር መጨረሻ በሚደርሳቸው የመረጃ ጥራት ደስተኛ የሚሆኑ የፌዴራል የክልል እና የወረዳ እቅድ አመራሮች ድርሻ 80 በመቶ ይሆናል፡፡ | የናሙና ቅኝት |
| በብሔራዊ ደረጃ አስተማማኝ የሆነ አመታዊ ስታትስቲካዊ አህጽሮት ማዘጋጀት | | |
| በክልል ደረጃ ስታትስቲካዊ አህጽሮት በማዘጋጀት ወደ ሁሉም ክልሎች ማሰራጨት | | |

| |
|---|
| በወረደ ደረጃ አጠር ያለ የሪፖርት ካርድ አዘጋጅቶ ለሁሉም ወረዳዎች ማሰራጨት |
| የትምህርት ቤት ሪፖርት  ካርድ አዘጋጅቶ ለትምህርት ቤቶች ማሰራጨት |
| ለክልሎች ወረዳዎችና ትምህርት ቤቶች አገልግሎት የሚሆን የአህጽሮተ -ጽሁፍና ሪፖርት ካርድ አጠቃቀም ላይ መመሪያ ማዘጋጀት |
| በክልልና ወረዳ ጽ/ቤቶች የእቅድ አመራርና የስታትስቲክስ የሥራ ኃላፊዎችን በመረጃ አጠቃቀም ዙሪያ አስተዳደር መረጃ አያያዝ ስልት ፲እንደአስፈላጊነቱ በTIMS, GIS IFMIS) ሥልጠና መስጠት |
| የትምህርት ቤት ካርድ አጠቃቀምን በተመለከተ ለትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን ሥልጠና መስጠት |

### ተግባር 3፡ በተለያዩ እርከኖች መካከል ጥሩ ትብብርና ተግባቦት መፍጠር

| አላማ፡- በአስተዳደር ውስጥ ያለውን ትብብር ለማሻሻል በሁሉም ደረጃ ያሉ የትምህርት አስተዳደር ሠራተኞች ሚናቸውን በግልጽ እንዲያውቁና የሚፈልጉዋቸውን መዛግብት በአፋጣኝ እንዲያገኙ ማድረግ | አራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር | ግብ |
|---|---|---|
| በኮምፒዩተር የተመዘገበ የሥራ ዝርዝር ያላቸው ሠራተኞች (በፐርሰንት) | የለም | 100 በመቶ |
| በሁሉም ደረጃ የሚገኙ ሠራተኞች በእንግሊዝኛና በአማርኛ የተጻፈ የተሟላ ተቋማዊና አስተዳደራዊ ማኑዋል እንዲኖራቸው ይደረጋል | የለም | በሁሉም ደረጃ በ2009 ዓ.ም ጥቅም ላይ ይውላል |

በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሐ ግብር መጨረሻ ውስጣዊና በየደረጃው ያለው ውጫዊ ግንኙነት ያለምንም መሻሻል ቀጥሏል (ይህ የመልካም ግንኙነት አለመኖር በአፈፃፀም ላይ ያላስፈላጊ ተጽእኖ ያደርጋል)። እነዚህ የተግባቦት ችግሮች የመረጃ ልውውጥን ስለሚገድቡ፣ ኃላፊዎች በቂ መረጃ ሳይኖራቸው ውሣኔዎችን ያሳልፋሉ። ከዚህ በተጨማሪ በአንድ መሥሪያ ቤትም ይሁን በተለያዩ መስሪያ ቤቶች በትብብር መሠራት ያለባቸው ፕሮግራሞች ግባቸውን ሳይመቱ ይቀራሉ። ከላይ በተግባር 2 ንዑስ ተግባር 3 “በመረጃ የተደገፈ ውሣኔ መስጠት” በሚለው ርዕስ ስር የተጠቀሱት ስትራቴጂዎች በአስተዳደርና በትምህርት ቤቶች ውስጥ ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል ይረዳሉ።

ትብብርን ለማሻሻል ጥረቶች ተደርገዋል። መንግሥት ቢ.ኤስ.ሲ. (BSC)[7] የተባለውን ዘዴ በመጠቀም ስትራተጂክ የሆኑ እቅዶችን በአመታዊና ወርሃዊ የሥራ ዝርዝር በመከፋፈል የተነደፉት ዓላማዎች ግባቸውን እንዲመቱ ያደርጋል። በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር መጨረሻ ቢ.ኤስ.ሲ. (BSC) በሁሉም የትምህርት አስተዳደር እርከኖች በሥራ ላይ እንዲውል በመደረጉ የተለያዩ ኃላፊዎች በስትራተጂክ ግቦች አንፃር ያለውን አፈፃፀም ለመከታተል አስችሏቸዋል።

7 የትምህርት ዘርፍ ለማት ሥራዎችን በትክክል ለማቀድ፣ ለመቆጣጠርና ለማስተዳደር ቢ.ኤስ.ሲ (BSC) እንዲተገበር ተደርጓል።

### ንዑስ ተግባር 1፡ የሥራ ዝርዝርና የትግበራ መመሪያ ጽሁፍ

በቀጣይ መደረግ ያለበት በስርዓቱ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ኃላፊ ከርሱ ምን እንደሚጠበቅ ማወቁን ማረጋገጥ ነው። አሁን ያሉት የሥራ ዝርዝሮች በጥቅል የቀረቡ (ለምሣሌ የአንድ ርዕሰ መምህር ፣ የሥራ ዝርዝር፣ የአንድ ኤክስፐርት የሥራ ዝርዝር) በመሆናቸው የግለሰብን ሚና ወይም ልዩ ሚና (ለምሣሌ ተዘዋዋሪ የአካቶ ትምህርት መምህራን) በግልጽ አያመለክቱም። በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር የያንዳንዱ ኃላፊ የሥራ ዝርዝር ተዘጋጅቶ በዲጂታል አሰራር ይሰፍራል። ይህ አሰራር ኃላፊዎች ከዝርዝር ሥራዎቻቸው ጋር የሚገናኙ ስትራተጂዎችን ለመንደፍና በተግባር ለማዋል ሥልጣን እንዲኖራቸው ያደርጋል። ከዚህ በተጨማሪ፣ ኃላፊዎች ከሥራ ባልደረቦቻቸው ምን እንደሚጠብቁ በሥራ ዝርዝሩ ስለሚገለጽ የአሰራር ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር ያደርጋል። አሰራሩ እየተጠናከረ ሲሄድ መዋቅሮችና ኃላፊነቶች በየጊዜው እየተገመገሙ የተሻሻሉ የሥራ ዝርዝሮች እንዲወጡ ይደረጋል።

ማብራሪያዎችን በመስጠትና የስራ ስታንዳርዶችን በማውጣት ኃላፊዎች የተሻለ የስራ አፈፃፀም እንዲኖራቸው መርዳት ይቻላል። በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር በትምህርት ሚኒስቴር በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ኤጀንሲ በክልል ትምህርት ቢሮዎችና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ኤጀንሲ እንደዚሁም በወረዳ ጽ/ቤት ለሚገኙ ሠራተኞች የሥራ ትግበራ መመሪያ ማጣቀሻ (operations hand book) ይዘጋጅላቸዋል። ይህ የሥራ ትግበራ መመሪያ ኃላፊዎች መደበኛ ሥራዎቻቸውን እንዴት እንደሚከናወኑና ችግር ሲያጋጥማቸው መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች በቀላሉ በሚገባ መንገድ ይዘጋጃሉ።

### ንኡስ ተግባር 2፦ የመረጃ አያያዝ ማዕከላትንና የመረጃ ልውውጥ አጠቃቀም ማሻሻል

በትምህርት አስተዳደር ስርዓቱ ውስጥ የተለያዩ የሰነድ መሰብሰቢያና መለዋወጫ መሣሪያዎች አሉ። ከነዚህ ውስጥ ዋነኛ የሆኑት የትምህርት ሚኒስቴር ቤተ መጽሐፍትና አይ.ሳይት (isite) ሲሆኑ በመርህ ደረጃ ሁሉም ሠራተኛ ሊጠቀምባቸው ይችላል። በአሁኑ ወቅት ያለው ዋናው ችግር የመረጃ መሣርያዎቹ አለመኖር ሣይሆን አጠቃቀማቸው ውሱን መሆን ነው።

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ወቅት አይ.ሳይትን (isiste) ለመጠቀም ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፡፡ አጠቃቀሙ ይበልጥ እንዲታወቅ ለማድረግም ራሱን የቻለ የስትራቴጂ ጽሁፍ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ ይውላል፡፡ በዚህ ረገድ ተመራጭ ሊሆን የሚችለው ስትራቴጂ ለሠራተኞቹ ስልጠና መስጠት ነው፡፡ ባለፉት ዓመታት የተከወኑትን ጨምሮ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች በዲጂታል ቴክኖሎጂ በአይ.ሳይት ለማስቀመጥ የቴክኒክ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

<table>
<tr><td>ስትራቴጂዎች</td><td colspan="2">መለኪያ (መነሻና ግብን ጨምሮ)</td><td>ምንጭ</td></tr>
<tr><td rowspan="2">የስራ ዝርዝርና የትግበራ ማጣቀሻ ጽሁፍ</td><td colspan="2">በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር መጨረሻ ዲጂታይዝድ የሥራ ዝርዝር የሚኖራቸው ኃላፊዎች ድርሻ መቶ በመቶ ይሆናል፡፡</td><td>የሰው ኃይል ጽ/ቤት</td></tr>
<tr><td colspan="2">የሥራ ትግበራ ማጣቀሻ ጽሁፍ የሚኖራቸው ኃላፊዎች ድርሻ መቶ በመቶ</td><td>የናሙና ጥናት</td></tr>
<tr><td colspan="4">የሥራ ዝርዝር ማዘጋጀትና ድጅታል ማድረግ</td></tr>
<tr><td colspan="4">ኃላፊዎች የሥራ ዝርዝራቸው እንዲያውቁ ማድረግ</td></tr>
<tr><td colspan="4">በፌዴራል ፣ በክልል፣ ለዞንና ወረዳዎች  አገልግሎት የሚውል የትግበራ ማጠቃሻ ጽሁፍ ማዘጋጀት</td></tr>
<tr><td colspan="4">የትግበራ ማጣቀሻ ጽሁፉን ማሰራጨት</td></tr>
<tr><td colspan="2" rowspan="2">የሰነድ ማዕከላትን ማጠናከርና የመረጃ ልውውጥ መድረኮችን በአግባቡ መጠቀም</td><td>በአይ.ሳይት(isite) የሚገኙ መዛግብት</td><td>አይ.ሳይት (isite)</td></tr>
<tr><td>ወርሃዊ የአይ.ሳይት (isite) ተጠቃሚዎች ቁጥር</td><td>አይ.ሳይት (isite)</td></tr>
<tr><td colspan="4">የሰነዶች ልውውጥ ስትራቴጂ መንደፍ</td></tr>
<tr><td colspan="4">በ (isite) ለማካተት እንዲቻል ሰነዶችን ዲጅታል ማድረግ</td></tr>
<tr><td colspan="4">በ (isite) አጠቃቀም ዙሪያ መረጃ የመስጠት ዘመቻ ማካሄድ</td></tr>
</table>

**ተግባር 4፡ ተገቢ የሆነ ክህሎት ያላቸው ሠራተኞች በቂ አቅርቦት በሁሉም ደረጃ እንዲኖር ማድረግ በየደረጃው ተፈላጊው ክህሎት ያላቸው ሠራተኞች በበቂ ሁኔታ መቅጠር**

| አላማ ፡- በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት አስተዳደር ሰራተኞች ኃላፊነታቸውን በብቃት ለመወጣት እንዲችሉ አግባብ ያለው ክህሎት ይኖራቸዋል፡፡ | አራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር | **ግብ** |
|---|---|---|
| ዝርዝር የቅጥር ማስታወቂያ በማውጣት የቴክኒክ ሙያ ያላቸው አዳዲስ ሠራተኞችን መቅጠር (በፐርሰንት) | የለም | 100 በመቶ |
| ከሥራ መስኮቻቸው ጋር በተያያዘ የሙያ ስልጠና የሚሰጣቸው የወረዳ ኃላፊዎች (በፐርሰንት) | የለም | 50 በመቶ |

ሠራተኞች በየክህሎታቸው አንፃር የሚመደቡበት መዋቅር የተቋማዊ ለውጥ ዘዴን በመጠቀም በሥራ ላይ ውሏል፡፡ እነዚህን ቦታዎች በቂ ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች ለመሙላት ረዥም ጊዜ በመውሰድ በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ሊከናወን አልቻለም፡፡

**ንኡስ ተግባር 1፡ የተቀጣሪዎች መረጃና ቅጥር**

በተቋማዊ ለውጥ የተሠራን ሥራ ከመደገፍ አንፃር መወሰድ ያለበት ቀጣዩ እርምጃ ከተቀመጠው መስፈርት ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ በተግባር 3 የተጠቀሱት የሥራ ዝርዝሮች በነዚህ ቦታዎች የሚመደቡ ሠራተኞች ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች ያብራራሉ፡፡ ስለዚህም በቴክኒክ ሙያ ለሚመለመሉ ሠራተኞች የሚሆን መስፈርት ለማዘጋጀት በጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ወቅት በቴክኒክ የሥራ መደብ የሚኖረው ቅጥር ፍፁም ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲካሄድ አስፈላጊው ጥረት ይደረጋል፡፡ አሁን በሥራ ላይ ያለው የቅጥር

ስርዓት በጥልቀት ከተጠና በኋላ መደረግ ያለበትን መሻሻል በመጠቆም ሂደቱ ይጀምራል። አዲሱ የቅጥር መስፈርትና የሚሻሻለው የምልመላ ሂደት ተገቢነት ያላቸው አዳዲስ ሠራተኞች ለመቅጠር ያስችላል።

**ንኡስ ተግባር 2፡ የሙያ ላይ እድገት ምክር ስልጠናና የሥራ ላይ እገዛ**

የሚሻሻለው የቅጥር ስርዓት ተገቢ የሆነ መረጃ ያላቸውን ሠራተኞች ለመቅጠር በሚያስችል ሲሆን፣ ነባርም ሆኑ አዲስ ሠራተኞች ተከታታይ የሙያ እድገት እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል። በፌዴራልና በክልል ደረጃ የሚገኙ ኃላፊዎች ስትራቴጂክ እቅድ የማዘጋጀት በቂ ክህሎት ያንሳቸዋል። በጀትን በየርእሱ እና በየትግበራ ዓይነቱ ከፋፍሎ ትንተና የማድረግ ችግር፣ ስትራቴጂክ የሆኑ ጉዳዮችን ከነአማራጮቻቸው በማዘጋጀት ፖሊሲውን በማሳመን ለዘርፈ የሚያስፈልገውን ግብአት የማስገኘት አቅም ማነስ በሪፖርት የቀረቡ ዋና ዋና የክህሎት ክፍተቶች ናቸው። ብዙዎቹ ሠራተኞች ይህን ክህሎት የሚያዳብሩት ከተቀጠሩ በኋላ ነው። በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ወቅት በዘርፉ የሚኖረው የሙያ ማሻሻያ በቅርጽ የተለየ ይሆናል።

ከላይ የተጠቀሱት፣ ክፍተቶች ለመሙላትና የሠራተኛውን የክህሎት ማሻሻልና ብቃት ለማሳደግ መደበኛ ስልጠናዎችና ወርክሾች ይሰጣሉ። በርካታ አጋር ድርጅቶች ሥልጠናዎችን የሚሰጡ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም (GEQIP) በትምህርት አስተዳደር መረጃ ስርዓት (EMIS) የሚሰጣቸው ወርክሾፖች ይጠቀሳሉ። ቢሆንም ግን ከስልጠና በኋላ (ወይም ምንም ስልጠና ሳይሰጥ በሥራ ላይ ስልጠና መጠናከር የሚገባቸው በርካታ ውስብስብ ክህሎቶች አሉ። የዚህ ዓይነት ድጋፍ በመጀመሪያ ደረጃ ለወረዳ ኃላፊዎች ይሰጣል። በአካባቢና በክልል ደረጃ ጠቃሚ የሆነ መረጃዎችን በመለየት ላይ ትኩረት ይደረጋል። በመቀጠል የክልል የዞን የወረዳ ኃላፊዎች በተግባር የተደገፈ የፖሊሲና የእቅድ መረጃዎች እንዲያገኙና የራሳቸውን የሥራ አፈፃፀም ትንተና እንዲያደርጉ ድጋፍ በማድረግ እንዲጠናከሩ ይደረጋል። ይህ አካሄድ አሁን በከፍተኛው መዋቅር ካለው የክህሎት ማሻሻያ ዘዴ የተለየ ከመሆኑ ባሻገር ወረዳዎች የክላስተር ሱፐርቪዥን ሥራና የትምህርት ቤት ውሣኔዎች እንዲያስተላልፉ ስለሚያስችላቸው ያልተማከለ አመራር ዓላማን የሚያጠናክር ነው።

የሙያ ማሻሻያ የቅርብ ሱፐርቫይዘር ክትትልን ያካትታል፡፡ ሥራዎች በወቅቱና በአግባቡ እንዲከናወኑ ስራ አስኪያጆች ሠራተኛውን በመደበኛነት እንዲያግዙ ይደረጋል፡፡ ይህ የእገዛ (mentoring) የሚደረገው ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ ችግር ሲያጋጥም አስቸኳይ እርምት እንዲደረግ ያስችላል፡፡

የሚሰጠው የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም ከእያንዳንዱ ሠራተኛ ልምድና እውቀት ጋር የተገናኘ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የማሻሻያ ፕሮግራሙ ለሁሉም በጅምላ የሚሰጥ አይነት ሳይሆን በያንዳንዱ ሠራተኛ ላይ በማተኮር በማቴሪያሎች አቅርቦት የተደገፉ ወርክሾፖች ኩርሶችና ሌሎች ስልጠናዎች የሚሰጡበት ነው፡፡

| ስትራቴጂዎች | አመልካቾች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| መስፈርትና ቅጥር | በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር የቴክኒክ ሠራተኞች የሚቀጠሩበት መስፈርት ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ ይውላል | የሰው ኃይል ጽ/ቤት |
| | በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር በግምገማ የሚሻሻለው የቅጥር ስርዓት ስራ ላይ ይውላል፡፡ | የሰው ኃይል ጽ/ቤት |
| ሁሉም የቴክኒካል የስራ መደቦች መስፈርት ይዘጋጅላቸዋል፡፡ | | |
| መስፈርቶቹን ሁሉም የሰው ኃይል ሠራተኞች እንዲያውቋቸው በማድረግ የቴክኒክ ሠራተኞችን ለመመልመል በጥቅም ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ | | |
| በወቅቱ በሥራ ላይ ያለውን የቴክኒክ ሠራተኞች የቅጥር ስርዓት በጥልቀት መገምገም | | |
| በግምገማው መሠረት መወሰድ ያለበትን እርምጃ ህጋዊ ማድረግ | | |
| የሙያ ማሻሻያ፡ ምክር ስልጠናና የሥራ ላይ ድጋፍ | ከሥራቸው ጋር በተገናኘ የሙያ ሥልጠና ተጠቃሚነት የሚሆኑ የወረዳ ኃላፊዎች ወደ 50 በመቶ እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ | የወረዳ ሪፖርቶች |
| | በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር በሚሰጣቸው ድጋፍና የማቴሪያል አቅርቦት እርካታቸውን የሚገልፁ የወረዳ ኃላፊዎች ብዛት 90 በመቶ ይሆናል | የናሙና ጥናት |
| | በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር መጨረሻ እያንዳንዱ መደብ/ሠራተኛ የሙያ እድገት ፕሮግራም ይወጣለታል | የሰው ኃይል ጽ/ቤት |
| በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት አመራሮች የክህሎት ፍላጐት ለማሳደግ ወርክሾፖችን ማዘጋጀት | | |

| | | |
|---|---|---|
| በየወረዳው የሚገኙ ኃላፊዎች የሚጠቀሙባቸው የድጋፍ ማቴሪያሎች ማዘጋጀት | | |
| የድጋፍ ማቴሪያሎቹን አጠቃቀም አስመልክቶ ለወረዳ ኃላፊዎች ወርክሾፖችን ማዘጋጀት | | |
| በሱፐርቫይዘርነት የሚመደቡ ኃላፊዎች በአመራርና ሚንተሪንግ ፕሮግራም የሚጠቀሙባቸው ጽሁፎችን ማዘጋጀት | | |
| ለእያንዳንዱ የሠራተኛ መደብ እና የሥራ ዝርዝር የሚሆን የሙያ ማሻሻያ መርሃ ግብር ማዘጋጀት | | |
| **ተግባር 5፡ ግብአትና የሥራ ሁኔታ** | | |
| አላማ፡- በአግባቡ ሥራቸውን እንዲያከናውኑ የክልልና የወረዳ ጽ/ቤቶች የሚያስፈልጋቸው የማቴሪያል እና የፋይናንስ ግብአት እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ | አራተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር | ግብ |
| ቢያንስ ዝቅተኛ የማቴሪያል፣ የፋይናንስ የግብአት ጣሪያ ያላቸው የክልል (ቴክኒክ፣ ሙያን ጨምሮ) የዞንና የወረዳ ጽ/ቤቶች | የለም | 100 በመቶ |

አንድ ተቋም ተገቢ መዋቅርና ብቁ ሰራተኞች ስላሉት ብቻ ውጤታማ አይሆንም፤ በቂ የማቴሪያልና የፋይናንስ አቅርቦት ያስፈልገዋል፡፡ በዚህም አመቺ የሥራ ሁኔታ በመፍጠር ሠራተኛውን ማነቃቃት ያስፈልጋል፡፡

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ሁሉም ተቋማት ቢያንስ ዝቅተኛ የሚባለውን የግብአት መጠን የሚያገኙበት ስታንዳርድ ልኬት የሚዘጋጅ ሲሆን ይህን በሚመለከትም መረጃ ይሰበሰባል፡፡ በመረጃው የተደገፉ የማቴሪያልና የፋይናንስ ስርጭት በማድረግ በጽ/ቤቶች መካከል ያለው ልዩነት እንዲቀረፍ ይደረጋል፡፡

| ስትራቴጂዎች | ማሳያዎች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | **ምንጭ** |
|---|---|---|
| ግብአቶችና የሥራ ሁኔታ | ክልሎች ፣ ዞኖችና ወረዳዎች ቢያንስ ዝቅተኛውን ግብአት የሚያገኙበት ስታንዳርድ /ልኬት ማዘጋጀት | የክልል ሪፖርቶች |
| | በስታንዳርዱ መሠረት ክልሎች ዞኖችና ወረዳዎች ቢያንስ ዝቅተኛ የሚባለውን የማቴሪያል እና የፋይናንስ ግብአት ያገኛሉ (100 በመቶ)፡፡ | የክልል ሪፖርቶች |
| ሁሉም ተቋማት ዝቅተኛ የሚባለውን ግብአት ሊያገኙ የሚችሉበት ስታንዳርድ /ልኬት ይዘጋጃል፡፡ | | |
| ግብአቱን ለመከታተል የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት | | |
| በግብአት ስርጭት ላይ ውሣኔ የሚሰጡ ክልሎች ፣ዞኖችና ወረዳ ጽ/ቤቶች ስለግብአቱ መረጃ እንዲኖራቸው ማድረግ | | |

## 6. ቅድሚያ የተሰጠው ፕሮግራም፡- አጠቃላይ የትምህርት ጥራት

**የዚህ ትኩረት የተሰጠው ፕሮግራም ግብ፡-** የአጠቃላይ ትምህርት ጥራትን በማሳደግ ህፃናት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ ማበረታታት እና ተማሪዎች ተገቢውን እውቀት፣ ክህሎት እና እሴት ያዳበሩ አምራችና ብቁ ዜጋ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡

***መግቢያ***

ምንም እንኳን በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራሙ መሠረት ከፍተኛ ጥረት ቢደረግም በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም የእቅድ ዘመን የተማሪ ትምህርትን የመቅሰም ሂደት (Student attainment) እና ውጤት (Learning outcome) የታቀደውን ያህል መሻሻል አልታየባቸውም፡፡[8] አጠቃላይ ሂደቱም አብዛኞቹ ተማሪዎች መሠረታዊ ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ ያስቻለ አልነበረም፡፡ ይህም ተማሪዎች አስራ ሁለተኛ ክፍልን እስኪያጠናቅቁና ከዚህም አልፎ የቴክኒክና ሙያ እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ውጤታቸው ላይ አሉታዊ የሆነ ተጽእኖ አሳድሯል፡፡ ስለሆነም ጥራት ያለው ትምህርትን በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች ማዳረስ የአምስተኛው የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራሙ የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ ይቀጥላል፡፡ አንዳንድ ተሞክሮዎችን በመከለስና በማዳበር እንዲሁም አዳዲስ ስልቶችን በመንደፍ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት አዎንታዊ ለውጥ/መሻሻል እንዲመጣ ይደረጋል፡፡

አምስተኛው የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራሙ የሚከተሉት ቁልፍ ተግባራት መሻሻል እንዲኖር አጽንኦት ይሰጣል፡፡

እነዚህም የመማር ማስተማር ሂደት ማሻሻል፣ የስርዓተ -ትምህርት አግባብነትና ይዘት፣ የአይሲቲ አጠቃቀምን ጨምሮ የማስተማሪያ ዘዴዎች ማሻሻል፣ የትምህርት አመራር አካላት ያላቸውን የሃብት አጠቃቀም የማስተዳደር እና ክትትል የማድረግ አቅም ማሳደግ እንዲሁም መምህራን አርአያ በመሆን የሚያስተምሩበት ተማሪዎችም በምቹ ሁኔታ ሊማሩበት የሚያስችል ጥራት ያለው የትምህርት ቤት ከባቢያዊ ሁኔታ መፍጠር የሚሉ ናቸው፡፡

የልዩ ፍላጎት ትምህርት ለሚያስፈልጋቸውና በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መሠረታዊ ክህሎቶችን ማዳበር ለሚገባቸው የአንደኛ ደረጃ ህፃናት ተማሪዎች የተለየ ትኩረት ይሰጣል፡፡ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ለሳይንስ፣ ለሂሣብ ለቴክኖሎጂ፣ ለስነዜጋ የትምህርት አይነቶች ትኩረት ይሰጣል፡፡ ይህም ሰላምን ከመገንባት ፣ ከመቻቻልና ዘለቄታዊ የሆነ ማህበራዊ መስተጋብር /አብሮነት/ ከመመስረት ጋር ትስስር ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪ አካባቢን እና ተፈጥሮን በመጠበቅና ብክነትን መከላከል/ ጋር አብሮ የሚሄድ ነው፡፡ የሚቀየሱት እስትራቴጂዎች በአጠቃላይ የወንዶችንም ሆነ የሴት ተማሪዎችን ፍላጎቶች ያማከሉ እና ሁሉም ተማሪ በትምህርት ቤትም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጪ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ የሆነ ህይወት እንዲመሩ የሚያስችሉ የህይወት ክህሎት ስልጠናዎችን ያካተተ ነው፡፡

በመሆኑም ይህ ፕሮግራም በዋናነት ያካተታቸው አምስቱ የትኩረት ዘርፎች በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ለማሻሻል ወሳኝ ሚና /ድርሻ/ አላቸው፡፡ ትኩረት ተሰጥቷቸው የተመረጡት የእነዚህ ስትራቴጂዎች ዋነኛ የጋራ ዓላማ በቅድመ መደበኛ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ትርጉም ያለው የትምህርት ጥራት እንዲመጣ ማስቻል ነው፡፡ ይሁን እንጂ የትምህርት ስርዓቱ በሚቀጥሉት አምስት አመታት ከ 12 ሚሊዩን በላይ አዲስ ገቢ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን ማስተናገድ የሚኖርበት ከመሆኑ ጋር በተያያዘ የስትራቴጂው አንዳንድ ዘርፎች በአንደኛ ደረጃ ትምህርት መሠረታዊ ክህሎቶች የማስተማር ሂደት ላይ ቀጥተኛ የሆነ አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው ማድረግ ረዥም ጊዜያትን ሊወስድ ይችላል፡፡

**የመምህራንና የትምህርት አመራር ባለሙያዎች ልማት፡-** አስተማሪነት ተመራጭነት ያለው ሙያ እንዲሆን ማድረግና የማስተማርን፣ የትምህርት አመራርን፣ የሱፐርቪዥንና የአስተዳደር አቅምን ማጎልበት


**ስርዓተ ትምህርት የትምህርት ማቴሪያሎች፡-** የተማሪዎችን የችሎታ ልዩነትና የተሳትፎ መጎልበት ታሳቢ ያደረገ የስርዓተ ትምህርት ክለሳ ማካሄድና የተማሪዎችን መሠረታዊ ክህሎት የሚያጎለብቱ የትምህርት ቁሳቁሶችን በበቂ ሁኔታ ማቅረብ

**የትምህርት ቤት ማሻሻያ ፕሮግራም፡-** ትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ሂደታቸውን በተገቢ ሁኔታ ለማካሄድ የሚያስችሏቸው መሠረታዊ ግብአቶች የተሟሉ መሆናቸውን መመዘንና ማረጋገጥ፣ እንዲሁም የአካባቢው ማህበረሰብ በትምህርት አስተዳደርና በውሣኔ አሰጣጥ እንዲሳተፍ ማበረታታት

**ኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ፡-** የአይሲቲ ቁሳቁሶችን ግብዓት በማስፋፋትና በማሻሻል በሁሉም ደረጃዎች አይሲቲ ለትምህርት ይበልጥ ጠቀሜታ ላይ እንዲውል ማድረግ፣ ለትምህርት ግብዓት የሚሆኑ መፃህፍትንና ሌሎች ማቴሪያሎችን ዲጂታል ማድረግና በስፋት ማሰራጨት፣ የትምህርት አሰጣጡን ለመደገፍ በሚያስችል መልኩ የመምህራንና የትምህርት አመራሩን አይሲቲ የመጠቀም ክህሎት ማዳበር

**የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ፡-** የመምህራንን የማስተማር ክህሎት በመገምገም የሙያ ፍቃድ ሰርቴፊኬት መስጠት፣ የትምህርት ቤቱን የመማር ማስተማር አካባቢ (environment) ሁኔታ መፈተሽ (inspection)፣ አጠቃላይ የትምህርት ስርዓቱን የአፈፃፀም ደረጃ ለመረዳት የተማሪዎችን ውጤት በቋሚነት መገምገም

**ሠንጠረዥ14፡- ለአጠቃላይ ትምህርት ጥራት መሻሻል አስተዋጽኦ ያላቸው ዘርፎች መዋቅር**



**ተግባር 1፡ የመምህራንና የትምህርት አመራሮች ልማት**

| ግብ፡- በሁሉም ተቋማት የማስተማርና የትምህርት አመራር ክህሎት መሻሻል የላቀ ተነሳሽነትና የስራ እርካታ መኖር | የአራተኛው ትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ድምር(ወ/ሴ) | ግብ (ድምር) (ወ/ሴ) |
|---|---|---|
| በየአመቱ ስራቸውን የሚለቁ መምህራን | 4 በመቶ | 2 በመቶ |
| በአስረኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተና ከ2.60 በላይ አምጥተው ወደ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት የሚቀላቀሉ አዲስ ተመዝጋቢዎች (የዩኒቨርስቲ ምሩቅ የሆኑትን ጨምሮ) ቁጥር በመቶኛ | የለም | 35 በመቶ |
| ዲፕሎማ ያላቸው የቅድመ መደበኛ መምህራን ቁጥር በመቶኛ | **0 በመቶ** (0/0) | 15 በመቶ15/15)* |
| በስራቸው መርካታቸውን ሪፖርት ያደረጉ መምህራን በመቶኛ | የለም | 90 በመቶ |
| ሙያው የሚጠይቀውን ብቃት በተገቢው ሁኔታ ያሟሉ ከአንደኛ አስከ አራተኛ ክፍል ደረጃዎች የሚገኙ መምህራን በመቶኛ | 55 በመቶ (63/48) | 100 በመቶ (100/100) |
| የሙያ ፈቃድ (ሰርተፊኬት) ያላቸው መምህራን (በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት) በመቶኛ | 0 | 70 በመቶ (70/70) |
| ሴት የትምህርት አመራሮች (ርዕሰ መምህራትና ሱፐርቫይዘሮች) በመቶኛ | 8 በመቶ | 20 በመቶ |
| የሙያ ፈቃድ ባላቸው አመራሮችና (ርዕሰ መምህራን) የሚተዳደሩ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ቁጥር በመቶኛ | 0 በመቶ | 100 በመቶ |

**በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃግብር ከ100000 በላይ ተጨማሪ የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን ይቀጠራሉ።*

**ንኡስ ተግባር 1፡ መምህርነትን ተመራጭ ወደሆነ ሙያ ማሸጋገር**

ሁሉም ተማሪዎች ተገቢውን ስልጠና የተከታተሉ፣ ተነሳሽነት ያላቸው፣ የማስተማር ሙያን የሚወዱና የተማሪዎቻቸውን ፍላጎትና አቅም የሚረዱ መምህራን ሊኖሯቸው ይገባል። ጥሩ መምህራን እያንዳንዱ ተማሪ ከመማር ማስተማር ሂደቱ ዘወትር ተጠቀሚ እንዲሆን በማድረግ ጥራቱ ወደተሻሻለ ትምህርት የሚደረገውን ጉዞ ያፋጥናሉ።

ይህን ታሳቢ በማድረግም መንግሥት በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ትግበራ ዘመን በሙያው ላይ ላሉና ወደሙያው ለሚገቡ መምህራን የስልጠና ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት አቅማቸውን ለማጐልበት ጥሯል። ይሁን እንጅ እ.ኤ.አ በ 2014 በትምህርት ሚኒስቴር ባካሄደው አንድ ጥናት 70 በመቶ የሚሆኑት መምህራን ተመሣሣይ ክፍያ የሚያስገኝ ሌላ የስራ እድል ቢሰጣቸው መምህርነትን ሙያ እንደሚለቁ ያመላክታል። መምህራን ለሙያቸው ያላቸው አመለካከት ይበልጥ አሉታዊ እንዲሆን ከሚያደርጉት ምክንያቶች መካከል ከሚኖሩበት ማህበረሰብ እውቅና አለማግኘት /ክበሬታን መነፈግ/ አና በትምህርት አመራርና በሰው ሃይል አስተዳደር የሚታዩ ድክመቶች ይጠቀሳሉ። ይህም የሚያመላክተው የመምህራንን የሙያ ብቃት ለማሻሻል ከሚደረጉ ጥረቶች በተጓዳኝ በሁሉም የሃገሪቱ ክልሎች የሚገኙ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ መምህራንን ለማነሳሳትና ለመደገፍ ለወደፊቱ ብዙ ስራዎች መሰራት እንዳለባቸው ነው።

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ዘመን "መምህርነትን ተመራጭ ወደ ሆነ ሙያ ማሸጋገርን" ትኩረት ያደረገ ስትራቴጂ ይተገበራል። ይህ ስትራቴጂ በመምህራን ፍላጎት ላይ በማተኮር የመምህርነት ሙያ ቀድሞ ወደነበረበት እውቅናና ዝና እንዲመለስ በማስቻል ላቅ ያለ ችሎታ ያላቸውን ወደ ሙያው በመሳብ ሁሉም መምህራን ተገቢውን ክብር ያገኙና ሙያቸውንም የሚያከብሩ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ምንም አንኳን ይህን መሰሉ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት (ለማስፈን) አምስት አመት በቂ ጊዜ ባይሆንም በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ዘመን የለውጡ መሠረት የሚጣልበት ይሆናል፤ በሂደትም በሙያው የሚቆዩ መምህራን ቁጥር ይጨምራል፤ በስራ ገበታቸው ላይ የሚገኙ መምህራን ቁጥር ያድጋል፣ በክፍል ውስጥ ያለው የመማር ማስተማር ጥራት መጎልበትን ተከትሎም የተማሪዎች ውጤት የሚሻሻልበት ሁኔታ ይፈጠራል።

ይህ ቁልፍ ተግባር የመምህራንን ሙያዊ ክህሎትና ልምድ ማዳበርን ታሳቢ ያደረገ ነው። ወደ መምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጆች ለመግባት ከሚያመለክቱበት ጊዜ ጀምሮ ሰልጣኞች አበረታች የሆኑ ሙያ ተኮር የእድገት እድሎች እንዲያገኙ በማድረግ መምህራንን በሚያመች መልኩ የትምህርት ስፔሻሊስቶች፣ ትምህርት አመራሮች፣ ክላስተር ሱፐርቫይዘሮች፣ ስነ ትምህርት ባለሙያዎችና

ኤክስፐርቶች እንዲሆኑ የማብቃት ስራ ይመቻቻል፡፡ ጠንካራ የአቻ ለአቻ አደረጃጀቶችን በመፍጠር መምህራን እርስ በርስ እንዲማማሩ፣ መልካም ተሞክሮዎቻቸውን እንዲያዳብሩና ልምዶቻቸውን እንዲለወዋጡ በማድረግ ሁሉም የአደረጃጀቱ አባላት የሚጠበቅባቸውን ሙያዊ ግዴታ በአግባቡ ስለመወጣታቸው ኃላፊነት እንዲወስዱ ይደረጋል፡፡ ክትትሉ ወደፊት ተማሪዎች ሙያውን አንዲቀላቀሉ የሚያግዙ የመምህራን የድጋፍና የማበረታተት እንቅስቃሴዎችን ያካትታል፡፡

ይህን መሰል ሙያ ተኮር የምክር አገልግሎት በሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች የመምህርነት ሙያ ቢቀላቀሉ ወደፊት ስለሚኖራቸው የስራ እድል ተገቢ ግንዛቤ አንዲጨብጡ ያደረጋል፡፡ የመምህራን ትምህርት የዕውቀት ማዕከላት በመምህራን ትምህርት ኮሌጆችና በተመረጡ ሶስት ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ የሚመሠረቱ ሲሆን ማዕከላቱን በማደራጀትና በክላስተር ሱፐርቫይዝ በማድረግ ለማዕከላቱ ከፍተኛ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

በአሁኑ ወቅት በትግበራ ላይ ያለውን የመምህራን ልማት ፖሊሲ በማጠናከር በሁሉም ክልሎች የመምህራን አመዳደብ ስርጭቱ  ፍትሃዊነትና የክህሎት ተመጣጣኝነት እንዲኖር አንዲሆን ይደረጋል፡፡ ከምደባ ጋር የተያያዙ የተለያዩ ማበረታቻዎችንና ጥቅማጥቅሞችን የሚያካትተው ይህ ፖሊሲ መምህራን እጅግም ተደራሽ ወዳልሆኑ የሃገሪቱ ክፍሎች እንዲሰማሩና የሚያጋጥሟቸውን ፈታኝ ሁኔታዎች መቋቋም የሚያስችሉ ድጋፎችን ይሰጣል፡፡

መንግሥት ይህንን ዘርፈ ብዙ ድጋፍ ለመምህራን ሲሰጥ መምህራን በላቀ ደረጃ ሙያዊ ግዴታቸውን በመወጣት ብቃታቸውን በማሳደግና ተነሳሽነታቸውን በመጨመር ያለባቸውን ሃገራዊ ውለታ ይወጣሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ በህብረተሰቡ ውስጥ የመምህርነት ሙያን በሚመለከት የሰረፀው የተዛባ አመለካከትም ይስተካከላል፡፡ የተለያዩ ማህበረሰቡን የሚያሳትፉ የውይይትና የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማዘጋጀት ትምህርት እና መምህራን ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ስለሚያበረክቱት ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ ገለፃ ይደረጋል፡፡

የማስተማር ሙያን ገጽታ መገንባትን ግብ ያደረገ ቀጣይነት ያለው ብሄራዊ የመገናኛ ብዙሃን ዘመቻን በማስተባበር በመስኩ ስለተመዘገቡ አንፀባራቂ ድሎች፣ መንግሥት ለዘርፉ ስለሚሰጠው ድጋፍ፣ ስለተከናወኑ ጥናቶች እና ትምህርታዊ ውድድሮች፣ እንዲሁም ሽልማቶችና ነፃ የትምህርት እድሎች እና የመሳሰሉት በፕሮግራም እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡

ንኡስ ተግባር 2. የመምህራን ስልጠናና የሙያ እድገት

መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት ጠቅላላ ይዘት በተገቢው ሁኔታ የማስተላለፍ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የመምህራኑ የብቃት ደረጃ ከፍተኛ እስካልሆነ ድረስ እውቀትን፣ ክህሎትንና እሴቶችን ወደ ተማሪዎች የማድረሱ ሂደት ደካማ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡ በቅርብ የተካሄደው የስርዓተ-ትምህርት ክለሳ መማር ማስተማሩ ይበልጥ ተማሪ ተኮር ሊሆን ይገባል በሚል አስተሳሰብ ስለተቃኘ መምህራን አሳታፊ የማስተማር ዘዴን እና ውጤታማ የክፍል ውስጥ አመራር በመከተል ተማሪዎች አብዛኛውን ክፍለ ጊዜ በትምህርታቸው ላይ እንዲያተኩሩ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህ አዳዲስ ስልቶች በተገቢው መንገድ ሲተገበሩ የተማሪዎችን በራስ የመተማመን ፣ የመሪነትና የፈጠራ ክህሎቶች በማሳደግ ሁሉንም ተማሪ ተጠቃሚ ያደርጋሉ፡፡

ይሁን እንጅ የተሻሻለው ስርዓተ ትምህርት በተገቢው ሁኔታ እንዳይተገበር ዋነኛው መሰናክል የመምህራን የማስተማር ክህሎት አናሳ መሆኑ ታይቷል፡፡ ከባህላዊ የአስተምሮት ዘይቤ ወደ ዘመናዊ የማስተማርና የመምህራን ትምህርት ዘዴ ሽግግር በሚደረግበት ወቅት ይህ ሁኔታ መከሰቱ አስገራሚ አይሆንም፡፡ ስለዚህም ሽግግሩ ይበልጥ እንዲፋጠን መንግሥት የቅድመ ሥራ ስልጠና የማሻሻል፣ ተከታታይ የመምህራን ሙያ ልማትን የማጎልበት እንዲሁም በሥራ ላይ ያሉትን መምህራንን አስፈላጊ የሙያ ላይ ስልጠና እንዲያገኙ ድጋፍ የመስጠት ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር የትግበራ ዘመን ሁሉም መምህራን የሚጠበቅባቸውን የብቃት ደረጃ ያሟላሉ፡፡ ይህም ማለት አንደኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን የሶስት አመት ዲፕሎማ ፣ የአንደኛና የሁለተኛ ሳይክል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መምህራን አንደኛ ወይም ሁለተኛ

ዲግሪ እንደየቅድመ ተከተላቸው፣ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መምህራን የአንድ አመት የተፋጠነ ስልጠና እንዲሁም የቅድመ መደበኛ ትምህርት (ECCE) አስተባባሪዎች ሰርተፊኬት ወይም ዲፕሎማ ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡ ይህን ለማሳካትም የመምህራን የትምህርት ደረጃ በአንፃራዊነት ዝቅተኛ የሆኑባቸው ክልሎችና አካባቢዎች የሚገኙ ሰልጣኞች ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡

**ቅድመ ሥራ ስልጠና**

የመምህራን ትምህርት ኮሌጅ እጩዎች የአመራረጥ ሂደት ይሻሻላል፤ ዝቅተኛ የመግቢያ መስፈርት ይቀመጣል፡፡ በተለይም በአሁኑ ወቅት በእጩ መምህራን መካከል የሚስተዋለውን ፆታዊ አለመመጣጠን ለማስቀረትና በተቻለ ፍጥነት በየአመቱ ከሚመጡት ሰልጣኝ መምህራን መካከል ሴቶች 50 በመቶ ወደ መምህራን ትምህርት ኮሌጆች እንዲገቡ ማስቻል እንደዚሁም ሁሉም ሰልጣኞች ስልጠናቸውን እንዲያጠናቅቁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ የመምህርነት ስልጠናን ላጠናቀቁ ተመራቂዎች የማስተማር ብቃታቸውን ለመለካት የሚያስችል ወጥ የሆነ መስፈርት ወይም ሃገር አቀፍ የመመዘኛ መመሪያ የለም፡፡ ሁሉም ክልሎች የየራሳቸው የሆኑ ስልቶችን የሚከተሉ በመሆኑ ከየመምህራን ትምህርት ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች የሚወጡ ተመራቂዎች ሊኖሯቸው የሚገቡ እውቀቶችንና ክህሎቶችን ወጥ በሆነ መልኩ ለመለየትና ለመለካት አያስችልም፡፡ በአሁኑ ወቅት ያሉትን የምዘና ዘዴዎች በመከለስና መልካም ተሞክሮዎችን በመለየት ለሁሉም የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት የሚያገለግል ሃገር አቀፍ መመሪያ ይዘጋጃል፡፡ የተጠናከረ የምዘና ሂደትና ተጨማሪ የጥራት ማረጋገጫ መኖር የመምህራን ትምህርት ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች በበቂ ሁኔታ የሰለጠኑ መምህራንን ማፍራት እንዲችሉ ይደረጋል፡፡

የማስተማር ክህሎትና አመለካከት መዳበር የሚጀምረው በመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ውስጥ ነው፡፡ የመምህራን ትምህርት አስተማሪዎች ሙያዊ ብቃትን ለማገዝ በማሰብ የከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም ቢቀረጽም ይህ ፕሮግራም የመምህራን ትምህርት አስተማሪዎች ዘመናዊ የማስተማር ዘዴዎችንና ቁልፍ የስነ ትምህርት (pedagogic) ክህሎቶችን ተጠቅመው እንዲያስተምሩ አላስቻለም፡፡ ስለሆነም የከፍተኛ

ዲፕሎማ ፕሮግራሙን በመገምገም የተሻሻለ ተከታታይ የመምህራን ሙያ ልማት ፕሮግራም ለመምህራን ትምህርት ባለሙያዎች ይዘጋጃል፡፡ የመምህራን ትምህርት ባለሙያዎች የሰልጣኞችን ፕራክቲከም (የተግባር ላይ ልምምድ) በጥልቀት ሱፐርቫይዝ የሚያደርጉበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ ይህ እርምጃ ዋነኛ አላማው የሰልጣኞችን የማስተማር ክህሎት ማዳበር እና በትምህርት ቤቶች ያለውን ውሱን ሃብት በአግባቡ በመጠቀም ምቹ የመማር ማስተማር ከባቢ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያስችላቸውን ብቃት ማጐልበት ነው፡፡

በተጨማሪም በዋናነት ለቅድመ መደበኛ ትምህርት የሚሰለጥኑ መምህራን በአንድ አመት ሰርቲፊኬት ወይም በተለያዩ ዓመት (multiyear) ስልጠና ዲፕሎማ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ የመጀመሪያ ዙር ሰልጣኞችን በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ-ግብር ሁለተኛ የትግበራ አመት እንደሚያስመርቅ የሚጠበቀው አዲሱ የቅድመ መደበኛና የmultiyear ዲፕሎማ ፕሮግራም ይበልጥ ተጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን አሁን ካሉት ሰባት ተቋማት በተጨማሪ ሁሉም የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች በስልጠናው እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በሃገሪቱ ያሉ በተለይም በህፃናት እንክብካቤና ትምህርት የማስተማር ዘዴ የሰለጠኑ የመምህራን ትምህርት ባለሙያዎች ቁጥር አናሳ በመሆኑና በመስኩ የተካኑ በቂ መምህራን በሁሉም የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች እንዲኖሩ ለማድረግ የህፃናት እንክብካቤና ትምህርት  መምህራን የስልጠና ፕሮግራም በማዕከል እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ በሁሉም የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የሚገኙ የህፃናት እንክብካቤና ትምህርት አስተማሪዎች ስልጠናውን ሲያጠናቅቁ በዘርፉ የሚታየውን የሰለጠነ ባለሙያ እጥረት ከመቅረፍ ባሻገር ወደፊት ለሚፈጠረው ፍላጎት በቂ የባለሙያዎች አቅርቦት እንዲኖር ያስችላል፡፡

በተመሣሣይ በአሁኑ ወቅት ጥቂት የተመረጡ ዩኒቨርስቲዎችና የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራንን በማሰልጠን ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህን ፕሮራሞች ይበልጥ ለማጠናከር የቅድመ መምህርነት ስልጠና (pre service) ሞጁዩሎች እንዲዘጋጁ ይደረጋል፡፡

ክልሎች የሚጠቀሙበት የማስተማሪያ ቋንቋ በትምህርት ጥራትና ፍትሐዊነት ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መሠረታዊ ክህሎቶችን ማዳበር እንዲችሉ በአራተኛው የትምህርት

ዘርፍ ልማት መርሃ-ግብር የትግበራ ዘመን የተጀመረው የአንደኛ መምህራንን በአፍ መፍቻ ቋንቋዎች የማስተማር ዘዴ ስልጠና ቀጣይ ይሆናል፡፡ በቅድመ ስራ ትምህርት እጩ መምህራን የሚሰጣቸው ስልጠና ወደፊት በሚመደቡባቸው ቦታዎች ያሉትን የማስተማሪያ ቋንቋዎች ተጠቅመው ማስተማር እንዲችሉ የሚያደርግ ነው፡፡ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶችን ለማስተማር የሚመለመሉ መምህራን መጠቀም የሚችሉ ከየአካባቢው የሚመረጡ ይሆናሉ፡፡ ከሌሎች ክልሎች በመምጣት በታዳጊ ክልሎች በመምህርነት የሚያገለግሉ መምህራን ሌሎች የትምህርት አይነቶች በብቃት ለማስተማር የሚያስችላቸው የቅድመ አስተማሪነት ስልጠናዎች ይሰጧቸዋል፡፡


ቋንቋ ነክ የሆኑ ችግሮች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርትም ይታያሉ፡፡ በአንድ በኩል አጠቃላይ የመምህራን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ደካማ መሆኑንና በሌላ በኩል የሁለተኛ ደረጃ የተማሪዎች ቅበላን በፍጥነት ለማሳደግ የተያዘውን እቅድ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ የመምህራን ትምህርት ስልጠና በሚሰጥባቸው ዩኒቨርስቲዎች የሚገኙትን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማሻሻያ ማዕከላት (ELIC) በማጠናከር ተቀጣሪ መምህራን እንግሊዝኛን በብቃት ለማስተማር የሚያስችላቸውን አቅም እንዲያጎለብቱ ይደረጋል፡፡ አይ.ሲ.ቲን በሁሉም የመምህራን ስልጠና ኮርሶች ውስጥ በማካተት እና በተግባራዊ ልምምድ በመደገፍ መምህራን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩና ቴክኖሎጂን በመጠቀም ተማሪዎቻቸውን ለመርዳት የሚያስችላቸውን አቅም ሊያዳብሩ ይገባል፡፡

በአብዛኛው እንደሚስተዋለው  አንድ አዲስ የማስተማሪያ ቋንቋን ለመማር ከሚፈለገው ጊዜ አንፃር ምናልባትም ይህ ስልጠና ብቻውን በቂ ሳይሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም ከአዲሱ የመምህራን አስተዳደር የኢንፎርሜሽን ስርዓት በሚገኘው መረጃ በመታገዝ የመምህራን ምልመላና ምደባ በሚያውቁት ቋንቋ መሠረት እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በዚህ መሠረት ሁሉም ተማሪዎች የተመረጠውን የማስተማሪያ ቋንቋ በአግባቡ መጠቀም የሚችል መምህር እንዲኖራቸው በማድረግ የትምህርት ፍትሃዊነትን ማሳደግና ተማሪዎች መሠታዊ ክሂሎችን እንዲጨብጡ ማድረግ ይቻላል፡፡

**የሙያ ላይ ስልጠና (In-service training)**

ሁሉም መምህራን በታቀዱ ተከታታይ የመምህራን ሙያ ልማት (CPD) ፕሮግራሞች እንዲሰለጥኑ ይደረጋል፡፡ ተከታታይ የመምህራን ሙያ ልማት ሂደት በትምህርት ቤት ደረጃ በአቻ ለአቻ ቡድኖች የሚመራ የሙያ የዕውቀት ስትራቴጂን የሚከተልና ልምድንና ተሞክሮን ለማጋራት የሚያስችሉ መርሃ ግብሮችን በመንደፍ የግለሰቦችን እሴት እውቀትና ክህሎት ማዳበር በሚሉ አስተሳሰቦች ይመራል፡፡ ፕሮግራሙ የሚቀረፀው የእያንዳንዱን መምህር ፍላጎት ለመደገፍና ሙያዊ ብቃቱን ለማሻሻል ነው፡፡ የተከታታይ የመምህራን የሙያ ልማት ፕሮግራም በሶስት ደረጃዎች የሚሰጥ ሲሆን እነሱም በውጭ ኤክስፐርት የሚሰጥ፣ በትምህርት ቤቶች ትስስርና ክላስተሮች የሚሰጥና በትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጥ ስልጠና ናቸው፡፡

**ሠንጠረዥ 15፡ ለመምህራን የሚሰጡ የተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም ሦስት ደረጃዎች**




በአሁኑ ጊዜ በመተግበር ላይ ያለው ተከታታይ የሙያ ልማት መዋቅራዊ ክለሳ ተደርጎለት የሚቀጥል ይሆናል፡፡ የተሻሻለው የተከታታይ የሙያ ልማት መዋቅር ቀደም ሲል የነበረውን በየደረጃው ለአዳዲስ መምህራን በክላስተር ኔትወርክ የሚሰጠውን የስርጸት ድጋፍ ይቀጥልበታል፡፡ በመቀጠልም ሶስቱን የተከታታይ ሙያ ልማት ኮርሶች በአዲስ መልክ በማደራጀትና በማስፋፋት ይበልጥ ጠቃሚ እንዲሆኑና ዘለቄታዊ ለሆነ የሙያ እድገት የሚያስፈልጉ ይዘቶችን በበቂ ሁኔታ እንዲያካትቱ ይደረጋል፡፡

በኮርሶቹ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ርእሶች የሚከተሉት ናቸው፤

- ፆታን ያማከለ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ላይ ማተኮር
- መሠረታዊ የቋንቋ ችሎታ (በተለይም በአፍ መፍቻ ቋንቋ ማስተማር) ፣ የማንበብ ፣ መፃፍና የመቀመር ክሂሎች
- ተከታተይ ምዘናን በማካሄድ የተማሪ ውጤት ክትትል ማድረግና ማገዝ
- ሳይንስ፣ ሒሳብና የኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂን መጠቀም

ከዚህ በተጨማሪ ስርዓተ ትምህርቱ በዳበረ ቁጥር (ስርዓተ-ትምህርት ቀረፃ የሚለውን ክፍል ይመልከቱ) መምህራን በተከለሱ እና በተመረጡ የተከታታይ ሙያ ልማት ሞድዩሎች አማካኝነት መረጃ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ እነዚህ ሞድዩሎች ማናቸውም አዲስ የስርዓተ- ትምህርት ይዘቶችን ለማቅረብ የሚያስፈልጉ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለማሻሻል የሚደረጉ ጥረቶችን ያግዛሉ፡፡

በመምህራን ፍላጎትና በአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታዎች በመመስረት በሚከተሉት ጉዳዮች ተከታታይ የሙያልማት ሞጁዩሎች ይዘጋጃሉ፡፡

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ፡-** ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም ተማሪዎች ለመስጠት ይቻል ዘንድ መምህራን በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማር ችሎታቸው እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡ የስርዓተ ትምህርቱ ማቴሪያሎች በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተቀረፁ በመሆኑ መምህራን የአጭር ጊዜ ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡

**አካቶ ትምህርት ፡-** የልዩ ፍላጎት ትምህርት ባለሙያዎች ስልጠና በሁሉም ክላስተሮች ይሰጣል፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ልማት ዘርፍ መጨረሻ 800 የሪሶርስ ማዕከላት የሚኖሩ ሲሆን እያንዳንዳቸው በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠነና በክላስተሩ ውስጥ የሚገኙ ትምህርት ቤቶችን የሚደግፍ አንድ ተዘዋዋሪ መምህር ይኖራቸዋል፡፡ በልዩ ፍላጎትና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የቅድመ መምህርነትና የስራ ላይ የስልጠና ሞድዩሎች በማዘጋጀት የመምህራን ክህሎት እንዲብር ይደረጋል፡፡

**እንግሊዝኛ ቋንቋ ፡-** ከአማርኛና የሲቪክስ ትምህርቶች በስተቀር የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ሁሉንም ትምህርት የሚማሩት በእንግሊዝኛ ነው፡፡ ስለሆነም በእንግሊዝኛ ቋንቋ ማሻሻያ ፕሮግራም (ELIC)

አማካኝነት አሁን በስራ ላይ ያሉትን መምህራን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎት ማሳደግ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡

**ሳይንስና ሒሳብ፡-** ለሳይንስና ሒሳብ የተሰጠው ትኩረት በሁሉም ደረጃዎች ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በሙከራ ደረጃ የነበረው የሳይንስና ሒሳብ ማበልፀጊያ ፕሮግራም በሁሉም ክልሎች ይስፋፋል፡፡ በክልል ደረጃ የሳይንስና ሒሳብ ማሰልጠኛ ዩኒቶችን በማደራጀት (በአብዛኛው በመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ውስጥ) አሁን ያለውን የፌዴራል የስልጠና ማዕከል እንዲያጠናክሩ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝም ለክልል አሰልጣኞችና መሪ መምህራን ስልጠናዎችን በመስጠት ሁሉም መምህራን ክህሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

**ትምህርት በአደጋ ወቅት፡-** ባለባቸው ቦታዎች፡- በተደጋጋሚ ለድንገተኛ አደጋ ተጋላጭ በሆኑ ቦታዎች የሚያስተምሩ መምህራን በአካባቢያቸው በተከሰተ አደጋ ምክንያት ትምህርት ቢስተጓጐል ክስተቱን ተቋቁመው የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማስቀጠል የሚያስችሏቸው ክሂሎችን እንዲያጎለብቱ ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በ2013 እ.ኤ.አ "Ethiopia፡ Minimum Standards for Education and Emergencies" "ኢትዮጵያ የአደጋ ጊዜ ትምህርት ዝቅተኛ መስፈርት" የተሰኘ መንግሥታዊ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡ ይህ ሰነድ በሁሉም የክልል የዞንና የወረዳ ትምህርት ቢሮዎችና በሁሉም የክልል ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከላት በቅርብ ይሰራጫል፡፡ የአደጋ ቀጠና በመባሉ አካባቢዎች (ጎርፍና ድርቅ የሚያጠቃቸውና ተደጋጋሚ የግጭት ስጋት የሚስተዋልባቸውን ጨምሮ) ለሚያስተምሩ ሁሉም መምህራን በትምህርት ቤት ውስጥ የሚፈጠሩ አደጋዎችን ስለመመከት፣ አደጋንና ጉዳትን ስለመቀነስ፣ ስለ ስነልቦና ድጋፍ አሰጣጥ፣ ስለ ትምህርት ለሰላም እና ስለፆታዊ ጥቃት የተሳለጠ ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡

### ንኡስ ተግባር 3. የአመራሮች ስልጠናና ሙያዊ ልማት

ርዕሳነ መምህራንና የክላስተር ሱፐርቫይዘሮች ከወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት (ወተመህ) (PSTA) ጋር የጋራ ምክክር በማድረግ የትምህርት ቤቱን የውሣኔ አሰጣጥና አስተዳደር ሂደት ይመራሉ፡፡ በመምህራን ላይ በተደረገ የዳሰሳ ጥናት እንደታየው የትምህርት ቤትና የሰው ኃይል አስተዳደር ጥራት

በመምህራን ተነሳሽነትና ውጤታማነት ላይ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ ጥራት ያለው የትምህርት አስተዳደር ተማሪዎች በፈጠራ፣ እውቀትን በማካፈል፣ መልካም ተሞክሮዎችን በመለየትና በማጎልበት የመማር አቅማቸውን እንዲያዳብሩ በማስቻል ረገድ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው፡፡

የትምህርት ቤት ጥራትን ለማሻሻል በሚደረገው እንቅስቃሴ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሚገጥሟቸው ዋና መሰናክሎች የትኞቹ ግብአቶችና ክንውኖች ወደሚፈለገው ውጤት ያደርሳሉ የሚለውን ለይቶ አለማወቅ ነው፡፡ ተጨማሪ አቅም አጎልብቶ ትምህርት ቤቱ ሊኖሩት የሚገቡ መሠረታዊ ግብአቶችን በማሟላት የተማሪዎችን የትምህርት ውጤት እንዴት ማሻሻል እንደሚቻል ያለው ግንዛቤ እጅግ አናሳ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ርዕሳነ መምህራንም ይሁኑ ሱፐርቫይዘሮች ሳይንሳዊ የክፍል ውስጥ ምልከታ ለማድረግና የመምህራንን አቅም ሊያጎለብት የሚችል አግባብነት ያለው ገንቢ ግብረ መልስ ለመስጠት የሚያስችል አቅም የላቸውም፡፡

የትምህርት አመራርና አስተዳደር ፕሮግራም ርዕሳነ መምህራንና የክላስተር ሱፐርቫይዘሮች መሠረታዊ የአመራርና የአስተዳደር ችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር የትግበራ ዘመን ይህን መሰሉ ድጋፍ ከ25000 በላይ ለሚሆኑ ርዕሳነ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የተሰጠ ሲሆን በተጓዳኝም ይህንን ለማስፈፀም የሚያስችሉ ሞጁዩሎችን የማሻሻልና የማሰራጨት ስራ ተከናውኗል፡፡ አዲሱ የስልጠና መርሃ ግብር ሰልጣኞች መሠረታዊ በሆኑ የሱፐርቪዥንና ተዛማጅ ርዕሶች (ለምሣሌ ስለ ተከታታይ ምዘና እንደዚሁ መምህራንን ለመደገፍ ታልሞ ስለሚካሄድ የክፍል ውስጥ ምልከታ) በንድፈ ሃሳብና በተግባር በማስደገፍ ለመምህራን የሥራ ላይ ድጋፍ የሚሰጡበት መንገድ ይመቻቻል፡፡ የፕሮግራሙ ሞጁዩሎች ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚገመገሙና እንደአስፈላጊነቱ የሚሻሻሉ ይሆናል፡፡ የሞጅዩሎቹን ይዘት በየጊዜው በመገምገም ወቅታዊ መሆናቸውን እንደዚሁም የትምህርት አመራር ፣ የትምህርት ቤቶች አስተዳደርና ድጋፍን የሚመለከቱ ርዕሶች መካተታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

የት/ቤት ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆኑ እገዛ የሚያደርግ ሁሉን አቀፍና ሊተገበር የሚችል የትምህርት አመራርና አስተዳደር ሰነድና የሀብት አጠቃቀም መመሪያ

(የትምህርት ማሻሻያ ፕሮግራም ዘርፍ የሚለውን ይመልከቱ) እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ ይህም በሁሉም ክልሎች የሚገኙ ሁሉም ትምህርትቤቶች የጥራት ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉ የሚያግዝና ለሁሉም የተከታታይ የሙያ ልማት ፕሮግራሞች ዋና ማዕቀፍ ሆኖ ያገለግላል፡፡

ርዕሰ መምህራን በተሰጣቸው ስልጠና በመታገዝ በትምህርት ቤት ደረጃ ሁሉም የጋራ አመራርና ኃላፊነትን የሚወሰድበትን አሰራር በመመስረት በት/ቤቱ መልካም የመማር ማስተማር ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ርዕሰ መምህራን ሁሉም መምህራን ከፆታዊ ጥቃትና ትንኮሳ ጋር በተያያዘ ስለሚነሱ ጉዳዬች መምህራን ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግና በመተዳደሪያ ደንቡ በተደነገገው መሠረት እልባት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

ጠንካራ የትምህርት አመራር እንዲፈጠር ወደፊት መሪ የመሆን ራዕይ ያለው የትኛውም መምህር ከትምህርት ቤቱ ድጋፍ እንዲያገኝና በአቅራቢያው ከሚገኙ የትምህርት ሱፐርቫይዘሮች አደረጃጀት ስልጠና እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡ በትምህርት አመራር ላይ የሴቶችን ተሳትፎ ለማጠናከር ብሎም በሙያው ውስጥ ያለውን ፍትሃዊነት ለማጎልበትና በጎ ተፅእኖዎችን ለመፍጠር በአየነቱ የተለየ ሴቶች ከአስተማሪነት ወደ መሪነት የሚያደርጉትን ሽግግር የሚደግፍና የሚያበረታታ ልዩ ፕሮግራም ይተገበራል፡፡

| ስትራቴጂዎች | አመልካች (አሁን ያለበት እና የታቀደውን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| የማስተማር ሙያ ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማዳበር | የማስተማር ሙያ ስላለው ጠቀሜታ ህብረተሰቡ ግንዛቤውን እንዲያዳብር በትምህርት ሚኒስትር አስተባባሪነት የሚደረጉ የቅስቀሳዘመቻዎች በአመት 8 ይደርሳሉ፡ | የኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ሪፖርቶች |
| | 60 በመቶ የሚሆኑ ወላጆች ማስተማርን ከፍተኛ ክብር ያለው ሙያ አድርገው በቀዳሚነት ይመርጣሉ | የዳሰሳ ጥናት ናሙና |
| | ወደ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት አዲስ ከሚገቡ ሰልጣኞች (የዩኒቨርስቲ ምሩቃንን ጨምሮ) በአስረኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተና ከ2.60 በላይ ያመጡ 35 በመቶይደርሳሉ፡፡ | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ፣ በዘመቻ የእውቅና ፕሮግራሞች በማካሄድ የማስተማር ሙያን ማህበራዊ ክብር /ደረጃ ከፍ ማድረግ | | |
| ብቃትንና የአፈፃፀም አቅምን መሠረት ያደረገ የደረጃ እድገት እና የማበረታቻ ዘዴዎች ማዘጋጀትና መተግበር | | |

| | | |
|---|---|---|
| ወደ መምህርነት ሙያ ለመግባት የሚያስችሉ መመዘኛዎችን ደረጃ ከፍ የሚያደርጉ የተሻሻለ የምልመላ መመሪያዎችን ማዘጋጀትና መተግበር | | |
| የመምህራን የሙያ እድገትና የትምህርት ደረጃ ለማሻሻል የሚያስችል ስርዓት ማዋቀር | በተከታታይ የመምህራን ሙያዊ ልማት ፕሮግራም አተገባበር የረኩ መምህራን 100 በመቶ ይደርሳሉ | ናሙና የዳሰሳ ጥናት |
| | በተከታታይ የመምህራን ሙያዊ ልማት ፕሮግራም አተገባበር የረኩ የመምህራን ትምህርት አስተማሪዎች 100 በመቶ ይደርሳሉ | ናሙና የዳሰሳ ጥናት |
| | በየአመቱ ስራቸውን የሚለቁ መምህራን ቁጥር ከ4 በመቶ ወደ 2 በመቶ ይወርዳል | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ሲስተም |
| በተከታታይ የሙያ ልማት በተለይም ፔዳጉጂ፣ ሳይንስና ሒሳብ፣ ተከታታይ ሙያና፣ መሠረታዊ ክሂሎችን ለማስተማር የሚዘጋጁትን ሞድዩሎች ጥራትና አግባብነት ማሳደግ | | |
| የመምህራን ትምህርት ባለሙያዎችን ተከታታይ የሙያ ልማት ፕሮግምን መገምገመና ማሻሻል | | |
| የመምህራን ትምህርት ባለሙያዎችን አቅም በተከታታይ የሙያ ልማት ፕሮግራም ማጎልበት | | |
| በተጠናከረ የክላስተር ኔትዎርክ አማካኝነት የመምህራን ሱፐርቪዥን ማከናወን | | |
| በሚፈለገው ደረጃ የሰለጠኑ መምህራንን ድርሻ ማሳደግ | በቅድመ መደበኛ ትምህርት በዲፕሎማ ደረጃ የሚያስተምሩ መምህራን ድርሻ 15 በመቶ ይሆናል | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | አስተማሪ ለመሆን የሚያበቃውን ደረጃ ሳያሟሉ በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አስተባባሪነት የሚያገለግሉት ቁጥር ወደ 20 በመቶ ዝቅ ይላል | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል ለማስተማር ደረጃውን የሚያሟሉ መምህራን ቁጥር ከ 55 በመቶ ወደ 100 በመቶ ያድጋል | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ሲስተም |
| | ከ5ኛ- 8ኛ ክፍል ለማስተማር ደረጃውን የሚያሟሉ መምህራን ቁጥር ከ92 በመቶ ወደ 100 በመቶ ያድጋል፡፡ | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | ከ 9ኛ - 12ኛ ክፍል ለማስተማር ደረጃውን የሚያሟሉ መምህራን ቁጥር ከ 95 በመቶ ወደ 100 በመቶ ያድጋል፡፡ | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | ከታች በተዘረዘሩት መስኮች ሙያዊ ብቃታቸው የተረጋገጠ የሴት መምህራን ቁጥር እንደሚከተለው ይሆናል፣ | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | በህፃናት እንክብካቤና ትምህርት 50 በመቶ ይደርሳል | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል ከ44 በመቶ | የትምህርት አመራር |

| | | |
|---|---|---|
| | ወደ 50 በመቶ ያድጋል | የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | ከ5ኛ -8ኛ ክፍል ከ28 በመቶ ወደ 45 በመቶ ያድጋል | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | ከ9ኛ -12ኛ ክፍል ከ16 በመቶ ወደ 35 በመቶ ያድጋል፡፡ | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | ከ1ኛ -12ኛ ክፍል ባሉት ደረጃዎች የሚያስተምሩ የሙያ ፈቃድ ሰርተፊኬት ያላቸው መምህራን ቁጥር 70 በመቶ ይደርሳል | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | የሙያ ፈቃድ ያላቸው የርዕሰ መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች ቁጥር 70 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| የተሻሻለው ስርዓተ ትምህርት በሁሉም የመምህራን ትምህርት ይተገበራል፡፡ | | |
| በመምህራን ትምህርት ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች የልዕቀት ማዕከላትን ማቋቋም | | |
| በመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የመምህራን ስልጠና እንቅስቃሴዎችን/ተግባራትን/ ማከናወን | | |
| የመምህራንን የሳይንስና ሒሳብ የማስተማር ችሎታና ብቃት ማሳደግ | ሒሳብና ሳይንስ ለማስተማር ፈቃድ የተሰጣቸው መምህራን ቁጥር 100 በመቶ ይሆናል፡፡ | የሙያ ፈቃድ |
| ጥራታቸው የተጠበቀ የሳይንስና ሒሳብ የስልጠና ሞጁሎችን መተግበር | | |
| በሶስት ክልሎች ከተጀመሩት የሳይንስና ሒሳብ የሙከራ ፕሮጀክቶች የተገኙ ልምዶችን በማጎልበት ለሁሉም ክልሎች ማዳረስ | | |
| በሁሉም ክልሎች የሳይንስና ሒሳብ የስልጠና ማዕከላትን ማቋቋም (ቅድሚያ በመምህራን ትምህርት ኮሌጆች እንዲታቀፉ በማድረግ ) | | |
| በሁሉም ክልል የሚገኙ የሒሳብና ሳይንስ የክልል አሰልጣኞችን አቅም መገንባት | | |
| በሁሉም ክልል የሚገኙ የሒሳብና ሳይንስ ቁልፍ ዋና መምህራንን አቅም ማጐልበት | | |
| የመምህራንን የአፍ መፍቻ እና እንግሊዝኛ ቋንቋ የማስተማር ክህሎት ማጐልበት | በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ክሂሎች ስልጠና ያገኙ መምህራን 100 በመቶ ይሆናል፡፡ | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት እና የሙያ ፈቃድ |
| | የእንግሊዝኛ ቋንቋ የጥራት ማሻሻያ ስልጠና የወሰዱ የእንግሊዝኛ መምህራን ቁጥር 70000 ይደርሳል፡፡ ከእነዚህም 50 በመቶ ያህሉ ሴቶች ይሆናሉ፡፡ | የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም |
| በትምህርት ቤት ደረጃ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የማጎልበት ስልጠና መስጠት | | |
| የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማዕከላትን ማጠናከር | | |
| በክልል ቋንቋዎች የተዘጋጁ የስርዓተ ትምህርት የካሪኩለም ግብዓቶችን ማቅረብ | | |
| የመምህራንን በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማር ብቃት የሚያጎለብቱ ወርክሾፖችን ማዘጋጀት | | |
| የመምህራን አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓትን በመጠቀም ቋንቋቸው ብዙ ባልተስፋፋበት አካባቢዎች የመምህራን አመዳደብን ማሻሻል፡፡ | | |

| ስትራተጂዎች | አመልካች/አሁን ያለበትና የታቀደው/ | ምንጭ |
|---|---|---|
| የመምህራንን አይሲቲን ለትምህርት የመጠቀም ሙያዊ ብቃት/ ችሎታ ማጎልበት | አይሲቲን በመጠቀም የትምህርት ሂደቱ ይበልጥ እንዲቀላጠፍ የሚያደርጉ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ቁጥር ከ69 በመቶ ወደ 100 በመቶ ያድጋል | የክልል ትምህርት ቢሮዎችና የአይሲቲ የልህቀት ማዕከላት ሪፖርቶች |
| | አይሲቲን በመጠቀም የትምህርት ሒደቱ ይበልጥ እንዲቀላጠፍ የሚያደርጉ የመጀመሪያ ደረጃ መምህራን ቁጥር ከ63 በመቶ ወደ 100 በመቶ ያድጋል | የክልል ትምህርት ቢሮዎችና የአይሲቲ የልህቀት ማዕከላት ሪፖርቶች |
| የትምህርት ቤት አመራሮች በአይ.ሲ.ቲ. አጠቃቀም ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ | | |
| አይሲቲ በሁሉም የመምህራን ትምህርት ኮርሶችና በስራ ላይ በሚሰጡ የስልጠና ፕሮግራሞች እንዲካተት ማድረግ | | |
| መምህራን አይሲቲን በመማር ማስተማሩ ሂደት እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚያውሉት ስልጠና መስጠት | | |
| መምህራን አይሲቲን በኢንተርኔት ግንኙነትና ከኢንተርኔት ግንኙነት ውጭ የመጠቀም ክሂላቸውን የሚያጎለብቱ ኮርሶች መቅረጽ | | |
| በልዩ ፍላጎት ትምህርት እና በአደጋ ጊዜ ትምህርት ዘርፍ ተገቢ እውቀት ያዳበሩ መምህራን ቁጥር /ብዛትን መጨመር | በልዩ ፍላጎት ትምህርት ዲግሪ ወይም ዲፕሎማ ያገኘ ቢያንስ አንድ መምህር ያላቸው ትምህርት ቤቶች ብዛት 24 በመቶ ይደርሳል | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | በልዩ ፍላጎት ትምህርት የሰለጠነ ጊዜያዊ አስተባባሪ መምህር ያላቸው የድጋፍ ማዕከላት ቁጥር 800 ይደርሳል | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | ለአደጋ ተጋላጭ በሆኑ ወረዳዎች ከሚገኙ ት/ቤቶች መካከል ጉዳትን በመቀነስና አደጋን በመከላከል ላይ ያተኮረ አጠቃላይ ስልጠና የተሰጣቸው ትምህርት ቤቶች ቁጥር 100 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የክልል ትምህርት ቢሮ ሪፖርቶች |
| የልዩ ፍላጎት ትምህርት በሥልጠና ወቅትና በስራ ላይ ስልጠናዎች መስጠት | | |
| ለመምህርነት ባለሙያዎች የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስልጠና መስጠት | | |
| መምህራንን በሁሉም ደረጃዎች በተገቢ መልኩ መመደብ የሚያስችል ስትራቴጂ መቅረጽ (በዞን፣ በወረዳ እና በክላስተር ደረጃዎች ) | | |
| ለአደጋ ተጋላጭ በሆኑ ቦታዎች የሚገኙ የትምህርት አመራሮች አደጋ በሚከሰትበት ወቅት ተገቢ ምላሽ መስጠት እንዲችሉ ስልጠናዎችን ማካሄድ | | |
| “Ethiopia Minimum Standards for Education and Emergencies” የተሰኘውን ሰነድ በበቂ ቁጥር በማተም ኮፒዎችን በሁሉም ክልሎች ፣ በዞንና ወረዳ ትምህርት ቢሮዎች እንዲሁም በቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲዎች ማሰራጨት | | |
| በሚፈልገው ደረጃ ሙያዊ ብቃታቸው የተረጋገጠ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮችን ምጣኔ/ብዛት ማሳደግ | ብቁ የሆኑ አመራር (ዲፕሎማ) ያሏቸው የቅድመ መደበኛ ት/ቤቶች ብዛት 100 በመቶ ይደርሳል | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | ብቃት ያላቸው አመራሮች (ዲፕሎማ) ያላቸው የመጀመሪያ ሳይክል (ከ1ኛ-4ኛ ክፍል) ት/ቤቶች ብዛት 100 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | ብቃት ያላቸው አመራሮች (ዲግሪ) ያላቸው የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች (ከ1ኛ-8ኛ ክፍል | የትምህርት አመራር |

| | | |
|---|---|---|
| | ወይም ከ5ኛ-8ኛ ክፍል) ብዛት 100 በመቶ ይደርሳል | የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | ብቃት ያላቸው አመራሮች (የማስተርስ ዲግሪ) ያላቸው ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች (ከ9ኛ-10ኛ ወይም ከ11ኛ-12ኛ ወይም ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ብዛት 100 በመቶ ይደርሳል | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| የቅድመ መደበኛ ትምህርት አመራር ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራም ማቋቋም | | |
| የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ ብቁ እጩ ተወዳዳሪዎች ወደ ትምህርት አመራርነት የሚሸጋገሩበት ስትራቴጂ መቀየስ | | |
| በትምህርት ቤት አመራርና ሱፐርቪዥን የሴቶችን ሚና/ተሳትፎ ማጎልበት | የሴት ርዕሰ መምህራን ድርሻ ከ9 በመቶ ወደ 20 በመቶ ከፍ ይላል | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | የሴት የትምህርት ቤት ሱፐርቫይዘሮች ድርሻ ከ4 በመቶ ወደ 20 በመቶ ያድጋል፡፡ | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| ሴቶች በተቻለ ፍጥነት ወደ ትምህርት ቤት አመራርነት እንዲመጡ የሚያስችል የስትራቴጂ መዘርጋት | | |
| ሴቶች ወደ መሪነት የመምጣት ተነሳሽነታቸውን እንዲያዳብሩ ያለመ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ማዘጋጀትና የቅስቀሳ ዘመቻዎችን ማካሄድ | | |
| ርዕሳነ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ለደረጃ እድገታቸው አስተዋጽኦ የሚያደርግ የተደራጀና ጥራት ያለው የተከታታይ የሙያ ልማት ፕሮግራሞችን እንዲወስዱ ማድረግ | በተሰጣቸው ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ የልማት ፕሮግራም እርካታቸውን የገለፁ የትምህርት አመራሮች ድርሻ 100 በመቶ ይሆናል፡፡ | የናሙና የዳሰሳ ጥናት |
| በተከታተይ የሙያ ማሻሻያ የልማት ፕሮግራም የትምህርት አመራሩን አቅም ማጎልበት | | |
| አዲሱን የአመራርና አስተዳደር ፕሮግራም ያጠናቀቁ የርዕሰ መምህራንን ቁጥር ማሳደግ | | |
| በፆታ ተኮር የትምህርት ዘዴ ስልጠና ያገኙ ርዕሰ መምህራንን ቁጥር ማሳደግ | | |
| በአካቶ ትምህርት ዙሪያ ስልጠና ያገኙ ርዕሰ መምህራንን ቁጥር ማሳደግ | | |

### ተግባር 2. ስርዓተ-ትምህርትና የመማር ማስተማር ግብዓት

| ግብ፦ ዝቅተኛ የመካከለኛ ገቢ ላላት ሃገር የሚመጥን ስርዓተ ትምህርት መንደፍ/መቅረጽ እና ለሁሉም መምህራንና ተማሪዎች እንደየፍላጎታቸው በቂ የመማር /ማስተማር ቁሳቁሶችን በተሟላ ሁኔታ ማቅረብ | በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም | ግብ |
|---|---|---|
| በ2017 እ.ኤ.አ አዲስ የስርዓተ-ትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል ማቋቋም | የለም | ማዕከሉን ማቋቋም |
| ዝቅተኛ የመካከለኛ ገቢ ላላት ሃገር በሚመጥን መልኩ የስርዓተ-ትምህርት ክለሳየተደረገባቸው የትምህርት አይነቶች ብዛት | የለም | 100 በመቶ |
| የተማሪና የመማሪያ መጽሃፍ ምጣኔ (በሁሉም ተቋማት፣ በሁሉም የትምህርት አይነቶች፣ በሁሉም ክፍሎችዙሪያ) | 1:1 | 1:1.2 |
| የተማሪዎችን መሠረታዊ የንባብና የቀመር ክህሎት ለማገዝ የሚያስችሉ ቢያንስ 20 እና ከዛ በላይ የሆነ ተጨማሪ የትምህርት ቁሳቁሶች ያላቸው የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ቁጥር | የለም | 100 በመቶ |
| አስፈላጊ የሆኑ ስርዓተ-ትምህርት ግብዓቶች የተሟሉላቸው የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ብዛት | የለም | 100 በመቶ |

**ንኡስ ተግባር 1፡ የስርዓተ -ትምህርት ቀረፃ**

በሶስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም የትግበራ ዘመን አጠቃላይ የሆነ ስርዓተ-ትምህርት ክለሳ ተከናውኗል፡፡ የተከለሰው ስርዓተ-ትምህርት በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም በሁሉም የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተግብሯል፡፡ በስርዓተ-ትምህርቱ ውስጥ እንዲጨመሩ የተደረጉ አዳዲስ ይዘቶች ጥሩ ተቀባይነትን ያገኙ ሲሆን መምህራን እነዚህን ውስብስብ ጽንሰ ሃሳቦች በተገቢው መልክ ለማስተማር ይችሉ ዘንድ የማስተማር ዘዴአቸውን ማጎልበት እንደሚጠበቅባቸው መገንዘብ ችለዋል፡፡

ቀጣዩ ሂደት ስርዓተ-ትምህርቱን በተጨባጭ ካሉት ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር ማጣጣምና ልዩነትን ያገናዘበ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ይህም መምህራን የስርዓተ-ትምህርት ይዘት ለተማሪው የሚሰጠውን ጠቀሜታ እንዲያጤኑና የመማር ማስተማሩ ሂደትም በተማሪው አቅም ፣ ፍላጎትና ዝንባሌ የተመሠረተ እንዲሆን ለማስቻል ይረዳል፡፡ ይህ አካሄድ የስርዓተ-ትምህርቱን አግባብነት ይበልጥ የሚያጎለብትና የልዩ ፍላጎት ትምህርት የሚያስፈልጋቸውን ጨምሮ ሁሉንም ተማሪዎች ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች ራሱን የቻለ ወጥ የሆነ ስርዓተ-ትምህርት የተነደፈ ሲሆን በዚህ በመመስረትም መመሪያዎችና ማኑዋሎች በመዘጋጀት ላይ ናቸው፡፡ ሁሉም ህፃናት መሠረታዊ የሆኑትን የማንበብና መፃፍ ያወቀመር ክሂሎች እንዲያደብሩ ለማስቻል ተጨማሪ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎችን ለማጎልበት የተጠናከረ ድጋፍና ርብርብ ይደረጋል፡፡ ከስርዓተ-ትምህርቱን ከማጎልበት እንቅስቃሴ በተጓዳኝ የቋንቋ ፖሊሲውን አተገባበር በመገምገም ፍትሐዊና ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም የማዳረሱን ሂደት እንዲያግዝ ይደረጋል፡፡ እነዚህን ውጥኖች በተሳካ መልኩ መፈፀም እንዲቻል የስርዓተ-ትምህርት ማበልፀጊያ እና የምርምር ማዕከል ይቋቋማል ፡፡

በወቅቱ ያለውን ስርዓተ -ትምህርት በጥልቀት ለመገምገም የሚያስችል አሰራር እንዲኖር ማድረግ የመጀመሪያው እርምጃ ይሆናል፡፡ ከተማሪዎች፣ መምህራን፣ የትምህርት አመራሮች፣ የማህበረሰብ ክፍሎችና ሌሎች የትምህርት ባለሙያዎች ጋር ምክክር በማድረግ መለወጥ ያለባቸው ጉዳዮችን የመለየት ስራ ይከናወናል፡፡ የስርዓተ -ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደቱን ሊያስተጓጉል ስለሚችል

በተቻለ መጠን አተገባበሩ ቀላል ማሻሻያዎችን በማድረግ ላይ እንዲወሰን ይደረጋል፡፡ የስርዓተ -ትምህርት ማሻሻያ እርምጃው ወጥነት እንዲኖረው ከፍተኛ ጥረት በማድረግ በክለሳው ሂደት የሚጨመሩ አዲስ የትምህርት ይዘቶች የሚፈጥሩ ሚያጎለብቱት የተማሪዎች የብቃት ዝርዝር፣ የመምህር መምሪያ እና የተከታተይ ምዘና አሰጣጥ መመሪያዎችን እንዲካተቱ ይደረጋል፡፡ በሁሉም የአጠቃላይ ትምህርት ደረጃዎች ከስርዓተ- ትምህርቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ የተከታታይ ምዘና ማኑዋሎች ይዘጋጁላቸዋል፡፡ ማኑዋሎቹ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የመማር ሂደት ለመከታተልና ለማገዝ የሚያስችላቸውን አቅም ይፈጥርላቸዋል፡፡ በክላስተር ወይም በወረዳ ደረጃ የተከናወነ የተከታታይ ምዘናን በመፈተሽ መምህራን የትምህርቱን ሂደት እንዲገመግሙና ተማሪዎችን ለማገዝ የሚያስችሉ ዘዴዎችን እንዲነድፉ ያስችላል፡፡

ማሻሻያው ዘመናዊ የቴክኖሎጂ እና የሙያ ዘርፎች በስርዓተ -ትምህርቱ በሰፊው እንዲካተቱ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥና ትምህርት የፈጠራና የኢንተርፐሪነርሽፕ አቅምን የሚፈጥር እንዲሆን ያለመ ነው፡፡ በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ቅድሚያ የተሰጣቸው ዘርፎች እንደሚያመለክቱት ሃገሪቱ በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ ብዛት ያለው የሰው ሃይል ያስፈልጋታል፡፡ ስለሆነም በስርዓተ -ትምህርት ክለሳው ለሳይንስና ቴክኖሎጂ አጽንኦት በመስጠት ምርታማነትን የሚያሳድጉና በእውቀት ላይ ለተመሠረተ ኢኮኖሚ የራሳቸውን የላቀ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችሉ ብቁ ዜጐችን ለመፍጠር ያስችላል፡፡ ማሻሻያው የወንዶችንም ሆነ የሴቶችን ፍላጎት ግምት ውስጥ ያስገባና የህይወት ክህሎትን በማካተት ተማሪዎች ስለኤች አይ ቪ /ኤድስ፣ ስነ-ተዋልዶና የአባላዘር በሽታዎች ያላቸውን ግንዛቤ በማሳደግ ሁሉም ተማሪዎች ሰላማዊና ጤነኛ ህይወት እንዲመሩ ይረዳል፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎች ቅርርብን ለማጎልበትና መደበኛና ኢ-መደበኛ በሆኑ ግንኙነቶች የህይወት ክህሎቶቻቸውን ይበልጥ እንዲያዳብሩ የስርዓተ -ትምህርቱ ክለሳ ተማሪዎች ከትምህርት ጎን ለጎን ለሚያከናውኗቸው ተግባራትና እንቅስቃሴዎች እንዲሁም ለሚመሰርቷቸው ህብረቶችና ክበቦች ትኩረት ይሰጣል፡፡

የስነ-ዜጋና ስነ ምግባር ትምህርቶች ሰላምን ከመገንባት፣ ከመቻቻል፣ ዘለቄታዊ የሆነ ማህበራዊ መስተጋብር ከመመስረት ጋር ስላላቸው ትስስር እንዲሁም አካባቢንና ተፈጥሮን ስለመንከባከብና ስለመጠበቅ በሁሉም ደረጃ በሚገኙ ተማሪዎች ገንዛቤውን ለመፍጠር ልዩ ትኩረት ይደረጋል፡፡ ይህም

ብዝሃነት ባለበት ማህበረሰብ መተማመንን፣ ሰላማዊ ትብብርንና መቻቻልን ለማጎልበት ያስችላል፡፡ የስርዓተ -ትምህርቱ ክለሳ ኢትዮጵያ መካከለኛ ገቢ ያላት ሃገር በምትሆንበት ጊዜ ሁሉም ህፃናትና ወጣቶች እጅግ ፈጣን ከሆነው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ጋር አብረው መጓዝ የሚያስችላቸውን ተገቢ ስልጠና ማግኘታቸውን ያረጋግጣል፡፡

መምህራን አዲሱን ስርዓተ -ትምህርት በሚተገብሩበት ወቅት የመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎቻቸውን ዳራ፣ ዝግጁነት፣ አቅም፣ ፍላጎትና ዝንባሌ ከግምት ውስጥ ያስገባል፡፡ ይህ ስልት በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ነገር ግን የተለያዩ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ በማሳደግ ላይ ያለመ ነው፡፡ አዲሱ ስርዓተ -ትምህርት መምህራን የእያንዳንዱን ተማሪ የትምህርት እድገትና ስኬት ይበልጥ እንዲያጎለብቱ አቅም ይፈጥራል፡፡

**ንኡስ ተግባር 2፡ የመማር ማስተማር ቁሳቁስ አቅርቦት**

በሁሉም ትምህርት ቤቶች ውጤታማ የመማር ማስተማር ሂደትን ለማምጣት በቂ የትምህርት መሳሪያ አቅርቦት መኖር ቅድሚያ የሚሰጠው ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ ግብዓቶች ዲቪዲዎችን፣ ራዲዮን እና የድህረ ገጽ ውጤቶችና የመሳሰሉትን ያጠቃልላሉ፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ-ግብር የትግበራ ዘመን የመማሪያ መፃህፍትና የመምህር መምሪያዎች የህትመትና ስርጭት ስርዓትን በመፈተሽ ሁሉም ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ ለመከታተል የሚያስችሏቸው ዋና ዋና መፃህፍትን የሚያገኙበት ሁኔታ ለመፍጠር ጠንካራ እንቅስቃሴ ይደረጋል፡፡

የመምህር መምሪያዎችን እንደአስፈላጊነቱ በመከለስ፣ መምህራን ተከታታይ ምዘናዎችን በማካሄድ ተማሪዎቻቸው ተለይተው የተቀመጡ ክህሎቶችን ስለማዳበራቸውና እያንዳንዱን የስርዓተ -ትምህርት ክፍል ለመገንዘብ የሚያስችል በቂ ችሎታ በተጨባጭ ስለመያዛቸው እንዲከታተሉ ይደረጋል፡፡ ከስርዓተ-ትምህርቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ አዳዲስ የመልመጃ መፃህፍት ተዘጋጅተው ለሙከራ ይሰራጫሉ፡፡ በዚህ ሂደትም መፃህፍቱ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥና የግላዊ ትምህርት እድገት የቱን ያህል እንደሚያጎለብቱ ይፈተሻል፡፡

በሁሉም የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች በትምህርት ቤቶች ደረጃ የሚገኙትን የመማሪያና ማስተማሪያ መፃህፍትን በበቂ መጠን በማቅረብ ስልጣኝ እጩ መምህራን ወደፊት ስለሚገለገሉባቸው ማቴሪያሎች የቅድሚያ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የስርዓተ -ትምህርት ማበልፀጊያ ኢንስቲትዩት ክልሎች የሚጠቀሙባቸውን ዲጂታል የመማርያ ቁሳቁስና ትምህርት ቤቶች የሚያስፈልጓቸው የሳይንስ ላቦራቶሪ እቃዎች የመለየትና የመምራት ኃላፊነት አለበት፡

በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች፣ ልክ እንደ መምህራን ማሰልጠኛዎች መፃፍ የማንበብና የመቀመር ክህሎት ለማሳደግ የሚያገለግሉ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ የትምህርት መሣሪያዎች አቅርቦት ታላቅ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል፡፡ ትምህርት ቤቶች በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎችን የማንበብና መቀመር ክህሎት ለማጎልበት የሚረዱ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ አጋዥ የንባብ ፖኬጆች እንዲኖሯቸው ይደረጋል፡፡ የተማሪዎችን መሠረታዊ የመቀመር ክህሎት ለማጎልበት የሚያግዙ ጥራዞች ተዘጋጅተው ለመምህራን ይሰጣሉ፡፡

ድንገተኛ አደጋዎች የብዙ ሰዎችን ህይወት አደጋ ላይ እንዳይጥሉና የመማር ማስተማሩን ሂደት እንዳያስተጓጉል ለማድረግ ይቻል ዘንድ ደህንነቱ የተጠበቀና አደጋዎችን ለመቋቋም የሚያስችል የትምህርት ቤት ከባቢ ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችሉ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡ ትምህርት ቤቶች የሚገኙባቸው አካባቢዎች ለድንገተኛ አደጋዎች (ለምሣሌ ድርቅ፣ ጎርፍና፣ ግጭት) የመጋለጥ ስጋት ያዣበበባቸው ቀጠናዎች ከሆኑ ትምህርት ቤቶቹ ደረጃቸውን የጠበቁ አደጋን የሚቋቋሙ የትምህርት መሣሪያዎች እንደኖሯቸው ይደረጋል፡፡ የዚህ ዓይነት የድጋፍ ማዕቀፍ ለትምህርት አመራርና ለመምህራን ከሚሰጠው ስልጠና ጋር ተዳምሮ ትምህርት ሳይቋረጥ እንዲካሄድ ይረዳል፡፡ የድጋፍ አቅርቦቱ የንጽህና መጠበቂያ መሣሪዎችንና ግብአቶችን /WASH/ እንደዚሁም የትምህርት /አመራር ኪቶችን ያካተተ ይሆናል፡፡ እነዚህ ቁሳቁሶች ጊዜያዊ መፍትሄ የሚሰጡ በመሆናቸው በክልላዊና በብሔራዊ ደረጃ በሚሰጡ ምላሾች ይጠናከራሉ፡፡

ሁሉም የክላስተር የድጋፍ ማዕከላት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የሚያግዙ ማቴሪያሎች እንዲኖሯቸው ይደረጋል፡፡ እነዚህ ማዕከላት የልዩ ፍላጐት ትምህርት ባለሙያዎች

ስለሚቀጠሩላቸው በመሆኑ ትምህርት ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ ቁሳቁሶቹንና ባለሙያዎቹን ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ፡፡

| ስትራቴጂዎች | አመልካች (አሁን ያለውና የታቀደው) | ምንጭ |
|---|---|---|
| ለህይወት ክህሎት፣ ለቴክኒክና ሙያ ተኮር ኢንተርፕረነርሽፕና ተያያዥ የትኩረት አቅጣጫዎች (መስኮች) አጽእኖት በመስጠት የትምህርትን ተገቢነት በማሻሻልና በተማሪዎች መካከል ያለውን የአቅም ልዩነት ባገናዘበ መልኩ ከአፀደ ህፃናት እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ያለውን ሃገር አቀፍ ስርዓተ-ትምህርት መከለስ | ዝቅተኛ የመካከለኛ ገቢ ኢኮኖሚ ላላቸው አገሮች አግባብነት ባለው ስርዓተ-ትምህርት የተዘጋጀላቸው የትምህርት አይነቶች ብዛት 100 በመቶ ይደርሳል | የአጋማሽና የአመታዊ ሪፖርቶች፤ ደሰሳዎች/የጥናት ውጤቶች |
| አሁን በስራ ያለውን የስርዓተ-ትምህርት ዳይሬክቶሬትን ማጠናከርና አዲስ የስርዓተ-ትምህርት ተቋም መመስረት | | |
| የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎት ያማከለና ተጨባጭ አውዳዊ ልዩነቶችን ያገናዘበ ስርዓተ-ትምህርት ለመንደፍ የማያስችል ስትራቴጂ መቀየስ | | |
| ከቅድመ መደበኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ በሚሰጡ ሁሉም የትምህርት አይነቶች የስርዓተ-ትምህርት ክለሳ ማድረግ | | |
| የሃገሪቱን አንድነትና ብዝሃነት በሚያጎለብት መልኩና የሁሉንም ብሔር ብሔረሰቦች ታሪክ በሚያካትት አግባብ ከ9-12ኛ ክፍል ላሉት ደረጃዎች የታሪክ ትምህርት ስርዓተ-ትምህርት መቅረጽ | | |
| በስርዓተ-ትምህርቱ ውስጥ ዋና ዋና በሆኑ የትምህርት መስኮች ውስጥ አይሲቲን ማካተት | | |
| የስርዓተ-ትምህርቱ ማሻሻል ሂደቱን በሚደግፍ መልኩ የቋንቋ ፖሊሲውን አተገባበር መፈተሽ | | |
| የስርዓተ-ትምህርት ክለሳ፣ በአሳታፊ የማስተማር ዘዴ ጠቀሜታነት እንዲሁም በተማሪዎች መካከል ስለሚኖር ልዩነት የመምህራንን ግንዛቤና አቅም ማጎልበት | አሳታፊ የማስተማር ዘዴንና ስልቶችን የሚተገብሩ መምህራንና የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አስተባባሪዎች ቁጥር 100 በመቶ ይደርሳል | የግምገማና ፍተሻ ሪፖርቶች፣ የሙያ ፈቃድ ሰርተፊኬት |
| የተሻሻለውን ስርዓተ-ትምህርት ለመተግበር የሚያስችል ስልጠና ለእጩ መምህራንና አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አስተባባሪዎች መስጠት | | |
| ዘላቂ የሆነ የሙያ ብቃት መሻሻልን ለመደገፍ በተከታታይ የሙያ ልማት ፕሮግራም ውስጥ የስርዓተ-ትምህርት ሞጅዩል ማካተት | | |
| ሁሉም ተማሪዎች ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያስችሉ የትምህርት ማቴሪያሉ በበቂ ይቀርቡላቸዋል፡፡ | የተማሪ መማሪያ መጽሃፍ ምጣኔ (በሁሉም ተቋማት፣ በሁሉም የትምህርት አይነቶች፣ በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ) ከ1፡1 ወደ 1፡1.2 ያድጋል | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | የተማሪና መማሪያ መጽሃፍ አጠቃቀም ምጣኔ ከ1፡0.4 ወደ 1፡0.7 ያድጋል | የናሙና ጥናት |

| | | |
|---|---|---|
| ተፈላጊ በሆኑ ቋንቋዎች የመማሪያ መፃህፍትን ማዘጋጀት፣ ማሳተምና ማሰራጨት | | |
| የትምህርት መሳሪያዎች የስርጭት ዘዴን መፈተሽና ማሻሻል | | |
| ለትምህርት የሚያስፈልጉ የትምህርት ማቴሪያሎችን ለሁሉም ት/ቤቶች በሚፈለገው መጠን ማቅረብ | | |
| ሁሉም አ. ክላሶች (O. Classes) መሠታዊ የትምህርት /ፖኬጆች/ ቁሳቁሶች እንዲኖሯቸው ማድረግ | | |
| ሁሉም የሪሶርስ ማዕከላት/ክላስተሮች በአደጋ ጊዜ ትምህርትን ለመቀጠል የሚያስችሉ የትምህርት መሳሪያዎች እንዲኖራቸው ማድረግ | | |
| ሁሉም የሪሶርስ ማዕከላት/ ክላስተሮች የልዩ ፍላጐት ትምህርት ለሚያስፈልጋቸው ህፃናት ቁሳቁስ እንዲኖራቸው ማድረግ | | |
| | የመማሪያ መጽሃፍና የመምህር መምሪያ ምጣኔ 40:1 ይሆናል | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| ሁሉም መምህራን በተገቢ ሁኔታ ለማስተማር የሚያስችላቸው መጻህፍት በበቂ ሁኔታ ያገኛሉ | የመምህርና የመምህር መምሪያ አጠቃቀም ምጣኔ 1:1 ይደርሳል | የክትትል ጥናት ሪፖርት /የናሙና የዳሰሳ ጥናት |
| ከአፀደ ህፃናት እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል የሚያገለግሉ የትምህርት ብቃትን (learning competencies) በዝርዝር የቀፉ የመምህር መምሪያዎችን ማሰራጨት | | |
| ከአፀደ ህፃናት አስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ለሚሰጡ ሁሉም የትምህርት አይነቶች ተከታታይ የምዘና አሰጣጥ መመሪያዎችን ማዘጋጀት | | |
| በጥንቃቂ የተመረጡ የቅድመ መደበኛ ደረጃ ተማሪዎችን የንባብና የመቀመር ክህሎት የሚያስጨብጡ የትምህርት ማቴሪያሎችን አቅርቦት ማሳደግ | እውቅና የተሰጣቸው ለተዛማጅ /ማጣቀሻ/ ንባብ የሚያገለግሉ ልዩ ቢያንስ ሃያ ልዩ ልዩ መፃህፍት ያሏቸው የመጀመሪያ ደረጃና የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት ብዛት 100 በመቶ ይደርሳል | የናሙና ዳሰሳ ጥናት<br><br>የት/ቤት ክትትል ሪፖርት |
| ለአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል /ቤቶች የማጠናከሪያ መፃህፍትን ማሰራጨት | | |
| በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች የንባብና የቀመር ክህሎታቸውን የሚያጎለብቱ በአፍ መፍቻ ቋንቋዎች መፃህፍትን ማዘጋጀት | | |
| ሁሉም ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ት/ቤቶች ትምህርት ለመቀጠል የሚያስችሉ ግብዓቶች ይኖሩዋቸዋል፡፡ | ደረጃውን የጠበቀ በአደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል የትምህርት ማቴሪያሎች ያሏቸው ት/ቤቶች ቁጥር | የናሙና ዳሰሳ ጥናት |
| | እነደአስፈላጊነቱ የአደጋ ጊዜ ፖኬጆችን ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል እቅድ ያላቸው ትምህርት ቤቶች ብዛት | የናሙና የዳሰሳ ጥናት |
| ደረጃቸውን የጠበቁ በአደጋ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉ የትምህርት ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት /WASH/ ጨምሮ | | |
| የአደጋ ጊዜ ፖኬጆችን ተጋላጭ ወደሆኑ ት/ቤቶች ማሰራጨት (WASH ጨምሮ) | | |

**ተግባር 3. የትምህርት ቤት ማሻሻያ ፕሮግራም**

| ግብ፦ ሁሉም ት/ቤቶች ከህብረተሰቡ በሚያገኙት ድጋፍ በመታገዝ ጥራቱ የተጠበቀ ትምህርት እንዲሰጥ የሚረዳ የአስተዳደርና የአመራር ሁኔታ ይፈጥራሉ፡፡ | በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር | ግብ |
|---|---|---|
| በማስታወቂያ ሰሌዳቸው ላይ የትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ የሚያስቀምጡ ት/ቤቶች (%) | የለም | 50 በመቶ |
| ከሚመደብላቸው መደበኛ በጀት ውስጥ ቢያንስ ግማሽ ያህሉን ለመማር ማስተማር ሂደት የሚያውሉ ት/ቤቶች (%) | የለም | 60 በመቶ |
| ከፍተኛ ጥራት ያለው የትምህርት ቤት የማሻሻያ እቅድ የሚነድፉና የሚተገብሩ ት/ቤቶች (%) | የለም | 100 በመቶ |
| ዘወትር በስራ ገበታቸው ላይ የሚገኙ መምህራን ብዛት | 88 በመቶ | 96 በመቶ |
| ግብዓትን ለመለካት የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉና ከዚያም በላይ ስኬት የሚያስመዘግቡ ት/ቤቶች (%) | የለም | 70 በመቶ |
| የስራ ሂደትን ለመለካት የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉና ከዚያም በላይ ስኬት የሚያስመዘግቡ ት/ቤቶች (%) | የለም | 70በ መቶ |

**ንኡስ ተግባር 1፡ የማህበረሰብ ተሳትፎ**

የትምህርት ቤት ማሻሻያ ፕሮግራም (SIP) የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል የሚያስችል ጠንካራ መሠረት የያዘ እንቅስቃሴ ነው፡፡ የፕሮግራሙ ዋና ትኩረት ማህበረሰቡን በትምህርት አመራርና አስተዳደር በንቃት በማሳተፍ ትምህተ ቤቶች ያላቸውን የፋይናንስ አቅም (ማለትም መደበኛና በድጎማ የሚያገኙትን በጀት) በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት እንዲሰጡና የመማር ማስተማር ሂደቱ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማድረግ ነው፡፡

በትምህርት ቤት ማሻሻያ ፕሮግራም መሠረት እያንዳንዱ ፕሮግራም በመንደፍ ከአንድ ት/ቤት የሚጠበቀውን መሠታዊ መመዘኛ ማሟላት ይገባዋል፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር

የትግበራ ዘመን አሁን በመከናወን ላይ ያለው የት/ቤት የውስጥ ምዘና እና ማህበረሰብን ያማከለ የውሣኔ አሰጣጥ ዘዴ እቅድ ቀጣይነት የኖረዋል፡፡ ትምህርት ቤቶች የወላጅ ፣ ተማሪና መምህር ህብረቶች (PSTAs) እንዲጠናከሩ ድጋፍ የሚደረግላቸው ሲሆን ማህበራቱም "በትምህርት ቤት ሪፖርት ካርዶች" አማካኝነት መረጃ እንዲደርሳቸው በማድረግ በመረጃ ላይ የተመሠረተ የውሣኔ አሰጣጥ ሂደት እንዲያዳብሩ ይደረጋል፡፡

በትምህርት ቤት አስተዳደርና ውሣኔ አሰጣጥ የህብረተሰቡን ተሳትፎ ለማሳደግ ሁለት የግንዛቤ ማዳበሪያ ስልቶች ተቀይሰዋል፡፡ በመጀመሪያ የመገናኛ ብዙሃንን (በራዲዮና ቴሌቪዥን እንደአስፈላጊነቱ የህትመት ሚዲያውንም በመጠቀም) በመጠቀም ዘመቻዎች ይከናወናሉ፡፡ እነዚህ ዘመቻዎች በትምህርት እንደአስፈላጊነቱ በትምህርት አመራር ህብረተሰብ ሊኖረው ስለሚገባ ተሳትፎ እንደዚሁም ትምህርት በህብረተሰቡ እሴቶች ግንባታ በሚኖረው ሚና ላይ ያተኩራሉ፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ በሌሎች ሴክተሮች (ለምሣሌ በጤናው ዘርፍ) እንደሚደረገው "የልማት ቡድኖችን" በማዋቀር የቤት ለቤት የፊት ለፊት ውይይቶች እንዲካሄዱና እያንዳንዱን አባወራና እማወራ እንዲሁም የማህበረሰቡ አባል በትምህርት ዙሪያ ተሳትፎው እንዲጎለብት ይሰራል፡፡ እነዚህ የልማት ቡድኖች በትምህርት ቤቶች አመራርና አስተዳደር የጎላ የህብረተሰብ ተሳትፎ እንዲያመጡ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከመነሻው በእንቅስቃሴ ላይ ያሉ የልማት ቡድን አባላት ተጨማሪ ስልጠና የሚያገኙባቸው አማራጮች ይዳሰሳሉ፡፡ ለምሣሌ ሁሉን ያማከለ መረጃ ለእያንዳንዱ ቤተሰብ ለመስጠት የሚያስችላቸው ተጨማሪ ስልጠና በጤናው ዘርፍ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ራሱን የቻለ የትምህርት የልማት ቡድን ሊቋቋም ይችላል፡፡

የትምህርት ቤት ሪፖርት ካርዶች በትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት የሚገኙ መረጃዎችን፣ በክትትልና በትምህርት ቤት ደረጃ የተገኙ አሃዞችን ወይም መረጃዎችን በቀላል ዘዴ አጠናቅረው ትምህርት ቤቶች ከህብረተሰቡ ጋር በጋራ የሚጠቀሙባቸው ይሆናሉ፡፡ የትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ ባልተማከለ መልክ በወረዳ ደረጃ የሚካሄድ ሲሆን ት/ቤቶችና ክላስተሮች መልካም ተሞክሮዎቻቸውን እንዲለዋወጡ ያስችላቸዋል፡፡

ንኡስ ተግባር 2፡- የትምህርት ቤት አካባቢ

የወላጅ ተማሪና መምህር ህብረቶች (PSTAs) ትምርት ቤቶች መሠረታዊ ደረጃ ያሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የትምህርት ቤት ማሻሻያ ፕሮግራምን (SLP) በመመርያነት ይጠቀማሉ፡፡ መመሪያዎቹ ውጤታማ የመማር ማስተማር እንቅስቃሴ እንዲኖር የሚያስችል የትምህርት አካባቢ ምን መምሰል እንዳለበት ያብራራሉ አምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ሲጠናቀቅ ሀሉም ት/ቤቶች መሠረታዊ የትምህርት ግብአት ፖኬጅ ይኖራቸዋል፡፡ ከአነዚህ ግብዓቶች ዋና ዋናዎቹ፣ አስፈላጊ ቁሳቁስና መሳሪያዎች የተሟሉለት ተገቢውን አገልግሎት የሚሰጥ ቤተ ሙከራ (ለ7ኛና 8ኛ ክፍሎችና ለሁሉም ሁለተኛ ደረጃ)፣ የትምህርት መሳሪያዎችን በጋራ መጠቀም የሚያስችል የትምህርት ማዕከል፣ ለንባብና ቀመር ክሂል መዳበር የሚያግዙ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተዘጋጁ በቂ የመለማመጃ መፃህፍትን የያዘ የትምህርት ቤት የንባብ ክበብ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የትምህርት ቤት አካባቢዎች ተደራሽ፣ አስተማማኝና ጤናማ መሆን አለባቸው፡፡ ይህንን ለማድረግም በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም የትግበራ ዘመን የመጨረሻ አመት የተሰራጨውን የትምህርት ቤቶች የመተዳደሪያ ደንብን በመተግበር ፆታዊ ጥቃቶችና ትንኮሳዎች እንዲቀንሱ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ጀአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ዘመን ሁሉም ት/ቤቶች በቂ የሆነ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ የተማሪዎችን የፆታ ልዩነት ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ በቂ የንጽህና መጠበቂያ አገልግሎቶችና የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተማሪዎች ለአጠቃቀም ምቹ የሆኑ መሠረታዊ አገልግሎቶች እንዲኖሯቸው ይደረጋል፡፡ ትምህርት ቤቶች የአካባቢያቸውን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የስፖርት ማዘውተሪያዎችን እንዲያስፋፉና እንዲያጠናክሩ ይደረጋል፡፡ የትምህርት ቤቶች የWASH አገልግሎት አሰጣጥ የ one wash ሃገር አቀፍ ስምምነትን የተከተለ ይሆናል፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር የመጀመሪያ አመት ለልዩ ፍላጎት ትምህርት በሚያስፈልጉ የመሠረታዊ አገልግሎቶች ፖኬጅ ስምምነት ላይ የሚደርስ ሲሆን በቀጣዩ አመት የሚተገበር ይሆናል፡፡

በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የተማሪዎችን የህይወት ክህሎት ለማሳደግ የሚረዱና ጤናማና አስተማማኝ የትምህርት ቤት አካባቢን ለመፍጠር የሚያስችሉ የተለያዩ የተማሪ አገልግሎት ማዕከላት ይቋቋማሉ፡፡

የተማሪ አገልግሎት ማዕከላቱ ዋና ትኩረት በኤች አይ ቪ/ኤድስ ፣ በአባለዘር በሽታዎች፣ በትምህርት ቤትና በተማሪ ጤንነትና አመጋገብ ላይ ያነጣጠረ ይሆናል፡፡ የተማሪ አገልግሎቶችን ተገቢነትና ተደራሽነት ለማሳደግ የትምህርት አስተዳደሩ በዚህ ዙሪያ ከሚንቀሳቀሱ የምግብ፣ መድሃኒትና ጤና አጠባበቅ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ከመሳሰሉት ሌሎች የመንግስት አካላትና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በቅርበት ይሰራል፡፡ ከፍተኛ የምግብ እጥረት በሚስተዋልባቸውና እጅግ ኋላ ቀር በሆኑ አካባቢዎች ለሚገኙ ትምህርት ቤቶች የምግብ አቅርቦት ይሰጣል፡፡ በመዘጋጀት ላይ የሚገኘው ዘርፈ ብዙ ሃገራዊ የትምህርት ቤት የምግብ አቅርቦት ስትራቴጂ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ስትራተጂ የሚተገበር ይሆናል፡፡ ስትራቴጂው የምግብ እጥረት ባለባቸው ቦታዎች የሚገኙ የቅድመ መደበኛና የመጀመሪያ ሳይክል ደረጃ ተማሪዎችንና ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች የሚመጡ ተማሪዎችን ቅድሚያ በመስጠት ይደግፋል፡፡

ትምህርት ቤቶችን ከበሽታ አምጭ ተህዋሳት የማጽዳትና መሰል የጤና አጠባበቅ እንቅስቃሴዎች “ከተማሪ አገልግሎት” ጋር በተያያዥነት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ የጤና አጠባበቅን፣ ትብብርን፣ የቡድን ስራንና አመለካከትን ለማጎልበት ያለውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ግምት ውስጥ በማስገባት የትምህርት ቤት ስፖርትን ማስፋፋት የት/ቤት ማሻሻያ ፕሮግራሙ ትኩረት የሚሰጠው ሌላው ጉዳይ ይሆናል፡፡ በየርእሱ “የትምህርት ቤት ክበቦችን” ከማቋቋም ይልቅ ሁሉን አቀፍ “የትምህርት ቤት አገልግሎት” በማቋቋም የተማሪዎችን መሠረታዊ የህይወት ክህሎት ስልጠና ከስፖርት ክበቦች ጋር በማቀናጀት ጤናማና አስተማማኝ የትምህርት ቤት አካባቢ እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡

**ንኡስ ተግባር 3፡ መማር ማስተማር**

ሁሉም መምህራን በአመት ውስጥ ቢያንስ አራት ሙሉ ቀናት በት/ቤቶች በሚዘጋጁ የውስጥ የሙያ ልማት መርሃ ግብሮች በመሳተፍ ማሳለፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በትምህርት ቤት ማሻሻያ ፕሮግራም የትምህርት ማህበረሰቡ፣ የት/ቤት ክላስተሮችና የድጋፍ መረቦች መምህራን በተከታታይ የሙያ ልማት መርሃ ግብሮች እንዲሳተፉና ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ተከታታይ የሙያ ልማት መርሃ ግብሩ መደበኛ የኮርስ ስልጠናዎችን፣ ከሌሎች መምህራን ወይም ሱፐርቫይዘሮች ጋር የሚደረጉ

የልምድ ልውውጥ መድረኮችን፣ አክሽን ሪሰርቾችን (ከተግባር የመነጨ ጥናት ማካሄድን)፣ የጥናት ቡድኖችን፣ የልምምድ ፕሮግራሞችን ወይም ሌሎች ተዛማጅ እንቅስቃሴዎችን ያካተተ ሊሆን ይችላል። የተከታታይ የሙያ ልማት መርሃ ግብሩ ዋና ይዘት በዚህ ሰነድ "የመምህራን ክህሎት እና የሙያ ልማት" በሚለው ንዑስ -ትግበራ ስር በተገለፀው መሠረት ይሆናል።

በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች በመማር ማስተማር፣ በትምህርት ቤት አደረጃጀትና አስተዳደር፣ በወላጆች ተሳትፎና በወላጅ ተማሪና መምህር ህብረት ሚና እጅግ የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ ስኬታማ ተሞክሮዎችን ማስተዋል ይቻላል። በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ- ግብር ዘመን በፌዴራልና በክልል ደረጃ ያሉ የትምህርት ማሻሻያ ፕሮግራም ሃላፊዎች ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማጥናት በየአመቱ የጥናት ግኝቶቻቸውን ወደ ሁሉም ትምህርት ቤቶች ያሰራጫሉ። የጥናት ውጤቶች ተከታታይ የሙያ ልማት እንቅስቃሴዎችን የሚያጎለብቱና የትምህርት አመራሮችንና የመምህራንን የስራ ተሞክሮ የሚያሻሽሉ ይሆናሉ። የትምህርት ቤት ማሻሻያ ፕሮግራሙ (SLP) መመርያ ትምህርት ቤቶች አሳታፊ የማስተማር ዘዴ እንዲኖር፣ ስርዓተ-ትምህርትን በተመለከተ ስለካሪኩለሙ በቂ ግንዛቤ እንዲፈጠርና መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም የትምህርት አሰጣጥ ሂደቱን ማጎልበት እንዲቻል የሚያግዙ እንቅስቃሴዎችን እንዲደግፉ ያበረታታል።

እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ከወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት (PSTA) ጋር በመተባበር በመሠረታዊ ክሂሎች ላይ ያተኮረ ውጤት ተኮር ተከታታይ የምዘና ሂደት በመንደፍ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤ ይህም መምህራን የተማሪዎችን አቅም ለመከታተልና እያንዳንዱ ተማሪ የሚጠበቅበት ደረጃ ላይ ለመድረስ የሚያደርገውን ጥረት ለመደገፍ ያስችላቸዋል። ተከታታይ ምዘናው ተማሪዎች ሊያዳብሩ በሚገባቸው መሠረታዊ ክህሎቶች ላይ ያተኮረና ተከታታይ ምዘና ለማከናወን የሚያስችሉ መመዘኛዎች በተደራጁበት የምዘና ቋት የሚደገፍ ነው። ክላስተሮች፣ ወረዳዎችና ክልሎች በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች የሚገኙ ተማሪዎች ሊኖሯቸው የሚገቡ መሠረታዊ ክሂሎችን በተመለከተ የተቀመጠውን መስፈርት ወጥ በሆነ መልኩ በመከታተል ችግሮች ሲኖሩ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወስድ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

የትምህርት ቤት ማሻሻያ ፕሮግራሙ ለተጠቀሱት የትኩረት ዘርፎች ቅድሚያ በመስጠት ትምህርት ቤቶች የተቀመጠውን ዝቅተኛ መስፈርት ማሟላት ይችሉ ዘንድ መምህራን ስርዓተ ትምህርቱን ለመተግበር የሚያስችል አቅም እንዲፈጥሩና ድጋፍ ሊሰጥዋቸው ይገባል፡፡

**ንኡስ ተግባር 4፡ የትምህርት ቤት አመራር**

የትምህርት አመራርና አስተዳደር ፕሮግራሙ በመረጃ ላይ የተመረኮዘ እቅድና ውሣኔ አሰጣጥን ለማምጣት እንዲያመች ተደርጎ በተዘጋጀው ዝርዝር መመሪያ በመታገዝ ርዕሰ መምህራን ከወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት (PSTA) ጋር የሚያደርጉትን መስተጋብር ያጠናክራል፡፡ የትምህርት አመራሮች ትምህርት ቤት ነክ ጉዳዮች እንዴት መፍታት እንዳለባቸው የሚያመላክት አጠቃላይ የትምህርት አስተዳደርና ሃብት አጠቃቀም ማኑዋል ይሰጣቸዋል፡፡ አነስተኛ ትምህርት ቤቶችና የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት የሚገለገሉበት የት/ቤት ማሻሻያ ፕሮግራም (SLP) መመሪያ በመዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡

የሚዘጋጁት ማቴርያሎች ሁሉ በአሁኑ ወቅት ካሉት የት/ቤት ማሻሻያ ፕሮግራም ሳይክሎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በትምህርት ቤት ደረጃ የሶስት አመት የስትራቴጂክ እቅድና አመታዊ የትግበራ እቅድ አዘገጃጀት ላይ የተመሠረቱ ይሆናሉ፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ-ግብር ት/ቤቶች በት/ቤት ማሻሻያ ፕሮግራም መዋቅር ከተካተቱት ዘርፎች መካከል ለመማር ማስተማር ዘርፉ ትኩረት በመስጠት ካላቸው ሃብት ከፍተኛውን ድርሻ ለዚሁ እንዲያውሉ ይበረታታሉ፡፡ የት/ቤቶችን ደረጃ ለመለየት በወጣው መስፈርት መሠረት፣ አቅማቸውን ከጊዜ ወደ ጊዜ ማጎልበት የቻሉና የተማሪዎቻቸውን ውጤት ማሳደግ የቻሉ ትምህርት ቤቶች የበለጠ የራስ አስተዳደር ነፃነት እየተሰጣቸው ይሄዳሉ፡፡

በእያንዳንዱ ክላስተር ቢያንስ አንድ ት/ቤት ወደ ሞዴልነት ደረጃ (በመመዘኛ መስፈርቱ ደረጃ አራትን በማሟላት) እንዲደርስና የልዩ ፍላጎት ትምህርትን ጨምሮ የሱፐርቪዥንና የጋይዳንስ ኃላፊነቶችን በብቃት እንዲወጣ ይጠበቃል፡፡ በክላስተር ደረጃ ምዘናዎችን በማዘጋጀት ቀስ በቀስ የተማሪዎች ምዘና

ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ እነዚህ ተግባራት ት/ቤቶች ጠንካራና ደካማ ጎኖቻቸውን እንዲፈትሹና ከሌሎች የክላስተር አባላት ጋር በመተባበር በክላስተር ደረጃ ያለውን አመራር ተጠቅመው የት/ቤት አስተዳደር ዘዴዎቻቸውንና የተማሪዎቻቸውን ውጤት እንዲያሻሽሉ ያስችሏቸዋል፡፡

| ስትራቴጂዎች | አመልካች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| የህብረተሰቡን ተሳትፎ ማሳደግ | ጠንካራ የወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት (PSTA) ያላቸው ት/ቤቶች ድርሻ 90 በመቶ ይደርሳል | የ5ኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ዓመታዊ ሪፖርቶች |
| | የትምህርት ቤት የሪፖርት ካርድ በማስታወቂያ ሰሌዳቸው የሚለጥፉ ት/ቤቶች ድርሻ 50 በመቶ ይደርሳል | የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም ሪፖርቶች |
| | ከፍተኛ ጥራት ያለው የት/ቤት ማሻሻያ ፕሮግራም የነደፉና ተግባራዊ ያደረጉ /ቤቶች ድርሻ 100 በመቶ ይደርሳል | የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም ሪፖርቶች |
| | በት/ቤት አስተዳደር ሂደቱ መርካታቸውን የሚገልፁ የወላጆች ድርሻ 75 በመቶ ይደርሳል | የናሙና የዳሰሳ ጥናት |
| | የመምህራን በስራ ገበታቸው ላይ የመገኘት ምጣኔ ከ88 በመቶ ወደ 96 በመቶ ከፍ ይላል | የናሙና የዳሰሳ ጥናት |
| | በት/ቤት ማሻሻያ ፕሮግራም ከተመደበላቸው በጀት ቢያንስ ግማሽ ያህሉን ለመማር ማስተማር ሂደቱ የሚያውሉ ት/ቤቶች ድርሻ 60 በመቶ ይደርሳል | የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም ሪፖርቶች |
| የልማት ቡድኖችንና የመገናኛ ብዙሃን ዘመቻዎችን በመጠቀም የህብረተሰቡን ተሳትፎ ማሳደግና ስለትምህርት ጠቀሜታ ያለውን ግንዛቤ ማሳደግ | | |
| የት/ቤት የሪፖርት ካርድ አጠቃቀምን ማጎልበት | | |
| በሁሉም ት/ቤቶች የወላጅ ተማሪ መምህር ማህበራትን ማቋቋም | | |
| ለት/ቤቶች አገልግሎት የሚውል አጠቃላይ የአስተዳደርና የሃብት አጠቀቀም ማኑዋል ማዘጋጀት | | |
| በት/ቤትና በወላጆች ህብረተሰብ መካከል ያለውን ግንኙነት ማጠናከር | | |
| ት/ቤቶች ምቹና ጤናማ የትምህርት አካባቢን ለመፍጠር የሚያስችሏቸው የቁሳቁስ የአገልግሎቶች ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ | የተቀመጠውን መስፈርቱን ያሟሉና ከዛም በላይ ስኬት ያስመዘገቡ የቅድመ መደበኛ ት/ቤቶች ቁጥር 60 በመቶ ይደርሳል፡፡ | ክትትል |
| | መስፈርቱን ያሟሉና ከዛም በላይ ስኬት ያስመዘገቡ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ቁጥር ከ25 በመቶ ወደ 70 በመቶ ያድጋል | ክትትል |
| | መስፈርቱን ያሟሉና ከዛም በላይ ስኬት ያስመዘገቡ | ክትትል |

| | | |
|---|---|---|
| | የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ቁጥር ከ40 በመቶ ወደ 75 በመቶ ያድጋል፡፡ | |
| | መስፈርቱን ያሟሉና ከዛም በላይ ስኬት ያስመዘገቡ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት ቁጥር 70 በመቶ ይደርሳል | ክትትል |
| | ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ደረጃውን የጠበቀ (በመጀመሪያው አመት ደረጃው ይወጣል) አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ ግብዓት የተሟላላቸው ት/ቤቶች ቁጥር ለመዋዕለ ህፃናት 75 በመቶ ፣ ለአንደኛ ደረጃ 35 በመቶ ፣ ለሁለተኛ ደረጃ 55 በመቶ ይደርሳል | ክትትል |
| | በቂ ግብአት ያላቸው የልዩ ፍላጎት ትምህርት የክላስተር ማዕከለት ቁጥር 800 ይደርሳል | ልዩ ድጋፍና አካቶ ትምህርት |
| ት/ቤቶች መሠረታዊ ግብአቶች የተሟሉላቸው እንዲሆኑ ማድረግ (ለምሣሌ ፣ ቤተ ሙከራዎች፣ ማጣቀሻ መፃህፍትና ቤተመፃህፍት፣ ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች የተዘጋጁ ማቴሪያሎች ይጨምራል) | | |
| ከትምህርት ጋር ተያያዥና ተያያዥ ያልሆኑ (extracurricular /co-curricular)ፕሮግራሞችንና ክበቦችን በሁሉም ት/ቤት መመስረትና ማጠናከር | | |
| ውጤታማ የሆነ የተማሪ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ስትራቴጂ መንደፍና ኤች አይቪ/ ኤድስን፣ የአባለዘር በሽታዎችንና የት/ቤት ጤና አጠባበቅንና አመጋገብ ጉዳዮችን ማካተት | | |
| መርጃ/አጋዥ መፃህፍትና ማቴሪያሎች በተማሪ አገልግሎት ማዕከላት በኩል ለተማሪዎች የሚሰራጩበትን ስትራቴጂ በመንደፍ፣ የአባላዘር በሽታዎችን፣ ጤና አጠባበቅና አመጋገብን እንዲሁም ኤች አየቪ/ኤድስን በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ በተማሪዎች መካከል ያለውን የመረጃ ልውውጥ ማሳደግ | | |
| በተማሪ አገልግሎት ማዕከላት በኩል ለተማሪዎች የአቻ ለአቻ ትምህርትና የህይወት ክህሎት ትምህርት በመስጠት በኤችአይቪ/ኤድስና በአባላዘር በሽታዎች ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ማሳደግ | | |
| በ One Wash መስፈርቶችን መሠረት የWash ቁሳቁሶችን ማቅረብ | | |
| ስፖርት ነክ ጉዳዮችና ፋሲሊቲዎችን የማስፋፋት እንቅስቃሴዎችን በሚመለከት እንደዚሁም ስለ ስፖርታዊ ውድድሮች መረጃ መለዋወጥ የሚያስችል ስርዓት እንዲኖር ማድረግ | | |
| ደረጃቸውን የጠበቁ አዳዲስ የመማሪያ ክፍሎችን (የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ሊጠቀሙባቸው በሚያስችል መልኩ) መገንባት | | |
| የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች በሚማሩባቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስፈልጓቸውን ማቴሪያሎች እንዲያገኙ ማድረግ | | |
| በክላስተር የመርጃ ማዕከላት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ግብዓቶችን እንዲሟሉ ማድረግ | | |
| በተመረጡ ት/ቤቶች /ክልሎች የበሽታ አዋጭ ህዋሳት የማስወገድ ፕሮግራሞችን ማካሄድ | | |
| ለት/ቤቶች የተዘጋጀውን የመተዳደሪያ ደንብ በመጠቀም የወሲብ ጥቃትን፣ ፆታዊ ትንኮሳንና ግጭቶችን በአግባቡ መመርመር | | |

| | | |
|---|---|---|
| በሁሉም ት/ቤቶች የንባብ ክበቦችን መመስረት | | |
| በት/ቤትና በህብረተሰቡ እንዲሁም በት/ቤትና በክላስተር መካከል ያለውን የድጋፍ ግንኙነት በማሻሻልና በማጠናከር እንደዚሁም የአቻ ለአቻ ትብብሮችን ትስስሮችን በማዳበር ተከታታይ ሙያዊ ልማትን በማቀላጠፍ ውጤታማ የመማር ማስተማር እንቅስቃሴ እንዲሻሻል ማድረግ | በክላስተርና በወረዳ የስራ ቡድኖች የተዘጋጁ ፈተናዎችን የሚጠቀሙ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ቁጥር 100 በመቶ ይደርሳል | የክትትል ትምህርት ቢሮ ሪፖርት |
| | በክላስተርና በወረዳ የስራ ቡድኖች የተዘጋጁ ፈተናዎችን የሚጠቀሙ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ቁጥር 100 በመቶ ይደርሳል | የክፍል ትምህርት ቢሮ ሪፖርት |
| አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ማህበረሰብን የማደራጃ መረጃ የመለዋወጫ የልህቀት ማዕከላት እንዲሆኑ ማጎልበት | | |
| በሁሉም የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተግባራዊ የትምህርት ማዕከላትን ማቋቋም | | |
| ት/ቤቶች ራሳቸውን እንዲገመግሙ ድጋፍ መስጠት | | |
| መልካም ተሞክሮዎችን ወደ ቅድመ መደበኛ፣ አንደኛና ሁለተኛ ት/ቤቶች ማሰራጨት | | |

**ተግባር 4፡ የኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ**

| | | |
|---|---|---|
| ግብ፡- ዲጂታል አሰራር እየተስፋፊ ባለበት ሁኔታ የአይሲቲ መሠረተ ልማቶችን፣ ቁሳቁሶችንና ግብአቶችን በማቅረብ የመማር ማስተማሩን ሂደት እና የተማሪዎችን አቅም ማጎልበት | 4ኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር | ግብ |
| በኮምፒውተር የተደገፈ ትምህርት የሚሰጡ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች (%) | 6 በመቶ | 50 በመቶ |
| ዲጅታል የትምህርት መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችል የኢንተርኔት ግንኙነት ያላቸው ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች (%) | 28 በመቶ | 50 በመቶ |
| በቴሌቢዥን የተደገፈ ትምህርት መስጠት የሚችሉ ሁለተኛ | 69 በመቶ | 100 በመቶ |

| | | |
|---|---|---|
| ደረጃ ት/ቤቶች (%) | | |
| የሬዲዮ ትምህርት ለመከታተል የሚያስችሉ የትምህርት ቁሳቁሶች የተሟሉላቸው የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች (%) | 63 በመቶ | 100 በመቶ |
| የልዩ ፍላጎት ትምህርት ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎች ሊጠቀሙባቸው በሚያስችል መልኩ የተዘጋጁ የዲጅታል የትምህርት ግብአቶች (%) | የለም | 100 በመቶ |

**ንኡስ ተግባር 1፡ የአይሲቲ መሠረተ ልማት ለመማር ማስተማር**

መንግሥት በትምህርት ውስጥ የአይሲቲ አጠቃቀም ይበልጥ በማስፋፋት የመማር ማስተማር ጥራትን እንዲሻሻል የማድረግ ቁርጠኛ አቋም አለው፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት እቅድ ወቅት የማስተማር ዘዴ ከትምህርት ይዘትና ቴክኖሎጂ ጋር የተሳለጠ የማድረጉ ሥራ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡

የአይሲቲ ቁሳቁሶች በትምህርት ቤት ደረጃ ተደራሽ እንዲሆኑ ከማድረግ ጀምሮ አይሲቲን ለትምህርት መጠቀም በተመለከተ በመዘጋጀት ላይ ያለው ፖሊሲ ፀድቆ በሥራ ላይ ይውላል፡፡ የዚህ ስትራቴጂ ዋና አካል 'ስኩልኔት ክላውድ ኮምፒውቲንግ' 'school NET Cloud —Computing' የተሰኘው መሠረተ ልማት ሲሆን መምህራንና ተማሪዎች ከማዕከል የተከማቹ የተለያዩ ዲጅታል መረጃዎችን ማግኘት የሚችሉበት ዋና መስመር ይሆናል፡፡ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግም በትምህርት ይዘት አደረጃጀት ዘዴ የሚታገዝ በበቂ ሁኔታ የተደራጀ የመረጃ ማዕከልና የኔትወርክ ኦፕሬሽን ማዕከል ይቋቋማል፡፡

በተጨማሪም፣ በርከት ያሉ ት/ቤቶች በነፃ ወይም በዝቅተኛ ክፍያ የኢንተርኔት አገልግሎት የሚያገኙና አርስ በእርስ የተገናኘ አጠቃላይ የኮምፒውተር ቤተሙከራ (የኤሌክትሮኒክ ብሬል ያካተተ) እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት በማይዳረስባቸው በአርብቶ አደርና በገጠር አካባቢ የሚገኙ

ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የትምህርት መረጃዎች የተጫነባቸው በፀሃይል ሃይል የሚሰሩ ኮምፒውተሮችና ሞባይሎች ይታደላሉ። አስተማማኝ የሆነ የእድሳትና የጥገና አገልግሎት እንዲኖር ለማስቻል የአይሲቲ መሳሪያዎች የጥገናና የእድሳት ወርክሾፖች /ማዕከላት በሁሉም ክልሎች ይቋቋማል።

**ንኡስ ተግባር 2፡ ለአይሲቲ የሚሆን የትምህርት ይዘት ዝግጅት**

ይህ ስትራቴጂ የትምህርት ይዘቶች ዲጅታል እንዲሆኑ በማድረግ ሁሉም አካላት ሊጠቀሙባቸው ወደሚያስችል ደረጃ የማበልፀግ እንቅስቃሴን ያካትታል። አይሲቲ በሁሉም ደረጃ ዋና ዋና በሆኑ የትምህርት አይነቶች ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል። ተማሪዎች በአይሲቲ ላይ ከተመሠረተ ትምህርት ተገቢውን ጠቀሜታ ለማግኘት ይችሉ ዘንድ በቂ የሆነ የአይሲቲ መሠረታዊ ክህሎት ሊኖራቸው ይገባል። አይሲቲን እንደ አንድ ራሱን የቻለ የትምህርት አይነት ነጥሎ ከማስተማር ይልቅ ተማሪዎች አይሲቲን ሬዲዮን፣ ቴሌቢዥንና ዲጅታል ቴክኖሎጅዎችን ጨምሮ እንዲጠቀሙ የሚያበረታቱ መልመጃዎች በሁሉም ዋና ዋና የትምህርት አይነቶች ውስጥ የሚካተቱ ይሆናል። ስርዓተ- ትምህርቱ በሚሻሻልበት ወቅት የዋና ዋና ክፍሎች የዲጅታል ይዘቶች እንዲበለጽጉ ይደረጋል።

የተማሪዎችንና የመምህራንን በኤሌክትሮኒክ እገዛ የመማር ባህልን ለማጎልበትና ከስርዓተ ትምህርቱ ይዘት ጋር ተመሣሣይ የሆነ የዲጅታል ትምህርታዊ መረጃ ክምችት መጠን እንዲጨምር ለማስቻል በሁሉም የትምህርት አይነቶች ዲጅታል ይዘቶችን የማበልፀግ ተግባር ይከናወናል። ከዚህ ጎን ለጎን ትኩረት በሚሹ ዋና ዋና ጉዳዮች (ለምሣሌ፣ በፆታ እኩልነት፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በWash ፣ በኤች አይቪ/ ኤድስና በአባላዘር በሽታዎች ዙሪያ) የሚያተኩሩ ተጨማሪ የዲጂታል ይዘቶች ይጎለብታል።

| ስትራቴጂዎች | አመልካች (መነሻና ግብን ጨመሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| በትምህርት ፕሮግራም ተቋማት ያላቸውን የአይሲቲ አቅም ማጎልበት | ትምህርትን ማገዝ የሚያስችል የአይሲቲ ፖሊሲ መጽደቅ | የፖሊሲ ሰነድ |
| በትምህርት ፕሮግራም ብሔራዊ የአይ.ሲ.ቲ. ኢንስቲትዩት ማቋቋም | | |
| በብሔራዊ ደረጃ ስልጠና በመስጠት የሰው ሃይል አቅምን ማሳደግ | | |
| በሁሉም ደረጃዎች የስኩልኔት 'SchoolNet' ኮምፒውቲንግ ሶልዩሺን | የተሻሻለ ትምህርት ለመስጠት የሚያግዙ የትምህርት መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችል | የሲስተም ሪፖርቶች |

| | | |
|---|---|---|
| ተቋማትን መመስረትና የአይሲቲ መሠረተ ልማት ማሻሻል | የኢንተርኔት አገልግሎት የተሟላባቸው ት/ቤቶች ቁጥር 58 በመቶ ይደርሳል | |
| | በኮምፒውተር የታገዘ ትምህርት መስጠት የሚችሉ ት/ቤቶች ቁጥር ከ6 በመቶ ወፌ 50 በመቶ ያድጋል | ከትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ሲስተም የተገኘ መረጃ |
| | በቴሌቪዥን የታገዘ ትምህርት መስጠት የሚችሉ ት/ቤቶች ቁጥር ከ69 በመቶ ወደ 100 በመቶ ያድጋል | ከትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት የሚገኝ መረጃ |
| | በሬዲዮ የታገዘ ትምህርት መስጠት የሚችሉ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ቁጥር ከ63 በመቶ ወደ 100 በመቶ ያድጋል | ከትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት የሚገኝ መረጃ |
| በትምህርት አስተዳደር ስርዓትና በትምህርት ይዘት አስተዳደር ዘዴ የሚታገዝ ብሔራዊ የዲጅታል የትምህርት መረጃ ቋት በመሆን የሚያገለግል በሙሉ አቅሙ የሚንቀሳቀስ፣ በበቂ ሁኔታ የተደራጀ የመረጃ ማዕከልና የኔትወርክ ኦፕሬሽን ማዕከል ማቋቋም | | |
| የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በነፃ ወይም በዝቅተኛ ዋጋ የኢንተርኔት አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ማጠናከር | | |
| እርስ በእርስ የተገናኘ አጠቃላይ የኮምፒውተር ቤተ ሙከራ (የኤሌክትሮኒክ ብሬልን ያካተተ)በተመረጡ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ፣ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆችና መምህራንን በሚያስለጥኑ ዩኒቨርስቲዎች ማቋቋም | | |
| በሁሉም ክልሎች የአይሲቲ መሳሪያዎች የጥገና ማዕከላትን ማቋቋም | | |
| በአርብቶ አደርና በገጠር ለሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በፀሐይ ኃይል የሚሰሩ ኮምፒውተሮችንና ሞባይሎችን ማቅረብ | | |
| ድጅታል የትምህርት ይዘቶች አጠቃቀም ባህልን ማጎልበት | በሁሉም ደረጃዎች የሚገኙ ተማሪዎች በሁሉም ስርዓተ ትምህርቶች የሚዘጋጁ ዲጂታል የትምህርት ይዘቶች 100 በመቶ ይሆናሉ | በአይሲቲ ማዕከል ሪፖርቶች |
| ከስርአተ-ትምህርቱ ጋር የተቀናጁ የብሮድካስትና ዲጅታል የትምህርት ግብአቶችን ማበልፀግ | | |
| የአካባቢ ጥበቃን በመሰሉ ትኩረት በሚሹና በተዛማጅ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ አካባቢያዊ የዲጅታል ትምህርት ይዘቶች እንዲሰራጩ ማድረግ | | |

**ተግባር 5፡ የትምህርት ጥራት ማረጋገጥ**

| ግብ፡- የጥራት ማረጋገጥ ሒደቶችን በመጠቀም የመምህሩን ፣ የተማሪውንና የትምህርት ቤቱን አቅም ከተቀመጡ መስፈርቶች አንፃር በመለካት ትምህርት መውሰድ፣ ልምዶችን መለዋወጥና ቀጣይ እንቅስቃሴዎችን ማሻሻል | በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብርድምር (ወ/ሴ) | ግብ ድምር(ወ/ሴ) |
|---|---|---|
| በውጪ አካል አንድ ጊዜ የጥራት ምዘና ያካሄዱ ተቋማት (%) | የለም | 100 በመቶ |
| የቁጥጥር እንቅስቃሴዎችን በማከናወን ላይ የሚገኙ ወረዳዎች (%) | የለም | 100 በመቶ |
| በድጋሚ ቁጥጥር ወቅት ከፍ ያለ ደረጃ ያገኙ የት/ቤቶች (%) | የለም | 55 በመቶ |
| የሙያ ፈቃድ ፍተሻ ሂደት ያካሄዱ መምህራን (%) | የለም | 90 በመቶ (90/90) |
| እውቅና የተሰጣቸው የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች | የለም | 100 በመቶ |
| በ4ኛ፣ 8ኛ፣10ኛ/12ኛ ክፍል ብሔራዊ የትምህርት ምዘናና በ10ኛ/12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናዎች ወቅት ከፈተናዎች ማደራጃ የተወሰዱ ጥያቄዎች (%) | የለም | 100 በመቶ |
| ከ2015 እ.ኤ.አ ጀምሮ የሚሰጥ የያንዳንዱ ፈተና ወይም ምዘና ሪፖርት (ቢያንስ አንድ አንድ ኮፒ) ያላቸው ወረዳዎች (%) | የለም | 100 በመቶ |
| 10ኛ ና 12ኛ ክፍል ከደረሱ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች መካከል ለብሔራዊ ፈተና የተቀመጡ (አስፈላጊ ማሻሻያ የተደረገባቸውን ጨምሮ) | የለም | 100 በመቶ (100/100) |

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ-ግብር የትምህርት ጥራት የማረጋገጥ ሒደቱ የሚጎለብት ሲሆን ለቢሮ ኃላፊዎች ፣ ለትምህርት አመራሮችና ለመምህራን አስፈላጊውን ተጨማሪ መረጃ በማቅረብ የትምህርት ግብአት አመዳደብና የውሣኔ አሰጣጡ ሂደት በሁሉም ትምህርት ቤቶች ይበልጥ ፍትሃዊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

**ንኡስ ተግባር 1፡ የትምህርት ቤት ክትትል/ ቁጥጥር**

እ.ኤ.አ በ2012 ትምህርት ቤቶችን ያሉበትን ደረጃ ለመቆጣጠርና በዚህም የሚገኘውን ውጤት መጠነ ሰፊ ለውጥ ለማካሄድ የሚያስችል የትምህርት ቤት የቁጥጥር ስርአት ተመስርቷል፡፡ የትምህርት ቤት የቁጥጥር ስልቱ የአያንዳንዱን ት/ቤት የትምህርት ግብዓት፣ ሒደትና ውጤት በመመዘን ባለአራት ደረጃ

የመለኪያ መስፈርት በማውጣት ለት/ቤቶች ከአንድ እስከ አራት ያሉትን ደረጃዎች ይሰጣል፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ-ግብር የትግበራ የመጀመሪያ አመት የተቆጣጣሪ ተቋሙ መዋቅራዊ አደረጃጀት የሚስፋፋና የሚጠናከር ሲሆን በሚከተሉት ሁለት ወይም ሶስት አመታት ውስጥ ተቋሙ ሙሉ አቅሙን ተጠቅሞ መንቀሳቀስ የሚያስችለው አቅም እንዲፈጥር ይደረጋል፡፡ የቅድመ መደበኛ ትምህርትን ልዩ ት/ቤቶችንና የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርቶችን ለመከታተል የሚያስችሉ የቁጥጥር መስፈርቶች ይዘጋጃሉ፡፡ በትግበራ እና በማስፋፋት ሂደቱ የመጀመሪያ አመታት በቁጥጥር መመሪያዎቹ ላይ ተደጋጋሚ ማሻሻያና ማስተካከያዎች በማድረግ፣ መመዘኛዎቹ ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠትና የተማሪዎች አቅም እንዲጎለብት ት/ቤቶች ሊያሟሉ የሚገባቸውን የግብዓት፣ ሒደትና ውጤት በትክክል መለካት የሚችሉ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ-ግብር ወቅት የትምህርት ቤቶች የቁጥጥር ስርዓት ራሱን ችሎ ሁሉንም ት/ቤቶች በአንድ ጊዜ የሚገመግም ሲሆን፣ በመጀመሪያው ቁጥጥር የሚጠበቀውን ደረጃ (ደረጃ ሶስት) ያላገኙ ት/ቤቶችን ዳግመኛ ቁጥጥር በማድረግ እርምጃዎችን ምላሾችን ይፈትሻል፡፡ እያንዳንዱ የት/ቤት ፍተሻ ለትምህርት አመራሮችና ለማህበረሰቡ ግብረ መልሶችን የሚሰጥና የት/ቤቱን ደረጃ ለማሳደግ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ያመላክታል፡፡ በተጨማሪም በወላጅ ተማሪ መምህር ህብረቶች (PSTA) አማካኝነት የት/ቤት አመራሮችና የማህበረሰቡ አካላት የራሳቸውን የግል ፍተሻ እንዲያከናውኑና ደካማና ጠንካራ ጎናቸውን እንዲለዩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ ከዚህ የሚገኘው መረጃ ለት/ቤት እቅድ ሂደቱ እንደዋና ግብዓት ሆኖ ያገለግላል፡፡

በትምህርት ቤት ደረጃ ከሚደረግ ግብረ መልስ ባለፈ፣ የቁጥጥር ስርዓቱ የትምህርት ግብዓት፣ ሒደትንና ውጤትን በተመለከተ በአጠቃላይ በትምህርት ዘርፍ ሴክተር ያሉትን ጥንካሬዎችና ድክመቶችን ለመረዳት ጥረት ያደርጋል፡፡ ከወረዳ እስከ ፌዴራል ደረጃ የሚገኙ ዋና ባለድርሻ አካላት (በየክልሉ የሚገኙ ፖሊሲ አውጭዎችን ጨምሮ) ይህን መረጃ በመጠቀም ለትምህርት ጥራት መሻሻል አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ይበረታታሉ፡፡

**ንኡስ ተግባር 2፡ የመምህራንና የትምህርት አመራር ሙያ ፈቃድ**

**የአጠቃላይ ትምህርቱ ንኡስ ዘርፍ**

ከአንድ አመት የስልጠና የስክር ወረቀት ጀምሮ እስከ ማስተርስ ዲግሪ ድረስ ያላቸው ከ450,000 በላይ መምህራንና የትምህርት አመራሮችን የያዘ ነው። በዚህ ሰነድ የመምህራን ስልጠናና ሙያዊ ልማት በሚለው ክፍል እንደተጠቀሰው፣ በአሁኑ ወቅት ያለው የመምህራን የማስተማር ክህሎት ውጤታማ የመማር ማስተማር ሒደትን ለመተግበር የሚያስችል አይደለም። በተመሣሣይም፣ መምህራን በሚያስተምሩት የትምህርት አይነት ያላቸው እውቀትና የክፍል አያያዝ ችሎታቸው ወጥነት ያለው አይደለም። የመምህራንና የትምህርት አመራር የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱ በገለልተኛነት ሙያተኞች ለደረጃቸው የሚመጥን የማስተማር የማስተዳደርና የመምራት ብቃት ማዳበራቸውን የማረጋገጥ ስራ ያከናውናል።

የሙያ ፈቃድ የመስጠት ሂደቱ በጅምር ላይ ያለ ነገር ግን በፍጥነት በማደግ ላይ ያለ እንቅስቃሴ ነው። በጽሁፍ ፈተናና በስራ ላይ በሚደረግ ምዘና በመጠቀም ለአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን ብቃት ያረጋግጣል። በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ-ግብር የትግበራ ዘመን የህፃናት እንክብካቤና ትምህርትን ሱፐርቫይዝ ለማድረግና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስትራቴጂ ይዘጋጃል። ይህን ከሌሎች የሙያ ብቃት መመዘኛዎች ጋር በማጣመር የህፃናት እንክብካቤና ትምህርት የሙያ ብቃት መስፈርቶችን ማጎልበት ያስችላል።

የሙያ ፈቃድ የመስጠቱ ስርአት መምህራን በቅድመ መምህርነትና በተከታታይ የሙያ ልማት መርሃ ግብሮች ያወቋቸውን /ያዳበሯቸውን ክሂሎች በክፍል ውስጥ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል። በሙያ ፈቃድ ሰጪው ዳይሬክቶሬትና በፌዴራልና ክልል ዩኒቶች ደረጃ የሚመራ የፈቃድ አሰጣጥ ግብረ ሃይል (ገምጋሚዎችና ከፍተኛ ገምጋሚዎች) በመቋቋም ላይ ይገኛል። መምህራን የሚጠበቅባቸውን የስነ ማስተማር ዘዴ እንዲያውቁና የሙያ ፈቃድ ለማግኘት የሚያበቃቸውን መመዘኛ እንዲያሟሉ የድጋፍና የምክር አገልግሎት ይሰጣቸዋል።

ለመምህራን የሙያ ፈቃድ ሰርተፊኬት በመስጠት የትምህርት ጥራት ከማረጋገጡ በተጨማሪ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆች የሚሰጠው የመምህራን ትምህርት ደረጃውን የጠበቀ ለመሆኑ የማረጋገጥ ስልጣን ይኖራቸዋል፡፡ የቅድመ አስተማሪነት ስልጠና በዚህ መልኩ ይበልጥ የተጠናከረ በማድረግና የመምህራኑን አቅም ከፍ በማድረግ የሚጠበቅባቸውን የደረጃ መስፈርት ለማሟላት የስራ ላይ ስልጠና የሚያስፈልጋቸውን የመምህራን ቁጥር መቀነስ ይቻላል፡፡ ይህም የተከታታይ የሙያ ልማት መርሃ ግብሩ የመምህራንን ክህሎትና ለሙያው ያላቸውን ፍቅር በማጎልበት ላይ ትኩረት እንዲያደርግ በር ይከፍታል፡፡

**ንኡስ ተግባር 3፡ ምዘናዎችና ፈተናዎች**

መደበኛ የሆነ የትምህርት ውጤት ምዘና ማካሄድ የትምህርት ግብዓቶች አቅርቦትን ለመወሰን፣ የመምህራን ስልጠና ስትራቴጂ ለውጦችን ለማድረግ፣ ስርአተ-ትምህርትን ለመምራትና የት/ቤት ግብዓቶችን ለመወሰን የሚያስችል የስርዓቱ ውጤት መፈተኛ መሳርያ ነው፡፡ በየአራት አመቱ የሚደረግ የአራተኛ፣ ስምንተኛ አስረኛና አስራ ሁለተኛ የክፍል ደረጃዎችን ለመገምገም የሚያስችል የብሄራዊ የመማር ዳሰሳ ሂደት ተፈጥሯል፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ-ግብር ዘመን በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ ያሉትን መሠረታዊ መስፈርቶችን (Minimum learning competencies) ታሳቢ ያደረገው ይህ ምዘና ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ እነዚህ ምዘናዎች እ.ኤ.አ በ2016 እና በ2020 የአራተኛና ስምንተኛ ክፍሎች ተማሪዎችን እ.ኤ.አ በ2018 የአስረኛና አስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎችን የትምህርት አቅም ለመለካት ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ የምዘናዎቹ ውጤቶች በተማሪዎች መካከል ያለውን የትምህርት ውጤት ልዩነት፣ በክልሎች ወይም በፆታ መካከል ያለውን ክፍተትና የትምህርት ውጤትን የሚወስኑ ተለውጦዎችን ለመለየትና የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ያስችላሉ፡፡

በታችኛው የክፍል ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች የዝቅተኛ ክፍል ደረጃ የንባብና የመቀመር እንዲሁም የሒሳብ ዳሰሰዎችን (EGRA, EGMA) በማካሄድ በትምህርት ሂደቱ ላይ የመጀመሪያ ፍተሻዎች ይከናወናሉ፡፡ የእነዚህ መሠረታዊ ክህሎቶች የፈተና ውጤት በመምህራን አሰለጣጠንና ሂደትና በአጋዥ የትምህርት ማቴሪያሎች አቅርቦት የተደረጉ ለውጦች ያስገኙትን ስኬት ለመለካት

ይቻላል፡፡ ደረጃቸውን የጠበቁ የምዘና ዘዴዎችን በመጠቀም ወጥ በሆነ መልኩ ተማሪዎችን በትምህርት ቤት ደረጃ በመመዘንና በሁለተኛና በሶስተኛ ክፍል ለሚያስተምሩ መምህራን ምዘናዎቹን እንዴት መተግበር እንዳለባቸው ስልጠና በመስጠት፣ የተሻለ አፈፃፀም ያሳዩትን ት/ቤቶች፣ ወረዳዎች፣ ዞኖችና ክልሎች በመለየት ሌሎቹ ተሞክሮ በመውሰድ ተመሣሣይ ሥራ እንዲሰሩ ጥረት ማድረግ ይገባል፡፡

በክልል ደረጃ ለስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ምዘና የሚሰጥ ሲሆን ፣ ብሄራዊ ፈተናዎች በአስረኛና አስራ ሁለተኛ ክፍሎች የሰጣሉ፡፡ በእነዚህ ምዘናዎች ተማሪዎች የሚያስመዘግቡት ውጤት ወደ ቀጣዩ የትምህርት ደረጃ የሚያደርጉትን ሽግግር ይወስናል፡፡

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ-ግብር ዘመን ሁሉንም የምዘናና የፈተና ሂደቶች ለመፈፀም መሟላት ያለባቸው ሦስት ጉዳዮች አሉ ፡- ሀ) ምዘናዎችን ከስርዓተ-ትምህርቱ ጋር የማጣጣም ስራ  ለ) የምዘና መሳሪያዎቹን ወጥ በማድረግ በየዓመቱ የተገኘውን ውጤት ማነፃፀርና ማወዳደር እንዲቻል ማድረግ ሐ) ሁሉም ምዘናዎችና ፈተናዎች ያለ ልዩነት ለሁሉም ተማሪዎች መስጠታቸውን ማረጋገጥ ናቸው፡፡ እነዚህ ሶሰት ተግባራት ከተማሪዎች ስነ ልቦናዊ ዝግጅት ጋር የተጣጣሙና ከስርዓተ-ትምህርቱ የሚመነጩ የምዘና ዘዴዎችን በሚያራምድ የምዘና ባንክ እንዲደራጁ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በመነሳት በእቅዱ የመጨረሻ ዘመን ሁሉም ብሔራዊ ፈተናዎችና የትምህርት ምዘናዎች ከስርአተ-ትምህርቱ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ካላቸው የባንኩ የምዘና ክምችት የተወሰዱ እንደሚሆኑ ይጠበቃል፡፡ የምዘናዎቹንና ፈተናዎቹን ጥራትና ፍትሐዊነት መጠበቅ እንዲቻል የፈተና አዘገጃጀትና አሰጣጥ ሂደቱ ብልሹ አሰራርን በሚቀንስ መልኩ ክትትል ይደረግበታል፡፡

ከእነዚህ ብሄራዊ ምዘናዎችና የምዘና ስርዓት ማሻሻያዎች በተጨማሪ፣ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ኢትዮጵያ ቀጠናዊና አለም አቀፋዊ የሆኑ የትምህርት አቅም ለመጠቀም ዝግጅት ታደርጋለች በዚህ አይነት ምዘናዎች በመሳተፍ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች በአለም ዙሪያ ከሚገኙ አቻዎቻቸው ጋር ሲነፃፀር ያላቸውን አቅም ለመረዳት ያስችላል፡፡ ከዚህ በሚገኘው ግብዓትም የመምህራን ስልጠናን ለማጠናከር፣ የስርአተ-ትምህርት ማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድና የወጣቶችንና የጎልማሶችን አለማቀፋዊ ተወዳዳሪነት ለማጎልበት ይረዳል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ

በተከታታይ ከፍተኛ አፈፃፀም ከሚያስመዘግቡ ሃገራትና በአጭር ጊዜ ፈጣን እምርታን ካስመዘገቡ ሃገራት ልምድ ለማካበትና ተሞክሮ ለመውሰድ ይረዳል፡፡

| ስትራቴጂዎች | አመልካች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| ለቅድመ መደበኛ ፣ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ ለአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት፣ ለጎልማሶች ትምህርት ማእከላትና ለመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ጥራቱን የጠበቀ ተከታታይ የቁጥጥር አገልግሎት መስጠት | በውጭ አካል ቢያንስ አንድ ጊዜ ቁጥጥር የተካሄደባቸው ተቋማት ቁጥር 100 በመቶ ይደርሳል | ክትትል/ቁጥጥር |
| | ሁለት ጊዜ የቁጥጥር የተከናወነባቸው ተቋማት 60 በመቶ ይደርሳሉ | ክትትል/ቁጥጥር |
| | የቁጥጥር ስራ የሚያከናውኑ ወረዳዎች ቁጥር 100 በመቶ ይደርሳል | ክትትል/ቁጥጥር |
| በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ የት/ቤት ተቆጣጣሪዎች ስልጠና መስጠት | | |
| የመቆጣጠሪያ ዶክዩሜንቶች ወቅታዊ እንዲሆኑ ማድረግ | | |
| የቁጥጥር አተገባበሩ ያስከተለውን ተጽእኖ ማጥናት | | |
| ትምህርት ቤቶች ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ፖሊሲ አውጪዎች የትምህርት ጥራት ጥረቶቻቸውን ለማሻሻል እንዲረዳቸው ከቁጥጥር የተገኙ ውጤቶችን እንዲያውቁ ማድረግ | የት/ቤታቸው የቁጥጥር ሪፖርት ቅጂ የማኖራቸው የት/ቤት አመራሮች 100 በመቶ ይደርሳል | ክትትል/ቁጥጥር |
| | የት/ቤት የቁጥጥር ሪፖርት ግኝቶችን በመጠቀም የት/ቤቱን ጥራት ለማሳደግ ያለሙ የት/ቤት ማሻሻያ እቅድ ያዘጋጁ ት/ቤቶች 50 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የት/ቤት የፋይናንስ ድጎማ ኦዲት ሪፖርቶች |
| አመታዊ የትምህት ቤት ቁጥጥር ሪፖርቶችን ማሰራጨት | | |
| የት/ቤት ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችሉ ድረ ገፆችና የመረጃ ቋት መመስረት | | |
| በት/ቤት ቁጥጥር ሂደት ለሚሳተፉ ወረዳዎች አመታዊ የት/ቤት ቁጥጥር ሪፖርቶች በወቅቱ እንዲደርሳቸው ማድረግ | | |
| የሙያ ፈቃድ የማግኘት ሂደቱን ያጠናቀቁ የመምህራንን ቁጥር ማሳደግ | የሙያ ፈቃድ የማግኘት ሂደቱን ያጠናቀቁ ከ1-4ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የወንድና ሴት መምህራን ቁጥር 90 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የሙያ ፈቃድ/የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | የሙያ ፈቃድ የማግኘት ሂደቱን ያጠናቀቁ ከ5-8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የወንድና ሴት መምህራን ቁጥር 90 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የሙያ ፈቃድ/የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | የሙያ ፈቃድ የማግኘት ሂደቱን ያጠናቀቁ ከ9-12ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የወንድና ሴት መምህራን ቁጥር 90 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የሙያ ፈቃድ/የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| የመምህራንና አስተባባሪዎች የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ መመዘኛዎችን የያዘ ሰነድ በሁሉም ደረጃዎች (ከቅድመ መደበኛ እስከ አስራ ሁለተኛ) እንደዚሁም በመምህራን ትምህርት ኮሌጆች እንዲዘጋጅ ማድረግ | | |
| ለልዩ ፍላጐት መምህራን (ለተዘዋዋሪ መምህራን ፣ ለብሬልና የምልክት ቋንቋ መምህራን ወዘተ) የሙያ ፈቃድ መመዘኛዎችን ማዘጋጀት | | |
| ሁሉም መምህራን ምዘናዎችንና ፈተናዎችን እንዲወስዱ ማድረግ | | |
| ከፍተኛ የግምገማ ባለሙያዎችን ማሰልጠን | | |
| የግምገማ ባለሙያዎችን ማሰልጠን | | |
| | የሙያ ፈቃድ ያላቸው ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ያሉ | የሙያ |

| | | |
|---|---|---|
| የሙያ ፈቃድ ያላቸው ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮችን ቁጥር ማሳደግ | ርዕሰ መምህራን ቁጥር 100 በመቶ ይደርሳል፡፡ | ፈቃድ/የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | የሙያ ፈቃድ ያላቸው ከ5ኛ-8ኛ ክፍል ያሉ መምህራን ቁጥር 100 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የሙያ ፈቃድ/የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | የሙያ ፈቃድ ያላቸው ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ያሉ ርዕሰ መምህራን ቁጥር 100 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የሙያ ፈቃድ/የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | የሙያ ፈቃድ ያላቸው ሱፐርቫይዘሮች ቁጥር 100 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የሙያ ፈቃድ/የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| የት/ቤት ርዕሰ መምህራን ምዘናዎችንና ፈተናዎችን እንዲወስዱ ማድረግ | | |
| ሱፐርቫይዘሮች ምዘናዎችንና ፈተናዎችን እንዲወስዱ ማድረግ | | |
| የመምህራን ትምህርት ኮሌጆችን መገምገግ የእውቅና ፈቃድ መስጠት | የእውቅና ፈቃድ ያገኙ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች 100 በመቶ ይደርሳሉ (በእቅዱ መጀመሪያ 36 የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ፈቃድ ይኖራቸዋል) | የሙያ ፈቃድ/የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ሲስተም |
| የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የእውቅና ፈቃድ ሰነዶችን እንዲያዘጋጁ መመሪያና ድጋፍ መስጠት | | |
| የላቀ ጥራት ያላቸው የመመዘኛ መሳሪያዎችን መንደፍና መተግበር | | |
| የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ ሂደቱን መዋቅር ማጠናከር | ሃገር አቀፍ የሙያ ፈቃድ አሰጣጥ ተቋም ራሱን ችሎ እንዲቋቋም ማድረግ | ነጋሪት ጋዜጣ |
| አጣሪ ኮሚቴዎችን ማዋቀር | | |
| ተገቢውን አገልግሎት የሚሰጥ የሙያ ፈቃድ የመረጃ ስርዓት ማቋቋም | | |
| የተማሪዎችን ውጤት ለመለካት ከሚሰጡ መደበኛ ፈተናዎች የሚገኘውን ውጤት በመጠቀም የማስተማሩን ሂደት መደገፍና የመማር ውጤቶችን ማሻሻል | እ.ኤ.አ ከ2015/16 ጀምሮ የሚሰጡ የሁሉም ምዘናዎችና ፈተናዎች ሪፖርት ቢያንስ አንድ አንድ ቅጅ ያላቸው ወረዳዎች 100 በመቶ ይሆናሉ፡፡ | NEAE |
| | ከምዘናና ፈተና ሪፖርቶች በሚገኙ ውጤቶች መሠረት የመምህራን ስልጠናና የቁጥጥር ሂደትን የሚተገብሩ የወረዳዎች (%) | የናሙና ዳሰሳ ጥናት |
| በሃገር አቀፍ ምዘናዎች የተገኙ ውጤቶችን ተንትኖ ሪፖርት ማዘጋጀት፤ ለ4ኛ፣ 8ኛ ብሄራዊ የመማር ዳሰሳ ለ10ኛ ና 12ኛ ክፍል ብሔራዊ የመማር ዳሰሳ፣ ለዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች የሂሣብና የንባብ ክህሎት ፈተናዎች | | |
| የአስረኛና አስራ ሁለተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተናዎች ሪፖርት ማዘጋጀት | | |
| የምዘና ዩኒት /የስራ ሂደት/ ያላቸው ክልሎች ቁጥር እንዲጨምር ማድረግ | | |
| ሪፖርቶችን በሁሉም ወረዳዎች ማሰራጨት | | |
| ሪፖርቶችን በትምህርት ሚኒስተር ድረ ገጽ ላይ መለጠፍ | | |
| ፈተናዎችና ምዘናዎች ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ማድረግና ከሃገር አቀፉ ስርዓተ-ትምህርት ጋር በእጅጉ የተጣጣሙ እንዲሆኑ ማስቻል፡፡ | በ4ኛ፣ 8ኛ ፣ 10ኛና 12ኛ ክፍል ብሄራዊ የትምህርት ምዘናና በ10ኛ /12ኛ ክፍል ፈተናዎች ከፈተናዎች ማደራጃ (ባንክ) የተወሰዱ ጥያቄዎች ብዛት 100 በመቶ | |

| | | |
|---|---|---|
| | ይደርሳሉ፡፡ | |
| ለብሔራዊ መማር ዳሰሳ (NLA) አገልግሎት የሚሆኑ የፈተና ጥያቄ ባንኮችን ማቋቋም | | |
| ለብሔራዊ ፈተናዎች የፈተና ጥያቄ ባንኮችን ማቋቋም | | |
| የፈተናና የምዘና መሳሪያዎችን ከተሻሻለው ስርዓተ-ትምህርት ጋር ማጣጣም | | |
| ብሔራዊ ፈተናዎችን ለመውሰድ የመመዝገቢያ ድረ ገጽ ማቋቋም | | |
| ፈተናዎችንና ምዘናዎችን በማዘጋጀትና በማካሄድ ለሁሉም ተማሪዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ | ፈተናውን ለመውሰድ ከተመዘገቡና በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀ ብሔራዊ ፈተና ከሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ውስጥ ፍላጎታቸውን ያማካለ የፈተና አቅርቦት የሚያገኙ ተማሪዎች ቁጥር 100 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| በፈተናዎችና በምዘናዎች የልዩ ትምህርት ፍላጎት ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎችን ፍላጎት ማሟላት የሚያስችል ስትራቴጂ መንደፍ | | |
| በቀጠናና በአለም አቀፍ ደረጃ በሚሰጡ ፈተናዎች መሳተፍ | ኢትዮጵያ በሁለት ቀጠናዊ ወይም አለማቀፋዊ ፈተናዎች ትሳተፋለች | NEAEA |
| በአለማቀፍ የትምህርት ምዘናዎች ለመሳተፍ የሚያስችል ብሔራዊ አደረጃጀት መፍጠር | | |
| የዋና ዋና የትምህርት አይነቶች ስርዓተ -ትምህርት በቀጠናው ከሚገኘው ስርዓተ ትምህርት ጋር በማመሳሰል ለአለማቀፋዊ ምዘናዎች ዝግጅት ማድረግ | | |
| ስርአተ-ትምህርቱን ከአለም አቀፍ ስርአት ጋር እንዲመሳሰል ማድረግ/ በዋና ዋና የትምህርት አይነቶች | | |
| ካሪኩለሙን ከአለምአቀፍ ካሪኩለም /መመሪያ ከተካተቱ ዋና ዋና ትምህርቶችና ምዘናዎች ጋር ማጣጣም፡፡ | | |

## 7. ቅድሚያ የተሰጠው ፕሮግራም፡- የአጠቃላይ ትምህርት ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት ፣ ውስጣዊ ብቃት

**የዚህ ቅድሚያ የተሰጠው ፕሮግራም አላማ፡-**

ማንኛውም ህጻን ለመደበኛ ትምህርት ብቁ የሚያደርገውን የቅድመ መጀመሪያ ትምህርት ተደራሽነት እንዲኖረውና በአቅራቢያ በሚገኙ ተቋማት እስከ 8ኛ ክፍልና የሁለት ዓመት የጠቅላላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መማር መቻሉን ማረጋገጥ ነው፡፡

**መግቢያ**

የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ዋና የተደራሽነትና የፍትሃዊነት ዓላማ የህፃናትንና የወጣቶችን ጠቅላላ የትምህርት ተሣትፎ ማሻሻልን ሲሆን፣ ሦስት በተለይ አጽንኦት የተሠጣቸው ደረጃዎችን ይይዛል፡፡ እነሱም (1) ሁሉም ህፃን ለመደበኛ ትምህርት ዝግጁ/ ብቁ የሚያደርገውን የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተጠቃሚ መሆኑን ማረጋገጥ (2) የሁለተኛ ሳይክል የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን እንደዚሁም (3) የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክልና የሁለተኛ ደረጃ አንደኛ ሳይክል

ትምህርት ተደራሽነትን በማሻሻል ቀጣይነት ያለው የጠቅላላ ትምህርት ተሳትፎ እንዲኖር ማስቻል ናቸው፡፡

ይህ ለማሳካት ቀጣይነት ያለው የስርዓት ማስፋፋትና የጥራት ዕድገትን፣ እንዲሁም ውስጣዊ ውጤታማነትን ለማሻሻል ትምህርት ማቋረጥና ክፍል መድገም በፍጥነት እንዲቀንሱ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ በተለያየ ምክንያት እኩል እድል ያልተመቻቸላቸው ህፃናትን ፍላጐት ማሟላት ቅድሚያ የሚሠጠው ጉዳይ ይሆናል፡፡ ይህን በማድረግም በፆታም ሆነ በችሎታ (አካላዊ እና አእምሯዊ)፣ በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥና በቤተሰብ ሁኔታ የተነሣ የሚፈጠር የትምህርት ኢፍትሃዊነት መቀነስ ይቻላል፡፡ በትምህርት ተደራሽነትና ፍትሃዊነት ጋር በተገናኘ በተደረገው የሁኔታዎች ትንተና የሚከተሉት አራት መሠረታዊ ጉዳዮች በትኩረት አቅጣጫነት ተለይተዋል፡፡ እነሱም የቅድመ መጀመሪያ፣ የመጀመሪያ፣ የሁለተኛና ለአዳጊ ክልሎች የሚሰጥ ልዩ የድጋፍ ፕሮግራም ናቸው፡፡

**ተግባር 1፡- ቅድመ መደበኛ**

| ዓላማ፡- ሁሉም ህፃን ለመደበኛ ትምህርት ዝግጁ የሚያደርገውን የቅድመ- መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማግኘቱን ማጋገጥ | በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ድምር (ወ/ሴ) | ግብ ድምር (ወ/ሴ) |
|---|---|---|
| ለቅድመ መጀመሪያ ጥቅል የቅበላ ምጣኔ (በምዝገባ ወቅት ዕድሜ 4-6 ዓመት) | 34 በመቶ (33/85) | 80 በመቶ (80/80) |
| የሁለት ወር የተፋጠነ የህፃናት ማብቃት ብሔራዊ ስትራቴጂና መርህ ፕሮግራም | የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ | የተተገበረ ስትራቴጂ |

የህፃናት እንክብካቤና ትምህርት በጠቅላላ ትምህርት ሴክተር ውስጥ ልዩ ትኩረት ከተሠጣቸው ጉዳዮች አንዱ ሆኗል፡፡ የተመጣጠነ ምግብ ባለበት ጤናማ አካባቢ የሚሠጥ ጥራት ያለው ትምህርት ተማሪዎች

ከፍ ባሉት የትምህርት ደረጃዎች የሚኖራቸውን የመማር አቅም በማሻሻል፣ ትምህርት ማቋረጥንና ክፍል መድገምን በመቀነስ የስርዓተ ትምህርቱን አዋጭነትና ውጤታማነት በማሻሻል በኩል አስተዋጽኦ ያበረክታል። ይህንን ከግንዛቤ በማስገባትና ባለፉት ሦስት ዓመታት የተመዘገበውን ስኬት በመከተል፣ የግሉን ሴክተር ከማስተባበርና ከማሳደግ ጐን ለጐን፣ መንግሥት ከመምህራን እስከ መማሪያ ክፍሎች አቅርቦት ብሎም የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በማቅረብ የቅድመ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ላይ ሙሉ ተሣትፎ ያደርጋል።

የህፃናት እንክብካቤና ትምህርት ከዜሮ እስከ ስድስት ዓመት ድረስ የሚዘልቅ ሲሆን በተለያዩ ዘዴዎች የሚሠጥ ነው። የህፃናት እንክብካቤና ትምህርት አገልግሎቶች በጤና ጥበቃ ሚኒስትር፣ በሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳዩ ሚኒስትር እና በትምህርት ሚኒስትር ትብብር ይቀርባሉ። በትምህርት ሚኒስትር የሚሰጡት የቅድመ መጀመሪያ ደረጃ አገልግሎቶች ዕድሜያቸው ከአራት እስከ ስድስት[9] ዓመት በሚሆኑ ህፃናት ላይ ያተኩራሉ። የቅድመ መጀመሪያ ትምህርት የመማር ባህልን በመፍጠርና ህፃናት የመማር መሠረታዊ ክሂሎች ባለቤት እንዲሆኑ ዝግጁነታቸውን ለማሻሻል የሚያስችሉ ወጪ ቆጣቢ ዘዴዎችን በማበርከት በኋላ ከፍ ባሉት የትምህርት ደረጃዎች ከተማሪዎች የሚጠበቁ መካከለኛና ከፍተኛ ክህሎቶችን ለማስጨበጥ የሚያስፈልገውን ኢንቨስትመንት ይቀንሣል።

በጥራትና በትኩረቱ የሚሰጥ የህፃናት እንክብካቤና ትምህርት በትምህርት ስርዓቱ ፍትሃዊነትን መጨመሪያ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል። መንግሥት የሚሰጠውን እድል ካላስፋፉ የህፃናት እንክብካቤ ትምህርት በአመዛኙ በከተሞች በሚገኙ በአንፃሩ ለሀብታም ቤተሰብ ልጆች የተገደበ ይሆናል። የህፃናት እንክብካቤና ትምህርት በቅድሚያ ዝቅተኛ የትምህርት ስኬት በተመዘገበባቸው አካባቢዎች (እና ከትምህርት ዕድል የመገለል የማቋረጥና ዝቅተኛ ውጤት የማስመዝገብ አደጋ የተጋለጡ አካባቢዎች) እንዲስፋፉ በማድረግ መንግሥት ድጋፉን ተጠቅመው ወደ አንደኛ ክፍል የሚሸጋገሩትን ህፃናትን

*9 ህፃናት ለቅድመ መጀመሪያ ትምህርት ለመግባት በምዝገባቸው ወቅት ከ-6 ሲሆን በዚህ ጽሁፍ ውስጥም ከዚህ በኋላ reference point ይሆናል።*

ውጤት ለማሳደግ ይሻል፡፡ ይህ አካሄድ ወደ ትምህርት ትምህርት ስርዓቱ የመግባትን ፍትሃዊነትን ያሻሽላል፡፡ በተጨማሪም፣ ዝቅተኛ ክፍያ አማራጭ በሆነባቸው ማህበረሰቦች ውስጥ የግሉ ሴክተር በህፃናት እንክብካቤና ትምህርት አገልግሎቶች አቅርቦት ረገድ እንዲበረታታ ይደረጋል፡፡ በተለይም ሁኔታዎች ባልተሟሉበት አካባቢ የሚገኙ ህፃናትን ተጠቃሚነት ሊያረጋግጡ የሚችሉ የግል ተቋማት ልዩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡ ይህ ድጋፍ ለምሣሌ የመሬት አቅርቦት ወይም ከቀረጥ ነፃ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አቅርቦትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የአራተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር ወቅት የህፃናት እንክብካቤና ትምህርት ስትራቴጂክ የትግበራ እቅድና መመሪያዎች ተዘጋጅቷል፡፡ ዶክዩሜንቱ ለአፀደ ህፃናት፣ ለ0 (ኦ) ክፍሎች፣ ለህፃናት አቻ- ላቻ እንደዚሁም ለተፋጠነ የህፃናት ማብቂያ ፕሮግራሞች፣ የሚሆኑ የተለያዩ ዘዴዎችን ከማብራራት በተጨማሪ በህፃናት ተሳትፎ አስተዋጽኦና ፈጠራ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በዚህ በመመስረት አንድ ህፃን አንደኛ ክፍል ከመግባቱ አስቀድሞ የሚከታተለው የሦስት ዓመት የአፀደ ህፃናት ሥርዓተ ትምህርት(ሦስተኛው ዓመት የ0 (ኦ) ክፍል ነው) ተቀምጧል፡፡ የህፃናት እንክብካቤና ትምህርት መምህራን ማሰልጠኛ ስርዓተ ትምህርት በአሁኑ ወቅት የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ይሄውም ከተማሪዎች ሥርዓተ ትምህርት ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያለው ነው፡፡ በ2020 የትምህርት ሥርዓቱ በቅድመ መጀመሪያ ትምህርት በአማካይ 80 በመቶ ጥቅል የወንድና ሴት ህፃናት የቅበላ ምጣኔ እንደሚያሳካ ይጠበቃል፡፡ እዚህ ግብ ላይ ለመድረስ ቅይጥ ዘዴዎች ይተገበራሉ፡፡ ይሁንና በመጀመሪያዎቹ የአምስተኛ መርሃ ግብር አመታት በሚደረጉ ሙከራዎች ከተለዩ በኂላ እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡ ዘዴዎቹ፣ ከአራት እስከ ስድስት ዓመት ለሚገኙ ህፃናት የሚሠጥ የሦስት ዓመት የአፀደ ህፃናት ፕሮግራም፣ ዕድሜያቸው ለመደበኛ ትምህርት የተቃረቡ ማለትም ስድስት ዓመት ለሞላቸው ህፃናት የ0 (ኦ) ክፍል ፕሮግራም፣ እንዲሁም ቀደም ሲል የትምህርት ዕድል ያልነበራቸው ህፃናት አንደኛ ክፍል ከመግባታቸው በፊት የሚሠጥ የተፋጠነ የህፃናት ማዘጋጃ ፕሮግራም ናቸው፡፡

የህፃናት አቻ-ላቻና የተፋጠነ የህፃናት ዝግጁነት ፕሮግራሞችን የመሰሉ ሌሎች አማራጮች እንደሁኔታው እድሜያቸው ከአራት እስከ ስድስት ለሆኑ ህፃናት በመስጠት ወደ ትምህርት የመሸጋገርያ አውድ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ የወላጆችን አቅምና የህፃናትን የትምህርት ዝግጁነት

የሚያጠናክሩ፣ ማህበረሰብን መሠረት ያደረጉ ሌሎች ዘዴዎች እንዲበረታቱ፣ እንዲቀመሩ፣ እንዲገመገሙና እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡ እነዚህም የህፃናት የጨወታ ቡድኖች (children's play circles) እና ልጅህን አስተምር የሚሉ ፕሮግራሞችን ማካሄድና ከጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ጋር በትብብር ወላጆች የልጆቻቸውን የተቀናጀ ዕድገት እንዲያፋጥኑ መደገፍን ያካትታሉ፡፡

ስርዓቱ ብቁ የሰው ኃይልና መሠረተ- ልማት ባልገነባበት በነዚህ የመጀመሪያ ዓመታት የህፃናት አቻ-ላቻ (child to child) እና የተፋጠኑ የማዘጋጀት ፕሮግራሞች ከፍተኛ ድርሻ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ እነዚህ ፕሮግራሞች የሚካሄዱት በቅድሚያ የሁለት ሣምንት ስልጠና (orientation) በሚሠጣቸው የመጀመሪያ ደረጃ መምህራን ይሆናል፡፡ ሥልጠናው የቅድመ መጀመሪያ ትምህርትን በሚያቀላጥፍ ክህሎትና እውቀት ላይ የሚያጠነጥን ሲሆን መምህራኑ ከስልጠና በኂላ በተገቢው የእድሜ ክልል እንዲመደቡ ይደረጋል፡፡ በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ደግሞ ልዩ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት አስተባባሪዎች ተመርጠው በህፃናት እንክብካቤና ትምህርት ለማስተማር ብቁ የሚያደርጋቸው የአንድ ወር የክረምት ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡ በተጨማሪም የሰላሳ ቀናት የሥራ ላይ ስልጠና (in service training) እና የሙያ ድጋፍ የሚሠጣቸው ይሆናል፡፡

በመሠረተ ልማትና በመምህራን ሥልጠና ረገድ አቅም መገንባት ሲቻል ለ0 (ኦ) ክፍልና አፀደ ህፃናት ፕሮግራሞች በተገቢው መንገድ እውቅና ያገኙ (certified) መምህራን የሚቀርቡ ይሆናል፡፡ ራሳቸውን የቻሉ አፀደ ህፃናት (ከትምህርት ቤት ጋር ያልተያያዙ) እንዲሁም በተናጠል ይሁን በጥምረት (ማለትም በትምህርት ቤት ቅጽር ውስጥ) ያሉ O (ኦ) ክፍሎች በፍጥነት በሚሠሩ የመማሪያ ክፍሎች ከበቂ የትምህርት መርጃ መሣሪያ አቅርቦት ጋር እንዲካሄዱ ይደረጋል፡፡ እያንዳንዱ ዘዴ የሚያስፈልገው የመጫወቻና የትምህርት አቅርቦት ደረጃ / መስፈርት መለየት የመጀመሪያው ተግባር ነው፡፡ መስፈርቶቹ የልዩ ትምህርት ፍላጐት ያላቸው ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚያስፈልጓቸውን መሠረታዊ ቁሳቁሶችንም ይለያሉ፡፡

መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት (ግለሰቦች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የእምነት ተቋማት፣ እና የሲቪል ሶሳይቲ ድርጅቶች CSO) በህፃናት እንክብካቤና ትምህርት በተለይም በአፀደ ህፃናት አቅርቦት

እንደሚሳተፉ ይጠበቃል፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ዘመን መንግሥት 50 በመቶ የሚሆኑትን አፀደ ህፃናት ሲያዘጋጅ ቀሪው ደግሞ መንግሥታዊ ባልሆነው ዘርፍ የሚሸፈን ይሆናል፡፡ የትምህርት ክፍያ በተመለከተ ወጪን በመቀነስና ከጥሬ ገንዘብ ክፍያ ውጭ ያሉ አማራጮችን በመፈተሽ ህፃናት ትምህርት ቤት የሚገቡበት መንገድ ይፈለጋል፡፡

ለቅድመ መጀመሪያ ትምህርት የሚወጡ መስፈርቶች በሁሉም ተቋማት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ፈቃድ ማግኘት የሚችሉት መስፈርቶቹን ሲያሟሉ ይሆናል፡፡ መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማድረግ ልዩ የማነቃቂያ ስትራተጂ ማውጣት ያስፈልጋል፡፡

የህፃናት እንክብካቤና ትምህርት መስፋፋት ወላጆች ልጆቻቸውን በአቅራቢያ ወደሚገኙ አፀደ ህፃናት እንዲልኩ፣ ለማህበረሰብ ተኮር ፕሮግራሞች በቂ ግብአት እንዲሰጥ ከሚደረግ የፖሊሲ ትውውቅ ሥራዎችና በየአመቱ ጠንካራ የቅስቀሳ ፕሮግራሞች ጋር የተሳሰረ ነው፡፡

በትምህርት ቤቶች በሚቋቋሙ የምግብ ፕሮግራሞች ፣ የላም ወተትና ቁርስ  እና የመሣሰሉ ምግቦች በማቅረብ የተማሪዎችን የመማር ፍላጐት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

| ስትራቴጂዎች | አመልካች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| ልጆች ቢያንስ የአንድ አመት በክፍል ውስጥ የሚሠጥ የቅድመ መጀመሪያ ትምህርት ያገኙ ዘንድ የ0 (ኦ) ክፍልና የአፀደ ህፃናትን አቅርቦት ማስፋት | ለቅድመ መጀመሪያ (ዕድሜ ከ4-6 ዓመት) የጥቅል ቅበላ ድርሻ ከ34 በመቶ ወደ 80 በመቶ ያድጋል | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | ቢያንስ የአንድ አመት የቅድመ መጀመሪያ ትምህርት የሚያገኙ ልጆች ቁጥር መቶ በመቶ ይሆናል፡፡ | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| ከትምህርት ውጤታማነት ጋር የተቆራኙና ሁኔታዎች ላልተመቻቹላቸው (disadvantaged) አካባቢዎችና ወገኖች ትኩረት የሠጠ ሀገር አቀፍ የቅድመ መጀመሪያ ትምህርት ማስፋፋት | | |
| በማህበረሰብ ልማትና ሀብት በመታገዝ፣ መሠረታዊ የሆኑ የመማር ማስተማሪያ መረጃ መሣሪያዎች የተሟሉለትና ልዩ ፍላጐት ላላቸው ልጆች ተደራሽ የሆነ 0 (ኦ) ክፍል በእያንዳንዱ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ መገንባት | | |
| የቅድመ መጀመሪያ ትምህርት በሚሰጥባቸው አካባቢዎች መሠረታዊ የንፁህ ውሃ አቅርቦት (Wash facilities) ማሟላት | | |

<table>
<tr><td colspan="3">የግሉን ሴክተር ማነቃቃትና መደገፍ ለማግኘት እንዲሁም የመንግሥትን የአፀደ ህፃናት የቅበላ ሽፋን 50 በመቶ ለማድረስ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን መቅረጽ</td></tr>
<tr><td colspan="3">የቅድመ መጀመሪያ ደረጃ መምህራንን በሰርቲፊኬትና በዲፕሎማ ኮርሶች በማሰልጠን በቂና ብቁ መምህራን እንዲያሰማሩ ሁሉንም የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ማጠናከር</td></tr>
<tr><td colspan="3">አካታች የቅድመ መጀመሪያ ትምህርትን ማሳደግና አካል ጉዳተኛና ሌሎች የልዩ ትምህርታዊ ፍላጐት ያላቸው ልጆችን የመማር እድል ለማስፋፋት ዘዴዎችን መቅረጽ</td></tr>
<tr><td colspan="3">አገር በቀል እውቀት በመተግበር የወላጆች ትምህርትን ማስፋፋት</td></tr>
<tr><td colspan="3">የህፃናት እንክብካቤና ትምህርት ካውንስል በየደረጃው መመስረትና ማጠናከር</td></tr>
<tr><td rowspan="2">የህፃን ለህፃን (child to child )እና የተፋጠነ የህፃናት ዝግጁነት ፕሮግራሞች ተደራሽነትን ማስፋፋት</td><td>ጥቅል የትምህርት ቅበላ ለቅድመ መጀመሪያ (ዕድሜ ከ4-6 ዓመት ከ34 በመቶ ወደ 80 በመቶ) ያድጋል</td><td>የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት</td></tr>
<tr><td>ኢ-መደበኛ የሆኑ የተፋጠነ የህፃናት ዝግጁነት እና የህፃን ለህፃን ፕሮግራሞች በብሄራዊ ደረጃ ስትራተጂ ይቀይስላቸዋል</td><td>SIP</td></tr>
<tr><td colspan="3">የተፋጠነ የህፃናት ዝግጁነት ፕሮግራሞችን ጨምሮ አዳዲስ ስትራቴጂ መንደፍ የሚያስችሉ ሙከራዎችን በማካሄድ፣ ከሙከራው ውጤቶች በመነሳት ሌሎች አውዳዊ ስትራቴጂዎችን ማስፋፋት</td></tr>
<tr><td colspan="3">ኢ-መደበኛ የማህበረሰብ አቀፍ የህፃናት ዝግጁነት እና የህፃን ለህፃን ፕሮግራሞች (የህፃናት የጫወታ ቡድኖችን (children's play circles) እና ልጅዎን ያስተምሩ ፕሮግራምን ("Educate your child programme") የካተተ ብሄራዊ ስትራቴጂ ማዘጋጀት)</td></tr>
<tr><td colspan="3">የልዩ ፍላጐ ትምህርት ያሏቸውን ጨምሮ ሁኔታዎች ያልተመቻቹላቸው (disadvantaged) ህፃናትን ለመደገፍ የሚያግዝ የዳሰሳ ጥናት (needs assessment) ማካሄድ</td></tr>
<tr><td colspan="3">የህፃን ለህፃን እና የህፃናት ዝግጁነት ፕሮግራሞች አስተባባሪዎችን ማሰልጠን</td></tr>
<tr><td colspan="3">መምህራን /አስተባባሪዎች ራቅ ባሉ አካባቢዎችና በታዳጊ ብሔሮች አካባቢ እንዲያስተምሩ ማበረታቻዎችን በማቅረብ ተነሳሽነትን መፍጠር</td></tr>
<tr><td colspan="3">የቅድመ መጀመሪያ ደረጃ መምህራን /አስተባባሪዎች በ0 (ኦ) ክፍል የህፃናት ዝግጁነት ፕሮግራም፣ በአፀደ ህፃናት ወይም በተወሰኑ የተፋጠኑ ፕሮግራሞች እንዲያስተምሩ በአመት ቢያንስ የ30 ቀናት የሥራ ላይ ሥልጠና ይሰጣል፡፡</td></tr>
<tr><td colspan="3">ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና ከሴቶች ህፃናትና የወጣቶች ጉዳይ ሚኒስትር ጋር በመተባበር በተለይ የምግብ ዋስትና ባልተረጋገጠባቸው አካባቢዎች የህፃናት ጤናና የተመጣጠነ ምግብ ፕሮግራሞችን መመስረት</td></tr>
</table>

**ተግባር 2፡ አንደኛ ደረጃ**

| አላማ፡- ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ተደራሽነትንና ተሣትፎን በማሣደግ ከአራት ወንዶችና ሴቶች ሦስቱ የአንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክልን እንዲያጠናቅቁ ማብቃት | አራተኛ የትምህርት ዘርፍ ፕሮግራም ጠቅላላ (ወ/ሴ) | ግብ ጠቅላላ (ወ/ሴ) |
|---|---|---|
| ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል የሚኖረው ጥቅል የትምህርት ድርሻ | 101 በመቶ(105/98) | 103 በመቶ (103/103) |
| ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል የሚኖረው ንጥር የትምህርት ድርሻ | 93 በመቶ (90/95) | 98 በመቶ (98/98) |
| ከአንድ እስከ ስምንት ላሉ የመጀመሪያ ክፍሎች | 0.93 | 1.0 |
| ስምንተኛ ክፍልን የሚያጠናቅቁ ተማሪዎች ብዛት | 47 በመቶ(47/47) | 74 በመቶ (74/74) |

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ቅበላ ከ101 በመቶ ወደ 103 በመቶ እንደሚጨምር ሲጠበቅ ንጥር ቅበላ ደግሞ ከ93 በመቶ ወደ 98 በመቶ ከፍ እንደሚል ይገመታል፡፡ ይህ ጭማሪ ሊሳካ የሚችለው በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል (ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል) ያለውን የትምህርት ተሳትፎ በማሳደግና የሴት ልጆችን ውጤታማነት በማሻሻል ሲሆን፣ የመጀመሪያ ደረጃ GPI ከ 0.93 ወደ 1.0 እንዲሻሻል ሲደረግ ነው፡፡

እነዚህን ግቦች ለማሣካት ተማሪዎች የመጀመሪያ ሳይክል ትምህርትን በማጠናቀቅ ወደ ሁለተኛ ሳይክል ሽግግር እንዲያደርጉ የትምህርት ቤቶች ተደራሽነት ላይ ልዩ ትኩረት ይደረጋል፡፡ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶችና በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላትም ያሉት የክፍል ደረጃዎች ቁጥር እንዲጨምርም አጋጣሚዎች ይመቻቻሉ፡፡ ይህ አካሄድ አዳዲስ ተቋማትን ከመገንባት ይልቅ በትምህርት ቤት ደረጃ ያለውን ሀብትን አሟጦ መጠቀም ያስችላል፡፡ በእያንዳንዱ ቀበሌ ቢያንስ አንድ ሙሉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል) ይኖራል፡፡ የየቀበሌው ሙሉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም ተማሪዎች ከመጀመሪያ ወደ ሁለተኛ በሚያደርጉት ሽግግር እንደ መሪ ክላስተር (cluster lead) ሆኖ ያገለግላል፡፡

አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላትም እንዲያድጉ ይደረጋል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ሁለት ወይም ሦስት ደረጃ የሚሠጡ ማዕከላት ሙሉ አራት ደረጃ መስጠት እንዲችሉ ይስፋፋሉ፡፡ በመሆኑም በመደበኛ ትምህርት ከሚሠጠው ስድስተኛ ክፍል ጋር አቻ ይሆናሉ፡፡ በሌላ በኩል አንዳንድ አማራጭ መሰረታዊ የትምህርት ማዕከላት ደግሞ ወደ መደበኛ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤትነት ከፍ እንዲል ይደረጋል፡፡ በተጨማሪ ለሚከፈቱት ሁለት የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ደረጃዎች ስርዓተ ትምህርትና ቁሳቁስ አቅርቦት በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ የመጀመሪያ ዓመት ወቅት በቅድሚያ ይከናወናሉ፡፡

ትምህርት ማቋረጥ በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ማብቂያ ላይም አይነተኛ ተግዳሮት ሆኖ ቆይቷል፡፡ ብዙዎቹ የጥራት ማሻሻያ ስትራቴጂዎች የማስተማርንና አጠቃላይ የትምህርት ቤቶችን አካባቢ ጥራት ለማሻሻል የታሰቡ ናቸው፡፡ ስትራተጂዎቹ የተሻሻለ የመማር ሁኔታ በመፍጠር ትምህርት የሚያቋርጡ ተማሪዎች ቁጥር በመቀነስና መሠረታዊ በሆኑት ክህሎቶች የተሻለ ውጤት እንዲመዘገብ ያስችላል ተብሎ ይገመታል፡፡ በተጨማሪም በኑሮና በሥራ ምክንያት ተማሪዎች ከትምህርታቸው እንዳይተጓጐሉ ተንቀሳቃሽ ትምህርት ቤቶችና ጥምር ክፍል ያላቸው ት/ቤቶች (multi grade schools) ይመሠረታሉ፡፡

ትምህርት ያቋረጡ ተማሪዎች ወደ መደበኛ የትምህርት ገበታ እንዲመለሱ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች እንደየሁኔታው ይተዋወቃሉ፣ ይሞከራሉ፣ ውጤታማ ሆነው ሲገኙ ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡ እነዚህ ስትራቴጂዎች ትምህርት በማቋረጥና ክፍል በመድገም ያሉትን ችግሮች ለመለየት በሚደረጉ ጥናቶች መሠረት የሚቀመሩ ይሆናሉ፡፡ በሁሉም ክልሎች የሚኖረውን የትምህርት ማቋረጥ ለመቀነስ የሚያስችል አንድ ብቸኛ መፍትሄ ሊኖር አይችልም፡፡ አካባቢያዊ ስትራቴጂዎችን ለማበረታታት ትምህርት ቤቶች በሪፖርት ካርዶችና መሰል መንገዶች መረጃ እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡

በትምህርት ተሣትፎ ሽፋን ላይ ያለውን ክፍተት ለመቀነስና “ትምህርት ለሁሉም” መርህን ለመተግበር በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ትምህርት ሚኒስቴር ለልዩ ፍላጐት ትምህርት ትኩረት በመስጠት ሁሉም ህፃናት ጥራት ያለው ትምህርት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ይህ ስትራቴጂ በመከለስ ላይ የሚገኝ ሲሆን “ማስተር ፕላኑ” በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ

ግብር የመጀመሪያ ዓመት ስራ ላይ ይውላል። እነዚህን ጥረቶች በማድረግ የአንደኛ ደረጃ የልዩ ፍላጐት ተማሪዎችን ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ ታቅዷል። እ.ኤ.አ በ2013/14 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተሣትፎ 4 በመቶ የነበረ ሲሆን አምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ሲጠናቀቅ 75 በመቶ እንደሚሆን ይጠበቃል። እነዚህ ግቦች ግብ መምታታቸውን ለመከታተልና መረጃ ለማግኘት ከ 2015 ጀምሮ የተሻሻለ ዘዴ ስራ ላይ ይውላል። ይህ የተሻሻለ የመከታተያ መንገድ የልዩ ፍላጐት ትምህርት ተማሪዎች ቅበላና ቆይታን በተመለከተ ክትትል ለሚያደርጉት መረጃ ይሰጣል።

የዲሞግራፊና የጤና ዳሰሳዎች በተጨማሪም ብሄራዊ የህዝብ ቆጠራ በአምስተኛው የልማት ፕሮግራም ወቅት የሚካሄዱ በመሆናቸው ትምህርት ሚኒስቴር የልዩ ፍላጐት ትምህርት ተማሪዎችን ሁኔታ ለመከታተል የሚያስችሉ መለኪያዎችን ለማካተት ጥረት ያደርጋል።

ከዚህ ባሻገር፣ ለእናቶች በሚሰጠው የጐልማሶች ትምህርት አማካኝነት ህፃናት የበለጠ የሚታገዙበት ሁኔታ ይመቻቻል። በተለይ ባልተመቻቸ አካባቢ ለሚኖሩ ሴቶችና ህፃናት የድጋፍ ፕሮግራሞች (ለምሣሌ፣ መኖሪያ ቤት በመስጠት የጽህፈት መሣሪያዎች በማቅረብና፣ ዩኒፎርም በማደል) በማዘጋጀት የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክልና ከዛም በላይ ወዳሉ የትምህርት ደረጃዎች ሽግግር ከፍ እንዲል ይደረጋል። እነዚህ እርምጃዎች በሙከራ ከታዩ በኂላ የሚገኘው ውጤት ለቀጣይ ውሣኔ ግብአት ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ “በብሔራዊ የትምህርት ቤት ምግብ አቅርቦት” ስትራቴጂን በማስፋፋት ተጨማሪ ድጋፍ እንዲሰጥ ይደረጋል።

| ስትራተጂዎች | አመልካች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| የአንደኛ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርትን ተደራሽ በማድረግ ተማሪዎች በየቀያቸው መማር መቻላቸውን ማረጋገጥ | የአንደኛ ክፍል ጥቅል የቅበላ መጠን ከ153 በመቶ ወደ 115 በመቶ ይወርዳል | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | የአንደኛ ክፍል ንጥር ቅበላ NIR ከ106 በመቶ ወደ 100 በመቶ ይወርዳል | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ጥቅል የቅበላ መጠን ከ101 በመቶ ወደ 103 በመቶ ያድጋል | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ጥቅል የቅበላ መጠን ከ67 በመቶ ወደ 95 በመቶ ያድጋል | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ሲስተም |
| | ስምንተኛ ክፍልን የማጠናቀቅ ቀምር ከ47 በመቶ ወደ 74 በመቶ ያድጋል | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| ት/ቤቶችን ለማስፋፋት፣ ከትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት ጋር በመቀናጀት የት/ቤቶች ካርታ ማዘጋጀት | | |
| በየቀኑ ቢያንስ አንድ ሙሉ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት (ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ) እንዲሃር ማድረግ በየቀበሌው ቢያንስ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ማስፋፋት | | |
| በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የንፁህ ውሃ አቅርቦት ማሟላት | | |
| አማራጭ መሰረታዊ ትምህርትን ወደ መደበኛ የአንደኛ ደረጃ እና አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት (ደረጃ 1-6) ለማሳደግ መመሪያ ማውጣት | | |
| የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ፕሮግራምን በማጠናከር ማዕከላት ቢያንስ አራት ደረጃዎችን እንደሁኔታውም ስድስት ደረጃዎች መስጠት እንዲችሉ ማድረግ | | |
| ሁኔታዎች ያልተመቻቹላቸውና መድልዎ የሚደረግባቸው ህፃናት ሙሉ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነት እንዲረጋገጥ ልዩ መቅረትጽ | 40 በመቶ የአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት ወደ መደበኛ የአንደኛ ደረጃነት ያድጋሉ (በቋሚነት በሠፈሩ አርብቶ አደር ማህበረሰቦች ውስጥ) | የልዩ ድጋፍ እና አካቶ ትምህርት |
| | 500 ተንቀሳቃሽ ት/ቤቶች ይመሰረታሉ | የልዩ ድጋፍ እና አካቶ ትምህርት |
| | ልዩ ፍላጐት የሚሹ ህፃናት የቅበላ መጠን ከ4 በመቶ ወደ 75 በመቶ ያድጋል | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| በቋሚነት በሠፈሩ አርብቶ አደር ማህበረሰቦች ውስጥ የሚገኙ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ማዕከላት ሙሉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እንዲሠጡ ማሣደግ | | |
| በአርብቶ አደርና ተራርቀው በሠፈሩ አካባቢዎች ተንቀሳቃሽ እና ባለብዙ ክፍል (multi grade) ት/ቤቶች መመሥረት | | |

| | | |
|---|---|---|
| ለአደጋ በተለይም ለድርቅ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ለሚገኙ ትምህርት ቤቶች ትምህርት መቀጠል የሚያስችሉ ስልጠናዎችና ቁሳቁሶች እንዲያገኙ ማድረግ | | |
| ህፃናትን ለማግኘት አስቸጋሪ በሆኑ በአርብቶ አደርና በከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የአዳሪ /ቋሚ መጠለያ (boarding /hostels) መመስረትና ማጠናከር በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ከሚገኙት 2 በመቶ | | |
| ለድህነት ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩና ምቹ ሁኔታዎች ይልተፈጠሩላቸው ህፃናት ወደ መጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል የሚያደርጉትን ሽግግር ለመደገፍ የነፃ ትምህርት ዕድል መስጠት | | |
| ብሔራዊ የት/ቤት የምግብ አቅርቦት ስትራቴጂን ማጠናቀቅና መተግበር | | |
| ከድሃና በገቢ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች የሚወለዱ ህፃናትን በትምህርት መሣሪያ ፣ በት/ቤት ምግብ አቅርቦትና በገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችሉ አማራጮችን መፈለግ | | |
| የልዩ ፍላጐት ትምህርት “ ማስተርፕላን” ማጠናቀቅና መተግበር | | |
| ዕድሜያቸው ከ7 እስከ 14 ሆኖ ከትምህርት ገበታ ወጪ የሆኑ ህፃናት የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ በማድረግ ቁጥራቸውን መቀነስ | ዕድሜያቸው ከ7-14 ሆኖ ከትምህርት ገበታ ውጪ የሆኑ ህፃናት ቁጥር ከ1.2 ሚሊዮን ወደ 0 ይወርዳል | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| ከትምህርት ገበታ ውጪ የሆኑ ወጣቶችን ለመለየትና የችግሩን ምክንያት ለማወቅ ምርመራ ማካሄድ | | |
| ተደራሽነታቸው አስቸጋሪ በሆኑ አካባቢዎች አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት፣ ተንቀሳቃሽ ት/ቤቶች፣ ባለብዙ ክፍል ት/ቤቶችና መጠለያ ሊፈጥሯቸው የሚችሉ ተፅዕኖዎች ጥናት ማካሄድ | | |
| ማህበረሰቡ በትምህርት ሴክተር ተሣታፊ እንዲሆን የትምህርት ልማት ቡድን በየደረጃው መመሥረት /ማጠናከር | | |
| ለትምህርት ሴክተሩ “ የትምህርት ልማት ቡድን” መመሪያ (manual) ማዘጋጀት | | |
| ህፃናት፣ በተለይም ሴቶች፣ ልዩ ትምህርት የሚያስፈልጋቸው ልጆች፣ ዕንለ ማውታን እንዲሁም የአርብቶ አደር ልጆች ወደ ት/ቤት እንዲመጡ በየዓመቱ የማህበረሰብ ቅስቀሳና የግንዛቤ ማሻሻያ ዘመቻዎችን ማካሄድ፡፡ | | |

## ተግባር 3፡ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት

| አላማ፡- መካከለኛና ከፍተኛ ክህሎት ያለው የሰው ሀይል ለማሰልጠንና ለማስተማር አስፈላጊ የሆነውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነት በፍጥነት ማስፋፋት | ESDP 4 ጠ (ሴ/ወ) | ግብ ጠ(ሴ/ወ) |
|---|---|---|
| የዘጠነኛና አስረኛ ክፍሎች ጥቅል የትምህርት ድርሻ | 39 በመቶ38/40) | 74 በመቶ (74/74) |
| የዘጠነኛና አስረኛ ክፍሎች ንጥር የትምህርት ድርሻ | 20 በመቶ (21/20) | 47 በመቶ(47/47) |
| GPI ለዘጠነኛና አስረኛ ክፍሎች | 0.94 | 1.00 |
| የአስራ አንደኛና አስራ ሁለተኛ ክፍሎች ጥቅር የትምህርት ድርሻ | 10 በመቶ (9/11) | 12 በመቶ(12/12) |
| GPI ለአስራ አንደኛና አስራ ሁለተኛ ክፍሎች | 0.85 | 0.96 |
| ዘጠነኛና አስረኛ ክፍሎች የሚያስተምሩ ት/ቤቶች ብዛት | 2108 | 6158 |

አንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚያጠናቅቁ ተማሪዎች ቁጥር እያደገ ሲሄድ አገሪቱ መውሰድ ያለባት ቀጣይ እርምጃ ኢኮኖሚው የሚጠይቀውን የመካከለኛና የከፍተኛ ደረጃ የሰው ሀብት ለማፍራት መሠረትና ድልድይ የሆነውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አገልግሎት ተደራሽነት በጥራት ማስቀጠል መቻል ነው፡፡

የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ-ግብር አንዱ ትልቅ እቅድ የሁለተኛ ደረጃ መጀመሪያ ሳይክል ጥቅል የትምህርት ድርሻ ሲጀምር ከነበረበት 39 በመቶ ወደ 74 በመቶ ማሣደግ ነው፡፡ ከአስረኛ ክፍል በኋላ 20በመቶ የሚሆኑት ተማሪዎች ወደ መሠናዶ ትምህርት (አስራ አንደኛና አስራ ሁለተኛ ክፍሎች) እንደሚሸጋገሩ የትምህርት ፖሊሲው ያትታል፡፡ በመቀጠልም ከሁለት ዓመት በኋላ እነዚህ ተማሪዎች ዩኒቨርስቲ ይገባሉ፡፡ ይህ ስሌት የ10ኛ እና 12ኛ ክፍልን ጥቅል የትምህርት ድርሻ አሳንሶ የሚያሳይ ይመስላል፡፡ ይሁንና በአምስተኛው መርሃ ግብር ወቅት በመሠናዶ ደረጃ ያለው ጥቅል ድርሻ ከ10 በመቶ ወደ 12 በመቶ ያድጋል፡፡ በተመሣሣይ የሴት ተማሪዎች ተደራሽነትና ውጤታማነት ላይ ትኩረት በማድረግ የሁለተኛ ደረጃ መጀመሪያ ሳይክል GPI ከ0.94 ወደ 1.00 የሁለተኛ ሣይክል ደግሞ ከ0.85 ወደ 0.96 ይጨምራል፡፡ (ይህም ጥቅል ተደራሽነቱ ለሴት 11.5 በመቶ እና ለወንዶች 12.0 በመቶ ጋር እኩል ይሆናል)፡፡ ከመምህራን፣ ከት/ቤት አካባቢና ከስርዓተ ትምህርት ክለሳ ተግባራት

በተጨማሪ፣ ሴት ተማሪዎች በትምህርታቸው ሁለተኛ ደረጃ ብሎም እስከ ከፍተኛ ትምህርት እንዲገፉ የሚያግዙ ፕሮግራሞችን በመጠቀም እነዚህ ቅምሮች ግብ ሊመቱ ይችላሉ፡፡

አንደኛ ደረጃ ትምህርትን በማጠናቀቅ ሁለተኛ ደረጃ ለመቀጠል እያደገ የመጣውን ፍላጐት ለማሟላት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ቁጥር እንዲጨመር ይደረጋል፡፡ ከዚህ ሌላ፣ በየአምስት የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ ቢያንስ አንዱ (የክላስተር ሪሶርስ ማዕከሉ) ጥምር አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የማስፋፋት ራዕይን ተከትሎም ከ3825 በላይ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከአንደኛ እስከ አስረኛ ክፍል ያለውን ትምህርት አንዲሸፍኑ ይደረጋል፡፡ ይህ አካሄድ በጋራ ሀብትን እና አመራርን ከመጠቀም የሚመነጭ ሲሆን በትምህርት ሚኒስቴር፣ በክልል ትምህርት ቢሮዎች፣ በዞንና ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች ትብብር በመላ አገሪቱ ያለው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ስርጭት የተሻለ እንዲሆን ይረዳል፡፡

ከአምስት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መካከል (እያንዳንዳቸው 15 አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ያስተናግዳሉ) አንዱ ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል የሚያስተምር ሙሉ ሁለተኛ ደረጃ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ደረጃቸውን የጠበቁ የመማሪያ ክፍሎች የሌላቸው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መሠረተ-ልማታቸውን በማሻሻል ተደራሽነት እንዲጨምር ይደረጋል፡፡

ቀደም ሲል አቅርቦቱ ባልነበረባቸው አካባቢዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አማራጭና ተደራሽነት ሲሟላ ፣ በፊት የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አቋርጠው የነበሩ ተማሪዎች በመደበኛ፣ በማታ ወይም በተከታታይ ትምህርት ወደ ትምህርት ገበታ እንዲመለሱ ዕድል ይሠጣቸዋል፡፡ ይህ የመልሶ ቅበላ ሂደት በማህበረሰብ ቅስቀሳና በግንዛቤ ማሣደጊያ ዘመቻዎች የሚታገዝ ሲሆን፣ ስምንተኛ ክፍል ያጠናቀቁ ተማሪዎች ወደ ዘጠነኛ ክፍል እንዲሸጋገሩ ለማበረታታትም ይውላል፡፡

ፈጣን መስፋፋት በሚኖርባቸው የመጀመሪያ ዓመታት ወቅት የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍል መምህራን ሙሉ የማስተማር ጫና ከመያዛቸው በፊት፣ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ መስፋፋት በተካሄደባቸው ት/ቤቶች ውስጥ ከሰባተኛ እስከ አስረኛ ያሉትን ክፍሎች እንዲሸፍኑ ይደረጋል፡፡ የሚስፋፉት ትምህርት

ቤቶች የክላስተር ሀብት ማዕከላት በመሆናቸው የተሻለ ብቃት ስለሚኖራቸው የተማሪ ቁጥር ቢጨምርም የመማሪያ ክፍሎችን የመያዝ ሙሉ አቅም አሟጠው እንዲጠቀሙ ያስችላቸዋል፡፡

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተደራሽነት ዝቅተኛ በሆነባቸው የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢ ህፃናት የአዳሪ ትምህርት እና የመጠለያ አማራጮች እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች ለሚመጡ ተማሪዎች የትምህርት መሣሪያና የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ የልዩ ትምህርት ፍላጐት " ማስተር ፕላን"ን እንደዚሁም የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚኖረውን የዕድገት ግምገማ መሠረት በማድረግ በአምስተኛው የልማት መርሃ ግብር መጨረሻ የልዩ ትምህርት ፍላጐት ተማሪዎች ቅበላ ሲጠናቀቅ ከ7 በመቶ ወደ 45 በመቶ እንዲያድግ ታቅዷል፡፡

<table>
<tr><td>ስትራቴጂዎች</td><td>አመልካች (መነሻና ግብን ጨምሮ)</td><td>ምንጭ</td></tr>
<tr><td rowspan="2">በሁሉም ክልሎች የሚገኙ ህፃናት እድል እንዲያገኙ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ማስፋፋት</td><td>የዘጠነኛ አስረኛ ክፍል ጥቅል ድርሻ ከ39 በመቶ ወደ 74 በመቶ ያድጋል</td><td rowspan="2">የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት</td></tr>
<tr><td>የአስራ አንደኛና አስራሁለተኛ ክፍል ጥቅል ድርሻ ከ10 በመቶ ወደ 12 በመቶ ያድጋል</td></tr>
<tr><td colspan="3">የት/ቤት ማስፋፊያ ግብን ለማሣደግ የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት ጋር በማቀናጀት የት/ቤት ካርታ ማዘጋጀት</td></tr>
<tr><td colspan="3">በየክላስተሩ ከአንደኛ እስከ አስረኛ ክፍል የሚያስተምሩ ሙሉ የአንደኛ ደረጃት/ቤቶች እንዲኖሩ ማድረግ</td></tr>
<tr><td colspan="3">የሁለተኛ ደረጃ መጀመሪያ ሳይክል የሚያስተምሩ ት/ቤቶች ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል እንዲያስተምሩ ማድረግ</td></tr>
<tr><td colspan="3">በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች መሠረታዊ የ wash አገልግሎት ማሟላት</td></tr>
<tr><td colspan="3">ተማሪዋች ወደ ትምህርት ገበታ እንዲመለሱ ለማበረታታት የማህበረሰብ ቅስቀሳና የግንዛቤ ማሳደጊያ ዘመቻዎችን ማካሄድ</td></tr>
<tr><td rowspan="2">ሁኔታዎች ላልተመቻቹላቸውና ለተገለሉ ህፃናትና ሙሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተደራሽነትን የሚያሰቀጥል ልዩ ፕሮግራም መንደፍ</td><td>25 በመቶ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የማታ ትምህርት ይሠጣሉ</td><td>የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት</td></tr>
<tr><td>የልዩ ትምህርት ፍላጐት ትምህርት ቅበላ ከ7 በመቶ ወደ 45 በመቶ ያድጋል</td><td>የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት</td></tr>
<tr><td colspan="3">ከማዕከል ውጪና በታዳጊ ብሔሮች የመምህራን ቅጥርን ማበረታታት</td></tr>
<tr><td colspan="3">ተደራሽነታቸው አስቸጋሪ በሆኑ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ለሚገኙ ልጆች የአዳሪ ት/ቤቶችና መጠለያዎችን መመሥረትና ማጠናከር</td></tr>
<tr><td colspan="3">በተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የማታ ትምህርት መጀመር</td></tr>
<tr><td colspan="3">ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች ለሚመጡ ልጆች እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች የትምህርት ቁሳቁስና የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ</td></tr>
<tr><td colspan="3">ለአደጋ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የሚገኙ ድሃ ህፃናት ነፃ የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ማድረግ</td></tr>
<tr><td colspan="3">የአደጋ መከላከል ፕሮግራምን ማሳደግና በአደጋ የተጐዱ ት/ቤቶችን መደገፍ</td></tr>
</table>

**ተግባር 4፡- ለአራቱ አዳጊ ክልሎች የሚሆን ልዩ የድጋፍ ፕሮግራም**

| | | |
|---|---|---|
| አላማ፡- አራቱ አዳጊ ክልሎች የትምህርት ብቃት በብሄራዊ ደረጃ ያለውን ስታንዳርድ እንዲያሟሉ የሚያስችሉዋቸው ክህሎቶች፣ ግብአቶችና አቅም ይኖራቸዋል፡፡ | አራተኛው የትምህርት ልማት መርሃ-ግብር ጠቅላላ (ሴ/ወ) | ግብ ጠቅላላ (ሴ/ወ) |
| የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ቅበላ በአዳጊ ክልሎች (በምዝገባ ወቅት እድሜ 4-6 ዓመት ) | 8 በመቶ (7/8) | 80 በመቶ (80/80) |
| በአፋር ክልል ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ጠቅላላ ቅበላ | 74 በመቶ (72/76) | 98 በመቶ (98/98) |
| በአዳጊ ክልሎች ውስጥ ከልዩ ድጋፍ ፕሮግራም ተጠቃሚ የሚሆኑ ወረዳዎች በመቶኛ | የለም | 100 በመቶ |


አራቱ የታዳጊ ክልል መንግሥታት፣ ማለትም አፋር፣ ሱማሌ፣ ጋምቤላና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ከብሔራዊ አማካይ አንፃር ዝቅተኛ የልማት ደረጃ ላይ ስለሚገኙ ታዳጊ ክልሎች በመባል ይታወቃሉ፡፡ ስለሆነም የፌዴራል መንግሥቱ የትምህርት ሚኒስቴር ግብአቶችን ጨምሮ፣ በተለያዩ ሴክተሮች ልዩ የድጋፍ ፕሮግራም ዘርግቷል፡፡

ዩኒቨርሳል የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለማሣካት በብሔራዊ ደረጃ ያለው እድገት ተስፋ ሰጭ ቢሆንም በክልሎች መካከል በተለይም በነዚህ በአራቱ አዳጊ ክልሎች በተደራሽነትና ተሳትፎ ረገድ እኩልነት አይታይባቸውም፡፡ በተጨማሪም፣ በክልሎች ውስጥ ምንም እንኳን ቁጥራቸው ትንሽ ቢሆንም በርካታ ያገሬው ተወላጆች  የመደበኛ ትምህርት ተሣታፊ አይደሉም፡፡ እነዚህ በክልሎች መካከልና በራሳቸው በክልሎቹ ውስጥ ያሉ ልዩነቶች ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኢፍትሃዊነት ፣ ከተማ ወይም ገጠር ከመሆን፣ ከብሄር፣ ከኑሮ እና ከቋንቋ ጋር በጥብቅ የተቆራኙ ናቸው፡፡ በነዚህ ክልሎች የሚኖሩ ወደ

ትምህርት ገበታ ሊመጡ የሚችሉ ተማሪዎችም የውሃ እጦት፣ ተደጋጋሚ ድርቅና የተፈጥሮ አደጋዎችን የመሠሉ ተግዳሮቶች ያጋጥሟቸዋል፡፡

ለታዳጊ ክልሎች የሚሰጠው ልዩ የድጋፍ ፕሮግራም ሦስት የአቅም ግንባታ ደረጃዎችን (ግለሰባዊ፣ ተቋማዊና አስቻይ አካባቢ (enabling environment) በመለየት በብዝሃ ሴክተር አካሄድ የነዚህ ክልሎች ዝቅተኛ የትምህርት ውጤታማነት መፍትሄ ሊያገኝ የሚችለው ከአቅራቢ ወገን ብቻ ስላልሆነ ይህ አሳታፊ ፕሮግራም አስፈላጊ ነው፡፡

**ሥንጠረዥ 16፡- የልዩ የድጋፍ ፕሮግራም ሦስቱ የአቅም ግንባታ ትኩረቶች**




እነዚህን ሦስት ደረጃዎች ከግንዛቤ በማስገባት የሚከተሉት ስትራቴጂዎች በልዩ የድጋፍ ፕሮግራሙ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ እነዚህ ስትራቴጂዎች በ2014 በተካሄደ የአቅም ክፍተት ትንተና እና ሌሎች ታዳጊ ክልሎችን የተመለከቱ ስትራቴጂዎች አንፃር በመቃኘት ይሠራባቸዋል፡፡

**የግል አቅም፡-** በአመራር ፣ በእቅድ አወጣጥ፣ በሪፖርትና መረጃ ልውውጥ ዙሪያ የአዐርና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎችን መስጠት፡፡ የስልጠና ፕሮግራሞቹ በአዳጊ ክልሎች ውስጥ ለሚገኙ የክልል ትምህርት ቢሮዎችና የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች 30 የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎችን ከመመደብ ጋር ይይዛል፡፡ ይህ አካሄድ የፕሮግራሙን ቀጣይነት በማረጋገጥና ከክልል- ክልል ሊኖር የሚችለውን የሰው ሀይል ፍልሰት ስለሚቀንስ ተመራጭነት ይኖረዋል፡፡

**ተቋማዊ አቅም፡-** የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ የሚከለስና የሚሻሻል ሲሆን ሌሎች መመሪያዎች፣ ማንዋሎችና አቅጣጫዎች የአዳጊ ክልሎችን የትምህርት ሴክተር ልማት ማገዝ በሚያስችል መልኩ ከአካባቢያዊ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ይቃኛሉ፡፡ ይህም፣ የአማራጭ ትምህርት

መመሪያ በማዘጋጀት ባህላዊ ት/ቤቶች የሚቀናጁበትን፣ አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ወደ ደረጃ ስድስት እና ወደ መደበኛ አንደኛ ደረጃ እንዲሻሻሉና እንዲያድጉ ይደረጋል፡፡ ብቁ የሆኑ ባለሙያዎች በአዳጊ ክልሎች በሚገኙ የትምህርት ጽ/ቤቶች ተመድበው እንዲሰሩ ለማበረታታት ኃላፊዎች የተሻሻለ የማትጊያና ማነቃቂያ ፖኬጅ እንዲፈላለግ ይደረጋል፡፡

**አስቻይ አካባቢ** (enabling environment)፡- *ሥራን ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁስና መሣሪያዎች እንዲሁም የገንዘብ ግብአቶች በሁሉም የትምህርት ጽ/ቤቶች እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘባቸው አካባቢዎች ደግሞ በትምህርት አስፈላጊነት ዙሪያ ግንዛቤ ለማሣደግና ማህበረሰቡን ለማንቃት የሬዲዮና የቴሌቪዥን ስርጭቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ "ብሄራዊ የአርብቶ አደሮች ትምህርት ካውንስል" የሚመሠረት ሲሆን፣ ካውንስሉ ጥናቶችንና ተግባቦታዊ ጥረቶችን የመደገፍ እንዲሁም መንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት የሚገኙ የመሠረተ ልማት፣ የባለሙያ፣ የንፁህ ውሃና በአርብቶ አደር አካባቢዎች የተመጣጠነ ምግብ አቅርቦት ግብአቶችን የማስተባበር ሚና ይኖረዋል፡፡*

| ስትራቴጂዎች | አመልካች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| የትምህርት ሴክተር ልማት ትግበራ ለማሻሻልና ለማዳበር የአዳጊ ክልሎችን አቅም ማጐልበት | በአዳጊ ክልሎች ጥቅል የቀድመ መደቦች ትምህርት ድርሻ (በምዝገባ ወቅት ዕድሜ 4-6 ዓመት) ከ8 በመቶ ወደ 80 በመቶያድጋል | የትምህርት አስተዳደር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | በአፋር ክልል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ቅበላ 98 በመቶ ይደርሳል | የትምህርት አስተዳደር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | በአዳጊ ክልሎች የቴክኒክ ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ቁጥር ከ24 ወደ 30 ያድጋል | የልዩ ድጋፍና አካቶ ትምህርት |
| | በአዳጊ ክልሎች የሚገኙ ወረዳዎች ሙሉ በሙሉ 100 በመቶ የልዩ ድጋፍ ፕሮግራም ተጠቃሚ ይሆናሉ | የልዩ ድጋፍና አካቶ ትምህርት |
| የልዩ ድጋፍ ፕሮግራም መመሪያዎችን ማዘጋጀት፣ ማጽደቅና ማሠራጨት | | |
| አራቱ አዳጊ ክልሎች በክልል፣ በወረዳና በት/ቤት ደረጃ ያላቸውን የእቅድና የአመራር አቅም እንዲያጐለብቱ የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪዎችን በመመደብ የልዩ ድጋፍ ፕሮግራምን ማጠናከር | | |
| በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የአዳጊ ክልሎች የትምህርት ባለስልጣናት፣ ኤክስፐርቶችና የት/ቤቶች ርዕሰ መምህራን የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ | | |
| የልዩ ድጋፍ ፕሮግራሞችን በመገምገም ስትራተጂክ ማሻሻያዎችን ማድረግ | | |
| ብሔራዊ የአርብቶ አደር ትምህርት ካውንስል መመስረት | | |

## 8. ቅድሚያ የተሰጠው መርሃግብር፡- የጎልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት

### የዚህ ቅድሚያ የተሰጠው መርሃግብር ዓላማ

“የጎልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርትን እድሜ ልክ ከመማር እድል ጋር በማስተሳሰር የሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የትምህርት ፍላጐት (በግል፣ በማህበርና በኢኮኖሚ ልማት) እንዲሟላ በማድረግ የሚማር ህብረተሰብ መፍጠር ነው፡፡

### መግቢያ

ትምህርት ያላገኘው የጎልማሳና ወጣት ቁጥር እጅግ ከፍተኛ መሆን ሃገሪቱ የአድገት ግቦቿን በተለይም እ.ኤ.አ በ2025 ዝቅተኛ የመካከለኛ ገቢ ካላቸው ሃገራት ተርታ ለመሰለፈ ያላትን ራዕይ ያደናቅፋል፡፡ የተማረ የጎልማሳ ቁጥር ማሳደግ ሌሎች የእድገት ግቦችንም ይደግፋል፡፡ የተማሩ ወላጆች ያሏቸው ህፃናት ረዘም ያለ የትምህርት ላይ ቆይታ የሚኖራቸው ሲሆን፣ እናቶች አንድ አመት የመማር ተጨማሪ እድል በተሰጣቸው ቁጥር የህፃናትን ሞት ከመቀነስና የህጻናትን ጤና ከማሻሻል ጋር ይያያዛል፡፡

በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ዘመን ብሔራዊ የጎልማሶች ትምህርት ስትራቴጂ (IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት)) የተለየ የፖሊሲ ትኩረት ተሰጥቶት ነበር፡፡ እድሜያቸው ከ15-60 ለሆኑ የሚሰጥ የሁለት አመት ፕሮግራም ሲሆን፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማንበብ የመፃፍና የመቀመር ክሂሎችን የሚያጎለብትና ተዛማጅ ተግባራዊ እውቀቶችንና ችሎታዎችን (ለምሣሌ ያህል የቤተሰብ ጤና የንፅህናን የጽዳት አጠባበቅን)  ያካተተ ነው፡፡ ፕሮግራሙ እርሻንና ጤናን ከመሰሉ ሌሎች የእድገት እንቅስቃሴዎች የተገኙ ተሞክሮዎችን እንደ ግብዓት የሚጠቀምና በሃገር በቀል እውቀቶች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በተጨማሪ የማንበብና የመቀመር ክህሎቶችን ከማህበረሰቡ የህይወት ዘይቤ ጋር በማስተሳሰር የግብርና (ከመስክ ውጭ ያሉ አንቅስቃሴዎችን ጨምሮ)፣ የጤና፣ የስነ ዜጋና የባህል ትምህርት ስልጠናዎችን ለመስጠት ፕሮግራሙ

ይፈጥራል፡፡ ለዚህ ግብ ስኬትም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት በሁሉም አቅጣጫ ርብርብና ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

ቀደም ባሉት አመታት የተከናወኑ የትምህርት ግምገማ ውጤቶችን መሠረት በማድረግ፣ የአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ-ግብር የመነሻ ግብ አድሜያቸው ከ15-60 ዓመት የሆኑ 36.4 ሚሊዮን ዜጎች ሁለት አመት እርዝማኔ ባለው የሴቶችና ጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ እ.ኤ.አ በ2012 የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የድጋፍ አሰጣጥ ክትትል የዳሰሳ ሪፖርት በአገሪቱ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ 20.4 ሚሊዮን ወጣቶችና ጎልማሶች ትምህርት እንዳላገኙ ያለውን ግምት አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም፣ የአራተኛው መርሃ-ግብርን ግብ በእጅጉ በማሻሻል በትግበራ ዘመኑ 19.4 ሚሊዮን ጎልማሶችንና ወጣቶችን በሁለት አመት የሴቶችና ጎልማሶች ትምህርት ለማሳተፍ እቅድ ተይዞ ነበር፡፡ ከነዚህም መካከል 7.2 ሚሊዮን ዜጎች (በሀገሪቱ ከሚገኙ እድሜያቸው ከ15-60 የሆኑ ትምህርት ያላገኙ ዜጎች 35 በመቶ የሚሆኑት) የሁለት አመት የሴቶችና ጎልማሶች ትምህርትን በማጠናቀቅ ተመርቀዋል፡፡ የትምህርት እድሉን ያላገኙት ቀሪዎቹ 13.4 ሚሊዮን ጉልማሶች (9.3 ሚሊዮን ሴቶችና 4.1 ሚሊዮን ወንዶች) በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ዘመን የሁለት አመቱን የሴቶችና ጎልማሶች ትምህርት በማጠናቀቅ እንዲመረቁ ይደረጋል፡፡

በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ዘመን በፌዴራልም ይሁን በክልል ደረጃ የተጠናከረ የተከታታይ ትምህርትና የእድሜ ልክ ትምህርት ለመቅረጽና ለመተግበር የሚያስችል ወጥ የሆነ ሞዴል አልነበረም፡፡ ውጤታማ የሆነ የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም አደረጃጀት ለመፍጠርና ለመተግበር እንደ ማነቆ የሚጠቀሱት፡- የፖሊሲና ደንብ ማዕቀፍ አለመኖር፣ አስፈላጊው የተከታታይ ትምህርት መዋቅር አለመኖርና የሰለጠነ የሰው ሃይል እጥረት፣ የተከታታይ ትምህርት በሌሎች የልማት ዘርፎች ስለሚያበረክተው አስተዋጽኦ ያለው ዝቅተኛ ግንዛቤና ፕሮግራሙን ለመተግበር የሚያስፈልጉ የገንዘብና የቁሳቁስ እጥረት መኖር ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ በብሔራዊ የጎልማሶች ትምህርት ስትራቴጂ የተነደፈው የሴቶችና ጎልማሶች ትምህርት ጽንሰ ሃሳብ እና ፕሮግራም ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ ፈጀ ብዙ ጥረቶችን በማድረግ፣ የሴቶችና ጎልማሶች

ትምህርት ባለሙያዎችን የቴክኒክ አቅም በክልልና በፌዴራል ደረጃ ለመገንባት ተችሏል፡፡ በፌዴራል ደረጃ በርከት ያሉ መመሪያዎችና የአሰራር ደንቦችን "በብሔራዊ የጎልማሶች ትምህርት ስትራቴጂ" አማካኝነት በመንደፍ ከ 2008 ጀምሮ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ቁሳቁሶች እንዲሻሻሉና ስልጠናዎች እንዲሰጡ ተደርገዋል፡፡ የጎልማሶችና ሴቶች ትምህርት ቁልፍ ባለሙያዎችንና የቴክኒክ ባለሙያዎችን በፌዴራል፣ በክልልና በወረዳ ደረጃ በመመደብ የሰለጠነ የሰው ሃይል አቅምን ማጎልበት ተችሏል፡፡ ብዛት ያላቸው የማህበረሰብ አስተባባሪዎች ተመልምለው ስልጠና ያገኙ ሲሆን ፕሮግራሙ በጀት እንዲያዝለት ተደርጓል፡፡ (የአስተባባሪዎች ብዛትም ይሁን የበጀት አመዳደቡ በሚፈለገው ደረጃ ባይሆንም)፡፡

በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር አተገባበር ግምገማ ተለይተው የታወቁ ዋና ዋና ችግሮች ከዚህ በታች ያሉት ናቸው፡፡

- የታቀደው ተቋማዊ አደረጃጀት፣ ብሔራዊ የጎልማሶች ትምህርት ቦርድን ጨምሮ ሙሉ በሙሉ ሊቋቋም አልቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት የጎልማሶች ትምህርት አሰጣጥ በተበጣጠሰ መልኩ እንዲቀጥልና ውጤታማ የሆነ የአፈፃፀም፣ የትብብር፣ የግንኙነትና የክትትል ሂደት እንዳይኖር አድርጐታል፡፡
- ሁሉም የክልል የጎልማሶች ትምህርት ቦርዶች ውጤታማ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ነበሩ ለማለት አይቻልም፡፡ ፕሮግራሙን ለመምራት ቁርጠኝነት ያላቸው ባለሙያዎች እጥረት ስለነበር አብዛኞቹ የትምህርት ማዕከላት የቴክኒክ ድጋፍ ማግኘት አልቻሉም፡፡
- በብዙ ክልሎች፣ በበጀት እጥረት፣ በአስተባባሪዎችና አስተባባሪ አሰልጣኞች አቅም ውስንነት ምክንያት የመማርያ ቁሳቁስን የማበልፀግ ችግሮች ታይተዋል፡፡ ብዙዎቹ ክልሎች በበጀት እጥረትና ውጤታማ ባልሆነ የሃብት አመዳደብ ምክንያት የአስተባባሪ መመሪያዎችን እና የተማሪዎች መፃህፍትን ማቅረብ አልቻሉም፡፡
- ከመሠረታዊ ትምህርት በኋላ፣ ቀጣይ ስትራቴጂና ስርዓተ -ትምህርት አለመኖር መሃይምነት እንዲያገረሽ ሊያደርግ ይችላል

- በማደግ ላይ በሚገኙ ክልሎች ያለው የሴቶችና የጎልማሶች ትምህርት ተሳትፎ በንፅፅር ዝቅተኛ ነው፡፡
- በየደረጃው የክትትል፣ የምዘናና ሪፖርት የመላክ አቅም ባለመኖሩ የሴቶችና ጎልማሶች ትምህርት ስለሚገኝበት ደረጃና በተሳታፊዎቹ የቀን ተቀን ህይወት ስለሚያበረክተው አስተዋጽኦ ውጤታማ ግምገማ ሊካሄድ አልቻለም፡፡
- በፕሮግራሙ ከአንደኛ ወደ ሁለተኛ አመት ያለው ሽግግር ዝቅተኛ መሆን የሚሸጋገሩ ተሳታፊዎች ቁጥር መቀነስ

እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ፣ ይህ የትኩረት ፕሮግራም አምስት መፍትሔዎችን ይተገበራል፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡-

- የሴቶችና ጎልማሶችን ትምህርት እንደዚሁም ድህረ- ሴቶችና ጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራሞችን በሁሉም ክልሎች ማስፋፋት
- በሴቶችና ጎልማሶች ትምህርትና ድህረ ፕሮግራሞች የሴቶችን ተሳትፎ ማጠናከር
- የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራሞችን በማደግ ላይ ባሉ ክልሎች ማስፋፋት
- የጎልማሶችና የሴቶች ትምህርት ጥራትን ማሳደግ
- በሁሉም ደረጃዎች በጎልማሶችና ሴቶች ትምህርት ጠንካራና ውጤታማ ተቋማዊ አደረጃጀት እንዲፈጠር ማድረግ

**ተግባር 1፡ የIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት)ና የድህረ IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ፕሮግራሞችን በሁሉም ክልሎች ማስፋፋት**

| ዓላማ ፡- ትምህርት ያገኙ ጎልማሶችን ቁጥር ማሳደግና መሃይምነት እንዳያገረሽ አማራጮችን ማቅረብ | በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ጠቅላላ (ወ/ሴ) | ግብ ጠቅላላ (ወ/ሴ) |
|---|---|---|
| እድሜያቸው ከ15-60 የሆኑ የሁለት አመቱን የጎልማሶችና ሴቶች ትምህርት ፕሮግራም አጠናቀው የተመረቁ ዜጎች (%) | 0 በመቶ | 100 በመቶ (100/100) |
| የጎልማሶችንና ሴቶች ትምህርት ፕሮግራም አጠናቀው በድህረ | የለም | 15 በመቶ |

| | | |
|---|---|---|
| መሠረታዊ እንቅስቃሴዎችና በማህበረሰብ የትምህርት ፕሮግራሞች በመሳተፍ ላይ የሚገኙ ሰልጣኞች (%) | | (15/15) |
| ከጐልማሶች ትምህርት ማእከልነት ወደ ማህበረሰብ ትምህርት ማአከልነት ያደጉ (%) | የለም | 25 በመቶ |

**ንኡስ ተግባር 1. ውጤታማ የሴቶችና ጎልማሶች ትምህርት መንደፍና መተግበር**

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ዘመን የANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት)ትኩረት የሴቶችና ጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራሞችን ተደራሽነት ማስፋፋት፣ በብሔራዊ የጎልማሶች ትምህርት ስትራቴጂ የተቀመጡትን ግቦች በመጠቀም ጥራትን ማሳካት ነው፡፡

በትምህርት ሚኒስትር ውስጥ የሚገኘው የANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ዩኒት ከብሔራዊና ክልላዊ የጎልማሶች ትምህርት ቦርዶች ጋር በጋራ በመስራትና ድጋፍ በማድረግ ከተግባር ጋር የተገናኘ የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራሞች እንዲታቀዱና በሥራ እንዲተገበሩ ያደርጋል፡፡ የጎልማሶችና የሴቶች ትምህርት ማዕከላትን በማህበረሰቡ መኖሪያ አካባቢ በቅርብ ርቀት በመመስረትና በማደራጀት ለጎልማሶች ያለውን ተደራሽነት ከፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ማዕከላቱ ከጎልማሶች ህይወት፣ የአኗኗር ሁኔታና ከማህበረሰቡ ፍላጐት ጋር ቅርብ ቁርኝት ያለው ተማሪ ተኮር የሆነ ስርአተ -ትምህርት ያዘጋጃሉ፡፡ አሁን በመሰጠት ላይ ያሉት የጎልማሶችና የሴቶች ትምህርት ፕሮግራሞች የልዩ ፍላጐት ትምህርት ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች ምንም የተለየ ትኩረት አይሰጡም፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ዘመን በሁሉም ክልሎች የፍላጐት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ በጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስፈልጉ የስርዓተ ትምህርት ክለሳና የትምህርት ቁሳቁሶች አቅርቦት እንደዚሁም የትምህርት ስልቶች ማሻሻያዎችን ለመለየት መረጃዎች ይሰበሰባሉ፡፡ ከእነዚህ ጥናቶች በመነሳት የጐልማሶችና ሴቶች ትምህርት ቁሳቁስ ዝግጅት፣ የመማርያ ማዕከላት መረጣና የአስተባባሪዎች ስልጠናን የሚመለከቱ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡

## ንኡስ ተግባር 2፡ ከማህበረሰቡ ጋር በመሆን የድህረ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራሞችን መቅረጽና መተግበር

የተማረ አካባቢን ለመፍጠር ዘላቂነት ያለው የትምህርት እንቅስቃሴን ማከናወን የግድ ነው፡፡ ይህ የሚመለከተው የሁለት አመት የጎልማሶችና ሴቶች ትምህርት ፕሮግራም ያጠናቀቁትን ብቻ ሳይሆን፣ በዚሁ ፕሮግራም ውስጥ በመሳተፍ ላይ ሚገኙትን ሰልጣኞችን ጭምር ነው፡፡ መሠረታዊ የማንበብና መፃፍ እንዲሁም የመቀመር ክህሎታቸውን በማጎልበት ሂደት ላይ የሚገኙ ተማሪዎች እነዚህን ክህሎቶቻቸውን በቀን ተቀን ህይወታቸው የመሞከር ፍላጎቱ አላቸው፡፡ ይህንን ፍላጎታቸውን እንዲያሟሉ ለልምምድና ሙከራ እድል የሚፈጥር የተማረ የትምህርት ከባቢ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡

የድህረ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራሞች ዋነኛ ትኩረት ከጎልማሶች ትምህርት በቅርብ በተመረቁ ወይም የእጅ አዙር ምሩቆች (neo-literate) ጎልማሶችና የማህበረሰብ ክፍሎች (የሁለት አመት የሴቶችና ጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ያጠናቀቁ፣ ፕሮግራሙን በመከታተል ላይ ያሉ ወይም መማር የሚፈልጉ) ላይ ነው፡፡ የድህረ መሠረታዊ ትምህርት አላማዎች መሠረታዊ ትምህርትን ማጠናከር፣ ለአዲስ ተማራቂዎች የመርጃ ቁሳቁሶችንና የመረጃ ምንጮችን ማቅረብ ሲሆን በተጨማሪም መደበኛ ያልሆኑ የትምህርት ስልቶች እንዲፈጠሩ በማድረግ ማህበረሰቡን በማገልገል ላይ ያተኩራሉ፡፡

የጎልማሳ ተማሪዎች ማህበሮች በአካባቢው መንግሥት ድጋፍ አበረታችነት የተከታታይ ትምህርት ማዕከላትን በማቋቋም ማዕከላቱ የጎልማሶችና ሴቶች ትምህርት ፕሮግራሞች፣ ሌሎች የጎልማሶች ትምህርቶች፣ ስልጠናና የኤክስቴንሽን እንቅስቃሴዎች የሚካሄዱባቸው ዋና ማደራጃዎች በመሆን ያገለግላሉ፡፡ የመሠረታዊ የትምህርት ስልጠናን ያጠናቀቁ ጎልማሶች ያገኟቸውን ክህሎቶች ጠብቀው መቆየት እንዲችሉና እያጎለበቷቸው እንዲሄዱ ለማድረግ ጠቃሚ የሆኑ የድህረ መሠረታዊ ትምህርት ግብዓቶች ማሟላት ወሳኝ ሚና አለው፡፡ የተከታታይ ትምህርት ማዕከላቱ ምቹ፣ መረጃ ሰጭ፣ ከተማሪዎች የአኗኗር ዘይቤ ጋር ተዛማጅ የሆኑ የተለያዩ የትምህርት ግብአቶች እንዲሟሉላቸው ይደረጋል፡፡ እነዚህ ማዕከላት ለማህበረሰቡ አባላት በቀላሉ ተደራሽና ለሌሎች የመንግሥት

አገልግሎቶችና የመረጃ አሰጣጥ ሂደቶች ማስተባበሪያ ቦታዎች ይሆናሉ፡፡ በመሆኑም የተከታታይ የትምህርት ማዕከላቱ የአካባቢው ህዝብ በተለያዩ ትምህርታዊና ቴክኒካዊ ስልጠናዎች በማሳተፍ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡ የተከታታይ ትምህርት ማዕከላት አካባቢያዊ የትብብር መድረኮች በመሆን በድህነት ቅነሳ ዙሪያ ያሉ ሃገር በቀል እውቀቶች ጎልብተው የአካባቢያቸውን ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ እድገት እንዲያቀላጥፉና የማህበረሰቡን የኑሮ ደረጃ እንዲያሻሽሉ ለማስቻል ያግዛሉ፡፡ የተከታታይ ትምህርት ማዕከላት የትምህርትና የመሠረታዊ ትምህርት ፣ የስልጠና፣ ትብብርና የእርስ በርስ ግንኙነት አውታር ፕሮግራሞችን ማካሄጃ ስፍራዎች መሆን ይችላሉ፡፡

በማዕከላቱ የተከታታይ ትምህርት አማራጮችን ከማቅረብ በተጨማሪ፣ የሚገኘውን የትምህርት ደረጃ የዝውውር መመሪያ ሕጋዊ ሰነድ ሆኖ እንዲፀድቅ ጥረት ይደረጋል፡፡ መመሪያው በጎልማሶችና ሴቶች ትምህርት ፕሮግራም የሁለት አመት ቆይታቸውን አጠናቀው የተመረቁ ጎልማሶች ተመጣጣኝ የብቃት ደረጃ ያላቸው መሆኑ እየተመዘነ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ማሰልጠኛዎች የመግባት ወይም መደበኛ ትምህርትን የመቀላቀል እድል እንዲያገኙ ያስችላል፡፡

| ስትራተጂዎች | አመልካች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
| --- | --- | --- |
| ውጤታማ የIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ፕሮግራሞችን መቅረጽና መተግበር | የሁለት አመት እርዝማኔ ያለውን የIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ኮርስ በማጠናቀቅ የሚመረቁ ከ15-60 ዓመት ያሉ ዜጎች 100 በመቶ ይደርሳል | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| በሁሉም ክልሎች ማቋቋም የጎልማሶች ትምህርት ማዕከላትን | | |
| የእያንዳንዱን ክልል ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘቡና ከስርአተ ትምህርቱ ጋር የተዛመዱ በወሳኝ የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች የትምህርት ማቴሪያሎች ማዘጋጀት | | |
| የጎልማሶች ትምህርት ተሳትፎን ለማጎልበት የሚያግዙ የግንዛቤ ማዳበሪያና የማህበረሰብ እንቅስቃሴ ዘመቻዎችን ማከናወን | | |
| የጎልማሶች ትምህርት የመግባቢያ ሰነድ ፈራሚዎችን ቁጥር ለማሳደግ ከሌሎች አጋር አካላት ጋር ግንኙነት ማጠናከር | | |
| የIEAE እና IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ፕሮግራሞችን ለመስጠት የሚችሉ አስተባባሪዎችን ማሰልጠን | | |
| ልዩ ፍላጐት በሚያስፈልጋቸው ጐልማሶች ዙሪያ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ፣ አስፈላጊው የስርዓተ ትምህርት ማሻሻያ፣ የትምህርት ቁሳቁስ አቅርቦትና የአስተባባሪዎች ስልጠና እንዲካሄድ ማድረግ | | |
| ማህበረሰቡን በማሳተፍ የድህረ መሰረታዊ ትምህርት ፕሮግራሞችን መቅረጽና መተግበር | ከዚህ በፊት ተማሪ ያልነበሩና እድሜያቸው 15-60 ዓመት የሆነ በተከታታይ ትምህርት ማዕከላት በሚሰጠው የድህረ መሠረታዊ ትምህርት እንቅስቃሴ የሚሳተፉ ዜጎች ብዛት 15 በመቶ ይደርሳል | የANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ዩኒት |

| | | |
|---|---|---|
| | ወደ ተከታታይ የትምህርት ማዕከልነት ደረጃ የሚያድጉ የጎልማሶች ትምህርት ማዕከላት 25 በመቶ ይደርሳል | የANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ዩኒት |
| ማህበረሰቡ ተከተታይ  የትምህርት ማዕከላትን እንዲያቋቁም ማገዝ | | |
| የተማሪ ማህበረሰብ በሚገኝበት አካባቢ የድህረ መሠረታዊ ትምህርት ማቴሪያሎች እንዲቀርቡ /እንዲገኙ ማድረግ | | |
| በዝቅተኛ ወጭ የተማሪ አካባቢን ለመፍጠር የሚያስችሉ ስልቶችን መንደፍ | | |
| የIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ምሩቃን ወደ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ወይም ወደ መደበኛ ትምህርት የሚዘዋወሩበትን እድል የሚፈጥር የዝውውር መመሪያ ማጽደቅ | | |

**ተግባር 2 በIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) እና ድህረ IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ**

| ዓላማ፡- በጎልማሶች ትምህርት የሴቶች ተሳትፎ መጨመር | በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም | ግብ |
|---|---|---|
| የሁለት  አመቱን የIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ፕሮግራም የሚያጠናቅቁ የሴት ተማራቂዎች (%) | 54 በመቶ | 70 በመቶ |
| የIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) እና የድህረ  IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) የሴት አስተባባሪዎች ቁጥር | የለም | 40 በመቶ |

ሴቶችን ማስተማር በቤተሰብ ገቢ ፣ በፆታ እኩልነትና የቤተሰብን አቅም በህብረተሰቡ የሚታዩው የእድሜ ልዩነት የሚያስከትለው ተጽእኖ በተመለከተ ሃገሪቱ በትክክለኛ አቅጣጫ ላይ ትገኛለች ማሳደግ ከፍተኛ የልማት ምንጭ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ ሴቶችን በማስተማር፣ መንግሥት የህፃናትን ሞት ለመቀነስ፣ ተላላፊ በሽታዎችን ለመቀነስ፣ እንደዚሁም የህፃናት አስተዳደግና የቤተሰብ እቅድን ለማስተማር የሚያደርገውን ጥረት ያግዛል፡፡ ሴቶችን በማስተማር ገቢ መጨመር፣ የፆታ እኩልነት ማጠናከርና በቤተሰብ ደረጃ ሴቶች የሚኖራቸው ክብር ማሳደግ እንደሚቻል ይታወቃል፡፡ በተጨማሪም ፣ የተማሩ ሴቶት ያለእድሜ ጋብቻን የሚቃወሙና ፣ ለኤች አይ ቪ እና ለመሳሰሉ በሽታዎች ያላቸው ተጋላጭነት ዝቅተኛ ከመሆኑ በተጨማሪ፣ ጤናና የህፃናት አስተዳደግን የሚመለከቱ ጽሑፎችን በማንበብ የልጆቻቸውን ህይወት ለማሻሻል ጥረት ያደርጋሉ፡፡

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ዘመን በጎልማሶችና ሴቶች ትምህርት ፕሮግራሞች የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ጥረት የሚደረገውም በዚህ ምክንያት ነው። በፕሮግራሙ ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብለው ከሚጠበቁት እድሜያቸው ከ15-60 ከሆኑ 19.4 ሚሊዮን ዜጎች መካከል 12.4 ሚሊዮኑ (64 በመቶ) ሴቶች ናቸው። ይሁን እንጂ፣ በመጀመሪያው የፕሮግራሙ የትገበራ አመታት የወንዶች ድርሻ ከፍ ያለ ስለነበር፣ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለው መመጣጠን ይበልጥ ሰፊ የሚያደርግ ይሆናል።

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ስትራተጂዎች ዋና ትኩረት በሚከተሉት ሶስት ጎዳዮች ላይ ያነጣጠረ ይሆናል። ሀ) የስርዓተ ትምህርቱና መጻሕፍቱ ማቴሪያሎች የፆታ እኩልነትን ይበልጥ ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ ለ) በIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ና በድህረ IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ፕሮግራሞች የሴት አስተባባሪዎችን ቁጥር ማሳደግ እና ሐ) በIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ና በድህረ IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ፕሮግራሞች የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ የሚያስችል የትምህርት አካባቢ መፍጠር

| ስትራተጂዎች | አመልካች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| በIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ና በድህረ IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ፕሮግራሞች የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ | የሁለት አመትን የ IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ፕሮግራም ያጠናቀቁ ሴቶች ቁጥር ከ54 በመቶ ወደ 70 በመቶ ከፍ ይላል | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | በIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ና በድህረ IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ፕሮግራሞች የሴት አስተባባሪዎች ቁጥር 40 በመቶ ይደርሳል | የጎልማሶችንና ሴቶች ትምህርት ዩኒት |

| |
|---|
| በፌዴራልና በክልል ደረጃ የስርዓተ ትምህርቱን ይዘት በመከለስ አግባብነቱንና ፣ ፆታን ያማካለ የመሆን አቅሙን በማጉልበት ለሴቶች ተሳትፎና ለህይወት ክህሎታቸው መዳበር ትኩረት መስጠት |
| ለበIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ና በድህረ IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) አስተባባሪዎች የምልመላ መስፈርት ማዘጋጀትና መስፈርቱ የሴቶችን ተሳትፎ የሚያበረታታ እንዲሆን ማስቻል |
| በጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራሞች የሴቶች ተሳትፎ እንዲጎለብት  የግንዛቤ መፍጠሪያ ዘመቻዎችንና የማህበረሰብ እንቅስቃሴዎችን መፍጠር |
| ሴቶችን ተጠቃሚ የሚያደርጉና ከሴቶች ህይወት ጋር ቀጥተኛ  ተያያዥነት ባላቸው ርእስ ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ የትምህርት ይዘቶችን ማዘጋጀት |
| የIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ማዕከላትን በተጠቃሚዎች የመኖሪያ አካባቢ በቅርብ ርቀት መገንባት |

**ተግባር 3፡ የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራሞችን በታዳጊ ክልሎች መጀመር**

| | | |
|---|---|---|
| ዓላማ፡- በአካባቢያዊ ልዩነቶች ላይ ያተኰረ የጎልማሶች ትምህርት አቅርቦት በታዳጊ ክልሎች እንዲጎለብት ማድረግ | በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር | ግብ |
| በጎልማሶች የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራሞች የሚሳተፉ በታዳጊ ክልሎች የሚኖሩ ጎልማሶች (ከIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ኮርሶች ውጪ)% | የለም | 15 በመቶ |
| በታዳጊ ክልሎች የጎልማሶች የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራሞችን የሚሰጡ የሚኒስተር መስሪያቤቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግል ተቋማት ቁጥር | የለም | በየክልሉ 5 |

ባለፉት ሃያ አመታት በታዳጊ ክልሎች የነበረው የመደበኛ ትምህርት ተደራሽነት ከሌሎች ክልሎች ጋር ሲነፃፀር በጣም ዝቅተኛ ነበር፡፡ ስለዚህም በእነዚህ ክልሎች የሚገኙ ጎልማሶች አምራች ዜጋ ለመሆን የሚያስችሏቸው መሠረታዊ ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ ቅድሚያ ሰጥቶ የመደገፍ እንቅስቃሴ ሊሰራ እንደሚገባ ሁኔታው አመላካች ነው፡፡ ይህንን ሁኔታ በማጤንና በታዳጊ ክልሎች ያለውን የባለሙያዎች፣ አስተባባሪዎችና አሰልጣኞች እጥረት ግምት ውስጥ በማስገባት በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ዘመን የሙከራ የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም በተመረጡ ታዳጊ ክለሎች ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የሚቀረጽና የሚተገበር ይሆናል፡፡

ይህ የሙከራ ፕሮግራም ጠንካራ ክትትልና ግምገማ የሚደረግበት ሲሆን፣ የሚገኘው ውጤት ፕሮግራሙን በሁሉም ታዳጊ ክልሎች ለማስፋፋት ሂደቱ የመነሻ ግብዓት ሆኖ ያገለግላል፡፡ ከIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ፕሮግራም ተሳታፊዎች ጋር

ትምህርታቸውና የህይወት ክህሎት ስልጠና ፍላጎቶችን በተመለከተ ምክክር ይደረጋል፡፡ የፍላጎት ዳሰሳው በወላጆች ትምህርት፣ በሙያ ስልጠና (በአካባቢው የሚገኙ ግብዓቶችንና የአካባቢውን ገበያ ባገናዘበ መልኩ)፣ እንዲሁም በኢንተርፕረነርሽፕ ስልጠና (የቢዝነስ ፕላን አዘገጃጀት፣ የገንዘብ አያያዝና ማርኬቲንግ) ዙሪያ ያተኮረ ይሆናል፡፡  ከዚህ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት የሚገኘው ውጤት የሙከራ ፕሮግራሙን ለመንደፍና የተሳታፊ ተማሪዎችንና የማህበረሰቡን ፍላጎት የሚያረካ መሆኑን ለመፈተሽ ይረዳል፡፡

| ስትራተጂዎች | አመልካች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| በታዳጊ ክልሎች ለሚገኙ ወጣቶችና ጎልማሶች የተከታታይ ትምህርትና የእድሜ ልክ የትምህርት አማራጮችን ተደራሽነት ማሳደግ | በተከታታይ የትምህርት ፕሮግራሞች የሚሳተፉ በታዳጊ ክልሎች የሚገኙ ጎልማሶች ድርሻ 15 በመቶ ይደርሳል (የFAE ኮርሶች ተሳታፊዎችን ሳይጨምር ) | ANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ዩኒት |
| | በእያንዳንዱ ታዳጊ ክልል የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራሞችን የሚሰጡ ቢያንስ አምስት የሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግል ተቋማት ይኖራሉ | ANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ዩኒት |
| የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራሞቹን አወቃቀር ለመለየት የሚረዱ ውይይቶችን በታዳጊ ክልሎች ከሚገኙ ወጣቶችና | | |

| |
|---|
| ጐልማሶች ጋር ማካሄድ |
| በታዳጊ ክልሎች የተከታታይ ትምህርት የሙከራፕሮግራሞችን ማካሄድ |
| በተመረጡ ስልቶች ላይ በመመስረት የተከታታይ ትምህርት ማቴሪያሎችን ማጎልበት |
| የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራሞችን በመገምገምና በመፈተሽ ለማስፋፋት ያላቸውን አመቺነት ማጤን |
| ለተከታታይ ትምህርትና የእድሜ ልክ ትምህርትን ለማስቀጠል ብሔራዊ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ማዘጋጀት |

**ተግባር 4፡ የANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት)ን (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ጥራት ማሻሻል**

| ዓላማ፡ ለትምህርት አሰጣጡ፣ ለትምህርት ቁሳቁስ አቅርቦቱና ለመምህራን ስልጠናው መሠታዊ መስፈርቶችን በማዘጋጀት፣ የጐልማሶች የተከታታይ ትምህርትን ጥራትና አግባብነት ማጎልበት | አራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር | ግብ |
|---|---|---|
| ለIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) እና ሁሉም የANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ፕሮግራሞች መሠረታዊ መስፈርቶችን ማዘጋጀትና መተግበር | የለም | ከ 2016 ጀምሮ በሁሉም ፕሮግራሞች |
| የኢንፎርሜሽን ሲስተም እና የጥራት ማረጋገጫ ስርዓቶች የ IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) እና ሌሎችን የANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት)ፕሮግራሞችን የሚደግፉበት ሁኔታ መፍጠርና በሥራ ላይ ማዋል | የለም | ለሁሉም ፕሮግራሞች እ.ኤ.አ በ2017 |
| ለተከታታይ የትምህርት ማዕከላት የሚያገለግል መሠረታዊ መስፈርት ማዘጋጀት | የለም | እ.ኤ.አ በ2016 |
| ሙሉ ስልጠና የሚሰጣቸው የIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) አስተባባሪዎች (%) | የለም | 80 በመቶ |
| በANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) እና ተዛማጅ ጉዳዮች ስልጠና የተሰጣቸው የፕሮግራም ማናጀሮችና ባለሙያዎች (%) | የለም | 80 በመቶ |

በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ብሔራዊው የIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ሥርዓተ ትምህርት በሁሉም ክልሎች እንዲተገበር የተደረገ ሲሆን ብሔራዊ የጎልማሶች ትምህርት ስትራቴጂና የአፈፃፀም መመሪያም እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡ የIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) የሱፐርቪዥን፣ የመማሪያ ማቴሪያሎችና መምሪያዎች (በተለያዩ ቋንቋዎች) እንዲዘጋጁና እንዲታተሙ ከማድረግ በተጨማሪ ሌሎች የስልጠና መመሪያዎች (የዋና አሰልጣኞች መመሪያና የአስተባባሪዎች የስልጠና መመሪያን ጨምሮ) እንዲዘጋጁና ከሰልጣኝ ጎልማሶች የአኗኗር ዘይቤ ጋር እንዲጣጣሙ ተደርገዋል፡፡ ይሁን እንጂ በአብዛኞቹ ክልሎች የIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) አስተባባሪዎች ስልጠና በብቃት እንዲከናወን የሚያስችል የዳበረ የጥራት ማረጋገጫ ስርዓት አልነበረም፡፡

በአብዛኞቹ ክልሎች ለ IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ፕሮግራሞች ደረጃውን የጠበቀ የአወቃቀር የአፈፃፀምና የምዘና አካሄድ ስልት ባለመጎልበቱ የትምህርት አሰጣጡ ወጥ የሆነ ጥራት እንዳይኖረውና ከተማሪዎቹ የህይወት ተሞክሮ ጋር ያለው ተዛማጅነት ዝቅ ያለ እንዲሆን አድርጓል፡፡ እነዚህ ምክንያቶች በ IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ፕሮግራሞች የሚሳተፉ ተማሪዎችን ከአንደኛ ወደ ሁለተኛ አመት የመሸጋገር መጠን ዝቅ እንዲልና ስለ ፕሮግራሙ ጥራትና አግባብነት በቂ የሆነ መረጃ እንዳይገኝ መንስኤ ሆኗል፡፡

በአምስተኛ የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ዘመን የ IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ፕሮግራምን አተገባበር ውጤታማነት ለመፈተሽ የሚያስችል ጥናት ይካሄዳል፡፡ ምዘናው የ IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ፕሮግራሞችን አደረጃጀት (አወቃቀር) እና ለሰልጣኞች የአኗኗር ዘይቤ መሻሻል ያበረከቱትን አስተዋጽኦ መፈተሽ ላይ ያተኮረ ይሆናል፡፡ የጥናቱ ውጤት የ IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) መሠረታዊ መመዘኛዎችን /መስፈርቶችን ለማዘጋጀት ግብዓት በመሆን ያገለግላል፡፡ መስፈርቶቹ ሁሉም ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ሃገር በቀል የሆነ፣ ጥራቱ የተረጋገጠ፣ ተገቢ ስልጠና ለተማሪዎችና አስተባባሪዎች መስጠት የሚያስችል የትምህርት ሂደት እንዲፈጠር የሚያደርግ የመመሪያ ሰነድ በመሆን ያገለግላሉ፡፡

አስተባባሪዎቹ የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት የቁጥጥር መሳሪያዎችን መጠቀም የሚያስችል ስልጠና እንዲወስዱና መረጃዎችን በወጥነት እንዲመዘግቡ ይደረጋል፡፡ የወረዳ የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ሲስተም ቢሮ ሰራተኞች በየሩብ አመቱ መረጃ የመሰብሰብና የመተንተን ኃላፊነት ያላቸው ሲሆን፣ የተገኙ ውጤቶችን እንደ ግብዓት በመውሰድ ከሙያ ባልደረቦቻቸው ጋር በመተባበር የIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ፕሮግራሞችን የማስተዳደር እና በተቀመጠው መሠረታዊ መስፈርት በመታገዝ ጠራታቸውን የማረጋገጥ ስራን ያከናውናሉ፡፡ የሙከራ የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራሙም በተመሣሣይ መንገድ ጥራቱ የተረጋገጠ ይሆናል፡፡ የክልል የጎልማሶች ትምህርት ቦርዶች መደበኛ ሪፖርቶች እንዲቀርቡላቸው የሚደረግ ሲሆን ክልሎች ተቋማትና የጎልማሳ ትምህርት ፕሮግራሞች ጋር የጋራ ትብብርን በማጠናከ የ IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ፕሮግራሞችን ጥራትና ተገቢነት በበላይነት የመቆጣጠር ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ለአስተባባሪዎች ስልጠና የመሠረታዊ መስፈርቶች መኖር እጅግ አስፈላጊና ለአጠቃላይ የስልጠናው ስርዓተ- ትምህርትና ለብቃት ምዘናው መሠረት ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ ለሱፐርቪዥን ፣ ለአደረጃጀት፣ ለትምህርት ማቴሪያሎች ማጎልበትና ሌሎች ተዛማጅ አላማዎች የሚያገለግል መነሻ መስፈርት ይዘጋጃል፡፡ የፕሮግራሙ ስርዓተ- ትምህርት ተግባራዊ ጠቀሜታው እንዲዳብርና በተለይም ለሴት ተማሪዎች ይበልጥ ምቹ እንዲሆን ማሻሻያ ይደረጋል፡፡ ምንም እንኳን የ IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ፕሮግራሞችን በአፍ መፍቻ ቋንቋዎች መንደፍና መተግበር የእያንዳንዱ ክልል ኃላፊነት ቢሆንም የአካባቢ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ልዩነት ያገናዘበ፣ ደረጃውን የጠበቀ፣ ወጥ የሆነ ስልት መቀየስ ሃብትን በጋራ የመጠቀም አማራጭን የሚፈጥርና በተያያዘም የትምህርት አሰጣጥ ጥራትን የሚያጎለብት አዎንታዊ እርምጃ ነው፡፡

| ስትራተጂዎች | አመልካች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| | ለአስተባባሪዎች የሚሰጠውን ሁሉንም የስልጠና ሂደቶች ያጠናቀቁ የIAFE አስተባባሪዎች 80 በመቶ ይደርሳል | ANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ዩኒት |

<table>
<tr><td rowspan="3">የANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ፕሮግራሞችን ጥራት ማሻሻል</td><td>በ ANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) እና ተዛማጅ ጉዳዮች ስልጠና የተሰጣቸው የፕሮግራም ማናጀሮችና ባለሙያዎች 50 በመቶ ይደርሳል</td><td>ANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ዩኒት</td></tr>
<tr><td>እ.ኤ.አ በ2016 የIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) እና ሁሉም የ ANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ፕሮግራሞች መሠረታዊ መስፈርቶች ተዘጋጅቶላቸው በተግባር ላይ ይውላሉ</td><td>ANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ዩኒት</td></tr>
<tr><td>እ.ኤ.አ በ2016 ለተከታታይ የትምህርት ማዕከላት መሠረታዊ መስፈርቶች ይዘጋጁላቸዋል</td><td>ANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ዩኒት</td></tr>
<tr><td colspan="3">IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት)ንና ሌሎች የ ANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ፕሮግራሞችን የሚደግፍ የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ሲስተም እና የጥራት ማረጋገጫ ስርዓትን ማሻሻል</td></tr>
<tr><td colspan="3">ለአስተባባሪዎች ስልጠናና የትምህርት ማቴሪያሎች አዘገጃጀት መሠረታዊ መስፈርት ማዘጋጀት</td></tr>
<tr><td colspan="3">ለዋና የ IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) አስተባባሪዎች ስልጠና መስጠት</td></tr>
<tr><td colspan="3">ለተከታታይ ትምህርት ማዕከላት መሠረታዊ መስፈርት ማዘጋጀት</td></tr>
<tr><td colspan="3">ምርጥ ተሞክሮዎችንና ልምዶችን ለመለዋወጥ የሚያስችሉ ክልል አቀፍ ወርክሾፖችን ማዘጋጀት</td></tr>
<tr><td colspan="3">ለተከታታይ ትምህርት ማዕከላት መልካም ተሞክሮዎችን ለማጎልበት የሚያስችሉ የማጠናከሪያ ግምገማዎችን ማካሄድ</td></tr>
<tr><td colspan="3">ለፕሮግራም ማናጀሮችና ባለሙያዎች በ IFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ተዛማጅ ርእሶች ዙሪያ ስልጠና መስጠት</td></tr>
<tr><td colspan="3">ብሄራዊ የጎልማሶች ትምህርት ስትራቴጂና መመሪያዎችን ለማስተዋወቅ ሁሉም በድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ የግንዛቤ ማስጨበጫ ወርክሾፖች ማዘጋጀት</td></tr>
<tr><td colspan="3">በሁሉም ክልሎች ያለውን ትግበራ ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል እቅድ ማዘጋጀት</td></tr>
<tr><td colspan="3">በየሩብ አመቱ የANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ተሳትፎንና አፈፃፀም በተመለከተ መረጃ መሰብሰብ</td></tr>
<tr><td colspan="3">የትምህርት ግብዓቶችን በአፍ መፍቻ ቋንቋ የማበልፀግ ሂደትን የሚደግፍ ስትራቴጂ በመንደፍ ክልሎች ነባራዊ ሁኔታቸውን በትክክልና በተገቢ ሁኔታ ያገናዘቡ ማቴሪያሎች እንዲኖሯቸው ማድረግ</td></tr>
<tr><td colspan="3">ANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ማቴሪያሎችን ለማዘጋጀት የሚያስችል የጥራት ማረጋገጫ መስፈርት ማርቀቅ</td></tr>
<tr><td colspan="3">የአደረጃጀት ዘዴዎች ላይ ትኩረት ያደረገ የIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) አተገባበርን ውጤታማነት መገምገም</td></tr>
<tr><td colspan="3">የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ሲስተም የቁጥጥር መሳሪያዎችን አጠቃቀምና የመረጃ አሰባሰብና አያያዝን በተመለከተ ለANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) አስተባባሪዎች ስልጠናዎችን መስጠት</td></tr>
</table>

**ተግባር 5፡ በሁሉም ደረጃዎች ላሉ ANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ፕሮግራሞች ጠንካራና ውጤታማ ተቋማዊ ስርዓትን መፍጠር**

| | | |
|---|---|---|
| ዓላማ፡ - የANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ፕሮግራሞችን በተገቢ ሁኔታ ለማደራጀትና ለመፈፀም የሚያስችል የፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት | በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር | ግብ |
| ለጎልማሶችና ለእድሜ ልክ ትምህርት የፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀትና በሥራ ላይ ማዋል | የለም | ሐምሌ 2016 |
| የANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ፕሮግራሞችን የሚደግፉ የክልል የጎልማሶች ትምህርት ቦርዶች ቁጥር | የለም | 11 |

በብሔራዊና በክልል ደረጃዎች የህግ ማዕቀፎችና የፖሊሲ አቅጣጫዎች አለመኖርና አግባብ ያለው ተቋማዊ አደረጃጀት አለመፈጠር በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ዘመን የANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ፕሮግራሞችን ስኬታማነት ገድቦታል፡፡ የብሔራዊ የጎልማሶች ትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎችን በመንደፍና ተቋማትን በማጠናከር ረገድ የጎላ ሚና አልተጫወተም፡፡ ከትምህርት ሚኒስተርና በክልል ደረጃ ከሚገኙ ተመሣሣይ አደረጃጀት ባላቸው ተቋማት ጋር በትብብር የተቋቋመው አዲሱ የANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ማስተባበሪያ ቢሮ ስራውን በአግባቡ ለማከናወን የሚያስችለው ግልጽ የፖሊሲ አቅጣጫ የለውም፡፡ የIFAE (የተቀናጀ ተግባር ተኮር ትምህርት) ፕሮግራም በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ዘመን በታቀደ መሠረት ተገቢውን የፋይናንስ ድጋፍ ከክልል ትምህርት ቢሮዎች ሊያገኝ አልቻለም፡፡

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ውጤታማ የሆነ የANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ተቋማዊ ስርዓት የሚፈጠርለት ሲሆን መሪ እቅዱን በማሻሻልና ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲመሩበትና እንዲፈጽሙት ይደረጋል፡፡ ብሔራዊው የጎልማሶች ትምህርት ቦርድና የቴክኒክ ኮሚቴዎች በሙሉ ሃይላቸው ወደ ስራ እንዲገቡ በትምህርት ሚኒስትር የANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ማስተባበሪያ ቢሮ አማካኝነት አስፈላጊው

የጽ/ቤት አገልግሎት እንዲሟላላቸው ይደረጋል፡፡ በተመሣሣይ መልኩ፣ የየክልሉ የጎልማሶች ትምህርት ቦርዶችም ሙሉ በሙሉ ስራቸውን የሚጀምሩ ሲሆን፣ የጽ/ቤት አገልግሎትና የባለሙያ ቡድኖች የምክር ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ክልሎች አጠቃላይ እና የተሳለጠ የእድሜ ልክ ትምህርት ስርዓት እንዲፈጥሩ ጥረት ይደረጋል፡፡ አመላካች ጥናቶችን በማካሄድ የANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ኤጀንሲ ማቋቋም በጎልማሶች ትምህርት እንቅስቃሴ የውስጥ ያለውን ተቋማዊ አደረጃጀት የቱን ያህል እንደሚያሻሽለው ይፈተሻል፡፡ ጥናቱ ኤጀንሲው ለመስራት የሚያስችለውን ህጋዊ ማዕቀፍና ተያያዥ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን የመለየት ስራ ላይ ያተኮረ ይሆናል፡፡

| ስትራተጂዎች | አመልካች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| በሁሉም ደረጃዎች የሚገኙ ANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት)ዎች ጠንካራና ውጤታማ ስርዓት እንዲኖራቸው ማድረግ | እ.ኤ.አ በ2016 ለጎልማሶች እና እድሜ ልክ ትምህርት የፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀትና መተግበር | የANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ዩኒት |
| | አስራ አንድ የክልል የጎልማሶች ትምህርት ቦርዶችን ለANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ፕሮግራሞች ድጋፍ ያደርጋሉ | የANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ዩኒት |
| የጎልማሶች ትምህርት ቦርዶችን አሰራር መገምገምና ማስተካከያ ለውጦችን መውሰድ | | |
| የባለድርሻ አካላት በእቅድ ዝግጅት ወቅት ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ | | |
| በብሔራዊ የጎልማሶች ትምህርት ቦርድ አማካኝነት የማስተባበር እንቅስቃሴዎችን ማጎልበት | | |
| ለANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ስትራቴጂዎች መሳካት በክልል ደረጃ የሚመደበውን የሃብት መጠን ማሳደግ | | |
| በፌዴራልና በክልል ደረጃ ለሚቋቋሙ የጎልማሶች ትምህርት ቦርዶች የጽ/ቤት አገልግሎቶችን ማቅረብ | | |
| ለANFE (የጐልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት) ኤጀንሲ ማቋቁም አዋጭነትን በተመለከተ ጠቋሚ ጥናት ማካሄድ | | |

## 9. ቅድሚያ የተሰጠው መርሃግብር፡ ፡- የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና

**የዚህ ቅድሚያ የተሰጠው መርሃግብር ዋና ግብ፡-**

*“ተወዳዳሪ የሆነ፣ ተነሳሽነት ያለውና የመፍጠርና የማጎልበት አቅም ያዳበረ የሰው ሃይል በዝቅተኛና መካከለኛ ደረጃ በማፍራት፣ ድህነትን ለመቀነስና የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማምጣት አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችል ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ጥራት ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና መስጠትና የቴክኖሎጅ ሽግግር ሂደትን ማጎልበት”*

**መግቢያ**

ባለፉት አምስት አመታት መንግሥት ስምንት የትኩረት ዘርፎችን በመለየት (ግብርና፣ ኢንዱስትሪ፣ የኢኮኖሚ መሠረተ ልማት ዝርጋታ፣ ጤና፣ ሆቴልና ቱሪዝም፣ ንግድ፣ ማዕድን፣ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች) በመረጃ ላይ የተመሠረተ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና እንቅስቃሴዎችን ሲያካሂድ ቆይቷል፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ብቃት ያለው የሰው ሃይልና አስፈላጊ ቴክኖሎጅዎችን በማሟላት የዘርፎቹን ተወዳዳሪነት ማረጋገጥ እንዲቻል ታቅዶ የተዘጋጀ ነው፡፡ በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ዘመን ከተመዘገቡት ስኬቶች መካከል የሙያ ደረጃ መስፈርቶች በማሳደግ፣ የምዘና ባለሙያዎችና የምዘና ማዕከላትን ማደራጀትና ሁሉም የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠናዎች ብቃት ባላቸው አሰልጣኞች እንዲከናወኑ መደረጉ ይገኙባቸዋል፡፡ በትብብር የሚካሄደው ስልጠና ተደራሽነትና ስልጠናውን በብቃት ያጠናቀቁ ሰልጣኞች ቁጥር እድገት አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም የኢንዱስትሪ የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች መመስረትና የአስፈላጊ ቴክኖሎጅዎች ሽግግር የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዝ ዘርፎች (MES) አቅም እንዲጎለብትና ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶችን ለመተካትና በገበያው ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቆየት በማለት እንዲንቀሳቀሱ አድርጓል፡፡

መንግሥት ትኩረት ካደረገባቸው ዘርፎች ጋር የጋራ የድርጊት መርሃ ግብር በመንደፍ ተገቢው የሰው ሃይል በማቅረብ ረገድ የታየው ውስንነት የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠናው በሃገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዳያደርግ ማነቆ ፈጥሯል፡፡ የአገልግሎት አሰጣጥ መስፈርትና (os)

የመለኪያ ስልት የማጎልበት ሂደቱ ይበልጥ መጠናከር የሚያሻው ሲሆን ከኢንዱስትሪዎች ጋር በመተባበርና ብቃት ያላቸው አሰልጣኞችን በመጠቀም የስልጠናው ተደራሽነት ከፍ ሊል ይገባል፡፡ የምርት ሂደት ሰንሰለቱን በመተንተን በገቢያው ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን ለማቅረብ ተፈላጊ የሆነው ቴክኖሎጂ መለየት ያስፈልጋል፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና የመረጃ አያያዝ ሲስተም እና የተሻሻለ የመረጃ አሰባሰብ ሂደት በትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ሲስተም በመታገዝ በመረጃ ላይ የተመረኮዘ እቅድ አነዳደፍ፣ አስተዳደርና አፈፃፀም እንዲኖር ያስችላል፡፡

ያሉትን ክፍተቶች ለመሙላትና የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት፣ ይህ የትኩረት ፕሮግራም በሶስት ተግባራት ላይ ያነጣጥራል፡፡ እነዚህም የሙያ ደረጃ መስፈርቶችና ምዘና፣ የሰልጣኞች ልማትና የተቋማዊ አቅም ግንባታ፣ እንደዚሁም የኢንዱስትሪ ግንኙነቶችና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራት ናቸው፡፡

**ተግባር 1፡- የሙያ ደረጃ መስፈርቶች ዝግጅትና ምዘና**

| ዓላማ፡- የሙያ ደረጃ መስፈርቶች ልማትና የምዘና ሂደት በኢንዱስትሪዎች ባለቤትነት እንዲመራ ማድረግ | በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ጠቅላላ (ወ/ሴ) | ግብ ጠቅላላ (ወ/ሴ) |
|---|---|---|
| የሰው ኃይላቸው በሙያ ደረጃ መስፈርቶች የተዋቀረባቸው የኢንዱስትሪ ዘርፎች መጠን (%) | 10 በመቶ | 60 በመቶ |
| ስልጠናቸውን አጠናቀው የሙያ ደረጃ ምዘና የወሰዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሰልጣኞች (መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ስልጠናን ጨምሮ) (%) | የለም* | 100 በመቶ (100/100) |
| ብቃት ያላቸው የኢንዱስትሪ ሰራተኞች ብዛት | 2 በመቶ | 35 በመቶ |

**እ.ኤ.አ በ2013/14 ዓ.ም 252,019 የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ምሩቃን ምዘናውን ወስደዋል፡፡*

የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ሂደቱ በሙያ ደረጃ መስፈርቶች የሚመራ ነዉ፡፡ መስፈርቶቹ በስልጠናው መስጠት ያለባቸውን የትምህርት ይዘቶችና በእያንዳንዱ ደረጃ ሊሟሉ የሚገባቸውን ብቃቶች ይወስናሉ፡፡ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠናና ትኩረት በተደረገባቸው ዘርፎች የጋራ ትብብር ሁለት መቶ አዳዲስ የሙያ ደረጃ መስፈርቶች ይዘጋጃሉ፡፡ ስልጠናቸውን ያጠናቀቁና ትኩረት በተሰጣቸው ዘርፎች የተሰማሩ በዝቅተኛና በመካከለኛ ደረጃ የሚገኙ ሰራተኞች በተከለሰው የሙያ ደረጃ መስፈርቶች የሚመዘኑና የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

### ንኡስ ተግባር 1፡ የዘርፎችን የባለቤትነት መንፈስ ማሳደግ

በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠናና በኢንዱስትሪ መካከል ያለው ትስስር እየተጠናከረ በመሄድ ላይ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ወቅት፣ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች የተወጣጡ ባለሙያዎች ከቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና አስተዳደሮች ጋር በጋራ በመስራት የገበያውን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ የሙያ ደረጃ መስፈርቶችን በማጎልበት ላይ ይገኛሉ፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ዘመን ኢንዱስትሪው በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ጠንካራ የአመራር ሚና እንዲኖረውና የሙያ ደረጃ መስፈርቶች ክለሳን ለመምራት ዘርፉ የሚያስፈልገውን የማስተካከያና የማጠናከሪያ እርምጃዎች እንዲወስድ ይደረጋል፡፡ እንደዚህ ያለው የትስስር መጎልበት የወደፊት ሰልጣኞችና ቀጣሪዎች በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ጠቀሜታ ላይ ያላቸው አመለካከትና ግንዛቤ የተስተካከለ እንዲሆን ይረዳል፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር መጨረሻ 60 በመቶ የሚሆኑ የኢንዱስትሪ ዘርፎች የየራሳቸውን የሙያ ደረጃ መስፈርቶች ሰነድ ያጎለብታሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ይህም በእነዚህ ዘርፎች የተሰማሩ ዝቅተኛና መካከለኛ ደረጃ ያላቸው ሰራተኞች የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶችን ያሟሉ እንዲሆኑ ያስችላል፡፡

ኢንዱስትሪ መር ወደሆነ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ዘዴ የሚደረገውን ሽግግር ለማፋጠን ትኩረት በተሰጣቸው ዘርፎች የሚገኙ ተቋማት የግንዛቤ ማዳበሪያ ስትራቴጂዎች ይተገበራሉ፡፡የግንዛቤ ማዳበር እንቅስቃሴው የሙያ ደረጃ መስፈርት እና የብቃት ማረጋገጫ መኖር በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናና ጥራትን ምን ያህል እንደሚያጎለብቱ በቂ መረጃ ይሰጣል፡፡ ትኩረት የተሰጣቸው

ዘርፎች ጥቅማቸውን የሚያስጠብቁላቸው ምክር ቤቶችን እንዲያቋቁሙ ይበረታታሉ፣ ምክር ቤቶቹ በተጨማሪ የሙያ ደረጃ መስፈርቶች አዘገጃጀትን እንደዚሁም የምዘናና የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ ሂደትን እንዲመሩ ይበረታታሉ፡፡ በተመሣሣይ፣ ምክር ቤቶቹ ለመንግስት የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና የትኩረት ዘርፉን በተመለከተ መረጃዎችን በተገቢው መልኩና በፍጥነት በማቀበል የመገናኛ መስመሮች ይሆናሉ፡፡

በስምንቱም የትኩረት ዘርፎች የቴክኒክ አማካሪ ቡድኖችና የቴክኒክ ባለሙያ ቡድኖች ይቋቋማሉ፡፡ እኒዚህ ቡድኖች የኢንዱስትሪ ባለሙያዎችን ከየስራ ቦታቸው በማሰባሰብ የሙያ ደረጃ መስፈርቶችን እንዲያዘጋጁና፣ በመስፈርቶቹ መሠረት የሥራ እንቅስቃሴዎችን በየእለቱ በመከታተል ጥራትን እንዲያረጋግጡ እነዚህ ቡድኖች የኢንዱስትሪዎችን የባለቤትነት መንፈስ እንዲያጐለብቱና፣ በመስፈርቶችና በሚሰጡ ስልጠናዎች እንዲሁም ምዘናዎች መካከል ያለው ትስስር እንዲጠናከር ያደርጋሉ፡፡

**ንኡስ ተግባር 2፡- ተደራሽ የሆነ ፣ ጥራት ያለው ምዘናና የማረጋገጥ አገልግሎት አሰጣጥን በመፍጠር የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥን ማሻሻል**

አዲስ የሙያ ደረጃ መስፈርት ሲዘጋጅ በገበያው ውስጥ የሚታየውን የቴክኖሎጂ ለውጥ ግምት ውስጥ ያስገቡ 293 አዳዲስ የምዘና መሳሪያዎችና በአሁኑ ወቅት ያሉት የምዘና መሳሪያዎች በመደበኛነት የሚሻሻሉበት አሰራር ይፈጠራል፡፡ ሁሉም የምዘና መሳሪያዎች የልዩ ትምህርት ፍላጎት ስልጣኞችን ባማከለ መልኩ ይዘጋጃሉ፡፡ የቴክኒክ አማካሪ ቡድኖቹና የቴክኒክ ባለሙያ ቡድኖቹ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርት ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር የምዘና ሂደቶችና የምዘና ውጤቶች ትኩረት የተሰጣቸው ዘርፎችን ፍላጎት በተገቢው መንገድ የሚያነጻባርቁና፣ የየዘርፎቹ ተገቢነት፣ አቅምና፣ በአመራሩ ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነት የሚያጠናክሩ ይሆናሉ፡፡

ምዘናውን የሚያከናውኑ የምዘና ባለሙያዎች ቁጥር ከ55,000 በላይ የሚደርስ ሲሆን፣ ይህም የመዛኞች የብቃት ማረጋገጫ የእውቅና መስፈርትን የተከተለና፣ ለምዘና የሚቀመጡ የተፈታኞችን ቁጥር ግምት

ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ ይህን ሂደት ከምዘና ማእከላት ጋር በማገናኘት የምዘናዎቹ ጥራት በሙያ ደረጃ መስፈርቶች ከተቀመጠው ጋር የተዛመደ መሆኑን የማረጋገጥ ስራ ይከናወናል፡፡ በተጨማሪም፣ ሁሉም የምዘና ባለሙያዎች (ነባሮቹም ሆኑ አዲሶቹ) የብቃት ምዘና እንዲወስዱና ዳግም ብቃታቸውን የሚያረጋግጥ የእውቅና ማስረጃ እንዲያገኙ በማድረግ የምዘና ባለሙያዎቹ አቅም የሙያ ደረጃ መስፈርቱ በሚያዘው መሰረት የደረሰ መሆኑን የማረጋገጥ ሂደት ይከናወናል፡፡ በዚህ ሂደት የአቅም ውስንነት ለሚታይባቸው የምዘና ባለሙያዎች በብሄራዊ የምዘና ባለሙያዎች የአቅም ልማት ማእከል አማካኝነት የማጎልበቻና የማሻሻያ ድጋፎች እንዲያገኙ በማድረግ በተከታታይ የስራ አፈጻጸም ግምገማ አማካኝነት ምዘናውን ደግመው እንዲወስዱና እንደገና የእውቅና ፈቃድ እንዲያገኙ ጥረት ይደረጋል፡፡ በኢንዱስትሪ የሚገኙ ሴት ባለሙያዎች ወደ የምዘና ባለሙያ ደረጃ እንዲያድጉ ቅድሚያ የሚሰጣቸውና ተመራጭነት የሚኖራቸው ይሆናል፡፡

የብቃት ማረጋገጫ ማእከላቱ የእውቅና ማረጋገጫ የሚያገኙት በኢትዮጵያ የደረጃ እውቅና መስጫ ቢሮ አማካኝነት ይሆናል፡፡ በዘርፉ ለንጽጽር ከተመረጡት ሃገራት ጋር በተደረሰው የትብብር ማዕቀፍ መሰረት አምስት የብቃት ማረጋገጫ ማእከላት አለማቀፋዊ የብቃት ማረጋገጫ የእውቅና ማስረጃ እንዲያገኙ ዝግጅት ይደረጋል፡፡ አለማቀፋዊ የብቃት ማረጋገጫ የእውቅና ማስረጃ የማግኘት እንቅስቃሴው የምዘና ሂደቶቹ ይበልጥ ውጤታማ የሆነ የሰው ሃይል ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት እንደሚያጠናክሩ ተጨማሪ ማስረጃ ይሆናል፡፡

ጥራት ያለው ምዘና በመጠቀም በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና የሚገኙ ብቃቶችን የማረጋገጥ ስራ ይከናወናል፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር መጨረሻ የምዘና ማእከላት ቁጥር ወደ 27,000 ከፍ እንዲል የሚደረግ ሲሆን በየወረዳው የሚገኙ ሰልጣኞች (ተጠቃሚ ያልሆኑ አካባቢዎች ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ) የምዘና ማእከላቱ ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ በተመሣሣይ በሁሉም ክፍለ ከተሞች ወይም ዞኖች የብቃት ማረጋገጫ ማእከላትን ቁጥር በማሳደግ እንቅስቃሴውን የመደገፍ ስራ ይከናወናል፡፡ የምዘና ማእከላትንና የብቃት ማረጋገጫ ማእከላትን በማስፋፋቱ ሂደት የልዩ ትምህርት ፍላጎት ለሚያስፈልጋቸው ሰልጣኞች ትምህርቱን ለማዳረስ የሚያስችሉ ልዩ የአገልግሎት

መስጫ ማእከላትን የማቋቋምና የማሻሻል ስራዎች ይካተታሉ፡፡ በሚካሄደው የምዘና ሂደት ሰልጣኞች ያሉባቸው የክህሎት ክፍተቶች ተቋማት፣ ኮሚሽኑና፣ ቢሮዎች እንዲያውቋቸው በማድረግ፣ በስልጠና ቁሳቁስና በስልጠና ዘዴዎች የሚፈለገውን ማሻሻያ እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡

| ስትራተጂዎች | አመልካች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| በኢንዱስትሪዎች ውስጥ ያለውን የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠናን በባለቤትነት የመያዝ አመለካከት ማሳደግና የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ከተቋም ተኮር ወደ ኢንዱስትሪ ተኮር እንዲሸጋገር ማስቻል | አዲስ የተቀረፁ የሙያ ደረጃ መስፈርቶች ቁጥር ከ650 ወደ 850 ከፍ ይላል፡፡ | የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ |
| | የሙያ ደረጃ መስፈርቶችን በመጠቀም የሰው ሀብት ልማታቸውን የሚያሳድጉ የኢንዱስትሪ ዘርፎች ብዛት ከ10 በመቶ ወደ 60 በመቶ ያድጋል፡፡ | የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ |
| በኢንዱስትሪዎች የሙያ ደረጃ መስፈርቶችን እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና የብቃት ማረጋገጫ መዋቅሮችን የመጠቀም ሂደት ማሳደግ | | |
| ትኩረት በተሰጣቸው ስምንቱም የሙያ መስኮች የቴክኒክና አማካሪ ቡድኖችንና የቴክኒክ ባለሙያ ቡድኖችን ማዋቀር | | |
| ትኩረት በተሰጣቸው መስኮች የብቃት ካውንስሎችን ማቋቋም | | |
| ከኢንዱስትሪው ጋር በመተባበር ከገበያው የሰው ኀይል ፍላጎት ለውጥ ጋር በተጣጣመ መልኩ የሙያ ደረጃ መስፈርቶችን ማዘጋጀትና ማሻሻል | | |
| መስፈርችን በማዘጋጀት/ የሙያ ምዘና በማካሄድ የብቃት ክፍተቶችን መለየትና ተገቢ ምላሽ መስጠት | | |
| የንግድ ግብርናና ዕደ ጥበባት ምክር ቤቶችን ማቋቋም | | |
| የምዘና ማዕከላትን አደረጃጀት ከክልሎች ወደ ዞን / ክፍለ ከተማና ወረዳ/ ቀበሌ ደረጃዎች ማስፋፋት | አዲስ ዕውቅና የተሰጣቸው የምዘና ማዕከላት ቁጥር ከ 3,816 ወደ 27,812 ያድጋል፡፡ | የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርት |

| | | |
|---|---|---|
| | | ስልጠና ኤጀንሲ |
| | ስልጠናቸውን አጠናቀው የብቃት ምዘና የወሰዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጣኞች (መደበኛና መደበኛ ያልሆኑትን ጨምሮ) ቁጥር 100 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ |
| | ብቃት ያላቸው የኢንዱስትሪ ሰራተኞች ቁጥር ከ2 በመቶ ወደ 35 በመቶ ያድጋል፡፡ | የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ |
| በኢንዱስትሪ ውስጥ የምዘና ማዕከላትን ተደራሽነት ማስፋት | | |
| ከተቋቋሙት የቴክኒክ አማካሪ ቡድኖችና የቴክኒክ ኤክስፐርቶች ቡድን ጋር በጋራ የምዘና መሳሪያዎችን ማጎልበትና ማሻሻል | | |
| በሁሉም የሙያ ዘርፎች ምዘና የተሰጣቸው በኢንዱስትሪዎች ውስጥ ልምምድ የሚያደርጉ ሰልጣኞችን ቁጥር ማሳደግ | | |
| የምዘና ባለሙያዎችን ጥራት በማሻሻል እና ስትራቴጂ በመንደፍ በከፍተኛ ደረጃ የሴቶችን ተሳትፎ ማጎልበት | | |
| የምዘናና ብቃት ማረጋገጥ ሂደቱ አለም አቀፋዊ ዕውቅና እንዲኖረው ማድረግ | | |
| ምዘናዎችን በማካሄድ በኢንዱስትሪዎች ውስጥ ልምምድ የሚያደርጉ በዝቅተኛና መካከለኛ ደረጃ ያለውን የሰው ኃይል የሙያ ብቃት ማረጋገጥ | | |
| የልዩ ትምህርት ፍላጎት ለሚሹ ሰልጣኞች የሚያገለግሉ የምዘና ማዕከላትንና መሳሪያዎችን ማደራጀት | | |
| የሙያ ደረጃ መስፈርቶችን አጠቃቀምና የምዘና ሂደቶችን አተገባበር በተመለከተ ምርምሮችን ማካሄድ | | |

**ተግባር 2፡- የሰልጣኞች ልማትና ተቋማዊ የአቅም ግንባታ**

| ዓላማ፡- የኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነትና ምርታማነት የሚያጎለብት በዝቅተኛና መካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ ብቁ የሰው ኃይል መፍጠር | አራተኛ የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ጠቅላላ (ወ/ሴ) | ግብ ጠቅላላ (ወ/ሴ) |
|---|---|---|
| በመደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና የቅበላ አቅም (ከ1-5 ባሉት ደረጃዎች) | 265,745<br>(135,530/130,215) | 564,054<br>(282,027/282,027) |
| የአጭር ጊዜ ስልጠና ወስደው ያጠናቀቁ ሰልጣኞች ቁጥር | 876,097 | 1,470,663 |
| ስልጠናቸውን ካጠናቀቁ ሰልጣኞች መካከል በምዘና ብቁ ብቃታቸው የተረጋገጠ (%) | 60 በመቶ | 75 በመቶ(75/75) |
| መደበኛውን የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ያጠናቀቁ ሰልጣኞች ስራ የማግኘት መጠን | 60 በመቶ | 90 በመቶ |
| አለማቀፍ የእውቅና ማረጋገጫ ያገኙ የእደ ጥበብ ሙያተኞች ቁጥር | 38 | 4000 |

**ንኡስ ተግባር 1፡- አቅማቸው የጎለበተ የኢንዱስትና የተቋማት አሰልጣኞች፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና አመራሮችና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች**

የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና በአምስት ደረጃዎች ተከፋፍሎ ( ከአንድ እስከ አምስት ያሉት ደረጃዎች አሉት፣ የስልጠና ላይ ቆይታው ከአንድ እስከ ሦስት አመት የሚፈጅ ሆኖ ከፍተኛው ደረጃ አምስተኛው ነው) በሁሉም ደረጃዎች(ደረጃ ሲ፣ ደረጃ ቢ እና ደረጃ ኤ በተሰኙ የክህሎት ደረጃቸው ከፍ እያለ የሚሄድ) ብቃት ባላቸው አሰልጣኞች ታግዞ በመሰጠት ላይ ይገኛል፡፡ዘርፉ እየተስፋፋ ሲሄድ የሚከሰተውን የሰልጣኞች ቅበላ አቅም ማደግን ታሳቢ ያደረገ ቀጣይነት ያለው የአሰልጣኞች ቅጥር ማከናወን አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም፣ የአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ትንተና እንደሚያመላክተው በአሁኑ ጊዜ ያለው የአሰልጣኞች ምደባ ፍላጎትን ያገናዘበ አይደለም፡፡ በተለይ በደረጃ ቢ እና በኢንዱስትሪው በሁሉም ደረጃዎች ከፍተኛ የአሰልጣኞች እጥረት ይስተዋላል፡፡

አሰልጣኞች ከኢንዱስትሪዎች እና ከቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት በቀጥታ እንዲመለመሉ ይደረጋል፡፡ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ሰልጣኞች ወደአሰልጣኝነት ደረጃ  በማሳደግ የስልጠና ስርአቱ ከወቅቱ ጋር የሚሄዱ ክህሎቶችን ማዳበር የሚያስችል እንዲሆን ያግዛል፡፡ የደረጃ ሲ ተቋማት አሰልጣኞች ከደረጃ አራትና ከዛ በላይ ስልጠና ከወሰዱ፣  በስነ ምግባርና በቴክኒክ ብቃታቸው ተወዳዳሪ ከሆኑና አሰልጣኝ ለመሆን የሚያስፈልገውን የሙያ ማዳበርያ ፕሮግራም ለማጠናቀቅ ፍላጎቱ ካላቸው ሰልጣኞች የሚመለመሉ ይሆናሉ፡፡ የደረጃ ሲ አሰልጣኞችን የመቅጠር ሂደት ለሴት አመልካቾች ቅድሚያ በመስጠት የሴት አሰልጣኞችን ድርሻ ወደ 32 በመቶ ለማድረስ ያለመ ይሆናል፡፡ የስልጠና ፍላጎትን መሰረት በማድረግ እንደአስፈላጊነቱ የአሰልጣኞችን ደረጃ የማጎልበት፣ ማለትም ከደረጃ ሲ ወደ ደረጃ ቢ፣ ከደረጃ ቢ ወደ ደረጃ ኤ የመሸጋገር እንቅስቃሴ ይደረጋል፡፡ ይህ ስልጠና በነባር የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ማሰልጠኛ ተቋማትና በተመረጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጆች በሚከፈቱ ተጨማሪ የሳተላይት ተቋማት ይሰጣል፡፡ የአስልጣኞች የደረጃ ማሻሻያ ስትራቴጂው ያለውን ፍላጎት በበቂ ማሟላት የማይችል ከሆነ፣ የደረጃ ቢ እና የደረጃ ኤ አሰልጣኞች ቅጥር በቀጥታ በገበያው ላይ ከሚገኘው የሰለጠነ የሰው ኃይል ሊፈፀም ይችላል፡፡

ስልጠናዎችን በትብብር ወይም በጋራ መስጠት የሚችሉና እንደ ምዘና ባለሙያዎች ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉ የኢንዱስትሪ አሰልጣኞችን በኢንዱስትሪ ልምምድ በማድረግ ላይ ከሚገኙ ሰልጣኞች መካከል ብቃታቸውን በተሻሻለው የሙያ ደረጃ መስፈርት አንፃር በመለካትና በብቃት ማዕከላት አማካኝነት የምዘና ዘዴዎችን የተመለከቱ ኮርሶችን በመስጠት መቅጠር ይቻላል፡፡ አሰልጣኞች በሚመዘኑበት ወቅት የሚስተዋሉ የብቃት ክፍተቶችን ለሚመለከታቸው ቀጣሪዎች ወይም ለቴክኒክና ሙያ ትምህርት ማሰልጠኛ ተቋማት በማሳወቅ የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ይደረጋል፡፡

ነባር ተቋማትና የኢንዱስትሪ አሰልጣኞች የአቅም ልማት ፕሮግራሞች በተለይም ቴክኖሎጂን ከማስተዋወቅ ጋር የተገናኙ ክህሎቶችን የሚያጎለብቱባቸው ድጋፎች ይደረጉላቸዋል፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ዘርፉ ለቴክኖሎጂ ሽግግሩ ዋና ድልድይ በመሆን ተጠናክሮ እንዲቀጥል በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም መጨረሻ ሁሉም ነባር የቴክኒክና ሙያ ትምህርት

አሰልጣኞች ስልጠና እንዲሰጣቸው በማድረግ ቴክኖሎጂን የማጎልበት ብቃታቸው 100% መድረሱ በግምገማ ይረጋገጣል፡፡ የፌደራሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ የምርምር ስትራቴጂ በማዘጋጀት በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ዘርፉና በገበያው ውስጥ ባለው የሰው ኃይል አቅርቦት ፍላጎት መካከል ስለሚታየው ትስስር ግንዛቤ እንዲዳብር ያደርጋል፡፡ የምርምር ስትራቴጂው ትኩረት ከሚያደርግባቸው ጉዳዮች መካከል ፤ የሙያ ደረጃ መስፈርት ምርምር፣ ምዘና፣ ስርዓተ- ትምህርት ቀረፃ፣ የጥራት ክትትል፣ የተቀናጀ ስልጠና፣ የምሩቃን ክትትልና የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ይገኙባቸዋል፡፡ ይህን መሰል ጥናቶች የሀገሪቱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና እንዲሻሻልና ይበልጥ እንዲጎለብት አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም የትግበራ ዘመን የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና አመራሮች በዘርፉ ውስጥ ከሚገኙ ዕጩዎች ወይም ሰልጣኞች መካከል እንዲመለመሉ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ ይህ ዘዴ ለውጡ ቀጣይነት ያለው እንዲሆን እገዛ ያደርጋል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ፣ የማሻሻያ ፕሮግራሙ በሙሉ በተግባር ላይ ሲውል በአሁኑ ወቅት 2% ብቻ የሆነውን የሴቶች የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና አመራር ድርሻ የሚያሳድግና ለሴቶች ተሳትፎ መጎልበት ቅድሚያ የሚሰጥ በመሆኑ ነው፡፡ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ የሴት አመራሮች ድርሻ ወደ 12% እንደሚያድግ ይጠበቃል፡፡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና አስተዳደሮችና የአመራር ሰራተኞች እንዲሁም የፌደራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ፣ የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ቢሮዎች፣ ኮሚሽኖች፣ ባለሙያዎች፣ የብቃት ማዕከላትና የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት በዘመናዊ የአስተዳደር ስልቶች ላይ ያተኮሩ የስራ ላይ የስልጠና መርሃ ግብሮች እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ እነዚህ የአጭር ጊዜና የረጅም ጊዜ የስልጠና ሂደቶች በድምሩ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት ያለውን አጠቃላይ የሰው ኃይል አስተዳደርና አመራር ሂደት የሚያሻሽሉ እንደሚሆኑ ይታመናል፡፡

**ንኡስ ተግባር 2፡- የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማትን በወረዳዎች በማስፋፋት ተደራሽነታቸውን ማሳደግ**

በአጠቃላይ ካሉት 1,348 የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት መካከል በአሁኑ ወቅት እስከ ደረጃ አምስት ስልጠና ለመስጠት የሚችሉት 334 የህዝብ እና 282 የግል ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ የአገልግሎት ማዕከላት ብቻ ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ 732 (325 የህዝብና 407 የግል) ተቋማት የአጭር ጊዜ ስልጠናዎችን ወይም እስከ ደረጃ ሁለት ያለውን መደበኛ ስልጠና የሚሰጡ ናቸው፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር መጨረሻ ዘመን እስከ ደረጃ አምስት ያሉትን ኮርሶች መስጠት የሚችሉ የህዝብ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ማሰልጠኛ ተቋማት እስከ አሁን ድረስ ባልተቋቋሙባቸው 462 ወረዳዎች ይመሰረታሉ፡፡ የማስፋፋት ሂደቱ ተቋማቱን የማጎልበትና አዳዲስ ተቋማትን የመገንባት እንቅስቃሴን ያካተተ ሆኖ ፣ ከእውቅና አሰጣጥ መመሪያው ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ በጥንቃቄ በተነደፈ ስትራቴጂ የሚመራና በታዳጊ ክልሎች ለሚካሄደው የልማት እንቅስቃሴ ቅድሚያ በመስጠት ተለይተው በታወቁ የልማት ኮሪደሮች ላይ ያተኮረ ይሆናል፡፡ በእያንዳንዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ማእከል የሚሰጠው ሥልጠና የአካባቢውን ማህበረሰብ ፍላጎት ያማከለ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይም የግል ተቋማት የቅበላ አቅም 20 በመቶ እንደሚደርስ ይጠበቃል፡፡

አዲስ የተገነባ ወይም ማሻሻያ የተደረገለት እያንዳንዱ ማዕከል ለአሰልጣኞችና ሰልጣኞች አስተማማኝና ጤናማ የሆነ የትምህርት አካባቢን የሚፈጥር ሆኖ ከትኩረት ዘርፎቹ በሚገኘው ግብዓትና ጥቆማ በመታገዝ ጥራቱም የተረጋገጠ ይሆናል፡፡ ለልዩ ትምህርት ፍላጎት ስልጠና መስፈርቶች የሚዘጋጁና በእያንዳንዱ ተቋም የሚተገበሩ ይሆናል፡፡ መስፈርቶቹም የአገልግሎት ተቋማትንና የመርጃ ማዕከላትን የማሻሻልና በአይነታቸው ልዩ የሆኑ ማቴሪያሎችን በጋራ በተገቢው መንገድ መጠቀም የሚያስችሉ ሆነው ይቀረፃሉ፡፡ ሂደቱ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሰልጣኞችን በሚያማክሉ  የመመሪያ ማሻሻያዎች ይደገፋል፡፡ በተቻለ መጠን የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት ዲዛይንና ግንባታ በተቻለ መጠን ዝቅተኛ የካርቦን መጠን ባላቸውና የኃይል ፍጆታቸውና አጠቃቀማቸው ዝቅተኛና ውጤታማ በሆኑ ዘዴዎችና ቁሳቁሶች በመታገዝ ለአካባቢ ጥበቃ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ይሆናሉ፡፡

በሁሉም ተቋማት በቂ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት፣ ፆታን ያማከለ የንፅህና መጠበቂያ አገልግሎት፣ የተማሪ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስችሉ ራሳቸውን የቻሉ የተለዩ ቦታዎች፣ የተማሪዎችን ጤና የኤች አይ ቪ ኤድስና የአባላዘር በሽታዎች ግንዛቤ የሚያጎለብቱ ማዕከላትን ጨምሮ እንዲቋቋሙ ይደረጋል፡፡ ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች (cross-cutting issues) የማስተባበሪያ ዩኒት በፌደራልና በክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲዎች ከቁልፍ ባለሙያ ጋር ይዋቀራል፡፡ ምንም እንኳ ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮችን መከታተል የጋራ ኃላፊነት ቢሆንም፣ ይህን መሰሉ አደረጃጀት በየደረጃው የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች፣ የመረጃ ልውውጥና የግኑኙነት ሂደቶች ሙሉ ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡

ሁሉንም የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማትና የኢንዱስትሪ የስራ ላይ ስልጠና ስፍራዎችን ብቃት የማረጋገጥ ስራ ይከናወናል፡፡ በመጀመሪያ፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ የጥራት መስፈርቶች ዕውቅና እንዲያገኙ በማድረግ፣ በማስከተልም በአራት ተቋማት የዓለም አቀፍ የጥራት ማረጋገጫ ተቋም ዕውቅና እንዲያገኙ ከተደረገ በኋላ ሁሉም የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና የፖሊ ቴክኒክ ተቋማት የዓለም አቀፍ የደረጃ መስፈርት ለማሟላት የሚያስችላቸውን ዝግጅት ያጠናቅቃሉ፡፡ ድግግሞሽ ያለበት የቴክኖሎጂ መስፋፋትን ለመቆጣጠርና የቴክኖሎጂ ማበልፀግያ የልህቀት ማዕከላት የሚቋቋሙበት መመርያ በማውጣት የቴክኖሎጂ ተቋማት ምርምር ልማትና ፈጠራ የሚያደርጉበት ሁኔታ ይጠናል፡፡

**ንኡስ ተግባር 3፡-ብቃት ያላቸው የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ምሩቃንን ማፍራት**

የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት ዋና ተግባር ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን በአግባቡ የሰለጠነና ብቃት ያለው የሰራተኛ ኃይል ማሟላት ነው፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ስትራቴጂ የተጀመረውን የሲስተም ለውጥ ለጥራት መጎልበት ትኩረት በሚሰጥ አዲስ መነቃቃት ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ ነው፡፡ ውጤት ተኮር የሆነና ለሁለተኛው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትኩረት ዘርፎች ፍላጎት ምላሽ የሚሰጥ የስልጠና ሂደት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

ሰልጣኞች ገበያ-መር የሆነ ስልጠና ማግኘት እንዲችሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማትን እንዲቀላቀሉ ይደረጋል። ሁለት ዓይነት የስልጠና አሰጣጥ ሂደቶች ይኖራሉ፤እነርሱም መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ስልጠና ናቸው። ስልጠናዎቹ ሲጠናቀቁ (በመደበኛም ይሁን መደበኛ ባልሆነው) ሰልጣኞች በሙያ ደረጃ መስፈርቶች የተገለፁትን ብቃቶች ማዳበራቸውን ለማረጋገጥ ምዘና ይሰጣል።

መደበኛ ስልጠናው በአጠቃላይ ትምህርት አስረኛ ክፍልን በሚያጠናቅቁ ተማሪዎች ላይ ያተኩራል። መደበኛ ፕሮግራሞቹ በአምስት ደረጃዎች የሚሰጡ ሆነው የተማሪዎች ቅበላው በአጠቃላይ ትምህርት የማጠቃለያ ፈተና ውጤት ላይ የተመሰረተ ይሆናል። በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር መጨረሻ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ዘርፍ በዚህ መሰሉ የመደበኛ ስልጠና የሚሳተፉ 564,054 ሰልጣኞች ይኖሩታል።

የስልጠና ሞጅዩሎቹ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማት የሚሰጥ መሰረታዊ ስልጠናና በሥራ ቦታ የሚሰጡ ስልጠናዎችን የሚያካትቱ ይሆናሉ። ይህ የተቋማትና የኢንዱስትሪ ተኮር ስልጠና ቅንጅት የትምህርት ጥራትና የተማሪዎች ክህሎቶችን የማዳበር ሂደት እንዲጎለብት ያደርጋል። ይህንን ስልት በመከተል በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር መጨረሻ ስልጠናውን የሚያጠናቅቁ ሰልጣኞች ብቃት ወደ 75 በመቶ የሚያድግ ሲሆን፣ የተመራቂዎች ስራ የማግኘት ዕድል ከ60 በመቶ ወደ 90 በመቶ ከፍ ይላል። በሁሉም የስልጠና ዘርፎች (ገበያ ተኮር በሆኑ ሙያዎች ተሳትፎ፣ በምዘና ውጤቶች፣ በመቀጠር አቅም) የሴቶች ድርሻ 50 በመቶ ይሆናል። በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ፍትሃዊ የሆነ የቅበላ አቅምን ለመፍጠር ተደራሽ ካልሆኑ አካባቢዎችና ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች የሚመጡ ተማሪዎች ከቦታ ቦታ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት ወጪ ስለሚኖርባቸው የተለየ የድጋፍ ስትራቴጂ ይዘጋጃል። ድጋፉም የቁሳቁስ አቅርቦትን፣ የመመገቢያ፣ የመኖሪያና ሌሎች መደበኛ ያልሆኑ ተመሳሳይ ድጋፎችን ሊያካትት ይችላሉ።

መደበኛ ያልሆኑ የአጫጭር ጊዜ ስልጠናዎች፣ ተጠቃሚዎችን የመለየት ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚተገበሩ ናቸው። ተጠቃሚዎቹ የቱንም ያህል አመታት ትምህርት የተከታተሉ ሊሆኑ ቢችሉም ስራ ለማግኘት የግድ አዳዲስ ክህሎቶችን ማጎልበት የሚያስፈልጋቸው መሆን አለባቸው። ለእነዚህ መሰል

ዜጋዎች የአጭር ጊዜ ስልጠና የሚሰጥ ሲሆን በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት አምስት የትግበራ አመታት ቁጥራቸው 1,470,663 ለሚደርሱ ሰልጣኞች እድሉን ለማዳረስ ታቅዷል፡፡ በኩባንያዎች የሚሰጥ ስልጠና መደበኛ ያልሆነ ስልጠና የሚታይ ሲሆን የሰራተኞችን ምርታማነት እና የኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነትና የምርትና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ለማጎልበት የሚያስችል ስልጠና ነው፡፡ ስልጠናው በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አስፈላጊ ክህሎቶችና ደረጃዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ሊሆን ይችላል፡፡

**ንኡስ ተግባር 4፡- የማኑፋክቸሪንግ ምርታማነትና ጥራት ለማሳደግ የብረታ ብረት ስራ አቅምን መገንባት**

በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ዘርፍ ከፍተኛ የኢንጅነሪንግ ክህሎት ስልጠና ለመስጠት የኢንጂነሪንግ የልህቀት ማዕከል ተቋቁሞ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር የትግበራ ዘመን፣ ነባሩ የኢንጅነሪንግ የልህቀት ማዕከል እንዲስፋፋና መሳሪያዎች እንዲሟሉለት የሚደረግ ሲሆን ተጨማሪ የብረታ ብረት ስራ ማዕከላት በአምስት የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት እንዲመሰረቱ ይደረጋል፡፡ እነዚህ ማዕከላት ሰልጣኞች ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የብረታ ብረት ስራ ክህሎት እንዲያዳብሩ የሚያስችሉ ስልጠናዎችን ይሰጣሉ፡፡ በሀገሪቱ በመስፋፋት ላይ የሚገኘው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚያስፈልገው ብቃት ያለው የሰው ኃይል አቅርቦት እንዲኖር ለማስቻል መሰረት ይጥላል፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር መጨረሻ እነዚህ ማዕከላት በአለም አቀፍ ደረጃ የምስክር ወረቀት ያላቸው የብረታ ብረት ሙያ ማስተሮች (አሰልጣኞች)፣ 4,000 አለም አቀፍ የምስክር ወረቀት ያላቸው የብረታ ብረት ባለሙያዎችና 4 አለም አቀፍ የምስክር ወረቀት ያላቸው የብረታ ብረት ሙያ ኢንጂነሮች እንዲያፈሩ ይጠበቃል፡፡ በብረታ ብረት ሥራ የሚደረገው ትኩረት በዚሁ የሚሰማሩ ኢንዱስትሪዎችን ውጤታማነት ይጨምራል፡፡ የልህቀት ማዕከሉ በዲዛይን፣ በናሙና ማጎልበትና ፍተሻ በተለይም ትራክተሮችን በአገር ውስጥ የማምረትን እንቅስቃሴ ያጠናክራል፡፡ በተጨማሪም፣ በመካከለኛ ደረጃ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች በአሰልጣኝ ባለሙያዎች በመታገዝ ምርታማነታቸውን እንዲያሳድጉና በአጠቃላይም የቴክኖሎጂ ናሙናዎችን የማጎልበትና የማሻሻል አቅም እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡

| ስትራተጂዎች | አመልካች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
| --- | --- | --- |
| አቅማቸው የጎለበተ የኢንዱስትሪና የተቋማት አሰልጣኞች፤ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ዘርፍ አመራሮችና የድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች እንዲኖሩ ማድረግ | ቴክኖሎጂን የማላመድ አቅማቸው 100 በመቶ የደረሰ ነባር የደረጃ ኤ፤ ቢ እና ሲ አሰልጣኞች ቁጥር 17382 ይሆናል። | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | የሴት አሰልጣኞች ቁጥር ከ 17 በመቶ ወደ 32 በመቶ ከፍ ይላል | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | የደረጃ ኤ፤ ቢ እና ሲ አሰልጣኞች ቁጥር 4,637፤ 16,271 እና 55,666 (እንደቅደም ተከተላቸው) ይደርሳል | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | የጋራ ስልጠናዎችን ለማካሄድ ፈቃድ የሚያገኙ የኢንዱስትሪ የስራ ቦታዎች ከ55,778 ወደ 108,668 ከፍ ይላል | የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ |
| በመንግስትና በግል የደረጃ ኤ፤ ቢ እና ሲ የተቋማትና የኢንዱስትሪ አሰልጣኞችን ማፍራት | | |
| ልምድ ባላቸው የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የአመራር ሃይል ክምችትን በመፍጠር የቴክኒክና ሙያ ትምህርት የአመራር ሃይልን አቅም ማጎልበት | | |
| ለታዳጊ ክልሎች የተለየ ድጋፍ ማድረግ | | |
| በፌደራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ፣ በክልልና በዞን የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ቢሮዎች እንደዚሁም በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማትና በብቃት ማዕከላት የሴት አመራሮችን ድርሻ ማሳደግ | | |
| ብቃት ያላቸው ኤክስፐርቶችን በመምረጥ በስልጠና ዘዴና በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ስትራቴጂ ዙሪያ እንዲያገኙ ማድረግ | | |
| በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማትና እና በገበያው ያለው የሰው ሃይል ፍላጎት ተዛምዶ ፍተሻ ለማድረግ የምርምር ስትራቴጂ ማዘጋጀት | | |
| የኢንዱስትሪና የተቋም አሰልጣኞች በተለይም ቴክኖሎጂን በማላመድን የአቅም ልማት መርሃግብር እንዲያገኙ ማድረግ | | |
| የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማትን ትስስር በማጎልበት ጥራት ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተደራሽነትን በሁሉም ወረዳዎች ማረጋገጥ | እስከ ደረጃ አራት ድረስ ስልጠና መስጠት እንዲችሉ የማስፋፋት ስራ የሚከናወንባቸው ተቋማት ቁጥር ከ334 ወደ 796 ከፍ ይላል | የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ |
| | የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት አጠቃላይ ቁጥር ከ1,023 ወደ 1,485 ከፍ ይላል | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ሲስተም |
| የእድገት ኮሪደሮችን በመጠቀም የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማትን ማስፋፋት፤ መገንባትና ግብአታቸውን ማሟላት | | |
| አለማቀፍ መስፈርትን መሠረት በማድረግ ለተቋማት ከአንድ እስከ አምስት ደረጃ በመስጠት አለማቀፍ የብረታ ብረት ስራ ማእከላት እንዲሆኑ ግብአቶችን ማሟላት | | |
| የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማትን ሁሉም ክልሎች ለማስፋፋት በሚደረገው እንቅስቃሴ የግሉ ዘርፍና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተሳትፎአቸውን እንዲያጠናክሩ ማድረግ | | |

| | | |
|---|---|---|
| ለልዩ ትምህርት ፍላጎት ስልጠና አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶችን ማዘጋጀት (ለምሳሌ፣ የአገልግሎት ተቋማትንና የመርጃ ማዕከላትን ማሻሻልና በአይነታቸው ልዩ የሆኑ ማቴሪያሎችን በጋራ በተገቢው መንገድ መጠቀም መቻል) | | |
| የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች፤ እንደዚሁም መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች የጋራ ስልጠናዎችን ለመስጠት የሚያስችላቸውን እውቅና እንዲያገኙ ማድረግ | | |
| የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች (የሳተላይት የቴክኒክ ተቋማት) የአሰልጣኞች ስልጠናን መስጠት እንዲችሉ አቅማቸውን ማሳደግ | | |
| ሁሉም የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማት በሃገር አቀፍ ደረጃ እውቅና እንዲኖራቸው ማድረግ | | |
| የኤች አይ ቪ/ ኤድስንና የአባላዘር በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን መፍጠር | | |
| ለአደጋ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ትምህርት ለመስጠት የሚያስችል አመቺ የሆነ የስልጠና ከባቢን መፍጠር | | |
| በሁሉም የፌደራልና የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲዎች ትኩረት ለተሰጣቸው ጉዳዮች(cross cutting issues) ማስተባበሪያ ዩኒቶችን ማቋቋም | | |
| ብሄራዊ የቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት ለመገንባት ያለውን የአቅም ዝግጁነት መገምገምና ስትራቴጂ ማዘጋጀት | | |
| የገበያውን ፍላጎት ለማሟላት የመደበኛና የአጭር ጊዜ ኮርስ ስልጠና የወሰዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ምሩቃንን ማፍራት | በመደበኛ ስልጠና የሚሳተፉ ሰልጣኞች ቁጥር ከ 265,745 ወደ 564,054 ያድጋል (ከዚህም ውስጥ 50 በመቶ ሴቶች ይሆናሉ) | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | የአጭር ጊዜ ኮርስ ስልጠና የወሰዱ ሰልጣኞች ቁጥር (በትግበራ ዘመኑ አምስት አመታት ጊዜ) ከ 876,097 ወደ 1,470,663 ያድጋል | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | የልዩ ፍላጎት ትምህርት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሰልጣኞች ቁጥር ከ 1,003 ወደ 3,060 ከፍ ይላል | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | ስልጠናውን በብቃት የሚያጠናቅቁ ሰልጣኞች መጠን ከ 60 በመቶ ወደ 75 በመቶ ያድጋል | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ሲስተም |
| | ስልጠናውን ያጠናቀቁ ምሩቃን ስራ የመቀጠር መጠን ከ 60 በመቶ ወደ 90 በመቶ ያድጋል | የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ |
| ጥራት ያለው የጋራ/ የህብረት ስልጠና ተደራሽነትን ማሳደግ | | |
| ትኩረት የተሰጣቸውን ጉዳዮች (Crosscutting issues) የሚመለከቱ በየደረጃው (በኤጀንሲዎች፤ በቢሮዎች፤ በተቋማት) የአደረጃጀት መዋቅር እንዲኖር ማድረግ | | |
| ለታዳጊ ክልሎች የተለየ ድጋፍ መስጠት | | |
| የልዩ ፍላጎት ሰልጣኞችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ መመሪያዎችን ማዘጋጀት፡፡ | | |
| በሁሉም የሙያ ዘርፎች ያለዉን የሴቶች ተሳትፎ ድርሻ ማሳደግ | | |
| ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን ለማካሄድ የሚያስችል የብረታ ብረት ሙያ ክህሎትን ማሳደግ | አለማቀፍ የብቃት የምስክር ወረቀት ያላቸው የብረታ ብረት ባለሙያዎች ቁጥር ከ 38 ወደ 4,000 ያድጋል | የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ |
| | አለማቀፍ የብቃት የምስክር ወረቀት ያላቸው የብረታ ብረት አሰልጣኞች ቁጥር ከ 5 ወደ 105 ያድጋል | የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ |
| በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማት የብረታ ብረት ሙያ ማእከላትን ማቋቋም | | |

| |
|---|
| የኢንጂነሪንግ የልህቀት ማእከልን ማስፋፋትና አለማቀፍ የብቃት ማረጋገጫ እውቅና እንዲያገኝ ማስቻል |
| ለቴክኒክና ሙያ ትምህርት አሰልጣኞች የብረታ ብረት ክህሎት ስልጠና መስጠት |
| የአሰልጣኞችን አቅም በማሳደግ የብረታ ብረት አሰልጣኝ (ማስተር የብረታ ብረት ባለሙያ) እንዲሆኑ ማድረግ |
| የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞችን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ድጋፍ ማድረግ |

**ተግባር 3፡- የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና የቴክኖሎጂ ሽግግር አገልግሎት**

| አላማ፡- በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች አማካኝነት የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞችን ምርት፤ የአገልግሎት ጥራትና ምርታማነት ማሳደግ | በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር | ግብ |
|---|---|---|
| በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች የሚደገፉ የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር | 463,573 | 567,115 |
| የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ያገኙ እና ተመዝነው ብቁ ሆነው የተገኙ የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር | 1,432,724 | 1,950,514 |
| የምርት ሂደት ሰንሰለት ትንተናን በመመርኮዝ የተለዩ እና ወደ መካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች የተላኩ የቴክኖሎጂ ፍላጎቶች ቁጥር | 3,388 | 7,379 |

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም መጨረሻ ከ 1.9 ሚሊዮን በላይ የሆኑ አንቀሳቃሾችን ያቀፉ 567,115 የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች አማካኝነት ድጋፍ ያገኛሉ፡፡ በዋናነት የአገልግሎት ሰጪዎቹን አሰልጣኞች አቅም በማጎልበት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ጥራትና ተደራሽነት እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡

በተጨማሪም፣ ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት የሚያስፈልጉ ቴክኖሎጂዎችን ለመለየት የሚያስችሉ 1,560 የምርት ሂደት ሰንሰለት ትንተና ቅድሚያ በተሰጣቸው ዘርፎች ይከናወናሉ፡፡ ተፈላጊ ቴክኖሎጂዎችን የመለየቱ ሂደት እንደተጠናቀቀና ቴክኖሎጂዎቹ እንደተገኙ ዲዛይን በመንደፍ (ከተሟላ ሰነድ ጋር

በማያያዝ) ናሙናዎችን ወደ ማምረት እንቅስቃሴ ይገባል፡፡ የሙከራ ናሙና ምርቱን በመፈተሽ ቴክኖሎጂውን ለማሸጋገር ያለውን ዝግጁነት የማረጋገጥ ስራ ይከናወናል፡፡ የሙከራ ምርቱ ፍተሻውን በማለፍ ማረጋገጫ እንደተሰጠው 89,583 የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች ይህንን ምርት በብዛት ለማምረት የሚያስችላቸውና በሽግግር የተገኙ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ሌሎች ምርቶችን ለማምረት የሚያስችላቸው ስልጠና ያገኛሉ፡፡ ይህንን ለማሳካት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት ከዩኒቨርስቲዎች፤ ከምርመር ተቋማት እና ከኢንዱስትሪዎች ጋር የመግባቢያ ሰነዶችን በመፈራረም ግንኙነታቸውን እንዲያጠናክሩ ይደረጋል፡፡

በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና አሰልጣኞች የሚከናወነውን የአቅም ክፍተት ትንተና መሰረት አድርጎ በሚዘጋጅ የአቅም ማጎልበቻ መርሃ ግብር አማካኝነት፣ የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች የቴክኒክና የስራ ፈጠራ ክህሎት እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች የአጭር ጊዜ ስልጠናዎችን በመጠቀም ክህሎታቸውን ማጎልበትና ያሉባቸውን የአቅም ክፍተቶች መሙላት ይችላሉ፡፡ የአቅም ክፍተቶችን ለመሙላት በሚሰጥ እያንዳንዱ ስልጠና ማጠናቀቂያ ላይ የአንቀሳቃሾችን ብቃት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ምዘናዎች ይሰጣሉ፡፡ የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች የሃብት ብክነትን እንዲቀነሱና ወጪ ቆጣቢነታቸውን እንዲያጠናክሩ ለማስቻል የምርት ሂደትን በማሳለጥ የምርት ጥራትንና ምርታማነትን የሚያጎለብተው የካይዘን አሰራር የድጋፍ ማእቀፉ አንድ አካል ይሆናል፡፡ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶችን የሚሰጡ ሁሉም የቴክኒክና ሙያ ትምህርት አሰልጣኞች በካይዘን መመሪያዎችና ዘዴዎች ስልጠና እንዲያገኙ የሚደረግ ሲሆን፣ ከስልጠናው የሚያገኟቸውን ተሞክሮዎች የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾችን አቅም በማጎልበት ጥቅም ላይ ያውላሉ፡፡

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር መጨረሻ 44 በመቶ የሚሆኑት የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች በማስተር የእደ ጥበብ ባለሙያዎች (በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ደረጃ አራትና በላይ ብቃት ባላቸው) የሚመሩ ይሆናል፡፡ ይህ ሂደት ጥራት ያለው ምርትን ወደ ውጭ የመላክ እንቅስቃሴን በማገዝ፣ በተለይም ኢንተርፕራይዞች ለውጭ ገበያ ማቅረብ ያለባቸውን 6 በመቶ ድርሻ

ለመወጣት የሚያስችል አቅም እንዲኖራቸው የማድረግ ግብ የመጀመሪያው እርምጃ ነው፡፡ ሂደቱን ለመደገፍ፣ በመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች፤ በመካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች እና በዩኒቨርስቲዎች መካከል አጋርነት ይመሰረታል፡፡

| ስትራተጂዎች | አመልካች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| ለሁሉም ነባርና አዲስ የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶችን እንዲያገኙ በማድረግ ምርታማነታቸውን፤ ተፈላጊነታቸውንና ተወዳዳሪነታቸውን ማሻሻል | በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች የሚደገፉ ነባር የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር ከ463,573 ወደ 501,505 ከፍ ይላል | የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ |
| | በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች የሚደገፉ አዲስ የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር ከ21,260 ወደ 65,610 ያድጋል | የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ |
| | የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች የሚያገኙና ተመዝነው ብቁ የሚሆኑ የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች ቁጥር ከ 1,432,724 ወደ 1,950,514 ያድጋል፡፡ | የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ |
| | የምርት ሂደት ሰንሰለት ትንተናን በመመርኮዝ የሚለዩ እና ወደ መካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች የሚላኩ የተፈላጊ ቴክኖሎጂዎች ቁጥር ከ 3,388 ወደ 7,379 ከፍ ይላል | የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ |
| የሙያ ደረጃ መስፈርቶችን በመከተል በሁሉም ዘርፎች የተሟላ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ፓኬጅ መስጠት | | |
| በታዳጊ ክልሎች ለመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጠው የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የተለየ እገዛ ማድረግ | | |
| ቴክኖሎጂዎችን ወደ መካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች ማሸጋገር( በምርት ሂደት ሰንሰለት ትንተና ተመስርቶ) | | |
| ትኩረት በተሰጣቸው የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ዘርፎች የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞችን ገቢ የማመንጨት እንቅስቃሴ መደገፍ | | |
| የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች የኤክስፖርት ደረጃን ያሟሉ ምርቶችንና ከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን ቴክኖሎጂዎች እንዲያመርቱ መደገፍ | በማስተር የእደ ጥበብ ባለሙያዎች የሚመሩ የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር ከ 0 በመቶ ወደ 44 በመቶ ከፍ ይላል | የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ |
| | የኤክስፖርት ደረጃን ያሟሉ ምርቶችን ማምረት የሚችሉ የማኑፋክቸሪንግ የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር ከ 0 በመቶ ወደ 6 በመቶ ያድጋል | የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ |
| በሁሉም ዘርፎች የምርት ሂደት ሰንሰለት መከለስና ማሳደግ | | |
| ለመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች አስፈላጊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ለመለየት በመደበኛነት የገበያ ጥናት ማካሄድ | | |
| አስፈላጊነታቸው ለተለዩ ቴክኖሎጂዎች አጠቃላይ መረጃዎችን ማደራጀት | | |
| በኢንዱስትሪዎችና በዩኒቨርስቲዎች መካከል የሚኖረውን ግንኙነት የሚመራ የመግባቢያ ሰነድ ማዘጋጀት | | |

| | 
|---|
| ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር የሙከራ ናሙናዎችን ማዳበር፤ ማምረትና መፈተን |
| የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞችን በመደገፍ ቴክኖሎጂን ማባዛት |
| የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞችና በቴክኖሎጂ ሽግግር ያለውን አስተዋጽኦ መመርመር |

## 10. ቅድሚያ የተሰጠው መርሃግብር፡- የከፍተኛ ትምህርት

### የዚህ ቅድሚያ የተሰጠው መርሃግብር ግብ፡-

“በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ተገቢውን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ያዳበሩ ብቃት ያላቸው ምሩቃንን ማፍራት፣ ለእውቀት መዳበርና ቴክኖሎጅ ሽግግር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ምርምሮችን የሃገር እድገትና የማህበረሰቡ ፍላጎት ባገናዘበ መልኩ ማካሄድ፣ ትምህርትና ምርምሮች ጠንካራ መነሻዎችና ምክንያቶች ላይ የተመሠረቱ ዲሞክራሲያዊ የሆኑ እና የብዝሀነት እሴቶችን በማክበር ላይ የተመረኮዙ ሃሣቦችን፣ አመለካከቶችን እና አቋሞችን የመፍጠርና የማዳበር እንዲሁም በነጻነት የመግለጽ እና የማንሸራሸር መርሆዎችን የሚያበረታቱ እንዲሆኑ ማረጋገጥ ናቸው”፡፡

### መግቢያ

በአሁኑ ዘመን፣ ህብረተሰቦች ፈጣንና  ኢፍትሃዊ በሆኑ አካባቢያዊና አለማቀፍ ሃይሎች አካል በሆኑ አዳዲስ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የባህል ፣ የቴከኖሎጅና አካባቢያዊ ለውጦች ተጽእኖ ሥር ናቸው፡፡ እነዚህ ለውጦች ክስተቶችና ተያይዘው የሚመጡ ተግዳሮቶች ብቃት ያላቸውና ተወዳዳሪ የሆኑ ግለሰቦችን ያቀፈ ትውልድ እንዲፈጠር ያስገድላሉ፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምርምርና የእድገት ቤተሙከራዎች በመሆን፣ አንድ ሃገር የሰው ሃይል አቅሙን እንዲገነባና በሃገራዊ ፣ ቀጠናዊና አለማቀፋዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በንቃት እንዲሳተፍ የሚያስችል ሁኔታን ይፈጥራሉ፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዋና ዋና ተግባራት የመማር ማስተማር (የእውቀት ሽግግር)፣ የምርምርና ፈጠራ (እውቀት ማዳበር) እና የማህበሰብ አገልግሎትና ተሳትፎ (እውቀትን ወደተግባር መቀየር) እንቅስቃሴዎች ናቸው፡፡ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የላቀ ብቃት ያላቸው ሳይንቲስቶችና ተመራማሪዎችን ከማፍራት በተጨማሪ፣ ተሰጥኦ ያላቸውን ሰዎች ወደ አካባቢው ማህበረሰብ የሚስቡ

ሃይሎች ናቸው፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምርምር በማካሄድ አዳዲስ እውቀቶችን የሚያጎለብቱ፣ የቴክኒክና የሙያ ድጋፎችን የሚያደርጉና በተቋማት ለሚከናወኑ የምርምርና የእድገት እንቅስቃሴዎች የአገልግሎት ማዕከላት በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች እውቀትን ለአካባቢው ህብረተሰብ በማሸጋገር ሳይወሰኑ፣ ከአለማቀፍ የትምህርትና የምርምር ማዕከላት የሚገኙ አዳዲስ እውቀቶች ወደ ማህበረሰቡ የሚደርሱበት የመሸጋገሪያ ድልድይ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ በተጨማሪም፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካባቢያዊ ግንኙቶችንና ትስስሮችን የሚያጎለብቱ፣ ተሰጥኦ ያላቸውን ግለሰቦች የሚስቡና በሃገሪቱ እንዲቆዩ የሚያደርጉ ኃይሎች ናቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ በሶስት የተለያዩ ዘመናት የተቋቋሙ 36 የህዝብ ዩኒቨርሲቲዎች (ምንም እንኳን 33ቱ ብቻ በመደበኛ ትምህርት አስራ ሁለተኛ ክፍል ያጠናቀቁ ተማሪዎችን የሚቀበሉ ቢሆንም) ፍትሃዊ በሆነ መልኩ በሁሉም የሃገሪቱ ክፍሎች እንዲገነቡ ተደርጓል (በቅርቡ የኮተቤ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ወደ ሙሉ ዩኒቨርሲቲነት እንደሚያድግ ይጠበቃል፡፡) ከነዚህ በተጨማሪ፣ አራት የግል ዩኒቨርስቲዎች (ዩኒቲ፣ ቅድስት ማርያም፣ አድማስና ሪፍትቫሊ) 94 የግል ዩኒቨርስቲ ኮሌጆችና ኮሌጆች በሃገሪቱ የከፍተኛ ደረጃ የሰው ሃይል በማልማት እንቅስቃሴዎች ተሳትፎ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነት በፍጥነት በማደግ ላይ ሲሆን፣ ሂደቱ ቀጣይ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ጥራት፣ ፍትሃዊነትና አግባብነትን ለማረጋገጥ በአምስተኛው የልማት መርሃ ግብር የሚከተሉት አምስት ተግባራት ተለይተዋል፡፡ እነዚህም ዩኒቨርስቲዎችን ማስፋፋትና ማጠናከር፣ ፍትሐዊነትን ማሳደግ፣ ተገቢነትና ጥራትን ማሳደግ፣ ምርምር የቴክኖሎጅ ሽግግርና የማህበረተሰብ ተሳትፎ እንዲሁም ተቋማዊ ትብብር አመራርና አስተዳደርን የሚመለከቱ ናቸው፡፡

**ተግባር 1፡- ዩኒቨርስቲዎችን ማስፋፋትና ማጠናከር**

| ዓላማ፡- ሃገር አቀፍ የተማሪ የቅበላ አቅምን በማሳደግ የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነትን ከፍ ማድረግ | አራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ጠቅላላ (ወ/ሴ) | ግብ ጠቅላላ (ወ/ሴ) |
|---|---|---|
| ከፍተኛ ትምህርት የቅበላ ምጣኔ | 9.4 በመቶ(6/13) | 15 በመቶ (14/17) |
| የህዝብ ዩኒቨርስቲዎች የሁለተኛ ዲግሪ (ማስተርስ) የተማሪ ቅበላ አቅም | 28,170 | 56,000 |

የሃገሪቱን እድገት ወደ ዝቅተኛ የመካከለኛ ገቢ ደረጃ እንዲያድግ ለማገዝና በዚህ ደረጃ የሚገኝ ኢኮኖሚ የሚፈልገው የሰለጠነ የሰው ሃይል በተገቢ መጠን መፍጠር እንዲቻል በመካሄድ ላይ ያለው የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነትን የማሳደግ እንቅስቃሴ ቀጣይነት ሊኖረው ይገባል፡፡

አሁንም ተደራሽነትን ለመጨመር እንዲቻል 11 አዳዲስ ዩኒቨርስቲዎች ይመሰረታሉ፡፡ ዩኒቨርሲቲዎቹ የሚቋቋሙበት ቦታ የሚወሰነው በአካባቢ ህዝብ ፍላጎትና በክልሎች መካከል ያለው ተደራሽነትን ከግንዛቤ በማስገባት ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን፣ የነባር ዩኒቨርስቲዎችን የተማሪ ቅበላ አቅም ለማሳደግ ተቋማቱን የማጠናከርና የማስፋፋት ስራ ይከናወናል፡፡ 36ቱም ነባር ዩኒቨርስቲዎች የተማሪ ቅበላ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ በማድረግ ትኩረት በተሰጣቸው የስልጠና ዘርፎች ያለውን የተማሪ ፍላጎት ማርካት እንዲችሉ ይደረጋል፡፡ የግል ዩኒቨርስቲዎች የሙያ ልማት እና የአመራር አቅም ማጎልበቻ እድሎችን እንዲፈጥሩ በማገዝ፣ በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (የግልም ይሁኑ የመንግሥት) ተመሣሣይ የጥራት ደረጃ ያለው ትምህርት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ እነዚህን እርምጃዎች በመውሰድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቅድመ ምረቃና የድህረ ምረቃ የተማሪ ቅበላ አቅም በድምሩ ከ600,000 በላይ ይደርሳል፡፡ ይህ እርምጃ በአሁኑ ወቅት ያለውን የ2.2 በመቶ  የተማሪ የቅበላ አቅም ምጣኔን በማሳደግ በሚቀጥሉት አምስት አመታት ዝቅተኛ የመካከለኛ ገቢ ባላቸው ሃገራት የሚታየውን ጥቅል ቅበላ ምጣኔ ለማሳካት ኢትዮጵያን ግማሽ መንገድ እንድትጓዝ ያስችላታል፡፡

<table>
<tr><th>ስትራተጂዎች</th><th>አመልካች (መነሻና ግብን ጨምሮ)</th><th>ምንጭ</th></tr>
<tr><td rowspan="4">የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቅድመ ምረቃና የድህረ ምረቃ የተማሪ ቅበላ አቅም ማሳደግ</td><td>11 አዳዲስ ዩኒቨርስቲዎችን በመመስረት አስራ ሁለተኛ ክፍል ያጠናቀቁ ተማሪዎችን የሚቀበሉ የህዝብ ዩኒቨርስቲዎችን ቁጥር ከ33 ወደ 44 ማሳደግ</td><td>የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት</td></tr>
<tr><td>የቅድመ ምረቃ ጥቅል የቅበላ ምጣኔ ከ9.4 በመቶ ወደ 15 በመቶ ያድጋል</td><td>የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት</td></tr>
<tr><td>መደበኛ የሁለተኛ ዲግሪ የቅበላ መጠን ከ28140 ወደ 56000 ያድጋል</td><td>የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት</td></tr>
<tr><td>መደበኛ የሶስተኛ /የዶክትሬት/ ዲግሪ የቅበላ መጠን ከ3169 ወደ 6500 ያድጋል</td><td>የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት</td></tr>
<tr><td colspan="3">አዳዲስ ዩኒቨርስቲዎችን መገንባት ፣ ማደራጀትና ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ</td></tr>
<tr><td colspan="3">ለቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች ቅድሚያ የሚሰጥ የትምህርት ፕሮግራም መሪ እቅድ /ማስተር ፕላን / መንደፍ</td></tr>
<tr><td colspan="3">ተቋማዊ የልማት ስትራቴጂ ማዘጋጀትና ለትግበራው የሚያስፈልገውን በቂ የሰው ሃይል መመደብ</td></tr>
<tr><td colspan="3">የነባር ዩኒቨርስቲዎችን መሠረተ ልማት እና የሰው ሀይል አቅም በማጠናከር የተቋማቱን የቅበላ አቅም ማሳደግ</td></tr>
<tr><td colspan="3">በቅበላ መሪ እቅዱ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት የሚያስችል የሰው ሃይልና የመሠረተ ልማት እቅድ ማዘጋጀትና መተግበር</td></tr>
<tr><td rowspan="2">የግል ዩኒቨርስቲዎችን ማጠናከር</td><td>የግል ዩኒቨርስቲዎች የቅድመ ምረቃ የቅበላ አቅም ከ28821 ወደ 50000 ያድጋል</td><td>የትምህርት ስትራቴጂ ማእከል</td></tr>
<tr><td>በግል ዩኒቨርስቲዎች መደበኛ የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ድርሻ 15 በመቶ ይደርሳል</td><td>የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት</td></tr>
<tr><td colspan="3">የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን አቅም ማጎልበት</td></tr>
<tr><td colspan="3">የመንግስትና የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጋራ አጋርነት እንዲፈጥሩ የሚያስችል አደረጃጀት ማዋቀር</td></tr>
<tr><td colspan="3">የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቂማት የሰራተኛና የአመራር አቅማቸውን እንዲገነቡ ማገዝ</td></tr>
</table>

**ተግባር 2፡ ፍትሐዊነትን ማጎልበት**

| ዓላማ፡- ወደ ኋላ በቀሩና በሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ያለውን የተሳትፎ ልዩነት ማጥበብ | አራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ጠቅላላ (ወ/ሴ) | ግብ ጠቅላላ (ወ/ሴ) |
|---|---|---|
| በቅድመ ምረቃ የሴት ተማሪዎች የተሳትፎ ምጣኔ | 32 በመቶ | 45 በመቶ |
| በቅድመ ምረቃ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ፕሮግራሞች የሴት ተማሪዎች የተሳትፎ ምጣኔ | 28 በመቶ | 45 በመቶ |
| የሴት መምህራን ድርሻ (%) | 12 በመቶ | 25 በመቶ |
| የልዩ ፍላጎት ትምህርት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ቁጥር | 1000 | 3000 |
| የታዳጊ ክልሎች ተማሪዎች ጥቅል የቅበላ ድርሻ ምጣኔ | 2.5 በመቶ (2012/13) | 5 በመቶ |

የከፍተኛ ትምህርት ስርዓት መስፋፋትና የቅበላ አቅም መጠን ለአንድ ሃገር እድገት ወሳኝ ቢሆንም ሂደቱ ፍትሐዊ በሆነ አኳኋን መተግበር ይኖርበታል፡፡ በማስተማር፣ በምርምር፣በአመራርና በአስተዳደር ቦታዎች ላይ የሴቶችን ድርሻ ማሳደግ የፖሊሲው ዋና ግብ ነው፡፡ ልዩ የቅበላ መስፈርት የመሳሰሉ አዎንታዊ የድጋፍ ፕሮግራሞች የሴቶች የትምህርት ተሳትፎን በማሳደግ ለውጥ እያስመዘገቡ ይገኛሉ፡፡ ከሳይንስ፣ ሂሳብ፣ ቴክኖሎጂ እና እንግሊዝኛ፣ መምህራን ጋር አብሮ መስራትን የመሳሰሉ አዳዲስ ፕሮግራሞችን በመጀመር የሁሉንም ተማሪዎች ውጤት እንዲሻሻልና በዚያውም ለሴት ተማሪዎች ልዩ

ትኩረት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ ሃብትን በጋራ የመጠቀም (ለምሣሌ የዩኒቨርስቲ ቤተሙከራዎችን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎችም እንዲገለገሉባቸው ማድረግ) አሰራር እንዲጀመር ይደረጋል፡፡ በመምህራን ፣ ተመራማሪዎችና አመራሮች የሚታየውን የፆታ ምጣኔ ለማስተካከል የሚረዳ አዲስ የሴት ባለሙያዎች የቅጥር ስልት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

ልዩ ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎች የከፍተኛ ትምህርት የተሻለ ተሳትፎና ውጤት እንዲያስመዘግቡ ጥረት ይደረጋል፡፡ ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች በብሄራዊ ደረጃ የተነደፈውን ለአካል ጉዳተኞች የአገልግሎትና የመሠረተ ልማት አቅርቦት ፖሊሲን በመከተል ግቢዎቻቸው እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎችን እንዲያስተናግዱ ይደረጋል፡፡ እጅግ በጣም ልዩ ትኩረትና ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎችን የከፍተኛ ትምህርት ፍላጐት ለማርካት፣ ሶስት ዩኒቨርስቲዎች ተለይተው አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን ማደራጀት የሚያስችላቸው ተጨማሪ እገዛ ይደረግላቸዋል፡፡ በሂደት፣ እነዚህ ዩኒቨርስቲዎች በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ያለውን የልዩ ፍላጎት ትምህርት ድጋፍ አሰጣጥ እንቅስቃሴ የማጎለበት ተግባርን በመሪነት እንዲያስተባብሩ ይደረጋል፡፡

በታዳጊ ክልሎች ያለውን የተማሪ ቅበላና ውጤታማነት ለማሻሻል፣ በሁሉም ዩኒቨርስቲዎች የአዎንታዊ ተጽእኖ (Affirmative Action) የተማሪ ቅበላ ፖሊሲ በተመሣሣይ ሁኔታ መተግበሩ ይቀጥላል፡፡ በክልሎች መካከል የሚታየውን የከፍተኛ ትምህርት አቅርቦት ምጣኔ በመገምገም የቅበላ /የድጋፍ ፖሊሲ ማሻሻያዎች ይደረጋሉ፡፡

| ስትራተጂዎች | አመልካች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| የሴቶችን የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎና ውጤታማነት ማሳደግ | በቅድመ ምረቃ ፕሮግራሞች የሴት ተማሪዎች የቅበላ ምጣኔ ከ32 በመቶ ወደ 45 በመቶ ያድጋል | የትምህርት አመራር የኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | በቅድመ ምረቃ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፕሮግራሞች የሴት ተማሪዎች የቅበላ ምጣኔ ከ28 በመቶ ወደ 45 በመቶ ያድጋል | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | በሁለተኛ ዲግሪ ፕሮግራሞች የሴት ተማሪዎች የቅበላ ምጣኔ ከ22 በመቶ ወደ 35 በመቶ ያድጋል | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | በሶስተኛ ዲግሪ ፕሮግራሞች የሴት ተማሪዎች የቅበላ ምጣኔ ከ12 በመቶ ወደ 20 በመቶ ያድጋል | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| ሀት ተማሪዎች ከፍተኛ ትምህርትን እንዲቀላቀሉና ውጤታማ እንዲሆኑ ልዩ ድጋፍ መስጠት | | |
| የክረምትና የሳምንት መጨረሻ (ቅዳሜና እሁድ) ተጨማሪ ፕሮግራሞችን በማካሄድ የሁለተኛ ደረጃ ሴት ተማሪዎች ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ | | |
| በትምህርት ላይ ለሚገኙ ሴት ተማሪዎች ተቋማዊና ዘላቂ የሆነ የአካዳሚክ፣ የኢኮኖሚ እና የስነ ልቦና ድጋፎችን ማድረግ | | |
| ሴት ተማሪዎች የማስተርስና የዶክትሬት ዲግሪ ፕሮግራሞች መከታተል እንዲችሉ ልዩ የትምህርት እድል መስጠት | | |
| የልዩ ፍላጎት ት/ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውና ከታዳጊ ክለሎች የሚመጡ ተማሪዎችን የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎና ውጤታማነት ማሳደግ | የልዩ ድጋፍ ፍላጎት የሚሹ ተማሪዎች የመመረቅ ምጣኔ 95 በመቶ ይደርሳል | የዩኒቨርስቲዎች ሪፖርቶች |
| | ከታዳጊ ክልሎች የሚመጡ ተማሪዎች ጥቅል የቅበላ ምጣኔ ከ2.5 በመቶ ወደ 5 በመቶ ከፍ ይላል | የዩኒቨርስቲዎች ሪፖርቶች |
| | ከታዳጊ ክልሎች የሚመጡ ተማሪዎች የመመረቅና ትምህርት ላይ የመቆየት (Retention) ምጣኔ 95 በመቶ ይደርሳል | የዩኒቨርስቲዎች ሪፖርቶች |
| | ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ቁጥር ከ1000 ወደ 3000 ያድጋል | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| የድጋፍ ልዩ የሚያስፈልጋቸውና ከታዳጊ ክልሎች የሚመጡ ተማሪዎች በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ደረጃዎች ተሳትፎ እንዲያደርጉና ውጤታማ እንዲሆኑ እገዛ ማድረግ | | |
| ዩኒቨርስቲዎች ለልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት የሚሆኑ፣ የመማሪያና ማስተማሪያ ቁሳቁሶች እንዲሟሉ ማድረግ | | |
| ሶስት ዩኒቨርስቲዎችን በመምረጥና አስፈላጊ ግብዓቶች እንዲሟሉላቸው በማድረግ የከፍተኛ ትምህርት የልዩ ፍላጐት ትምህርት መሪ ተቋማት እንዲሆኑ ማድረግ | | |
| ለልዩ ፍላጎት ትምህርት የተዘጋጀውን ልዩ የቅበላ ፖሊሲ ማሻሻል | | |
| የልዩ ፍላጐትና የታዳጊ ክልል ተማሪዎች ተቋማዊ እና ዘላቂ የሆነ የአካዳሚክ፣ የኢኮኖሚና የስነ ልቦና ድጋፎችን እንዲያገኙ ማድረግ | | |
| ሴቶች በማስተማር፣ በምርምርና በአመራር ደረጃዎች ያላቸውን ተሳትፎና ውጤታማነት ማሳደግ | የሴት መምህራን ድርሻ /ምጣኔ ከ12 በመቶ ወደ 25 በመቶ ያድጋል | የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት |
| | የሴት ተማሪዎች በታዋቂ የጥናት መጽሔቶች ላይ ያሳተሟቸው የጥናት ጽሁፎች ድርሻ 15 በመቶ ይደርሳል | የዩኒቨርስቲዎች ሪፖርቶች |
| | በዩኒቨርሲቲ ቦርዶች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ ድርሻ ወደ 25 በመቶ ይደርሳል | የዩኒቨርስቲዎች ሪፖርቶች |
| | በየተቋሙ በመካከለኛና ዝቅተኛ አመራት ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ ከ5 በመቶ ወደ 30 በመቶ ያድጋል | የዩኒቨርሲቲዎች ሪፖርቶች |
| በእያንዳንዱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ቢያንስ አንድ ሴት ከፍተኛ አመራር ደረጃ ላይ እንድትደርስ ይደረጋል | | |
| የዩኒቨርስቲ ቦርዶችና ከፍተኛ የአመራር ደረጃዎች አወቃቀር የሴቶችን ውክልና የሚያሳድግ እንዲሆን የሚያስችሉ መመሪያዎች ማዘጋጀትና መተግበር | | |
| ሴቶች በሁሉም ደረጃዎች ባሉት የአመራርና የአስተዳደር እርከኖች እንዲሳተፉ የሚያበረታታና ውጤታማ እንዲሆኑ እገዛ የሚያደርግ የሴቶች የተሰጥኦ ማበልፀጊያ ማዕከል ማዘጋጀትና መተግበር | | |

**ተግባር 3፡ የትምህርት ተገቢነትንና ጥራትን ማሻሻል**

| ዓላማ፡- የትምህርት ብቃታቸው የተረጋገጠ በቂ የመምህራን አቅርቦት እንደዚሁም የትምህርት ግብአቶች በማመቻቸት፣ በፍላጐት ላይ በተመሠረቱ የትምህርት ፕሮግራሞች ምሩቆችን ማፍራት | በ4ኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ጠቅላላ (ሴ/ወ) | ግብ ጠቅላላ (ሴ/ወ) |
|---|---|---|
| ከምረቃ በኂላ ባሉት 12 ወራት ውስጥ በመስካቸው ስራ የሚቀጠሩ ምሩቃን ምጣኔ | የለም | 80 በመቶ |
| የመምህራን የትምህርት ደረጃ ምጥጥን (የመጀመሪያ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ) | 27፡58፡15 | 0፡70፡30 |
| በቅድመ ምረቃ የመጀመሪያ ዓመት ትምህርት የሚያጠናቅቁ ምጣኔ | የለም | 95 በመቶ (95/95) |
| በቅድመ ምረቃ ትምህርት የሚመረቁ ምጣኔ | የለም | 70 በመቶ (70/70) |

ባለፉት አምስት አመታት ወደ ከፍተኛ ትምህርት የሚገቡ ተማሪዎች ቁጥር በፍጥነት ያደገ ሲሆን፣ በአምስተኛው መርሃ ግብርም ይህ እድገት እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡ በፈጣን ሁኔታ በማደግ ላይ የሚገኘው ትምህርት ውጤታማና ስልታዊ በሆነ መንገድ ካልተመራ ጥራቱና ተገቢነቱ ሊቀንስ ይችላል፡፡ ጥራትና ተገቢነት የከፍተኛ ትምህርት የእውቅና መመዘኛ ናቸው፡፡

በዚህም ምክንያት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት ተገቢነትና ጥራት እንዲሁም የትምህርት ፕሮግራሞች ምዘና እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ የማኑፋክቸሪንግና ሌሎች የኢንዱስትሪ እድገቶች በሳይንስና

ቴክኖሎጂ ክህሎት ላይ የበለጠ ያተኩራሉ። ስለዚህም፣ በአራተኛው የትምህርት ልማት እቅድ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እና ከማህራዊ ሳይንስ የነበራቸው 70:30 የፕሮግራም ድርሻ እንደተጠበቀ ይቀጥላል።

በትምህርት ተቋማት ውስጥ የተቋማት አካዳሚክ ኮሚቴዎችን በማጠናከርና በማቋቋም ጥራትን ማረጋገጥ ይቻላል። አሁን ያለው የአቻ ለአቻ የግምገማ ሂደት ብቁ ሆኖ ባለመገኘቱ አዲስ ራሱን የቻለና ገለልተኛ የሆነ አካል እንዲቋቋም ይደረጋል። በከፍተኛ ትምህርት ተገቢነትና ጥራት ኤጀንሲ (HERQA) አስተባባሪነት የሚካሄደው የውጭ ግምገማ ለኤጀንሲው ተጨማሪ ስልጣን እንዲሰጥና እንዲጠናከር ይደረጋል። ከአምስተኛው የልማት መርሃ ግብር አንደኛ ዓመት ጀምሮ አዲስ በተቋቋመው ብሔራዊ የጥራት ማስጠበቂያ ማዕቀፍ (National Qualifications Framework) አማካኝነት ተቋማት አገራዊና አለማቀፋዊ ደረጃዎች ማሟላታቸውን ክትትል ይደረጋል። ይህን ማዕቀፍ ለማስተግበር እያንዳንዱ ትምህርት ተቋም የሚሰጣቸውን የዲግሪ መረሃ- ግብር ፕሮግራሞች ለከፍተኛ ትምህርት የትምህርት ጥራትና ተገቢነት ኤጀንሲ ማቅረብ ይገባዋል። ይህ ከተደረገ በኂላ ተቀባይነት ካለው ተቋም ከፍተኛ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎች በብሔራዊ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ ይደረጋል።

ተገቢ ክህሎትና የቴክኖሎጂ ክሂል ያላቸው ምሩቃን መኖር ከታቀደው ግብ ላይ ለመድረስ ወሳኝ ናቸው። ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የዲግሪ ፕሮግራሞች በስራ ዓለም፣ በኢንዱስትሪና በምርምር ስራ ብቁ የሆኑ፣ በሆነ እውቀት፣ ክሂል፣ የስራ ተነሳሽትና ተወዳዳሪነት ባህሪ የተላበሱ ምሩቆችን ማፍራት አለባቸው። የዲግሪ መረሀ- ግብሮችን ጥራና ተገቢነት እንዲሁም መዋቅር ለማሻሻል የሞጁል ዝግጅት ሂደት ተጠናቅቋል። ዩኒቨርሲቲዎች ከፀደቁት ሞጁሎች መካከል የየራሳቸውን መርሃ- ግብር እንዲለዩ ያስችላቸዋል። ይህም ሆኖ በተለያዩ የሞጁል ዝግጅቶች ድግግሞሽና ግልጸኝነት የጎደለው ተያያዥነት ይታያል። በአምስተኛው መርሃ ግብር ዘመን ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ከትምህርት የእቅድ ማዕከል (Education Strategy Centre) እያንዳንዱን ፕሮግራም በመገምገም ድግግሞሽን ለመቀነስ፣ ስርዓተ ትምህርቱን ወቅታዊ ለማድረግ የትምህርት ውጤት/ ብቃት ላይ በጋራ ይሰራሉ። በመጨረሻም፣

ዩኒቨርሲቲዎች ግልጽ የሆኑ ድግግሞሽ የሌሉባቸው ሞጅዩሎች የተዘጋጁላቸው የዲግሪ ፕሮግራሞችን መለየት ይችላሉ፡፡

ይህ የስርዓተ ትምህርት ክለሳ የኢንዱስትሪ አጋሮችን እርዳታና ምክር ያካትታል፡፡ የዩንቨርሲቲዎችና የኢንዱስትሪዎች አጋርነት መጠናከር የሁለትዮሽ ጥቅም ይሰጣል/ይኖሩታል፡፡ ዩኒቨርሲቲዎች በስርዓተ ትምህርት ክለሳ ወቅት የኢንዱስትሪ አጋሮችን ድጋፍና ምክር ይጠይቃሉ፡፡ የኢንዱስትሪ ባለሙያዎች ተማሪዎችን እንዲመክሩና እንዲያስተምሩ ይጋበዛሉ፡፡ በዩኒቨርሲቲዎች አቅራቢያ በሚገኙ ኢንዱስትሪዎች የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆችና አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ተማሪዎች የስራ ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ ተማሪዎችን ያበረታታል፡፡ ይህ አቀራረብ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ ተገቢው ክሂል፣ የስነ ልቦና ዝግጅት፣ አመለካከትና የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ገበያው የሚጠይቀውን ክሂል ትንበያና የአገሪቱን የወደፊት ግብ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መር ኢኮኖሚን ግምት ውስጥ በማስገባት የዲግሪና የልዩ ስልጠና ኮርሶች ይሻሻላሉ፡፡ የገበያ ፍላጐት መረጃ ማግኘት እንዲቻል ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከመሳሰሉት ተቋማት ጋር የጠበቀ ቁርኝት ይመሰረታል፡፡

የዩኒቨርሲቲ መምህራን፣ የመጀመሪያና የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች መምህራን የተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና በ5ኛው የትምህርት ልማት መርሃ ግብር የትኩረት አቅጣጫ ሁኖ ይቀጥላል፡፡ የመምህራን የትምህርት ዝግጅት ምጥጥን 0፡70፡30 ለመጀመሪያ ዲግሪ፣ ሁለተኛ ዲግሪና ሶስተኛ ዲግሪ በቅደም ተከተላቸው መሰረት ግቡ እስከሚደርስ ይቀጥላል፡፡ በአራተኛው የትምህርት እቅድ መርሃ-ግብር እንደነበረው ሁሉ መምህራን ከመጀመሪያ ዲግሪ ወደ ሁለተኛ ዲግሪ እንዲሸጋገሩ ድጋፍ ይደረጋል፡፡ ሴት መምህራን ለሁለተኛ ዲግሪና ለሶስተኛ ዲግሪ ፕሮግራሞች እንዲመዘገቡ አዎንታዊ ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በአዲስ መምህራን ቅጥርና እድገት እንዲሁ ለሴቶች ልዩ ድጋፍ የሚደረግ ሲሆን፣ ምርምር እንዲያካሂዱና በአመራር ቦታ እንዲቀመጡም ይበረታታሉ፡፡

| ስትራተጂዎች | አመልካቾች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| የትምህርት መረሃ-ግብሮችን ትምህርት ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ፕሮግራሞች ልዩ ትኩረት በመስጠት የትምህርት አሰጣጥ አግባብነትና ጥራትን ማሳደግ | በተመረቁ በ12 ወራት ውስጥ ስራ የተቀጠሩ ምሩቃን ምጣኔ 80 በመቶ ይደርሳል | የተመራቂዎች ክትትል ጥናቶች (tracer studies) |
| | የ2ኛና የ3ኛ ዲግሪ ምሩቃን ምጣኔ 95 በመቶ | የዩኒቨርሲቲዎች ሪፖርቶች |
| | የመጀመሪያ ዓመትን የሚያጠናቅቁ የዲፕሎማ ተማሪዎች ምጣኔ 95 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የዩኒቨርሲቲዎች ሪፖርቶች |
| | የሁለተኛ ዲግሪ ምሩቃን ምጣኔ 70 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የዩኒቨርሲቲዎች ሪፖርቶች |
| ለዋና ዋና ሴክተሮች የሚያስፈልገው የሰው ሀይል ልማት መገመት | | |
| በተቀመጡት ልኬቶች መሰረት የትምህርት ዝግጅት ጥራትና ተቀባይነትን ማረጋገጥ መተግበር፣ | | |
| ብሔራዊ ጥራትን ለማረጋገጥ ቅድሚያ በሚሰጣቸው መስኮች የመውጫ ፈተናዎች ስርዓትን ማቀድና መተግበር፣ | | |
| የተማሪዎችን የተግባር ልምምድ ፕሮግራም ተግባራዊ ማድረግ፣ | | |
| የዩኒቨርሲቲዎችን /ኮሌጆችን ቀደምት ተማሪዎች/alumni/ ብሔራዊና ተቋማዊ የመረጃ ስርዓት መመስረትና የተመራቂዎች ክትትልና ጥናት ማድረግ፣ | | |
| የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፕሮግራሞች ከህብረተሰብ ሳይንስና ከሰብዓዊ ሳይንስ ጋር ያለውን ምጥጥን በ70፡30 ማስቀጠል | | |
| የሳይንስና ቴክኖሎጂ ተቋሞችን ቁጥር ማሳደግና የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎችን ወደ ዓለም አቀፍ የልሕቀት ማዕከል ደረጃ ማሳደግ፤ | | |
| በእያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ ቢያንስ የሶስት መስኮችን ልሕቀት በመለየት በልዩ ስልጠና/ specialism/ ማዕከልነት መጨመር፣ | | |
| ባሉት የድህረ-ምረቃ መረሃ-ግብሮች ያለውን የተገቢነትና የአቅም ክፍተት መለየት፣ | | |
| የስርዓተ ትምህርት ክለሳ ለማድረግ የሚያግዝ ገለልተኛ የሆነ አካል ማቋቋም | | |
| ውስጣዊ የስርዓተ ትምህርት ኮሚቴዎች መመስረትና ማጠናከር፣ | | |

| ስትራተጂዎች | አመልካቾች (መነሻና ግብን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| የተቀመጠውን የጥራ ልኬት የሚያሟሉና በተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና የሚሳተፉ መምህራንን ቁጥር ማሳደግ | 27:58:15 የነበረው የመምህራን የትምህርት ደረጃ (አንደኛ ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ ዲግሪ) ስብጥር 0:70:30 ይደርሳል | የትምህርት አስተዳደር የመረጃ ስርዓት |
| | የመምህር ተማሪ ምጣኔ ከ 1:23 ወደ 1:19 ዝቅ ይላል | የትምህርት አስተዳደር የመረጃ ስርዓት |
| | ተከታታይ የሙያ ማሻሻያን አጠናቀውና የሙያ ልኬቱን አሟተው የሙያ ምስክር ወረቀት ያገኙ ምጣኔ 60 በመቶ ይደርሳል | የዩኒቨርሲቲዎች ሪፖርቶች |
| የመምህራን አቅርቦት ምንጮችን ማስፋፋት (በተለይ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ)፣ | | |
| በድህረ ምረቃ መረሃ-ግብር ተመዝጋቢዎችን በአገር ውስጥ ማስፋፋት (የውጭ ሀገር የትምህርት እድሎችንም ማስፋፋት፣) | | |
| በተመረጡ ዩኒቨርሲቲዎች በመምህራን ትምህርት የልህቀት ማእከል መመስረት፣ | | |
| የላቁ የተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ማዕከላትን መመስረትና ወደ ተግባር ማስገባት፣ | | |
| የተቋማትን ፍላጎትና የተማሪዎች ምዝገባ ዕድገት መሰረት ያደረገ የመምህራን ቅጥር ማካሄድ፣ | | |

| ስልቶች | አመልካቾች (መነሻና መድረሻን ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| የትምህርት መረጃ ማእከላትንና የትምህር ፖሊሲዎችን ማሳደግ፣ | የዋና የማጣቀሻ መጽሐፍትና ተማሪ ጥምረት 1:5 ይሆናል፡፡ | የዩኒቨርሲቲዎች ሪፖርቶች |
| | የዲጂታል ቤተ-መጽሐፍት ተጠቃሚ ተማሪዎች ድርሻ 100 በመቶ ይሆናል | የዩኒቨርሲቲዎች ሪፖርቶች |
| | በኢንፎርሜሽ ኮመኒኬሽን የተደገፉ ምርጥ የመማሪያ ክፍሎች 25 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የዩኒቨርሲቲዎች ሪፖርቶች |
| | የቤተ-ሙከራና የወርክ ሾፕ ፋሲሊቲዎችን ለሚያስፈልጋቸው ሁሉም ኮርሶች ቁሳቁሶችን የሚያሟ ዩኒቨርሲቲዎች 100 በመቶ ይሆናሉ፣ | የዩኒቨርሲቲዎች ሪፖርቶች |
| ለሳይንስና ቴክኖሎጂ የትምህርት ቁሳቁሶች ፍላጎት ልኬት/standard/ ማዘጋጀትና መተግበር፣ | | |
| የትምህርት ቁሳቁስ ዕድገት ዕቅድ ማዘጋጀትና መተግበር፣ | | |
| በሳይንስና ቴክኖሎጂ የአካዳሚክ ስታፍ ድጋፍ ሰጭዎች በትምህርት ቁሳቁሶች አያያዝ ለማሳደግ የትምህርት ፋሲሊቲዎች አያያዝ ዕቅድ ማዘጋጀትና መተግበር፣ | | |
| በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎችና አስፈላጊ የመማሪያ ክፍሎች የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ እና የኢንተርኔት አገልግሎት ማሟላት፣ | | |

**ተግባር 4፡ ምርምር፣የቴክኖሎጂ ሽግግርና የህብረተሰብ ተሳትፎ**

| ዓላማ፡- ምርምርና የህብረተሰብ ተሳትፎን ትኩረቱ ያደረገ ጥራቱን የጠበቀና ተገቢ የሆነ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ | አራተኛው የትምህርት ሴክተር ልማት ዕቅድ ድምር (ወ/ሴ) | ግብ ድምር (ወ/ሴ) |
|---|---|---|
| ከኢንዱስትሪዎች የሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ በመቶኛ፣ ከአለም አቀፍ ምንጮች | የለም | 50 በመቶ |
| በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ስራ ላይ ልምድ የሚያለዋውጡ የሕዝብ ዩኒቨርሲቲዎች በመቶኛ፣ | በመቶኛ | 100 በመቶ |
| በዩኒቨርሲቲዎችና በኢንዱስትሪዎች በጋራ የሚካሄዱ የምርምር ፕሮጀክቶች በመቶኛ፣ | የለም | 50% |
| ከቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ንዑስ ማዕከላት ጋር በመቀናጀት በውጤታማነት የተተገበሩ ቴክኖሎጂዎች ቁጥር፣ | የለም | 500 |

የዩኒቨርስቲዎች የምርምር አቅም በዝቅተኛ የምርምር ፋይናንስ በጀትና ባሉአቸው ጥቂት ተመራማሪዎች ምክንያት የተገታ ነው፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ዕቅድ የከፍተኛ ትምህርት ንዑስ ዘርፍ በመንግስት የሚጸድቅ በጀት ያስፈልገዋል፡፡ ይህ እያንዳንዱ ተቋም በራሱ የመወሰን ስልጣንን ስለሚሰጥ ለምርምር የሚመደበው በጀት ከፍ ያደርጋል፤ ምርምሮችም አለምአቀፍ ልኬትን እንዲያሟ ያደርጋል፡፡ የድህረ ምረቃ ዕድልን በተለይ የዶክትሬት ዲግሪ ትምህርትን በአገር ውስጥ ባሉ ዩኒቨርሲቲዎች በማስፋፋትና ከውጭ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ጋር በትብብር በመስራት የዩኒቨርሲቲዎችን የምርምር አቅም ማሳደግ ይቻላል፡፡ ምርምሮችን ከጥራት አንፃር በማየት በበጀት አመዳደብ ላይ ትኩረት ይሰጣል፡፡ የምርምር ተግባራት በኢንዱስትሪና በሌሎች አጋር ድርጅቶች እንዲደገፉ ይደረጋል፡፡ ምርምርን ከህብረተሰብ አገልግሎት ጋር ማቀናጀት የምርምርን ተገቢነትና ጥራት ያሻሽላል፡፡

በዩኒቨርሲቲዎችና ከኢንዱስትሪዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር በወጡት ስትራተጂዎች በመጠቀም፣ የምርምር አጀንዳዎችን በመለየትና በእውቀትና በተግባር መካከል ያለውን ግንኙነት በእጅጉ ለማሻሻል ይቻላል፡፡ በንግድና በትምህርት ተቋማት መካከል ቅርርብ በመፍጠር (ለምሣሌ የሙከራ ዩኒቶች ያሉዋቸው የሳይንስ ፓርኮችን በማቋቋም) ዩኒቨርሲዎች ተጨማሪ ገቢ ማግኘት ይችላሉ፡፡ ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት በመተባበር የመካከለኛና አነስተኛ ኢንዱስትሪ ኢንተርፕራይዞች ምርታማነትን ማሳደግ የሚችሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፡፡

በተመሳሳይ፣ ለትምህርት ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች ግንኙነት እንዲፈጥሩ በማድረግ፣ የትምህርት ተገቢነትና ጥራትን ከማሻሻል በተጨማሪ፣ ወደ ከፍተኛ ትምህርት የሚገቡ ተማሪዎች የተሻለ ዝግጅት እንዲኖራቸው ይረዳል፡፡ እያንዳንዱ የህዝብ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም በግቢው ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚሰጥ 'መሰል' (adopted) ተቋም በማቋቋም፣ የማስተማር ልምምድ እንዲካሄድበት ያደርጋል፤ በተጨማሪም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ለከፍተኛ ትምህርት ያላቸውን ዝግጁነት ያሻሽላል፡፡

በከፍተኛ ትምህርት ሰፊ የማስፋፋት ሥራ እየተካሄደ ቢሆንም፣ ብዙሃኑ በተቋሙ ገብተው መማር ስለማይችሉ፣ ቀጥታ ተጠቃሚ አይሆኑም፡፡ ቢሆንም፣ ዩኒቨርሲቲዎች ከብሄራዊ የልማት እቅድ ጋር የተገናኙ ምርምሮችን በማካሄድ ህብረተሰቡን ማገልገል ይኖርባቸዋል፡፡ ስለሆነም፣ የማህበረሰቡን ፍላጎት ለይቶ ምርምሮችን ለማካሄድ የሚያስችል ፈንድ ማግኘት ይቻል ዘንድ የአመራርና የአስተዳደር ሠራተኞች ጥራት እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡

| ስትራተጂዎች | አመልካቾች (መነሻና ግብ ጨምሮ) | ምንጭ |
|---|---|---|
| የዩኒቨርሲቲና የኢንዱስትሪን አጋርነት፣ ምርምርን፣ የህብረተሰብ ተሳትፎን እንደዚሁም፣ ለምርምር የሚያስፈልግን በጀት ለማጉልበት ብሄራዊና ተቋማዊ አጀንዳ መቅረጽ | ብሔራዊ የምርምርና የህብረተሰብ ተሳትፎ ማዕቀፍ ማዘጋጀት፣ | የትምህርት ስትራተጂ ማዕከል |
| | ከተቋማት የስራ ማስኬጃ በጀት ለምርምር የሚመደበው ዓመታዊ በጀት 5 በመቶ ይደርሳል፣ | ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር |
| | ከኢንዱትሪና ከአለም አቀፍ ምንጮች የሚገኘው በጀት 50 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የዩኒቨርሲቲ ሪፖርቶች |
| ብሔራዊ የምርምርና የሕብረተሰብ ተሳትፎ ማዕቀፍ ለማዘጋጀት የሚያስችል የብዙ ሴክተሮች አጋሮችን ያጣመረ ፓናል ማካሄድ፣ | | |
| ተቋማዊ ምርምርና ሕብረተሰብ የተሳተፈበት ዕቅድ ለመንደፍ የሚያስችል ብሔራዊ ፓናል ማዘጋጀት፣ | | |
| ለምርምር ስራ የሀብት አሰባሰብና አጠቃቀም ስርዓት መዘርጋት፣ | | |
| ለምርምር ስራ ህብረተሰቡን ማሳተፍና ከተቋማት ሀብት ማሰባሰብና መጠቀም የሚያስችል መመሪያ ማዘጋጀት፣ | | |
| በውድድር፣በተገቢነትና በአወንታዊ ተግባር ላይ በመመስረት ለምርምር ስራ የሚያስፈልገውን ሀብት የሚመድብ አካል መፍጠር፣ | | |
| ከውጭ ሀገራት የሚገኘውን ዝቅተኛ የምርምር ገንዘብ ከፍ ለማድረግ ዓለም አቀፋዊ አጋርነት መመስረት፣ | | |
| በብሔራዊ ደረጃ በተቀመጠው የምርምር አቅጣጫ (አጀንዳ) መሰረት ሁሉንም ዩኒቨርሲቲዎች በማሳተፍ የምርምርና የህብረተሰብ ተሳትፎ ስትራቴጂ መቅረፅ፣ ግማሽ የሚሆነውን የምርምር ገንዘብ ከኢንዱስትሪና ከዓለም አቀፍ ምንጮች ለመሰብሰብ የሚያስችል ስትራቴጂ መቅረጽ፣ | | |
| ምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት አሰጣጥን ለማጠናከር የዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎችን (የአስተዳርን ሰራተኞችን) አቅም የማጎልበት ስራ ማከናወን፣ | 40 በመቶ የዩኒቨርሲቲ መምህራን በምርምር ይሳተፋሉ፣ | የዩኒቨርሲቲ ሪፖርት |
| | 20 በመቶ የድርህረ ምረቃ ተማሪዎችና 50 በመቶ የዶክትሬት ዲግሪ ያላቸው መምህራን የሚገኙባቸው የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ቁጥር 3 ይሆናል፡፡ | የትምህርት ስትራተጂ ማዕከል |
| | የምርምር ውጤታቸው ተጠናቆ ለቴክኖሎጂ፣ ለፈጠራ ስራ የተላለፉ የምርምር ስራዎች 80 በመቶ ይደርሳል፡፡ | የዩኒቨርሲቲ ሪፖርቶች |
| | እያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ በቅርቡ የሚገኝ አንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤትን በማገዝ በትብብር ይሰራል | የዩኒቨርሲቲ ሪፖርቶች |
| የወጣት ተመራማሪዎችን በማማከርና አመራር በመስጠት አቅም የሚያጎለብቱ ቡድኖች የሚቋቋሙበትን ስርዓት መዘርጋት፣ | | |
| ለዩኒቨርሲቲዎችና ኢንዱስትሪዎች የጋራ አገልግሎት የሚሆኑ የምርምር ማዕከላትን በጋራ መመስረት፣ | | |
| ቅድሚያ በተሰጣቸው ርዕሶች ምርምር ለሚያካሂዱ ዩኒቨርሲቲዎች ተገቢ ተመራማሪዎችና ፋሲልቲዎች ማሟላት | | |
| የምርምር ዩኒቨርሲቲዎችን ለመምረጥ መስፈርቶችን ማዘጋጀትና አቅጣጫዎችን መለየት | | |
| የዩኒቨርሲቲ አባላትን በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት ስራ ለማጎልበት የሚያስችል ብሔራዊ የምርምር አስተዳደርና የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት፣ | | |
| ምርጥ የዩኒቨርሲቲና የኢንዱስትሪ ትስስርና ስልታዊ መረጃ አያያዝን፣ ተሞክሮን ለማስፋፋ የሚያስችል ዳታ ቤዝ መመስረት፣ | | |
| ለምርምርና ለማህበረሰብ አገልግሎት ብሔራዊ የቁጥጥር፣ የክትትልና የግምገማ ስርዓት መገንባት፣ | | |
| በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት አጋር አካላትን በቋሚነት ማጠናከር | በተለያየ ደረጃ የሚሳተፉ የአጋር አካላት ምክር ቤቶች ቁጥር 54 ይደርሳል፣ | የትምህርት ዕቅድ ማህከል |
| | በስራ ፈጠራ የሙከራ ማዕከላትን በማቋቋም የቢዝነስ ኢንተርፕራዞችን የሚያነቃቁ ዩኒቨርሲቲዎች 100 በመቶ ይደርሳል፣ | የዩኒቨርሲቲ ሪፖርቶች |
| | በዩኒቨርሲቲዎችና በኢንዱስትሪዎች በጋራ የሚካሄዱ የምርምር ፕሮጀክቶች 50% ይደርሳል፣ | የዩኒቨርሲቲ ሪፖርቶች |
| | ከቴክኒክና ሙያ ንዑስ ማዕከላት ጋር በትብብር ተሞክረው በስራ ላይ የሚውሉ ቴክኖሎጂዎች 500 ይደርሳሉ፣ | የዩኒቨርሲቲ ሪፖርቶች |
| በብሔራዊ ደረጃና በእያንዳንዱ ክልል የምርምርና የልማት ምክር ቤትን መመስረት | | |
| ዩኒቨርሲቲዎችና ኢንዱስትሪዎች በጋራ የምርምርና የማህበረሰብ ልማት ፕሮጀክቶችን ማቀድና መተግበር፣ | | |
| የተመረጡ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ልሕቀት ደረጃ እንዲደርሱ መርዳት፣ | | |
| የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ወይም የኮንትራት ፕሮጀክቶችን ለማሳደግ የዩኒቨርሲቲዎችንና የኢንዱስትሪዎችን/የቢዝነስ/ ግንኙነቶችን ማጠናከር፣ | | |

**ተግባር 5፡ ተቋማዊ ትብብር፣አመራርና አስተዳደር**

| ዓላማ፡- ከአገር ውስጥና ከውጭ አጋሮች ጋር በመተባበር ዩኒቨርሲቲዎች ሀብትን በአግባቡ ይጠቀማሉ፣ | አራተኛው የትምህርት ልማት መርሃ ግብር | ግብ |
|---|---|---|
| በትግበራ ኦዲት ንፁህ የሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች በመቶኛ | 0 በመቶ | 100 በመቶ |
| ብሔራዊ/አገራዊ የአመራርና የአስተዳደር መመልመያ መመሪያን ተግባር ላይ ያዋሉ ተቋማት በመቶኛ፣ | | 100 በመቶ |
| ወጭ የሚጋሩ ተማሪዎች በመቶኛ፣ | 15 በመቶ | 20 በመቶ |

**ንዑስ ተግባር 1፡ ተቋማዊ ትብብር**

በክልል፣ በብሔራዊና በአለምአቀፋዊ ደረጃ ተቋማዊ ትብብር እንዲኖር ይደረጋል፡፡ አዋሳኝ/ ተቀራራቢ የሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች የስራ ግንኙነታውን እንዲያጠነክሩ በማበረታታት ቤተ-ሙከራዎች፣ ወርክሾፖችን ቤተ-መጽሐፍቶችን በጋራ ከመጠቀም ባሻገር፣ መምህራን፣ የልምድ፣ የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ልውውጥ እንዲያዳብሩ ይደረጋል፡፡

በኢትዮጵያና በዓለም አቀፍ ተቋማት መካከል ያለውን ግንኙነት በማጠናከርና ውይይቶችን በማካሄድ የአካዳሚክ ፕሮግራሞችና የምርምር ስራዎች እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር የሚደረገው ግንኑነት በዋነኛነት ልምድ ፣ እውቀትን ፣ ቴክኖሎጂን ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ልምዶችን በመለዋወጥ ያለመ ነው፡፡ የመማርና የመመራመር ተግባርን ለማነሳሳት የመምህራንና የተማሪዎች ልውውጥ ይደረጋል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት አለማቀፋዊነትን በተመለከተ ክትትልና ግምገማ የሚያካሂድ ብሄራዊ መ/ቤት በማቋቋም ኢንተርናሽናል ኮንፈረንሶችን እንዲመራ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪ፣ እያንዳንዱ

ዩኒቨርሲቲ ኢንተርናሽናል ቢሮ (Liaison office) እንዲያቋቋምና አለም አቀፍ የትብብር ስትራተጂ ተቀርጾ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

**ንኡስ ተግባር 2፡ አመራርና አስተዳደር**

የከፍተኛ ትምህርት ስርዓትን ለማጠናከር በሥራ ልምምድና በሥራ ላይ ስልጠና ተቋማዊ አመራር እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ የዩኒቨርሲቲ ቦርድ የመሳሰሉት አገራዊና ተቋማዊ የአስተዳደር ስርዓቶች በማሻሻል የተቋማት የመወሰን ስልጣንና ኃላፊነት እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ አዲስ የቦርድ አባላትንና ነባር የቦርድ አባላትን በማጠናከር የአቅም ማጎልበቻ መርሃ ግብር ይዘረጋል፡፡ የዚህ ዋና ዓላማ መሰረታዊ የዩኒቨርስቲ አመራር መርሆችን ለመጋራት ነዉ፡፡

አገራዊና ተቋማዊ የአስተዳደር ሥርኣት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወደ ላቀ ደረጃ ይደርሳል፡፡ በዚህም መሰረት ፣ የዩኒቨርሲቲዎችን ኃላፊነት ለማጠናከር፣ ተቋማዊ የጥራት ማረጋገጫ ስርዓት ለመዘርጋተ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማዊ መዋቅሩን ለመከለስ፣ የዩኒቨርስቲ ግቢ ለተማሪዎችና ለዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ ምቹ ለማድረግ የሚያስችል ህግ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ ይህ ያልተማከለ አሠራር የዩኒቨርስቲ አመራር አካላት አብዛኛውን ጊዜያቸውን በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ከማሳለፍ ይልቅ እስትራቴጂክ በሆኑ ጉዳዮች እንዲያሳልፉ ያደርጋል፡፡

የዩኒቨርስቲ የአስተዳደር ስርዓት ከሚጠበቀው የኢኮኖሚ ደረጃ መድረሱን፣ ሀብትን በአግባቡና በብቃት መጠቀሙ፣ የትግበራ ኦዲት ተዘጋጅቶ በሁሉም ተቋማት መሰራጨቱ፣ በተቀመጠው የኦዲት ጊዜ ሁሉም ዩኒቨርስቲዎች ራሣቸውን ኦዲት የሚያደርጉባቸው መመሪያዎች ተዘጋጅተው በሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ የኒቨርስቲዎች የውስጥ ገቢያቸውን የሚያሳድጉበትና ሀብታቸውንና የውስጥ ገቢያቸውን በአግባቡ የሚጠቀሙበት ብሄራዊ መመሪያ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከአካዳሚያዊ አገልግሎት ውጭ የሆኑ የተማሪዎች አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ብሄራዊ ስትራተጂ ይዘጋጃል፡፡

ለከፍተኛ ትምህርት ለአንድ ዓመት የሚወጣው ወጪ ለአጠቃላይ ትምህርት ከሚወጣው የአንድ ዓመት ሥራ ማስኬጃ በሐያ እጅ ይበልጣል፡፡[12] ይህን ሁኔታ በመገንዘብና የግል የከፍተኛ ትምህርት አትራፊነትን ከግምት ውስጥ በማስገባት የወጭ መጋራት ፖሊሲ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ ፖሊሲው ተማሪዎች ከተመረቁ በኋላ በስራ ላይ ሲሆኑ 15 በመቶ ታክስ እንዲከፍሉ ያዛል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ከተመረቁ ተማሪዎች የሚሰበሰበው ታክስ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ የወደፊት የማስፋፋት ስራ ለመስራት አያስችልም፡፡ ይሁን እንጂ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ሂደቱን እንደገና በመፈተሽ ተማሪዎች ከምረቃ በኋላ በዝርዝር ከሚወጡ ወጭዎች በአማካይ 20% በታክስ መልክ መመለስ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እንደገና የሚከለሰው ፖሊሲ ከድሃ ቤተሰብ ለሚመጡት ተማሪዎች ልዩ ችሮታና ነፃ የትምህርት ዕድል በሰፊው ይሰጣል፡፡

<table>
<tr><th>ስትራተጂዎች</th><th>አመልካች (መነሻና ግብን ጨምሮ)</th><th>ምንጭ</th></tr>
<tr><td>በሁሉም ደረጃዎች የአመራር አቅምን ማጠናከር፣</td><td>የከፍተኛ ደረጃ አመራሮች ስልጠና 100 በመቶ ይደርሳል፣</td><td>የዩኒቨርስቲ ሪፖርቶች</td></tr>
<tr><td></td><td>የሥራ ልምምድ ስልጠና የሚወስዱ አዳዲስ ሰራተኞች 100 በመቶ ይደርሳል፣</td><td>ከዩኒቨርስቲ ሪፖርቶች</td></tr>
<tr><td colspan="3">አገራዊ የዩኒቨርስቲ ፕሬዜዳንቶችና ም/ፕሬዜዳንቶች፣ የቦርድ አባላት የአመራር ማሰልጠና ማዕከል መመስረት፣</td></tr>
<tr><td colspan="3">ለሁሉም የማሰልጠኛ ማዕከላት የሥራ ልምምድ ስልጠናና የክሂል ስልጠና ማቴሪያሎች በአገር ደረጃ ማዘጋጀት፣</td></tr>
</table>

[12] *ስሌቱ በያንዳንዱ ተማሪ የመደበኛ በጀት ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ ካፒታል በጀትን አይጨምርም*

| | | |
|---|---|---|
| የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን አገራዊና ተቋማዊ አስተዳደር ስርዓት ማሳደግ፣ | የተሻሻለውን የዩኒቨርስቲ መተዳደሪያ ሕግ የሚተገበሩ ተቋማት 100 በመቶ ይደርሳል፣ | የዩኒቨርስቲ ሪፖርቶች |
| | የጠራ የአተገባበር ኦዲት ያላቸው ዩኒቨርስቲዎች 100 በመቶ ይደርሳል፣ | የአጠቃላይ ኦዲት መስሪያ ቤት |
| | አካዳሚያዊ ባልሆኑት የዩኒቨርስቲ ግልጋሎት የሚረኩ ተማሪዎች መጠን 95 በመቶ ይደርሳል፣ | የናሙና ምልከታ |
| ከዩኒቨርስቲዎች ጋር በመተባበር በዩኒቨርሲቲ ቦርድና አመራሮች ሹመት ላይ ብሄራዊ መመሪያ በማውጣት ተግባር ላይ እንዲውል ማድረግ | | |
| የዩኒቨርስቲዎችን ተጠያቂነትና ኃላፊነት በየደረጃው ያልተማከለ ለማድረግ ሕጎችን መከለስ፣ | | |
| የዩኒቨርስቲዎችን የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ሥርዓት ለማጠናከር አገራዊ ልኬት ማዘጋጀት፣ | | |
| ለዩኒቨርስቲዎች ግቢ ውበት (መዝናኛ፣የቦታ አቀማመጥ ወዘተ.) ዝቅተኛ አገራዊ ልኬት ማዘጋጀት፣ | | |
| በዩኒቨርስቲ ግቢ ምቹ የሆነ የመማር ማስተማር ሁኔታን ለማስፈን አገራዊ ደንቦችን ማውጣትና መተግበር፣ | | |
| የከፍተኛ ትምህርት የፋይናንስ ምንጭን ማሻሻል፣ | ተቋማት ለዓመታዊው መደበኛ በጀት የሚያደርጉት አስተዋጽኦ 10 በመቶ ደርሳል | የዩኒቨርስቲ ሪፖርቶች |
| | የተማሪዎች የወጭ መጋራት መጠን ከ15 በመቶ ወደ 20 በመቶ ያድጋል፣ | የዩኒቨርስቲ ሪፖርቶች |
| ለተማሪዎች የብድር አገልግሎትና ብድር የመመለስ ሥርዓት መዘርጋት፣ | | |
| በብሎክ ግራንት መመሪያ የገንዘብ አርዳታን ማቀድ፣ መሞከር መተግበር፣ | | |
| አካዳሚያዊ ላልሆኑ የተማሪዎች አገልግሎት አሰጣጥ አማራጭ መንገዶችን ማስተዋወቅ፣ | ለተማሪዎች የመኝታ፣የጤና አገልግሎት አሰጣጥ አማራጭ አገራዊ ስልት መቀየስና መተግበር፣ | የትምህርት ስትራተጂ ማዕከል |
| | በግቢና በአካባቢ በኤች አይቪ ኤድስንና አደገኛ መድሀኒቶችና አደንዛዥ ዕጽ ችግሮች በተመለከተ ብሄራዊ መመሪያ ማውጣት | ስልታዊ የትምህርት ማዕከል |
| በዓለምአቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችና በአገራዊ ሁኔታዎች በመመስረት አካዳሚያዊ ላልሆኑ የተማሪዎች አገልግሎት አሰጣጥ ብሄራዊ ስትራተጂ ማውጣት | | |
| አካዳሚያዊ ላልሆኑ የተማሪዎች አገልግሎት አሰጣጥ አማራጮችን ለመጠቀም የሚያስችል ተቋማዊ አቅም መገንባት፣ | | |
| ዓለምአቀፋዊነትን ማስፋፋት | ከዓለምአቀፋዊ አጋሮች ጋር የሚካሄዱ የአካዳሚ መርሀ ግብሮች ምጣኔ 10 በመቶ ይደርሳል፣ | የትምህርት ስትራተጂ ማዕከል |
| | የውጭ መምህራን ምጣኔ ከ8 በመቶ ወደ 10 በመቶ ያድጋል፣ | የትምህርት አስተዳደር መረጃ ሥርዓት |
| | ከውጭ ዩኒቨርስቲዎች ጋር በጋራ የሚካሄዱ የምርምር ስራዎች 20 በመቶ ይደርሳሉ፣ | የትምህርት ስትራተጂ ማዕከል |
| በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ዓለምአቀፋዊነት ላይ አገራዊ ፖሊሲና ስትራቴጂ ማዘጋጀትና ማጽደቅ፣ | | |
| በከፍተኛ ትምህርት ዓለማቀፋዊነት ላይ የገበያ፣የቁጥጥርና የግምገማ አገራዊ ቡድን መመስረት፣ | | |
| ዩኒቨርስቲዎችን በማስፋፋትና ተቀጽላ ካምፓሶችን በመመስረት የውጭ ተማሪዎችን ለመሳብ የሚያስችል ስትራቴጂ መቅረጽና መተግበር፣ | | |
| የዩኒቨርስቲ መምህራ የውጭ ሀገር ጉብኝቶች እንዲያካሂዱና ተማሪዎች በዓለማቀፋዊ የልምድ ልውውጥ መርሀ ግብሮች እንዲሳተፉ መደገፍ፣ | | |

## 11. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን /cross-cutting issues/ በተመለከተ የቀረበ ማጠቃለያ

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሀ ግብር ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች በየንዑስ ዘርፉ ተካተው ይቀርባሉ፡፡ እነዚህ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ጎልተው ሳይታዩ ስለሚችሉ በዚህ የማጠቃለያ ምዕራፍ ተካተው እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

ይህ ምዕራፍ፣ ዘርፈ ብዙ የሆኑት ጉዳዮች በዕቅዱ መሠረት በትክክል በየንዑስ ዘርፉ መተግበራቸውን ማረጋገጥ ከማስቻሉ በተጨማሪ፣ አንባቢ እያንዳንዱ ጉዳይ እንዴት እንደሚተገበርና ዝርዝሮቹ በየትኛው የእቅድ ክፍል እንደሚገኙ በፍጥነት ማየት እንዲችል ይረዳል፡፡

ቅድሚያ ከተሰጣቸው መርሃግብሮች አንዱ በሆነው የአመራር አቅም ግንባታ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች እንዴት እንደሚስተናገዱ ስትራተጂዎችን ይዘረዝራል፡፡ በያንዳንዱ የእቅድ ሂደት የክትትልና የቁጥጥር ቡድን/ዩኒት በፌዴራልና በክልል ደረጃ ይቋቋማል፡፡ በእያንዳንዱ ዞን (አስፈላጊ ሲሆን) በወረዳ፣ በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የዚህ ዓይነት ተግባር የሚከታተል አካል በሌለበት አንድ ሰው ተመርጦ ክትትሉን እንዲያከናውን ይደረጋል፡፡ ይህ መዋቅር የኤች አይቪ ኤድስ፣የሥርዓተ ጾታና የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተወካዮች የሚያከናውኑትን ስራ የሚደግም ሳይሆን እነዚህን አካላት የሚደግፍ ነው፡፡ ለእያንዳንዱ ዘርፈ ብዙ ጉዳይ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃግብር ቅድሚያ በተሰጣቸው ፕሮግራሞች ውስጥ ለያንዳንዱ ዘርፈ ብዙ ጉዳይ የተተለመው ስትራተጂ እንደሚከተለው ነው፤

### ሥርዓተ ጾታ

በጾታ ክፍተቶች ላይ የሚያተኩሩ ስትራቴጂዎች በየቦታው ስለሚገኙ እዚህ አልተካተቱም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁሉም አመልካቾች በሥርዓተ ጾታ አስፈላጊ በሆነበት ተለይተዋል፡፡

### የልዩ ፍላጎትና አካቶ ትምህርት

በልዩ ፍላጎት ትምህርት ማሻሻል ላይ የሚያተኩሩ ስትራቴጂዎች በየቦታው ቀርበዋል ፣ ስለዚህም በዚህ ተለይተው አልቀረቡም፡፡

**ኤችአይቪ ኤድስ**

**የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት**

**ተግባር 3፡ የትምህርት ቤት ማሻሻል መርሃ ግብር**

ብቃት ያለው የተማሪዎች አገልግሎት ለመስጠት በሚወጣው ስትራተጂ ውስጥ የኤች አይቪ ኤድስ፣ የአደገኛ መድሃኒቶችና ዕጾች፣ ጤናና ሥርዓተ ምግብ ትምህርት እንዲካተት ማድረግ፤

አጋዥ መጻሕፍትንና ሌሎች ቁሳቁሶችን በተማሪዎች አገልግሎት በኩል በመስጠት የኤች አይቪ ኤድስ፣ የአደገኛ መድሃኒቶችና ዕጾች፣ ጤናና ሥርዓተ ምግብ በመሳሰሉ ርዕሶች ከተማሪዎች ጋር የመረጃ ልውውጥ ስትራቴጂ መቀየስ፣

ስለኤች አይቪ ኤድስ፣ አደገኛ መድሃኒቶችና ዕጾች በተማሪዎች አገልግሎት አማካኝነት አቻ ለአቻ ትምህርትና የሕይወት ክሕሎት ስልጠና መስጠት፣

**ተግባር 4፡ የመረጃና የግንኙነት ቴክኖሎጂ**

በዘርፈ ብዙ ጉዳዮችና ተዛማጅ ርዕሶች 'የአካባቢ እንክብካቤ' እና የመሳሰሉት መረጃዎች በዲጂታል መሳሪያዎች ማስተላለፍ፣

**ጎልማሶች**

**ተግባር 2፡ በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት የሴቶችን ተሳትፎ ማሻሻል**

የሥርዓተ ትምህርቱን ይዘቶች በፌደራልና በክልል ደረጃ ክለሳ በማድረግ ማሻሻል (ተገቢነቱን፣ ለስርዓተ ጾታ ምላሽ የሚሰጥ /ለሴቶች ቅድሚያየሚሰጥ/ እንዲሆን፣ለሕይወት ክህሎት ትኩረት በመስጠት)፣

**የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና**

**ተግባር 2፡ የሰልጣኞች ዕድገትና ተቋማዊ አቅም ግንባታ**

ስለኤች አይቪ ኤድስ፣ አደገኛ መድሃኒቶችና ዕጾች የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት መስጠት፣

## ከፍተኛ ትምህርት

### ተግባር 5፡ ተቋማዊ ትብብር፣አመራርና አስተዳደር

በዩኒቨርስቲ ግቢና አካባቢ ስለኤች አይቪ ኤድስ፣ ስለአደገኛ መድሃኒቶችና ዕጾች መከላከል በብሔራዊ/አገራዊ ደረጃ መመሪያ ማዘጋጀትና መተግበር፣

## ትምህርት በአደጋ ጊዜ

### የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት

### ተግባር 1፡ የመምህራንና የአመራሮች ልማት

ለአደጋዎችና ለችግሮች በውጤታማነት ምላሽ መስጠት እንዲችሉ ለር/መምህራን ስልጠና መስጠት፣

ለአደጋዎችና ለችግሮች በውጤታማነት ምላሽ መስጠት እንዲችሉ ለመምህራን ስልጠና መስጠት፣

ለአስቸኳይ ጊዜ "ኢትዮጵያ፡ የትምህርት የአደጋ ወቅት ልኬቶች" የሚለውን ጽሁፍ በማሳተም በሁሉም ክልሎች፤ዞኖችና ወረዳዎች እንዲሁም በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ኤጀንሲዎች እንዲሰራጨ ማድረግ፣

### ተግባር 2፡ ሥርዓተ ትምህርት፣የመማሪያና ማስተማሪያ ቁሳቁሶች

የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ማዕከሎችን፣ የጉድኝት ማዕከሎችን በአደጋ ወይም በችግር ጊዜ ትምህርት ማስቀጠል እንዲችሉ በትምህርት መርጃ መሳሪያዎች እንዲሟሉላቸው ማድረግ፣

ለአደጋ ጊዜ ለመማር ማስተማር ፓኬጅ ልኬት ማዘጋጀት፣ (ውሃ፣ ንጽህናና ጤናንም ጨምሮ)፣

### የአጠቃላይ ትምህርት ተደራሽነት

### ተግባር 2፤ አንደኛ ደረጃ

ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑ ትምህርት ቤቶች (በተለይም በድርቅ የሚጠቁ) በአደጋ ጊዜ ትምህርት ማስቀጠል የሚያስችላቸውን ስልጠና መስጠት፣የትምህርት ቁሳቁስ ማሟላት፣

**ተግባር 3፡ ሁለተኛ ደረጃ**

ለችግር ወይንም ለአደጋ ለተጋለጡ ትምህርት ቤቶች ትምህርት መስጠትና መደገፍ፣

**የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና**

**ተግባር 2፡ የሰልጣኝ ተማሪዎችንና የተቋሙን አቅም ማጎልበት**

ለአደጋ ጊዜ የሚሆን ምቹ የሆነ ስልጠና የሚሰጥበትን ሁኔታ ማመቻቸት

**የተመጣጠነ ምግብ በትምህርት ቤት**

**የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት**

**ተግባር 3፡ የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ ግብር**

ምቹና ማራኪ ሆነ የትምህርት ቤት አካባቢ ለመፍጠር የትምህርት ቤቶችን ግብዓት ማሟላት፣

ስለኤችአይቪ ኤድስ፣ አደገኛ መድሃኒቶችና እጾች፣ እንዲሁም ስለ ጤናና ሥርዓተ ምግብ ተማሪዎች በቂ መረጃ መለዋወጥ እንዲችሉ አጋዥ የንባብ መጻሕፍቶች የሚገኙበትንና የሚሰራጩበትን ስትራቴጂ መቅረጽ፣

**ተግባር 4፡ የመረጃና የግንኙነት ቴክኖሎጂ**

በዘርፈ ብዙ ወይም ቅድሚያ ትኩረት በሚሹ ጉዳዮችና 'የአካባቢ እንክብካቤ' እና የመሳሰሉ መረጀዎችን በመሰሉ ጉዳዮች ላይ በዲጂታል መሳሪያዎች ማስተላለፍ፣

**የአጠቃላይ ትምህርት አቅርቦት**

**ተግባር 1፡ ቅድመ መደበኛ ትምህርት**

የሕጻናት ጤናና ምግብ መርሃ ግብሮችን መመስረት፣ (ምግብ አጠር በሆኑ አካባቢዎች በአመዛኙ ምገባ ላይ በማተኮር፣ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ከሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር)

**ተግባር 2፡ አንደኛ ደረጃ**

አገራዊ የትምህርት ቤቶች ምገባ ስትራቴጂን ማጠናቀቅና መተግበር፣

ከድሃ ወይም ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ቤተሰቦች ለመጡ ሕጻናት የትምህርት ቁሳቁሶች፣ምግብና የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙበትን አማራጭ መፈለግ፣

**ጎልማሶች**

**ተግባር 2፡ በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርትና በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት መርሃ ግብር የሴቶችን ተሳትፎ ማሻሻል፣**

የሥርዓተ ትምህርቱን ይዘት በፌደራልና በክልለ ደረጃ በማሻሻል ለተገቢነት፣ ለሥርዓተ ጾታ፣ ለሴቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት፣እንዲሁም ለሕይወት ክህሎት ምላሽ የሚሰጥ እንዲሆን ማድረግ

**የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና**

**ተግባር 5፡ ተቋማዊ ትብብር፣ አመራርና አስተዳደር**

በዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችና በአገር ውስጥ ተጨባጭ ሁኔታዎች በመመስረት አካዳሚያዊ ላልሆኑ የተማሪዎች አገልግሎቶች አገራዊ ስትራቴጂ መቅረጽ፣

አካዳሚያዊ ያልሆኑ የተማሪዎች አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስችል ተቋማዊ አቅም መገንባትና መተግበር፣

**ከፍተኛ ትምህርት**

**ተግባር 5፡ ተቋማዊ ትብብር፣ አመራርና አስተዳደር**

በዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችና በአገር ውስጥ ተጨባጭ ሁኔታዎች በመመስረት አካዳሚያዊ ላልሆኑ የተማሪዎች አገልግሎቶች አገራዊ ስትራቴጂ መቅረጽ፣

አካዳሚያዊ ያልሆኑ የተማሪዎች አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስችል አቋማዊ ተአቅም መገንባትና መተግባር፣

**አደገኛ እጾችንና መድሃኒቶችን መከላከል፣**

**የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት**

ተግባር 3፡ የትምህርት ጥራት ማሻሻል መርሃ ግብር

ስለ ኤች አይቪ ኤድስ፣ስለ አደገኛ መድሃኒቶችና አደንዛዥ እጾች፣ ስለ ጤናና ሥርዓተ ምግብ፣ በትምህርት ቤት ለተማሪዎች የመረጃ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ስትራቴጂ መቅረጽና በብቃት መተግበር፣

ስለ አደገኛ መድሃኒቶችና አደንዛዥ እጾች፣ ስለ ጤናና ሥርዓተ ምግብ፣ ስለ ኤችአይቪ ኤድስ በቂ መረጃ ተማሪዎች መለዋወጥ እንዲችሉ አጋዥ የንባብ መጻሕፍቶችን የሚገኙበትንና የሚሰራጩበትን ስትራቴጂ መቅረጽ፣

ስለ ሕይወት ክህሎት ስልጠና፣ ስለ አደገኛ መድሃኒቶችና አደንዛዥ እጾች ግንዛቤ፣ በተማሪዎች አገልግሎቶች የአቻ ለአቻ ትምህርት መስጠት፣

**ተግባር 4፡ የመረጃና የግንኙነት ቴክኖሎጂ**

በዘርፈ ብዙ ጉዳዮችና ተዛማጅ ርእሶች (የአካባቢ እንክብካቤ በመሳሰሉት) በዲጂታል መሳሪያ እንዲሠራጩ ማድረግ

**የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና**

**ተግባር 2፡ የሰልጣኞች ልማትና ተቋማዊ የአቅም ግንባታ**

በኤች አይቪ ኤድስና በአደገኛ መድሃኒቶችና ዕጽ የግንዛቤ ማሳደጊያ ትምህርት መስጠት

**ከፍተኛ ትምህርት**

**ተግባር 5 ተቋማዊ ትብብር፣ አመራርና አስተዳደር**

በዓለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችና በአገራዊ ተጨባጭ ሁኔታ በመመስረት አካዳሚያዊ ላልሆኑ የተማሪዎች አገልግሎት አገራዊ ስትራቴጂ መቅረጽ፣

አካዳሚያዊ ላልሆኑ የተማሪዎች አገልግሎት አማራጮችን ለመጠቀም የሚያስችል ተቋማዊ አቅም መገንባት፣

**ውሃ፣ ንጽህናና ጤና**

**የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት**

**ተግባር 2፡ ሥርዓተ ትምህርት፣ የመማርና ማስተማር መሣሪያዎች**

በአስቸኳይ ጊዜ የመማርና ማስተማር መሳሪያዎች (ውሃ ንጽህናና ጤናን ጨምሮ) ፓኬጅ ማዘጋጀት፣

በአደጋ ጊዜ ለትምህርት ቤቶች ፓኬጆችን (ውሃ ጤናና ንጽህናን ጨምሮ) ማሰራጨት

**ተግባር 3፡ የትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ ግብር**

በውሃ፣ጤናና ንጽህና ልኬት በመመስረት ሪሶርስ ማሰራጨት

**ተግባር 4፡ የመረጃና የግንኙነት ቴክኖሎጂ**

በዘርፈ ብዙ ጉዳዮችና ተዛማጅ ርእሶች (አካባቢ እንክብካቤ በመሳሰሉት) መረጃን ዲጂታል መሳሪያዎች ማስተላለፍ

**የአጠቃላይ ትምህርት ተደራሽነት**

**ተግባር 1፡ ቅድመ መደበኛ**

በቅድመ መደበኛ መሰረታዊ የውሃ፣ጤናና ንጽህና ሪሶርስ ማሰራጨት፣

**ተግባር 2፡ አንደኛ ደረጃ**

በአንደኛ ደረጃ መሰረታዊ የውሃ፣ጤናና ንጽህና ሪሶርስ ማሰራጨት፣

**ተግባር 3፡ ሁለተኛ ደረጃ**

በሁለተኛ ደረጃ መሰረታዊ የውሃ፣ጤናና ንጽህና ሪሶርስ ማሰራጨት፣

# የአምስተኛው ትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ትግበራና የፋይናንስ አቅርቦት

## 12. ትግበራ ፣ ክትትልና ግምገማ

### ጠቅለላ የአሰራር ማእቀፍ

የአምስተኛው ትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ትግበራ ክትትልና ግምገማ አጠቃላይ የአሰራር ማእቀፍ ማን ምን እንደሚሰራና በምን መንገድ ስራው እንደሚሰራ በዝርዝር ቀርቧል፡፡

በማእቀፉ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የክልል ትምህርት ቢሮዎች፣ የወረዳ ትምህርት ቢሮዎችና ሌሎች የተለያዩ ድርጅቶች ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ እያንዳንዱ ቢሮ ተጠያቂነትና ሥራውን የማሻሻል ኃላፊነት አለበት፡፡ የተለያዩ መስሪያ ቤቶች ክንውኖችንና ስትራቴጅዎችን በሚያመቻቸው መንገድ እንዲተገብሩ ማእቀፉ ይፈቅዳል፡፡ በትምህርት ስርአቱ መስተካከል ያለባቸው የስትራተጂ አቅጣጫዎች ካሉ በከፍተኛው እርከን እንዲስተካከሉ ይደረጋል፡፡ የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር አላማዎች፣ ውጤቶችና ክንውኖችን በመደበኛነት ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በማእቀፉ፣ በግልጽ የሰፈሩና የሚጠበቁ አፈፃፀሞች ተዛማጅ ከሆኑ የክትትልና ግምገማ ሂደቶች አንፃር እንዲታዩ ይሆናል፡፡ በሲስተም ደረጃ የአምስተኛው ትምህርት ዘርፍ ፕሮግራም ቅድሚያ የተሰጣቸው ተግባራትን ሂደት ለመከታተል የቁልፍ ተግባራት አፈፃፀም አመላካቾች (KPI- key performance indicators) ተለይተው ወጥተዋል፡፡ እነዚህ የአፈፃፀም አመላካቾች፣ ልክ እንደ ሃገራቱ ትምህርትና ስልጠና ስርዓት በተሳትፎ፣ በተደራሽነት፣ በጥራትና በውጤት ላይ፣ በተለይም በሚከተሉት ላይ ያተኩራሉ፣

- ሁሉም፣ በተለይም ተጠቃሚ ያልነበሩ የህብረተሰብ ክፍሎች እኩል የተሳትፎ እድል እንዲኖራቸው ማድረግ
- የሁሉንም ህፃናት ፣ ወጣቶችና ጉልማሶች ፍላጐት የሚያሟላ ጥራት ያለው ትምህርት መስጠት
- እውቀትን በማሻሻልና የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማከናወን ለማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ እድገት አስተዋጽኦ የሚያደርግ ብቁ ዜጋ እንዲኖር ማድረግ

- የትምህርት እቅዱን ማስፈፀም የሚችል አመራር፣ ማኔጅሜንትና አስተዳደር በየደረጃው እንዲኖር ለማድረግ ግብአትን በተሳለጠ መንገድ ማንቀሳቀስ
- ህፃናት ፣ ወጣቶችና ጐልማሶች ተመሣሣይ የሚያደርጉዋቸውን አመለካከቶችና ልምዶች እንዲቀስሙ ማድረግና፣ ልዩነቶችን በፀጋ እንዲቀበሉ ማድረግ።

የማእቀፉ ዋና አላማ፣ በግምገማ ላይ በመመስረት ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን በየጊዜው በማሻሻል የተሻለ ውጤት እንዲመጣ ማድረግ ነው። ይህ የአፈፃፀም መከታተያ ማእቀፍ የትምህርት ተቋማት በደረሱባቸው ውጤቶች ላይ በመመርኰዝ የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ያስችላቸዋል።

**የትግበራ መዋቅሮችና ሂደቶች**

የትምህርት ዘርፉ ልማት ሚዛናዊና ፍትሃዊ እንዲሆን የትምህርት ሚኒስቴር፣ የክልል ትምህርት ቢሮዎች፣ ዞኖችና የወረዳ ጽህፈት ቤቶች በእቅድ፣ በክትትልና በግምገማ የየራሳቸውን ሚና ይጫወታሉ። ከአስር አመታት በፊት በሥራ ላይ መዋል የጀመረው ያልተማከለ አሰራር ወረዳዎች በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ከፍተኛ ኃላፊነት እንዲኖራቸው አድርጓል። በፌዴራል ደረጃ በተዋቀረው አሰራር መሠረት ከክልሎች በሚሰጣቸው ድጋፍ ወረዳዎች ኃላፊነቱን ተረክበው በመስራት ላይ ይገኛሉ።

ይህ ያልተማከለ አሰራር በቢ.ፒ.አር አሰራር ተቋማዊ መሻሻል ተደርጐበት እንዲጠናከር ሆኗል። የቢ.ፒ.አር አሰራር በየደረጃው ካለው ሠራተኛ ምን እንደሚጠበቅ በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ያለው ግንኙነት ምን መምሰል እንዳለበት በግልጽ ለማስቀመጥ የረዳ ሲሆን፣ በየተቋሙ መኖር የሚገባውን የሰው ኃይልና የስልጣን ደረጃ በመለየት የተሳለጠ አሰራር እንዲኖር ረድቷል።

**በፌዴራል ደረጃ የሚቋቋሙ አስፈፃሚ ቡድኖች**


በማዕከል ደረጃ የሚከናወኑ ሥራዎችን፣ በየዘርፉ የሚመለከታቸውን አካላት የሚያስተባብርና ከእቅድ አንጻር ክትትልና ክንውን የሚያካሂድ ቡድን ያስፈልጋል። በፌዴራል ደረጃ የሚቋቋሙ አራት ቡድኖች ከታች የተዘረዘሩትን ጉዳዮች እንዲያስፈጽሙ ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል።

1. **ብሔራዊ የአመራር ቡድን፡-** ይህ ቡድን በትምህርት ሚኒስትሩ የሚመራ ሆኖ በዓመት ሁለት ጊዜ ይገናኛል፡፡ ቡድኑ በትምህርቱ ዘርፍ የሚከናወኑ ተግባሮችን ሁሉ በበላይነት የሚመራ ሆኖ ዋና ዋና የሆኑ የስትራተጂና የአፈፃፀም መሻሻሎች ሲያስፈልጉ ውሣኔ ይሰጣል፡፡ ብሔራዊ አስፈፃሚ ቡድኑ ምክትል ሚኒስትሮች ፣ የክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊዎችን፣ የዩኒቨርስቲ ዲኖች፣ ከየክልሉ ቴክኒክና ሙያ ኃለፊዎችና ዳይሬክተሮችን በአባልነት ይይዛል፡፡ ሌሎች ጉዳዩ በቅርብ የሚመለከታቸው ህዝባዊ ወገኖች (የሙያ ማህበራት ተወካዮች) እና አጋዥ ድርጅቶችም እንዲኖሩበት ይደረጋል፡፡
2. **የንዑስ ዘርፍ ብሄራዊ አማካሪ ቡድኖች፡-** በሚመለከተው ዘርፍ ምክትል ሚኒስቴር የሚመራ ሆኖ በዓመት አራት ጊዜ ይሰበሰባል፡፡ በየዘርፉ ያሉትን ስትራቴጂዎች እየገመገመ በማሻሻል የተሻለ አፈፃፀም እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ይህ ቡድን በየዘርፉ የክልል ኃላፊዎችንና ዳይሬክተሮችን (ከከፍተኛ ትምህርት ውጭ) ያካትታል፡፡ በየዘርፉ የሚመለከታቸው ህዝባዊ ማህበራት ተወካዮችና አጋዥ ድርጅቶችም እንዲወከሉ ይደረጋል፡፡ የከፍተኛ ትምህርትን በተመለከተ፣ የክልል ተወካዮች ምትክ የፌዴራል ዳይሬክተሮች፣ የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ ተወካዮች፣ የትምህርት ስትራቴጂ ማእከልንና የዩኒቨርስቲ ዲኖችና ምክትል ዲኖች የብሔራዊ አማካሪ ቡድን አባለት ይሆናሉ፡፡ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት፣ ብሄራዊ አማካሪ ቡድን የየተቋማቱን ዲኖች ያቀፈ ሆኖ በዓመት አንድ ጊዜ ይገናኛል፡፡
3. **የንዑስ ዘርፍ የክትትል የቴክኒክ ቡድኖች፡-**ቡድኖቹ በአጠቃላይ ትምህርት እቅድና ሃብት አጠቃቀም ዳይሬክቶሬት የሚመሩ ሲሆን፣ የፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና የከፍተኛ ትምህርት የእቅድ ኃላፊዎች አባላት ይሆናሉ፡፡ እነርሱም በዓመት አራት ስብሰባዎች ያካሂዳሉ፡፡ በየክልሉ ፣ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና በዩኒቨርስቲዎች የእቅድ አፈፃፀም ሂደት በመገምገም መሠረታዊ የሆኑ የትግበራ ውሣኔዎችን ይሰጣሉ፡፡ አጠቃላይ ትምህርትን በተመለከተ የየክልሉ የፕላን ኃላፊዎች፣ ቴክኒክና ሙያን በተመለከተ የያንዳንዱ ተቋም የፕላን ኃላፊዎች፣ ዲኖችና ምክትል ዲኖች በየቡድኑ የሚካተቱ ሲሆኑ፣ በዩኒቨርስቲው ዘርፍ በፌዴራል ደረጃ ያሉ ሁሉም ሠራተኞችና የዩኒቨርስቲ ቦርዶች ተወካዮች በአባልነት እንዲኖሩ ይደረጋል፡፡

4. **የትምህርት ሥራ አፈፃፀም የቴክኒክ ቡድን፡-** ይህ ቡድን በፌዴራል እቅድና ሃብት አጠቃቀም ዳይሬክቶሬትና በአጋዥ ድርጅቶች በሚመረጥ አንድ ተወካይ በጥምር የሚመራ ሆኖ፣ ስብሰባውን በየወሩ ያካሂዳል፡፡ ቡድኑ በትምህርት ዘርፍ አጋዥ የሆኑት ሁሉንም ድርጅቶች የሚያካትት ሲሆን፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የአምስተኛው ትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብርን አተገባበር በመከታተል፣ በየዘርፉ በውጤት የተመሠረተ የሃብት ክፍፍል ላይ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

እያንዳንዱ የክትትል የቴክኒክ ቡድን፣ ቡድኑን በሚመራው ቢሮ የራሱ የሆነ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል፡፡ እነዚህ ጽ/ቤቶች የአማካሪ ቡድኖችንና የብሔራዊ አስፈፃሚ ቡድንን ስብሰባዎች የማደራጀት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በዝቅተኛ እርከን ያሉ አካላት በአተገባበር ላይ ውሣኔ መስጠት ይችላሉ፡፡ የከፍተኛ አመራር ውሣኔ የሚያስፈልግ ከሆነ፣ ጉዳዩን እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡ በአፈፃፀም መዋቅሩ የሚገኙ የላይኛውና የታችኛው አካላት ውሣኔዎችን እንዲያውቋቸው ይደረጋል፡፡

**ሠንጠረዥ 17፡ የትግበራ መዋቅር ጠቅላላ እይታ**



**የክልል አመራር ቡድኖች**

እያንዳንዱ ክልል ግልጽ የሆነ የአተገባበር መዋቅር እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡ ክልሎች አንድ ዓይነት ሞዴል መከተል ባይኖርባቸውም፣ አስፈፃሚዎቹ ሦስት ተግባሮችን ማስፈፀም መቻል ይኖርባቸዋል አመራር፣ ምክክር እና ክትትል (ጽሕፈት ቤት እንዲኖር በማድረግ)፡፡ ይህ የሚመለከተው አጠቃላይ ትምህርትንና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትን ሲሆን መዋቅሩ ከፍተኛ ትምህርትን አይመለከትም (ዘርፉ በትምህርት ሚኒስቴር የሚመራ ስለሆነ)፡፡

በአሁኑ ወቅት ያሉት መዋቅሮች በተቻለ መጠን ትግበራውን እንዲያካሂዱ ይደረጋል፡፡ ከክልል ቡድኖች የሚገኝ መረጃ በፌዴራል ደረጃ ለሚገኙት ክትትል ፣ የምክክርና የአመራር ቡድኖች እንደ ግብአት ሆኖ ያገለግላል፡፡ በትምህርት ሚኒስቴር የእቅድና ሃብት አመዳደብ ዳይሬክቶሬት ሥር የሚቋቋመው የሥራ አፈፃፀም ቴክኒክ ቡድን ጽህፈት ቤት፣ ሁሉም ክልሎችና የፌዴራል መንግሥቱ ኃላፊነታቸውን እንዲፈጽሙ የማገዝ ኃላፊነት አለበት፡፡

<u>**የየክፍሉ የስራ ስትራቴጂክ እቅዶች፣ አመታዊ የአፈፃፀም እቅዶችና ቢ.ኤስ.ሲ(BSC)**</u>

የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር ስትራቴጂክ አላማዎች ወጥ የሆነ አፈፃፀም እንዲኖራቸው እያንዳንዱ የሥራ ክፍል (ዳይሬክቶሬት) የራሱ የሆነ ስትራቴጂክ እቅድና ዓመታዊ የአፈፃፀም እቅድ ሊኖረው ይገባል፡፡ አመታዊ የአፈፃፀም እቅዶቹ የሚከናወነውን ሥራ በመዘርዘር ለዚሁ የሚያስፈልገውን በጀትና የፋይናንስ ምንጭ ይለያሉ፡፡ ይህ አሰራር በፌዴራል ፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ በተመሣሣይ መንገድ ይካሄዳል፡፡

የሥራ ክፍሎች (ደይሬክቶሬቶች) በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ የታቀዱትን ሰፋፊ አላማዎች በተግባር ለማስፈፀም የራሳቸው የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ያወጣሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት አመታዊ የአፈፃፀም እቅዶችን አውጥተው ወደታችኛው አካል በማውረድ አስተዳደሮች በየደረጃቸው በየአመቱ ማከናወን ያለባቸውን የሥራ ዝርዝሮች እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡ የሥራ ዝርዝሮቹ በድምር ሲታዩ ውጤት ያመላክታሉ፡፡

የቢ.ኤስ.ሲ. (Balanced scorecard) አሰራር ዘዴ በአሁኑ ጊዜ በሁሉም የትምህርት አስተዳደር ደረጃዎች በመተግበር ላይ ነው። ይህ ዘዴ የስትራቴጂክ እቅዱን ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ ባሉት ደረጃዎች ወደ አመታዊና ወርሃዊ የሥራ ዝርዝር የማሸጋገርያ መሣሪያ ሆኖ በማገልገል። እቅድ አውጭዎችን ምን መሠራትና ፣ ምን መለካት እንዳለበት መለየት እንዲችሉ ይረዳቸዋል፤ ኃላፊዎችም ከስትራተጂው አንፃር ክንውኖቻቸውን እንዲከታተሉ ያስችላቸዋል። በቢ.ኤስ.ሲ. የታቀዱ የሥራ ዝርዝሮች ስምምነት ከተደረሰባቸው ስትራቴጂክ አላማዎች አንፃር የተተለሙ መሆናቸውን በጥልቀት መመርመር የስፈልጋል። የቢ.ኤስ.ሲ. (BSC) አሰራር በእያንዳንዱ የሥራ ዝርዝር አንፃር የሚከተሉትን ይመረምራል፤

- በዓመቱ ውስጥ ይደረስበታል የተባለው እያንዳንዱ ግብና የሂደቱ አመላካች መለኪያዎች
- የተጠበቀውን ግብ ለመምታት የሚያስችሉ በጥንቃቄና በትኩረት የተነደፉ የሥራ ዝርዝሮች
- እያንዳንዱ ሥራ የሚወስደው ጊዜ
- በኃላፊነት የሚያስፈጽመው ክፍል ወይም ግለሰብ

**ሠንጠረዥ 18፡ አምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብርን የየወሩ የሥራ ዕቅድ ኃላፊ ድረስ ማውረድ**

የአምስተኛው ትምህርት ዘርፍ ስትራቴጂክ እቅዶች (5 አመት) → ክ/ት/ቢሮ/ከፍተኛ ት/ቴ/ክ/ዩ ዳይሬክቶሬት ስትራቴጂክ እቅዶች (5 ዓመት)

አመታዊ የትግበራ እቅድ (የአንድ ዓመት)

በ.ቢ.ኤስ.ሲ የሥራ መረጣና ትግበራ (ወርሃዊና አመታዊ)

**የክትትል፣ ዳሰሳና ግምገማ ሂደት**

አምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር በሚከተለው ውጤት ተኮር አሰራር በመመርኮዝ ከክትትልና ዳሰሳ በተጨማሪ ግምገማን በማጠናከር በአፈፃፀም ላይ የሚያተኩር አካሄድ ይኖረዋል። በቁልፍ ተግባራት አፈፃፀም አመልካቾች (KPIs) እንደተንፀባረቀው ስትራቴጂክ በሆኑ የትምህርት

ጉዳዮች ክንውን ላይ ትኩረት ይደረጋል፡፡ በትምህርት ዘርፍ ያሉት የተለያዩ ፕሮግራሞችም በመካከለኛ ደረጃ መፈፀም ያለባቸው አላማዎችና የአፈፃፀም አመላካቾች ያሏቸው ሲሆን፣ በዚህ መሠረት ክትትል ይደረግባቸዋል፡፡ የክትትል፣ ዳሰሳና ግምገማ ሂደቶቹ የተዛመዱ ፣ የቅደም ተከተል ትስስር ያላቸውና በተከታታይነት የሚካሄዱ ዓመታዊ፣ ጊዜና ሁሉን አቀፍ ናቸው፡፡ የክትትል፣ ዳሰሳና ግምገማ ሂደቱ በሁሉም ደረጃዎችና ዘርፎች ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**የእቅድ አፈፃፀምን ለመከታተል የሚያስችሉ የመረጃ ምንጮች (በተለይ በትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት (EMIS) እና በአጠቃላይ ትምህርት የጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም (GEQIP)**

የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ፕሮግራምን ለመከታተል የሚያስችሉ የመረጃ ምንጮች ተለይተው ታውቀዋል፡፡ ይሄ እስካሁን ድረስ መረጃ ያልተሰበሰበባቸውንና ሪፖርት የሌላቸውንም ይጨምራል፡፡

1. በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር ሁሉንም ንዑስ ዘርፎች ለመከታተል ቀዳሚው መረጃ የማግኛ መንገድ የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ሲስተም (EMIS) ይሆናል፡፡ ይህ ስርዓት በአራተኛው ፕሮግራም ወቅት እየተጠናከረ የሄደ ሲሆን፣ በሁሉም ትምህርት ቤቶች፣ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶችና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመታዊ መረጃ እንዲሰበሰብ አስችሏል፡፡ በየወረዳው ጽ/ቤት የኢንፎርሜሽን ሲስተሙ የተዘረጋ ሲሆን ከየወረዳዎቹ የሚገኙት የተለያዩ ትምህርት ነክ መረጃዎች ተደምረው ሃገራዊውን ስታስትቲክስ ያመለክታሉ፡፡ በጉልማሶችና ኢ-መደበኛ ትምህርት ተቋማትና በማህበረሰብ ትምህርት ማእከሎች ያለውን መረጃ አሰባሰብ ለማጠናከር ልዩ ጥረት ይደረጋል፡፡
2. በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር አጠቃላይ ትምህርት የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ስርዓት (EMIS) ከትምህርት ቤት አመራር ኢንፎርሜሽን ሲስተምና (SMIS) ከመምህራን አመራር ኢንፎርሜሽን ሲስተም (TMIS) የሚገኘውን መረጃ እንዲያካትት ተደርጐ ይስፋፋል፡፡ ብዛትና ጥራት አስተማማኝነቱ የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ሲስተም (EMIS) ከደረሰበት ደረጃ ዝቅ ያለና ለማቀድ አመቺ አይደለም፡፡ በአምስተኛው ፕሮግራም፣ በኢንፎርሜሽን ሲስተሙ የተካተቱት መጠይቆች በቀላል መንገድ ሲተነተኑ የስትራቴጂውን

ዓላማዎች ለመከታተል የሚያስችሉ ሆነው ይሻሻላሉ። ከዚህ ውጭ፣ ሌላ ቀልጣፋ አሰራር ሊዘጋጅ ቢችልም ከመሠረታዊው የትምህርት አመራር ኢንፎርሜሽን ሲስተም (EMIS) ጋር የተዛመደ መሆን ይኖርበታል።

3. ከትምህርት አመራር መረጃ ስርዓት (EMIS) መረጃ ምንጭነት በተጨማሪ የአጠቃላይ ትምህርት የጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም (GEQIP) ለክትትልና ግምገማ የሚጠቀምባቸው ሪፖርቶች ተጠቃለው ይቀርባሉ። አጠቃላይ ትምህርትን የሚመለከት በEMIS ሊገኝ ያልቻለ መረጃ በGEQIP ክትትል ማድረግ የሚቻልበት መንገድ ተለይቶ ታውቋል። ለምሣሌ፣ ኢንስፔክሽን የተካሄደባቸው ትምህርት ቤቶች ብዛት በሪፖርት መልክ ለGEQIP ይደርሳል፤ የማስተማር ፈቃድ የተሰጣቸው መምህራን ምን ያህል እንደሆኑ በGEQIP በየጊዜው ይታወቃል። ከዚህ በተጨማሪ GEQIP የተለያዩ የጽሑፍ መረጃዎች ይደርሱታል፤ ለምሣሌ፣ የመምህራን ልማት ፕሮግራምና የትምህርት ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራም ዳይሬክቶሬቶች፣ ትምህርት ቤቶች ሥራዎቻቸውን እንዴት እያካሄዱ እንደሆነ መደበኛ ሪፖርት ለ GEQIP ይልካሉ። ከዚህ ሌላ በመደበኛነት የሚካሄዱ የሥራ ቦታ ጉብኝቶች የመረጃ ተጨማሪ ግብአቶች ናቸው።

4. በብዙ ቦታዎች EMIS እና GEQIP መረጃን ለመሰብሰብ አመቺ የማይሆኑበት ምክንያት አለ። በተለይም አነስተኛ የተቋማት ግንኙነት ባለባቸው የቴክኒክና ሙያ ት/ቤቶችና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከ EMIS ውጭ በቀጥታ ለማእከለ መረጃ ማስተላለፋቸው የተለመደ አሰራር ነው። እነዚህ መረጃዎች ለአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ እንዴት ክትትል ተጨማሪ ግብአቶች ናቸው።

5. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የአለም ባንክ የሚጠቀምባቸው የአገልግሎት አሰጣጥ አመልካቾች እና የመሳሰሉት ጥናቶችና ግምገማዎች በእርዳታም ይሁን በክፍያ ለዚሁ አገልግሎት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ይቻላል። አጋዥ ድርጅቶችም በተለያየ ጊዜ የፕሮግራም ግምገማ እንደዚሁም የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋሉ።

ምንም መረጃ ያልተገኘበት ሁኔታ ሲፈጠር፣ ትምህርት ሚኒስቴር መረጃው የሚገኝበትን ዘዴ ይፈልጋል፡፡ ብቁ የሆነ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሥራ ላይ እንዲውል ከተደረገ፣ የእቅድ ትግበራው ሲጀምር የአጭር ጊዜ ዳሰሳዎችና ሪፖርቶች በተቀናጀ መልኩ የሚገለፁበት መሠረታዊ አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡ የመረጃ አሰባሰብ ስርአቱ ምን ያህል ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ከወረዳና ክልል ትምህርት ቢሮዎች ጋር ምክክር ይደረጋል፡፡ በእቅዱ መሠረት በየአመቱ ሊከናወኑ የሚገባቸው ግቦች ከተመዘገበው የመነሻ ወለል ይጀምራሉ፣ የተሰበሰቡት መረጃዎች እድገቱንና ሂደቱን ለመለካት የማያስችሉ ከሆኑ መለኪያዎቹ ውድቅ እንዲሆኑ ወይም እንዲሻሻሉ ይደረጋል፡፡

**በማእከልና በየደረጃው የሚከናወኑ የየእለት ክትትሎች**

በአምስተኛው ትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር በየአመቱ መተግበር ያለባቸውን እቅዶችና ግቦች አፈፃፀም ለመከታተል በየወሩ ስብሰባዎች ይካሄዳሉ፡፡ ትምህርት ሚኒስቴርና ክልሎች (የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ኤጀንሲን ጨምሮ) በአምስተኛው መርሃ ግብር ከተዘረዘሩት ዋና ዋና የአፈፃፀም አመላካቾች (KPI) አንፃር የተገኙትን ውጤቶች በየሦስት ወሩ ሪፖርት ያዘጋጃሉ፡፡ ሪፖርቶቹ እያንዳንዱ የክትትል ቴክኒካል ቡድን ጽ/ቤት በሚያወጣው መመርያና መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በመጠቀም ሥራ ፈፃሚ አካላቱ በየሦስት ወሩ የሚያቀርቡትን ሪፖርት ያጠቃለለ ይሆናል፡፡

ሪፖርቶቹ፣ ዩኒቨርስቲዎች ፣ የቴክኒክና ሙያ ተቋማትና ወረዳዎች ለየራሳቸው ከመስፈርቶቹ አንጻር የደረሱበትን ደረጃ የሚያመላክቱ፣ በእቅድና በአፈፃፀም መካከል ልዩነቶች ካሉም በምን ምክንያት ሊፈጠሩ እንደቻሉ መግለጫ የያዙ መሆን ይገባቸዋል፡፡ እነዚህ የሦስት ወር የክትትለ ሪፖርቶች የእቅዶች የአፈፃፀም ሂደት፣ የትግበራ ክንውኖች፣ የተገኘ የውጤት፣ በጀት አጠቃቀምና በቀጣይ ምን መከናወን እንዳለበት በሚሉ ነጥቦች ላይ ያተኩራሉ፡፡

ሪፖርቶቹን እያንዳንዱ የቴክኒክ ተቆጣጣሪ ቡድን መሪ እንዲረከባቸው ይደረጋል፡፡ ይህ የሚደረገው ሂደቱን ለመገምገም፣ ችግሮችን አይቶና እንከኖችን ለይቶ ማስተካከያ እርምጃዎችን ለመጠቆም ነው፡፡ እያንዳንዱ ሪፖርት በቴክኒክ ተቆጣጣሪው ቡድን ከታየ በኋላ የንዑስ ሴክተር ሪፖርቱ ለሚመለከተው

ብሔራዊ አማካሪ ቡድን ይቀርባል፡፡ ሪፖርቱ ለከፍተኛ ውሣኔ አሰጣጥ እንደግብአት ሆኖ ያገለግላል፡፡ ብሔራዊ የአማካሪዎች ቡድን ሪፖርቶቹን ከተመለከተ በኋላ የተገኙትን ውጤቶች ከአስተያየት ጋር በጠቅላላ የትምህርት የቴክኒክ ስራ ቡድን ዋና ፀሀፊ ተዘጋጅቶ ለብሔራዊ ስቲሪንግ ኰሚቴ ይቀርባል፡፡

እያንዳንዱ የሩብ ዓመት የተሻለ አፈፃፀም እንዲኖረው  ሊከተላቸው የሚገቡ አምስት(5) አስፈላጊ ደረጃዎች አሉ፡፡ እነዚህም፡-

ሀ. ከዋና ዋና የአፈፃፀም አመላካቾች አንፃር የተከናወኑ ሥራዎችን በማስመልከት ትምህርት ሚኒስቴርና ክልሎች ሪፖርቶችን ያዘጋጃሉ፡፡

ለ. የንዑስ ሴክተሮችን እንቅስቃሴ ለመመልከት የቴክኒክ ተቆጣጣሪ ቡድኖች ይገናኛሉ፡፡

ሐ. የተካሄዱ  አንቅስቃሴዎችን የሚዘረዝር (ከብሔራዊ ቁልፍ የክንውን አመልካቾች አንፃር) እንዲሁም ብሔራዊ አማካሪ ቡድኖች ሊፈጽሙዋቸው የሚገቡ ነጥቦችን የሚጠቁም አንድ የተጠናከረ የንዑስ ሴክተር ተቆጣጣሪ ሪፖርት ይቀርባል፡፡

መ. ብሔራዊ አማካሪ ቡድኖች የንዑስ ሴክተሩን እንቅስቃሴ ለመመልከት ይገናኛሉ፡፡

ሠ. የተካሄዱ እንቅስቃሴዎችን (ከብሔራዊ ቁልፍ የክንውን አመልካቾች አንፃር) የሚዘረዝርና መከናወን የሚገባቸውን ነጥቦች የሚጠቁም የተጠናከረ የሴክተር ተቆጣጣሪ ሪፖርት ለብሔራዊ የስትሪንድ ኰሚቴ ይቀርባል፡፡

የብሔራዊ ስትሪንግ ኰሚቴው በየስድስት (6) ወሩ ይገናኛል፡፡ (ረ) ከዚህ በታች የሚገኘው ሠንጠረዥ (ከሀ-ረ የተመለከቱትን እንቅስቃሴዎች) በወር ሁለት (2) ጊዜ የሚሠሩ ቀጣይነት ያላቸውን ክንውኖች የሚጠቁም ሲሆን፣ ጠንካራ አፈፃፀም ሊኖር የሚችለው በእያንዳንዱ ሩብ ዓመት መፈፀም ያለባቸው በቅደም ተከተላቸው ሲከናወኑ ብቻ ይሆናል፡፡ እንዲህ የተጨናነቀ ፕሮግራምን ለማሣካት በየደረጃው ያሉ የቴክኒክ ተቆጣጣሪ ዋና ፀሀፊዎች መስዋዕትነትንና ጠንካራ የስራ ግንኙነትን ይጠይቃል፡፡

**ሠንጠረዥ 19፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር የክትትልና ትግበራ መርሐግብር**

| ወር | በወሩ መጀመሪያ አጋማሽ የሚከናወኑ ስራዎች | በወሩ ሁለተኛ ግማሽ የሚከናወኑ ስራዎች |
|---|---|---|
| 1 | (ሀ) ሩብ 1 | (ለ) ሩብ 1 |
| 2 | (ሐ) ሩብ 1 | (መ) ሩብ 1 |
| 3 | (ሠ) ሩብ 1 | (ሀ) ሩብ 2 |
| 4 | (ለ) ሩብ 1 | (ሐ) ሩብ 2 |
| 5 | (መ) ሩብ 1 | (ሠ) ሩብ 2 |
| 6 | (ረ) ግማሽ 1 | |
| 7 | (ሀ) ሩብ 1 | (ለ) ሩብ 3 |
| 8 | (ሐ) ሩብ 1 | (መ) ሩብ 3 |
| 9 | (ሠ) ሩብ 1 | (ሀ) ሩብ 4 |
| 10 | (ለ) ሩብ 1 | (ሐ) ሩብ 4 |
| 11 | (መ) ሩብ 1 | (ሠ) ሩብ 4 |
| | (ረ) ግማሽ 2 | |

**የጣምራ ምልከታ ተልዕኮና  የአመታዊ ምልከታ ስብሰባዎች ከባለድርሻ አካላት ጋር**

በመንግሥት አካላትና በለጋሽ ድርጅቶች ጥምረት በየአመቱ የምልከታ ተልዕኮው መካሄድ ይኖርበታል፡፡ በትምህርት ቴክኒክ ስራ ቡድን በሚወሰነው መሠረት በተመረጡ ጉዳዮች ላይ በማተኰር ውይይት ይደረጋል፡፡ በጥናትና ምርምር ከሚገኘው መረጃ በመመስረት በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር በታቀደው መሠረት ክንውኖችን መገምገም ያስፈልጋል፡፡

ይህ አመታዊ የምልከታ ስብሰባ መንግሥትና ባለድርሻ አካላት በሥራ ላይ ያጋጠሙትን ችግሮች እንዲመለከቱ ከማስቻሉ በተጨማሪ የመርሃ ግብሩ ስትራቴጂዎች እና አላማዎች ላይ በአገር አቀፍ ደረጃ መግባባት እንዲኖር እድል ይፈጥራል፡፡ እያንዳንዱ አመታዊ የምልከታ ስብሰባ ለቀጣዩ አመት አመታዊ የትግበራ እቅድና በጀት መሠረት ሆኖ እንዲያገለግል ይጠበቃል፡፡ የጣምራ ስብሰባው በየወሩ ከሚዘጋጁት የብሔራዊ ስቲሪንግ ኰሚቴ ስብሰባዎች ከአንዱ ጋር እንዲገናኝ ተደርጎ እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

የፌዴራል ቴክኒክ ተቆጣጣሪ ቡድን ዋና ፀሐፊ አመታዊው የምልከታ ስብሰባ ላይ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን የማዘጋጀትና የማስተባበር ኃላፊነት አለበት፡፡ በየስድስት ወሩ የሚዘጋጀውን ሪፖርት መሠረት በማድረግ አንድ ወጥ የሆነ ዓመታዊ ሪፖርት ለብሔራዊ ስቲሪንግ ኰሚቴ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

**የአጋማሽ ወቅትና የመጨረሻ ግምገማ**

በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ወቅት ትኩረት በደረገባቸው ግቦች ሁሉ በቋሚነት ቁጥጥር የተደረገ ቢሆንም የግምገማ ሂደቱ ውሱንነት ነበረው፡፡ ቀጣይ አላማዎችንና ማስተካከያዎችን ለማስተዋወቅ የተደረገ የአጋማሽም ሆነ የመጨረሻ ግምገማ አልተካሄደም፡፡ በአራተኛው የትምህርት ሴክተር ልማት ወቅት የነበረውን መርሃ ግብሩን ከአጠቃላይ ብሔራዊ የልማት ዓላማዎች ጋር አስተሳስሮ ያለማዬት ችግር በአምስተኛው ፕሮግራም እርምት ይደረግበታል፡፡

አምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ከ2008 - 2012 ዓ.ም ይተገበራል፡፡ በሁለተኛው አመት ጣምራ ምልከታ ተልዕኮና አመታዊ የምልከታ ስብሰባ ወቅት ወሳኝ የሆኑ አካላት እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡ ይህ የአጋማሽ ወቅት ምዘና የሚካሄደው 2009 ዓ.ም ሁለተኛው አጋማሽ ላይ ሲሆን፣ የመጨረሻው ምዘና ደግሞ በ2011 ዓ.ም የመጀመሪያ አጋማሽ የሚከናወን ይሆናል፡፡ አስፈላጊ ማስተካከያዎች እንዲደረጉና ለቀጣዩ የሴክተሩ አላማዎች አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው ለማድረግ የአጋማሹ እና የመጨረሻው ምዘና የሚተነትኑ ሪፖርቶች በየደረጃው ላሉት ሁሉ እንዲቀርቡ ይደረጋሉ፡፡

በ2009 የሚካሄደው የጣምራ ምልከታ ተልዕኮና አመታዊ ግምገማ ከታች በተዘረዘሩት ዋና ዋና የክንውን አመላካቾች መሠረት ይሆናል፡፡ ለዚህ ምዘና የሚያገለግሉ አቅጣጫ ጠቋሚ ነጥቦች የሚወሰዱት ለብሔራዊ አማካሪው ቡድን ከሚቀርቡት ቋሚ የአፈፃፀም ሪፖርቶች ውስጥ ነው፡፡ ይህ ምዘና የትምህርትን ውጤታማነት፣ ጥቅም ፣ ወጪ ቅነሣንና ዘላቂነትን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሲሆን፣ በመጨረሻዎቹ ሶስት የትግበራ አመታትም መወሰድ ያለባቸውን የማስተካከያ እርምጃዎች የሚጠቁም ይሆናል፡፡

በ2011 ዓ.ም የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ የሚደረገው የመጨረሻ ምዘና በውጭ ተቋራጭ የሚከናወን ሲሆን፣ እያንዳንዱ የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ዋና የክንውን አመልካቾችን የሚገመግም ይሆናል፡፡ ለዚህ ምዘና የሚያገለግሉ አቅጣጫ ጠቋሚና ወሣኝ ነጥቦች ለብሔራዊ አማካሪ ቡድኑ ከሚቀርበው ቋሚ የአፈፃፀም መመዘኛ ሪፖርት የሚወሰዱ ሲሆን ውጤቶቹም ብሔራዊ የስቲሪንግ ኮሚቴው በአጋማሽ ምዘና ወቅት አቅጣጫ በሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ የተመሠረቱ ይሆናሉ፡፡ የዚህ ሙከራ አላማም ከአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም አተገባበር ጠቃሚ ትምህርትን መዞ በመውጣት ስድስተኛውን የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራምን ለመቅረጽ የሚያገለግሉ አቅጣጫ ጠቋሚ ነጥቦችን ለማወቅ ነው፡፡ የትምህርት ውጤታማነት፣ ጥቅም፣ ወጭ ቅነሣ እና ዘላቂነት በዚህ ምዘና ከግምት ውስጥ የሚገቡ ዋና ዋና ነጥቦች ናቸው፡፡

ከነዚህ ውስጣዊ ሪፖርቶች በተጨማሪ፣ የትምህርት ሚኒስቴር የዕቅድና የሀብት ስምሪት ዳይሬክቶሬት በፍላጐት ላይ የተመሠረቱ የአጭር ጊዜ ጥናቶችን ያዘጋጃል፡፡ ከጥናቶቹ የሚገኘው ውጤት የብሔራዊ

አማካሪ ቡድኖችንና የብሔራዊ ስቲሪንግ ቡድን በሚያደርጓቸው የፖሊሲ ደረጃ ስብሰባዎች እንደ ግብዓትነት ያገለግላሉ፡፡ እነዚህ የአጭር ጊዜ ጥናቶች የሚያገለግሉት (ሀ) ፕሮግራሞቹን በተቀናጀ መልኩ በማጥናት የፈጠራ ችሎታን ለማጎልበትና አስተማሪ የሆኑትን ለቀጣይ ዕቅድና የልማት ፕሮግራም ግብአት እንዲሆኑ ለማድረግ  (ለ) አፈፃፀምን ከተለያዩ መመዘኛዎች አንፃር ለመመዘንና የናሙና ጥናት የሚያስፈልጋቸውን ለመለየት ፣ እንደዚሁም በትምህርት አመራር መረጃ ስርዓት በመደበኛነት ክትትል የማይደረግባቸውን ጉዳዮች ለመለየት እና (ሐ) በትምህርት አመራር መረጃ ስርዓቱ የተገኙ ልኬቶችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ነው፡፡

**ዋና ዋና የአፈፃፀም አመላካቾች** (key performance Indicators)

የሥራ አፈፃፀምን መረጃ መሰብሰብ መጠቀምና ከዋና ዋና አመላካቾች አንፃር መተንተን የክትትልና ግምገማው ስርዓት መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር የሚጠበቁ ዋና ዋና ውጤቶች በተደራጁ አመላካች መስፈርቶች አንፃር ይመዘናሉ፡፡ ዋና ዋና የአፈፃፀም አመላካቾቹ የተደራጁት ከስትራቴጂክ የትምህርት ውጤቶች አንፃር ነው፡፡ እነዚህ አመላካቾች ቅድሚያ ከተሰጣቸው ግቦች አንጻር የተነደፉ ሲሆን በአራተኛው የትምህርት ሴክተር ፕሮግራም ወቅት በጥቅም ላይ የዋሉ (ቀጣይ ክትትል እንዲኖር ስለሚያስችል) እና ሌሎች በተለይ ለአምስተኛው ፕሮግራም ጠቃሚ ናቸው የተባሉ ናቸው፡፡ ዋና ዋና የአፈፃፀም አመላካቾቹ ጉዳዩ በሚመለከታቸው አካላት፣ በህብረተሰቡ እና በልማት አጋሮች ስምምነት የተደረገባቸው ናቸው፡፡

መስፈርቶቹ በቁጥር ውስን ቢሆኑም (እየተገነባ ያለውን የቁጥጥርና የግምገማ አሠራርን ለማጎልበት እና የአስተዳደር ሂደቱን ቀላል ለማድረግ ሲባል) አስተማማኝ በሆነ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገድ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፣ መስፈርቶቹ የአምስተኛውን የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር የተለያዩ ግቦች (ለምሣሌ የተሻሻለ የትምህርት ተደራሽነት ፍትሃዊነት ጠቀሜታ፣ ጥራትና የተሻለ አመራር) እንዲያንፀባርቁ በማድረግ ወጥ የሆነ የክትትል ስርዓት እንዲኖር የሚያስችሉ መስፈርቶች ናቸው፡፡ ዋና ዋና የአፈፃፀም አመላካቾቹ ሠንጠረዥ የመርሃ ግብሩን የየአመቱ ግቦች የሚያሳይ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱም የፆታ ስብጥርን ያመላክታል፡፡

**ሠንጠረዥ 20፡ የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር የዋና ዋና አፈፃፀም አመልካቾች (KPI) (እንደአስፈላጊነቱ በፆታ ተለይተዋል)**

| KPI (ዋና ዋና የአፈፃፀም አመልካቾች) እንደአስፈላጊነቱ በፆታ ተለይተዋል | መነሻ (ካልተጠቀሰ በቀር -2006 ዓ.ም) | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **ፋይናንስና አመራር** | | | | | | |
| ለትምህርት ስልጠና በመንግሥት የተመደበ በመቶ | 23.3 (2012/13) | 25.0 | 25.0 | 25.0 | 25.0 | 25.0 |
| ሁሉም አካላት የሚተገብርዋቸው የሁሉ ተኰር ጉዳዮች አመታዊ እቅዶች | የለም | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ለእቅድና አመራር አገልግሎት የትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ የሚቀበሉ | 0 | 10 | 20 | 30 | 40 | 50 |
| የስትራቴጂ ዕቅድ ያላቸው የ5ኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ተግባሪ "አህዶች"(የፌዴራል ዳይሬክቶሬቶች፣ የቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ የክልል ትምህርት | የለም | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቢሮዎች እና ቴ/ሙ/ኤጀንሲዎች፣ ዩኒቨርስቲዎች) | | | | | | |
| **ተደራሽነት** | | | | | | |
| የቅድመ አንደኛ ደረጃ የተማሪ ቅበላ በመቶኛ | 33/35 | 48/50 | 56/58 | 64/65 | 72/73 | 80/80 |
| የአንደኛ ክፍል የተጣራ ቅበላ በመቶኛ | 102/109 | 102/107 | 101/105 | 100/103 | 99/100 | 98/98 |
| ከክፍል 1-4 አማራጭ የመሠረታዊ ትምህርትን ጨምሮ አጠቃላይ የተማሪ ቅበላ በመቶኛ | 131/143 | 122/132 | 120/129 | 118/124 | 116/120 | 115/115 |
| ከክፍል 1-4 አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጨምሮ የተጣራ ቅበላ በመቶኛ | 104/112 | 104/110 | 130/107 | 102/105 | 101/103 | 100/100 |
| ከክፍል 5-8 አጠቃላይ የተማሪ ቅበላ በመቶኛ | 63/65 | 67/70 | 74/75 | 82/83 | 90/90 | 95/95 |
| ከክፍል 5-8 የተጣራ የተማሪ ቅበላ በመቶኛ | 50/49 | 53/52 | 56/55 | 59/59 | 62/62 | 65/65 |
| ከክፍል 1-8 በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አጠቃላይ የተማሪ ቅበላ በመቶኛ | 98/105 | 93/102 | 96/103 | 99/105 | 102/106 | 106/106 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ከክፍል 1-8 በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የተጣራ ቅበላ በመቶኛ | 90/95 | 91/95 | 93/96 | 94/96 | 96/97 | 98/98 |
| ከክፍል 9-10 አጠቃላይ የተማሪ ቅበላ በመቶኛ | 37/40 | 41/44 | 48/50 | 55/55 | 62/62 | 74/74 |
| ከክፍል 9-10 የተጣራ ቅበላ በመቶኛ | 21/20 | 24/24 | 28/28 | 34/34 | 41/41 | 47/47 |
| ለቴክኒክና ሙያ መደበኛ ስልጠና የተመለመሉ ተማሪዎች ብዛት | 265/45 | 280006 | 304775 | 365154 | 447248 | 564054 |
| የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች አጠቃላይ የተማሪ ቅበላ በመቶኛ | 6/13 | 7/13 | 8/14 | 10/15 | 12/16 | 14/17 |
| አድሜያቸው ከ15-60 የሚሆኑ የ2 አመት የተቀናጀ የጎልማሶች ትምህርት የተከታተሉ | 0/0 | 30/55 | 47/67 | 79/87 | 98/99 | 100/100 |
| **ብቃት** | | | | | | |
| ከ1ኛ ክፍል አቋርጠው የሚወጡ በመቶኛ | 23/21 | 20/19 | 17/15 | 13/12 | 9/8 | 5/5 |
| ከ1ኛ -8ኛ ክፍል ባለው አቋርጠው የሚወጡ በመቶኛ | 11/21 | 10/10 | 9/9 | 7/7 | 4/4 | 2/2 |
| ከ1ኛ -8ኛ ክፍል የሚደግሙ | 8/9 | 7/7 | 6/6 | 4/5 | 3/3 | 2/2 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| እስከ 5ኛ ክፍል የሚደርሱ | 57/54 | 59/57 | 62/61 | 64/63 | 68/68 | 70/70 |
| 8ኛ ክፍልን የሚያጠናቅቁ | 47/47 | 50/50 | 55/55 | 61/61 | 67/67 | 74/74 |
| በኢንዱስትሪ ማስፋፊያ አገልግሎቶች የተደገፉ ጠቅላላ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች | 428529 | 429608 | 430864 | 437337 | 448008 | 464169 |
| ዩኒቨርስቲ ላይ አንደኛ አመት የሚጨርሱ | የለም | 95/95 | 95/95 | 95/95 | 95/95 | 95/95 |
| **ጥራት** | | | | | | |
| በህፃናት እንክብካቤ ትምህርት ዲፕሎማ ያላቸው የቅድመ አንደኛ ደረጃ መምህራን | 0/0 | 0/0 | 2/2 | 5/5 | 9/9 | 15/15 |
| ብቃት የሚያሟሉ 1-4ኛ ክፍል መምህራን ድርሻ በመቶኛ | 63/48 | 70/58 | 77/68 | 84/79 | 92/89 | 100/100 |
| ፈቃድ የተሰጣቸው የ1-12ኛ ክፍል መምህራን በመቶኛ | 0/0 | 10/10 | 21/21 | 38/38 | 55/55 | 70/70 |
| በደረጃ 3 ወይም ከዛ በላይ የሚገኙ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች በመቶኛ | 21 | 29 | 37 | 44 | 52/60 | |
| በደረጃ 3 ወይም ከዛ በላይ የሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በመቶኛ | 30 | 36 | 42 | 48 | 54 | 60 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| KPI ቁልፍ የክንውን አመልካቾች (ሁሉም ዓላማዎች እንደአስፈላጊነቱ ሴት/ወንድ ተብለው ተገልጸዋል | መሠረታዊ መነሻ (ካልተጠቀሰ 2006 ውስድ) | | | | | |
| የስርጭትና የዲጂታል ቴክኖሎጂ ድጋፍ ተደራሽነት ያላቸው (ከ1-12) ያሉ ት/ቤቶች በመቶኛ | 46 | 53 | 63 | 73 | 79 | 83 |
| ብቃታቸው በፈተና የተረጋገጠ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ያጠናቀቁ በመቶኛ | 60 | 63/63 | 66/66 | 69/69 | 72/72 | 75/75 |
| ቅድሚያ በተሰጣቸው ሴክተሮች የቴ/ሙ/ስልጠና የሥራ ደረጃ የፀደቀላቸው | 650 | 701 | 738 | 775 | 812 | 850 |
| በዩኒቨርስቲዎች ያለው የመምህራን ስብጥር (የመጀመሪየ ፣ የሁለተኛ ፣ የሶስተኛ ዲግሪ) | 27፡58፡15 | 22፡60፡18 | 16፡63፡21 | 11፡65፡24 | 5፡68፡27 | 0፡70፡30 |
| **ፍትሐዊነት** | | | | | | |
| የፆታ ስብጥር አመልካች በቅድመ አንደኛ ደረጃ በመቶኛ | 0.95 | 0.96 | 0.97 | 0.98 | 0.99 | 1.00 |
| የፆታ ስብጥር አመልካች ከ1ኛ -8ኛ | 0.93 | 0.94 | 0.95 | 0.96 | 0.98 | 1.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ክፍል በመቶኛ | | | | | | |
| የፆታ ስብጥር አመልካች ከ9ኛ - 12ኛ ክፍል በመቶኛ | 0.91 | 0.92 | 0.94 | 0.96 | 0.98 | 1.00 |
| በቴክኒክና ሙያ ትምህርት የሴቶች ድርሻ በመቶኛ | 51 | 50 | 50 | 50 | 50 | 50 |
| ወደ ዩኒቨርስቲ ከሚገቡ ተማሪዎች ውስጥ የሴቶች ድርሻ በመቶኛ | 32 | 34 | 36 | 38 | 41 | 45 |
| የተቀናጀ የጎልማሶች ትምህርት (የሁለት አመት ስልጠና) ውስጥ የሴቶች ድርሻ በመቶኛ | የለም | 56 | 62 | 67 | 69 | 70 |
| በልዩ ፍላጎት ትምህርት የህፃናት ቅበላ (ከ1ኛ -8ኛ ክፍል) | 4 | 18 | 32 | 47 | 61 | 75 |
| በልዩ ፍላጎት ትምህርት የተማሪዎች ቅበላ (ከ9ኛ -12 ክፍል) | 7 | 15 | 22 | 30 | 37 | 45 |
| ሴቶች በትምህርት አመራር ላይ ያላቸው ድርሻ (በርዕሰ መምህርነትና ሱፐርቫይዘርነት) በመቶኛ | 8 | 9 | 10 | 13 | 16 | 20 |
| **ውጤቶች** | | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ከመደበኛ በታች"ወይም በላይ የሆነ ቋንቋ የማንበብና መረዳት ደረጃ ይዘው የሚመጡ የ2ኛ ክፍል ተማሪዎች በመቶኛ | ሠንሠረዥ 7ን ይመልከቱ | | 60/60 | | | 95/95 |
| መደበኛ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ቋንቋን የማንበብና መረዳት ደረጃ ይዘው የሚመጡ የ2ኛ ክፍል ተማሪዎች በመቶኛ | ሠንሠረዥ 7ን ይመልከቱ | | 40/40 | | | 70/70 |
| በዝቅተኛ ክፍል የሂሣብ ትምህርት ዳሰሳ መደበኛና ከዚያ በላይ ያገኙ ተማሪዎች በመቶኛ | | | | | 70/70 | |
| በብሔራዊ ትምህርት ምዘና 50% እና ከዚያ በላይ ያስመዘገቡ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች (ድምር ውጤት) በመቶኛ | 25 (2012) | 35/35 | | | | 50/50 |
| በብሔራዊ ትምህርት 50% እና ከዚያ በላይ ያስመዘገቡ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ( ድምር ውጤት ) በመቶኛ | 8 (2012) | 30/30 | | | | 50/50 |
| በብሔራዊ ትምህርት ምዘና 50% እና ከዚያ በላይ ያስመዘገቡ የ10ኛ | 23 | | | 50/50 | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ክፍል ተማሪዎች (አማካይ ውጤት) በመቶኛ | | | | | | |
| በብሔራዊ ትምህርት ምዘና 50% እና ከዚያ በላይ ያስመዘገቡ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች (አማካይ ውጤት) በመቶኛ | 34 | | | 70/70 | | |
| በ10ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና (ማለፊያ ነጥብ) 2.0 ወይም ከዚያ በላይ ያስመዘገቡ ተማሪዎች በመቶኛ | 64/76 (2014/15) | 68/78 | 73/81 | 78/84 | 84/87 | 90/90 |
| በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ፈተና ወቅት 350 (ማለፊያ) እና ከዛ በላይ ያመጡ ተማሪዎች (የተፈጥሮ ሣይንስት ስትሪም) | 41/51 (2014/15) | 47/56 | 54/61 | 61/66 | 68/71 | 75/75 |
| በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና 350 (ማለፊያ) እና ከዛ በላይ ያመጡ ተማሪዎች በመቶኛ (የማህበራዊ ሣይንስ ስትሪም) | 21/32 | 28/37 | 35/42 | 42/47 | 49/52 | 56/57 |
| በእሴት ሠንሠለት ትንተና ተለይተው ለጥቃቅንና አነስተኛ | 2627 | 3252 | 3623 | 4066 | 4635 | 5442 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ኢንተርፕራይዞች የተላለፉ ቴክኖሎጂዎች ብዛት | | | | | | |
| በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቀው በ12 ወራት ውስጥ በተማሩት ትምህርት ቅጥር ያገኙ ተማሪዎች ድርሻ በመቶኛ | የለም | 80 | 80 | 80 | 80 | 80 |

## 13. የፋይናንስ አደረጃጀት

አምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ለማስተግበር የሚያስፈልገው ወጪ የተለያዩ ዘርፎች አሉት፡፡ እነዚህም እንደሚከተለው ይመደባሉ፣

- በፖሊሲ ዓላማዎች በመመስረት የቅበላና የውስጥ ብቃት ግቦችን በመገመት
- ተፈላጊ ግብዓትን ከግምት በማስገባት (ለምሣሌ የተማሪ /ክፍል ጥመርታ ወይም የተማሪ/ መጽሐፍት ጥመርታ)
- የአንዳንድ ግዥዎች ዋጋና በአምስት ዓመት ሊኖራቸው የሚችለው ጭማሪ በግምት ውስጥ በማስገባት (ለምሣሌ፣ ደመወዝ)

የቅድሚያ ፕሮግራሞቹ ዝርዝር የተለያዩ ግቦችን ጠቅሷል፡፡ እነዚህን ግቦች መሠረት በማድረግ ለአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም የሚያስፈልገው ጠቅላላ ወጪ በንዑስ ዘርፍና በመደብ በመከፋፈል ግምት ላይ ተደርሷል፡፡ ከዚህ በመነሳት፣ ሊገኝ የሚችለው የፋይናንስ ትንበያም ተደርጓል፡፡ ይህም የፋይናንስ ክፍተቱን ለማወቅ ይረዳል፡፡ የአጠቃላይ ትምህርት ፋይናንስ ሽፋን ኃላፊነትን የሚወስዱት በአብዛኛው ክልሎች በመሆናቸው ትግበራው ክልሎችና ወረዳዎች በሚኖራቸው ሚና ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡

በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር በፋይናንስ ምንጭ አንፃር የነበረው አካሄድና ወደፊት (2015) የሚጠበቀው ህዝብ በትምህርት ወጪ የህዝብ ተሳትፎን (Education public expenditure Review) ዳሰሳ የትምህርት ፋይናንስ ሂደት ምን መምሰል እንዳለበት ልምድ ይገኝባቸዋል፡፡

## የትምህርት ፋይናንስ ዳሰሳ

ከ1995 -2004ዓ.ም በነበሩት ዓመታት ውስጥ መንግሥት ለትምህርት ያወጣው ወጭ በ70% ማደጉን ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው በዋናነት በዘርፉ መስፋፋት፣ ማለትም ከ1ኛ -12ኛ ክፍል የነበረው አጠቃላይ የተማሪዎች ብዛት ከ10 ሚሊዮን ወደ 19 ሚሊዮን ከፍ ማለቱና በዚህ ጊዜ ውስጥ የመምህራን ደሞዝ በእጥፍ ማደጉ ነው፡፡ ከ2002 -2004 በተካሄደው የሶስተኛው ትውልድ ዩኒቨርስቲዎች ግንባታ ከፍተኛ የሆነ የካፒታል በጀት ተመድቧል፡፡ ከ1988-1996 ዓ.ም በነበረው ጊዜ ውስጥ በየዓመቱ 20% የክል የመንግስት በጀት ትምህርት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ እነዚህ አሀዞች ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ጋር ሲነፃፀሩ የተሻሉ ሆነው እናገኛቸዋለን፣ ለምሣሌ ያክል ሩዋንዳ፣ ኬንያና ታንዛኒያ የትምህርት በጀታቸው  ከ17 እስከ 18 % ሲሆን ከሠሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገሮችም  በአማካይ 19%ነው፡፡

ቀደም ሲል የመደበኛና ካፒታል የትምህርት በጀት እያንዳንዳቸው እኩል 20 በመቶ ድርሻ የነበራቸው ሲሆን፣ በሂደት በአሁኑ ወቅት ለትምህርት ከሚመደበው 33 በመቶ በጀት 13 በመቶ ብቻ ለካፒታል ወጪ የተመደበ ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ከትምህርት መስፋፋት ጋር የዘዋዋሪ በጀቱ አየጨመረ እንደሄደና ከትምህርት ውጭ ያሉት ሴክተሮች (ለምሣሌ የትራንስፖርት ሴክተር) ባደጉ ቁጥር የትምህርት ካፒታል በጀት እየቀነሰ እንደሚሄድ ነው፡፡

ለትምህርት የሚመደበው ተዘዋዋሪ ወጪ ከፍ ማለቱ በየወረዳዎቹ ያለው የትምህርት ወጪ ድርሻ አመላካች ነው፡፡ (አጠቃላይ 60 በመቶ የሚሆነው ለደመወዝ የሚወጣ ሲሆን የትምህርት ድርሻው ወደ 79% አድጓል)፡፡

በየደረጃው ለትምህርት የሚሰጠው ትኩረት እንዳለ ሆኖ፣ በቤተሰቦች የሚታየው የትምህርት ፍላጐት ማደግ፣ የመፃህፍትና ሌሎች አገልግሎቶች ዋጋ መናር፣ መምህራን በሥርዓቱ ውስጥ ለማቆየት የሚያስፈልገው ወጭ መጨመር ሲታይ በቀጣይ ጊዜያት የትምህርት ሴክተሩ የፋይናንስ ተግዳሮቶች ሊያጋጥሙት ይችላሉ፡፡

የፋይናንስ አመዳደቡን በየንዑስ ሴክተሩ ዘርፍ ስንመለከት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለውጥ አልታየበትም፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወጪ ግን ጨምሯል፡፡ የሁለተኛ ትውልድ ዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ከተጀመረበት 1991 ዓ.ም ጀምሮ ከፍተኛ ወጪ የተደረገበት ንዑስ ሴክተር የከፍተኛ ትምህርት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ትምህርት ከአጠቃላዩ የትምህርት ወጪ 42 በመቶ ድርሻ ያለው ሲሆን፣ ይህም የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ድምር ወጪ ጋር እኩል ያደርገዋል(የአንደኛ ደረጃ ድርሻ 32 በመቶ ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ 10% ነው)፡፡ በከፍተኛ ትምህርት ለአንድ ተማሪ የሚደረገው መደበኛ ወጪ ከአንደኛ ደረጃ ተማሪ በ26 እጥፍ ከሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ወጪ ደግሞ በ10 እጥፍ ይበልጣል፡፡

በነዚህ ጊዜያት የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ድርሻ ከ11 በመቶ ወደ 6 በመቶ የወረደ ሲሆን፣ ለልዩ ፍላጐት ፣ ለጐልማሶችና ለአማራጭ ትምህርት የሚመደበው ወጪ በጣም ዝቅተኛ መስሎ ቢታይም ፣ ለነዚህ ዘርፎች የሚውለው አንዳንዱ ወጪ በአንደኛ ትምህርት ወጪ ጋር አብሮ ላይ የተጠቃለለ ይመስላል፡፡ በመደበኛ በጀት ወጪ ከፍተኛውን ድርሻ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የያዘ ሆኖ (45%) ከፍተኛ ትምህርት 25% ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት 12% ቴክኒክና ሙያ ደግሞ 5% ድርሻ አላቸው፡፡

ከመደበኛው በጀት ውስጥ ለደመወዝ የሚከፈለው ፣ በአንደኛ ደረጃ 90 በመቶ በሁለተኛ ደረጃ ከ80 በመቶ በላይ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት 50 በመቶ ፣ በከፍተኛ ትምህርት ደግሞ ከ40 በመቶ በታች ነው፡፡ በከፍተኛ ትምህርት ከ50 በመቶ በላይ በጀት ከትምህርት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ለሌላቸው ለምግብ ለመኝታና ለሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮች የሚመደብ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ጐልቶ የሚታየው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በጀት ቀስ በቀስ በሁለተኛ ደረጃና በከፍተኛ ትምህርት እድገት ምክንያት በመቀነስ ላይ ይገኛል፡፡

## ዋጋን ለመተመን የወጡ መስፈርቶች

### ለቅበላና ውስጣዊ ብቃት

የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ወጭዎች በዋና የፖሊሲ አላማዎች በመመስረት ቅበላና የውስጥ ብቃት ግቦችን ያማከሉ ናቸው፡፡ መንግሥት በ2025 እ.ኤ.አ ሀገሪቱ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ታችኛው ጎራ ለማሠለፍ ባለው ራዕይ መሠረት የተለያዩ ዓላማዎች ተዘርዝረዋል፡፡ እነዚህም፡- በትግበራው ዘመን መጨረሻ  የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ሙሉ ለሙሉ ተደራሽ ማድረግ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በማስፋፋት በ2025 ለሁሉም ለማዳረስ ፣ እንዲሁም በቅድመ ምረቃም ይሁን በቴክኒክ ስልጠና የመካከለኛና ከፍተኛ ሙያ ያላቸው እና ለመካከለኛ ኢኮኖሚ ግንባታ ብቁ የሆኑ ዜጎችን ማፍራት ይገኙበታል፡፡

በቅድመ መጀመርያ ፣ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት፣ በሁለተኛ ደረጃ፣ በቴ/ሙ/ትምህርት እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ሊኖር የሚችለው የተማሪዎች ቅበላ በአብዛኛው ከታች ክፍል ባለው ቅበላ ይወሰናል፡፡ በወቅቱ ባለው ፖሊሲ መሠረት ከ8ኛ-9ኛ ክፍል የሚደረገው የክፍል ዝውውር በተማሪዎች ብዛት የሚወሰን ሲሆን፣ የ10ኛ ክፍል መልቀቂያ ከወሰዱ በኋላ በቴ/ሙ/ትምህርት ወይም በመሰናዶ ትምህርት ይመደባሉ፡፡ ቅድሚያ በተሰጣቸው ፕሮግራሞች ዝርዝር እንደተብራራው ሁሉም ግቦች በግልጽ ሰፍረዋል፡፡ በጣም አስፈላጊ የሆኑት እዚህ በዝርዝር በድጋሚ ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ግቦች በ2012 ዓ.ም ይሣካሉ ተብለው የተያዙ ናቸው፡፡

- የቅድመ መጀመሪያ ጥቅል የተማሪ ቅበላ 80% ይደርሣል
- የ1ኛ ክፍል ጥቅል ቅበላ 112% ይደርሳል
- ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል ጥቅል ቅበላ 115% ይደርሳል
- ከ5ኛ -8ኛ ክፍል ጥቅል ቅበላ 95% ይደርሳል
- ከ9ኛ -10ኛ ክፍል ጥቅል ቅበላ  74% ይደርሳል
- ከ1ኛ ክፍል አቋርጠው የሚወጡ ተማሪዎች  5% ይደርሳል

- ❖ ከሌሎች ክፍሎች አቋርጠው የሚወጡ ተማሪዎች 2% ይደርሳል
- ❖ በአጠቃላይ ትምህርት በሁሉም ክፍሎች የሚደግሙ ተማሪዎች 2% ይደርሣል
- ❖ ከ10ኛ ክፍል ፈተና በኋላ 20% ተማሪዎች ወደ መሠናዶ ትምህርት የሚገቡ ሲሆን ቀሪዎቹ በመምህራን ትምህርት ወይም ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሊቀጥሉ ይችላሉ፡፡
- ❖ የ2 አመት የጎልማሶች ተግባራዊ ስልጠና የሚወስዱ ሰዎች ድርሻ 100% ይደርሣል
- ❖ ከ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ 90% ወደ ዩኒቨርስቲ ይገባሉ፡፡

**በሀብት አጠቃቀም ታሳቢ የተደረጉ መለኪያዎች**

በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃ ግብር የሚኖሩት ቀጣይ የትምህርት ማስፋፊያና ማሻሻያ ሥራዎች ወጪ በቀጣይነት በሥራ ላይ የምናውለው የሰው ሀብትና የቁሳቁስ ሀብት ደረጃን መሠረት ያደረገ ሲሆን ዋና ዋናዎቹም ከዚህ በታች ተመልክተዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 21፡ ወጭን ለማቀድ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ልኬታዎች**

| ደረጃ | ልኬታ |
|---|---|
| የቅድመ መጀመሪያ ትምህርት | |
| የተማሪዎች ብዛት (በየክፍሉ) | 50 |
| በ2012 ብቃታቸው የተረጋገጠ መምህራን በመቶኛ | 100% |
| መንግሥታዊ ባልሆኑ መዋዕለ ህፃናት የሚገቡ በመቶኛ | 50% |
| **የአንደኛ ደረጃ ትምህርት** | |
| መንግሥታዊ ባልሆኑ ትምህርት ቤቶች የሚገቡ በመቶኛ | 4% |
| የተማሪዎች ብዛት (በየክፍሉ) | 50 |
| የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ተማሪዎች ብዛት (በየአስተባባሪው) | 30 |
| በሁለት ፈረቃ የሚያስተምሩ | 35% |
| በወጪ ቅነሳ የተሰሩ የመማሪያ ክፍሎች በመቶኛ | 70% |
| በ2012 ብቃታቸው የተረጋገጠ መምህራን በመቶኛ | 100% |
| **የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት** | |
| መንግስታዊ ባልሆኑ ትምህርትቤቶች የሚገቡ በመቶኛ | 6% |

| | |
|---|---|
| በአንድ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ብዛት | 40 |
| አዳሪ ተማሪዎች ብዛት በመቶኛ | 4% |
| **የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት** | |
| የሠለጠኑ አስተባባሪዎች በመቶኛ | 80% |
| ወደ ማህበረሰብ ትምህርት ማዕከል ያደጉ የጎልማሶች ትምህርት ማዕከላት በመቶኛ | 50% |
| **ቴክኒክና ሙያ ትምህርት** | |
| በ1/2፣ 3/4 እና 5ኛ ደረጃ ያለው የተማሪዎች ስብጥር | 18:3:1 |
| መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት የሚገቡ በመቶኛ | 20% |
| የአሠልጣኝና ተማሪ ስብጥር (መደበኛ ስልጠና) | 25 |
| **ከፍተኛ ትምህርት** | |
| መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት የሚገቡ በመቶኛ | 33% |
| የተማሪ መምህር ስብጥር | 1፣19 |

### ለወጭ ታሣቢ የተደረጉ

ሁሉም ወጭዎች ታሳቢ የሆኑት በኢትዮጵያ ብር ነው፡፡ ይህ እቅድ ይፋ ሲሆን አንድ የአሜሪካ ዶላር በ20 የኢትዮጵያ ብር በመመንዘር ነው፡፡ ሁሉም ወጭዎች የ2008 ዓ.ም ዋጋን በመንተራስ የተሰሉ ሲሆን የነበረውን ግሽበት ከግምት ውስጥ አስገብተዋል፡፡ አብዛኛውን ድርሻ የሚወስደው የመምህራን ደሞዝ ስሌት መሠረት የደረገው በቅርቡ በ2007 ዓ.ም የመንግሥት የትምህርት ወጪ ዳሰሳ ላይ ከተወሰደ መረጃ ነው፡፡ የደሞዝ ወጭን በተመለከተ (መምህራንም ሆኑ ሌሎች ደሞዝተኞች)፣ የደመወዝ ማስተካከያ ጭማሪ ይኖራል በሚል ታሳቢ የተወሰደ ነው፡፡


### የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር ጠቅላላ ወጭ

ከታች የሚገኘው ሠንጠረዥ የመርሃግብሩን አጠቃላይ ወጭ፣ በየንዑስ ሴክተሩ ያለውን ወጭ ከፋፍሎ ያስቀመጣል፡፡ አጠቃላይ የ5 ዓመቱ ወጭ 454 ቢሊዮን ብር እንደሚሆን ተገምቷል፡፡ ይህ ወጭ ከ2008 እስከ 2012 ዓ.ም እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ጭማሪው የትምህርት ስርዓቱ በተስፋፋ ቁጥር (በተለይም የከፍተኛ ትምህርትና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት) በሚኖረው የመደበኛ በጀት እድገት ምክንያት የሚፈጠር ነው፡፡

**ሠንጠረዥ 22፡ የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር አጠቃላይ ወጭ (በሚሊዮን ብር)**

| | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አጠቃላይ ወጭ | 73,635 | 81,350 | 91,831 | 98,781 | 108,225 | 453,822 |

**ሠንጠረዥ 23፡ የ5ኛ የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር አጠቃላይ ወጭ በንዑስ ሴክተር በአመት እና በፕሮግራሙ ቆይታ (በሚልዮን ብር)**





| | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|
| አስተዳደር (በሚል ኢ.ት.ብር) | 4197 | 4989 | 6026 | 6901 | 8017 |
| ከፍተኛ ትምህርት (“ “) | 24649 | 28089 | 30925 | 33897 | 34830 |
| ቴክኒክና ሙያ (“ “) | 14624 | 14889 | 15184 | 15566 | 16340 |
| አጠቃላይ ወጭ (“ “) | 30165 | 33383 | 39697 | 42416 | 49038 |

የንዑስ ሴክተሮች አጠቃላይ ወጪ ከ2008 እስከ 2012 እየጨመረ የሚሄድ ሲሆን፣ ለዚህም ምክንያቱ በሁሉም መስክ የተማሪ ቅበላ ሲያድግ የሚኖረው የካፒታል እና መደበኛ በጀት መጨመር ነው፡፡ በዚያው መጠን በትምህርት ቤቶች ኢንስፔክሽን በመምህራን ፈቃድ አሰጣጥና አስተዳደር፣ እንደዚሁም በመሰል ምክንያቶች የአስተዳደር በጀቱ አጥፍ ያክል ይጨምራል፡፡ በአጠቃላይ፣ የትምህርት በጀቱ በአጠቃላዩ የትምህርት ንዑስ ሴክተር (የቅድመ 1ኛ ደረጃ ፣ የ1ኛ ደረጃ፣ የ2ኛ ደረጃ፣ የጐልማሶችና የመምህራን ኮሌጆች) 30 ሚሊዮን ወደ 50 ሚሊዮን ያድጋል፡፡ ይህ የሚያሳየው፣ የትምህርት ሂደቱ ፈጣን እንደሚሆንና አንደኛ ክፍልን የሚያጠናቅቁና በሁለተኛ ደረጃ አጠቃላይ ትምህርት የሚሳተፉ

ተማሪዎች ቁጥር “ሁሉም ይማር” በሚል የተቀመጠው አለማቀፋዊ መስፈርት እውን ለማድረግ የሚደረገውን ጉዞ የሚያመላክት ነው፡፡

**ሠንጠረዥ 24፡ በ5ኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር የየንዑስ ሴክተር ድርሻ (በዓመት)**





| | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | 5ኛ የት/ዘ/ል/ፕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አስተዳደር (% ዘርፍ) | 6% | 6% | 7% | 7% | 7% | 7% |
| ከፍተኛ ትምህርት (% ዘርፍ) | 33% | 35% | 34% | 32% | 34% | 34% |
| ቴክኒክና ሙያ (% ዘርፍ) | 20% | 18% | 17% | 16% | 17% | 17% |
| አጠቃላይ (% ዘርፍ) | 41% | 41% | 13% | 43% | 43% | 43% |

በጥቅል የበጀት ፍላጎት ውስጥ የሚታዩት ለውጦች ትንሽ ቢሆኑም፣ በእያንዳንዱ ንዑስ ሴክተር ውስጥ ግን ትርጉም ያለው የድርሻ መጠን ያመጣሉ፡፡ አጠቃላይ ትምህርት ትልቁን የበጀት ድርሻ የሚወስድ ሲሆን እስከ 2012 ዓ.ም ባለው ጊዜ እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ይህ ማለት፣ የፕሮግራሙ 43% በጀት ለአጠቃላይ ትምህርት የተመደበ ነው፡፡ የቴክኒክና ሙያ እና የከፍተኛ ትምህርት ድርሻ ከ2008 እስከ 2012 ባለው ጊዜ በትንሹ እየቀነሰ ቢሄድም አጠቃላይ የዓመቱ በጀት ግን ይቀንሳል ማለት አይደለም፡፡ እንዲያውም ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ለዩኒቨርስቲ የሚመደበው በጀት በየአመቱ ይጨምራል፡፡ ስለዚህ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና የዩኒቨርስቲዎች በጀት ያነሰ ነው መባሉ፣ የአጠቃላይ ትምህርት ፈጣን እድገት የሚያስከትለውን የሃብት /በጀት ፍላጐት ለማሳየት ነው፡፡

የከፍተኛ ትምህርት በጀት በትንሹ ቢቀንስም የፕሮግራሙን 34% በጀት ድርሻ ይወስዳል፡፡ ቴክኒክና ሙያ 17% አጠቃላይ ትምህርት ደግሞ 43% ድርሻ አላቸው፡፡ በሦስተኛውና አራተኛው የትምህርት ዘርፍ ፕሮግራሞች የታየውና በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ የሚጠበቀው የከፍተኛ ትምህርት መስፋፋት ስትራቴጂካዊ የሆነ የፖሊሲ ምላሽ ያስፈልገዋል፡፡

**በሠንጠረዥ 25፡ የየአመቱ የአጠቃላይ ትምህርት ድርሻና የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ መርሃግብር ድርሻ**





| | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | 5ኛ የት/ዘ/ል/ፕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ጉልማሶች(% ንዑስ ዘርፍ) | 7% | 7% | 7% | 6% | 5% | 6% |
| የመ/ራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ (% ንዑስ ዘርፍ) | 4% | 4% | 4% | 4% | 3% | 4% |
| ሁለተኛ ደረጃ (% ንዑስ ዘርፍ) | 22% | 23% | 24% | 28% | 30% | 26% |
| አንደኛ ደረጃ (% ንዑስ ዘርፍ) | 64% | 62% | 60% | 54% | 50% | 57% |
| የቅድመ 1ኛ ደረጃ (% ንዑስ ዘርፍ) | 3% | 4% | 6% | 8% | 11% | 7% |

ለትምህርት ዘርፍ ከተመደበው ጠቅላላ ድርሻ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ከ3 በመቶ ወደ 22 በመቶ በማደግ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ደግሞ ከ11 በመቶ ወደ 30 በመቶ ከፍ በማለት ከፍተኛ የሆነ ድርሻ እንዲኖራቸው ሆኗል፡፡ ለነዚህ ደረጃዎች የሚሰጠው ትኩረት ሲጨምር፣ በአንፃሩ የሌሎቹ ድርሻ ይቀንሳል፡፡ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ መምህራንን የሚያስለጥኑት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች በጀት በየአመቱ እየጨመረ የሚሄድ ቢሆንም ካጠቃላይ ትምህርት የሚኖረው ድርሻ በትንሹ ከ4 በመቶ ወደ 3 በመቶ ይወርዳል፡፡ በተመሣሣይ፣ በዚህ ፕሮግራም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ድርሻ ከ64 በመቶ ወደ 57

በመቶ፣ የጐልማሶች ትምህርት ደግሞ ከ7 በመቶ ወደ 5 በመቶ ይወርዳል (የሚመደብላቸው ሃብት እንዳለ ሆኖ)፡፡

በመደበኛና ካፒታል በጀት በመለየት አመዳደቡን ስንመለከት፣ ለከፍተኛ ትምህርት የሚመደበው የህንፃ ግንባታ የካፒታል በጀት ከፍ ያለ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ለከፍተኛ ትምህርት ከሚመደበው በጀት አንድ ሦስተኛው ለማስፋፊያ የሚውል ማለትም፣ አስራ አንድ ዩኒቨርሲቲዎችን እና በየወረዳው አንድ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤትን ለመክፈት የሚውል ነው፡፡ በአጠቃላይ ትምህርት አብዛኛው በጀት የሚመደበው ለደመወዝ ነው፡፡ በተጨማሪም የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፋሲሊቲዎች ማስፋፊያ በጀት (የውሃ፣ ጽዳት ወዘተ ጨምሮ) ለአጠቃላይ ትምህርት ከተመደበው በጀት የአንድ ሦስተኛ ድርሻ አለው፡፡

**ሠንጠረዥ 26፡ በዕቅድ ዘመን የካፒታልና መደበኛ በጀት (በየደረጃው በመቶኛ)**




<u>**የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር ፋይናንስ**</u>

<u>**የመንግሥት በጀትና የፋይናንስ ክፍተት**</u>

የአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር አጠቃላይ ወጭ በ2008 ዓ.ም ከሚኖረው 74 ቢሊዮን ብር በ2012 ዓ.ም 108 ሚሊዮን ብር ይደርሳል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ እነዚህ ወጭዎች ከሀገር


ውስጥ እና ከውጭ በሚገኝ የገንዘብ ምንጭ ይሸፈናሉ፡፡ በዋናነት መንግስት በፌዴራልና በክልል በሚመደብ በጀት ብዙውን ድርሻ ይይዛል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ መንግሥት በ2008 ዓ.ም ለትምህርት የሚመድበው በጀት 59 ቢሊዮን ብር ሲሆን ይህ እያደገ በ2012 ዓ.ም ወደ 95 ቢሊዮን ብር ያሻቅባል (ይግ ግምት የተወሰደው በየአመቱ የ10% እድገት ይኖራል፡፡ ከዚህም ውስጥ ለትምህርት 24 እስከ 25 በመቶ ይመደባል ከሚል ስሌት በመነሳት ነው)፡፡ በዚህ መሠረት ፕሮግራሙን ለማስፈፀም ሊኖር የሚችለው የፋይናንስ ክፍተት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 27፡ በእያንዳንዱ የፕሮግራም አመት ሊኖር የሚችለው የፋይናንስ ክፍተት (በሚሊዮን )**

| | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | ጠቅላላ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| (ሀ) አጠቃላይ ወጭ | 73635 | 81350 | 91831 | 98781 | 108225 | 453822 |
| (ለ) የመንግሥት በጀት | 58838 | 66944 | 76102 | 86445 | 95362 | 383691 |
| ልዩነት (ሀ-ለ) | 14796 | 14406 | 15729 | 12336 | 12863 | 70131 |

አጠቃላይ የፋይናንስ ክፍተቱ 70 ቢሊዮን ብር ሲሆን በየዓመቱ ሲከፋፈል ይሄንኑ ድምር እናገኛለን፡፡ አመታዊ ክፍተቱ ከ4.8 ቢሊዮን ብር ወደ 15.7 ቢሊዮን (በ2010 ዓ.ም) ከፍ ሲል በመርሃግብሩ የመጨረሻ አመት ወደ 12.9 ቢሊዮን ብር ይወርዳል፡፡

**ሠንጠረዥ 28፡ የአምስተኛው ትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር ፋይናንስ ክፍተት (በሚሊዮን ብር እና በመቶኛ)**




| | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 |
|---|---|---|---|---|---|
| የገንዘብ ክፍተት (ሚ.ብር) | 14796 | | 15729 | 12336 | 12863 |
| የመንግሥት በጀት (ሚ.ብር) | 58838 | 66904 | 76102 | 86445 | 95362 |
| የገንዘብ ክፍተት (ከስፈላጊው%) | 20% | 18% | 17% | 12% | 12% |

በአጠቃላይ እቅዱ በአማካይ የ15 በመቶ ክፍተት የሚኖር ሲሆን፣ በመጀመሪያው አመታት የሚኖረው 20 በመቶ ክፍተት በመጨረሻ ሁለቱ ዓመታት ወደ 12 በመቶ ይወርዳል፡፡ በመጀመሪያ የእቅዱ አመታት በሚኖሩት የካፒታል ግንባታዎች ምክንያት በመጀመሪያዎቹ አመታት ክፍተቱ ከፍ ብሎ ይታያል (በተለይም አዳዲስ ዩኒቨርስቲዎች የሚገነቡ በመሆናቸው)፡፡ በሌላ በኩል፣ በመጨረሻዎቹ የፕሮግራሙ አመታት መንግሥት ጠንካራ የበጀት አመዳደብ ይኖረዋል በሚል የክፍተት ልዩነቱ ዝቅ ይላል ተብሎ ተገምቷል፡፡

እቅዱ ከከፍተኛ ፍላጐት አንፃር የተመሠረተ ሲሆን፣ በጥንቃቄ የሚዘጋጅ የዋጋ እና የፋይናንስ አመዳደብን በመከተል ሦስት የፋይናንስ ምንጮችን ተጠቅሞ ግቦቹን ማሳካት ይቻላል፣ እነዚህም፡- (ሀ) መንግሥት (የክፍተት ልዩነቱ ላይ ተጽዕኖ ማድረግ የሚችል) (ለ) ለጋሽ አጋራትና መንግሥታዊ

ያልሆኑ ድርጅቶች (ክፍተቱን ለመሸፈን አቅም የሚፈጥሩ) (ሐ) የማህበረሰቡ አስተዋጽኦ (በተመሣሣይ መልኩ ክፍተት ለመሸፈን አቅም የሚፈጥር) ናቸው፡፡

<u>መንግሥት</u>

የትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲ ከወጣበት 1986 ዓ.ም ጀምሮ ሀገሪቱ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተራ እስክትመደብ ድረስ ትምህርት የመንግሥት ቀዳሚ ዘርፍ ሆኖ ይቀጥላል፡፡ የመንግሥት በጀት አመዳደብ (1) በአጠቃላይ ሀገራዊ እድገት (2) በዚህ የሀገራዊ ምርት እድገት ላይ መንግሥት በሚኖረው ድርሻ እና (3) መንግሥት ለትምህርት የሚመድበው የበጀት ድርሻ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

**አጠቃላይ ሀገራዊ እድገት፡-** ኢትዮጵያ ላለፉት አስር (10) ዓመታት 10% የሚደርስ ጠንካራ ሀገራዊ እድገት እንዳስመዘገበች የአለም ባንክ ፣ አለም አቀፍ የገንዘብ ተቋም እና የኢትዮጵያ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ይፋ ያደረጉ ሲሆን ይህ እድገት በፕሮግራሙ ዘመን እንደሚቀጥል ይገመታል፡፡

**የመንግሥት ገቢዎች በሀገራዊ እድገቱ ያላቸው ድርሻ፡-** የኢትዮጵያ የግብር አሰባሰብ ደካማ የነበረ ቢሆንም በቅርቡ ግን እየተሻሻለ መጥቷል፡፡ ይህ መሻሻል የታየው በጣም ጠንካራ የማዕከላዊ እና ክልላዊ የታክስ አስተዳደር አሠራሮች በመፈጠራቸውና የታክስ መሠረቱም እየሰፋ በመሄዱ ነው፡፡ በካፒታልና መደበኛ በጀት ቀስ በቀስ ያለ እድገት እየታየ ሲሆን ለአጠቃላዩ እድገቱ ታክስ ያለው ድርሻ በቁጥር ሲገለጽ 0.5% እና 1% (በተከታታይ) ነው፡፡ ይህ ለውጥ ሊመዘገብ የቻለው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጠንካራ የግብር አሰባሰብ አቅም እንዲፈጠር በመደረጉ ነው፡፡

**ለትምህርት ዘርፍ መንግሥት የሚሰጠው የበጀት ድርሻ፡-** ላለፉት አስር (10) ዓመታት ትምህርት ከ20-25 % የሚደርስ ድርሻ ነበረው፡፡ በቅርቡ ለትምህርት በተሰጠው ትኩረት ምክንያት ድርሻው ወደ 25% ያደገ ሲሆን በፌዴራል እና በክልል መንግሥታት መካከል የተፈጠረው ጠንካራ ፖለቲካዊ ትስስርም ለዚህ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ የትምህርት አቅርቦት ፍላጐት ከአካባቢ የሚጀምር ሲሆን የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ለዚህ ምላሽ ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡ በዕቅዱ የመጀመሪያ አመታት ለትምህርት 25% በጀት የተመደበ ሲሆን በአጠቃላይ በአምስቱ አመታት ደግሞ ከ24-25% ድርሻ ተሰጦታል፡፡ ከዋናው

የትምህርት በጀት በተጨማሪ፣ የፌዴራል መንግሥቱ "የምእተ አመቱ የልማት ግቦች ፈንድ" በሚል እስከ 2007 ያካሄደው የገንዘብ ድጐማ "ዘላቂ የልማት ግቦች" በሚል ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ ይህ ፈንድ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት ያስቻለ ሲሆን አሁንም ተጨማሪ የፋይናንስ ግብአት በመሆን ለአጠቃላይ ትምህርት የልማት ግቦች አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

### ለጋሽ አጋሮችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

የለጋሾች አስተዋጽኦ ከአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር ጋር እንዲሁም ከመንግሥት ተግባራት ጋር ሲቀናጅ  የፋይናንስ ክፍተቱን ይቀንሰዋል፡፡ መንግሥት ትምህርትን የሚደግፍ ተጨማሪ ግብአት በጥቅም ላይ በማዋል ስኬታማ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በአለፉት አምስት አመታት ለጋሾች ለትምህርት ያበረከቱት ፋይናንስ በዓመት 400 ሚሊዬን ዶላር (ስምንት ቢሊዮን ብር ያክል) ይሆናል (ለዋና ዋና ፕሮጀክቶች የተሰጠና በትምህርት የቴክኒክ ሥራ ቡድን (ETWG) አስተባባሪነት የተከናወኑ ሥራዎችን የተመለከተ ነው)፡፡ ይህ ገንዘብ ሲሰላ በዚህ እቅድ ውስጥ ከሚኖረው አመታዊ የፈንድ ክፍተት 50-60 በመቶ የሚያክል ነው፡፡ አዲስ ስለሚፈጠሩ ፕሮጀክቶች እርግጠኛ መሆን ባይቻልም፣ ብዙ ነባር ፕሮጀክቶች በቀጣይነት እየተካሄዱ በመሆናቸው ቢያንስ የዋና ዋና ለጋሾች እገዛ በአምስተኛው የትምህርት ልማት መርሃግብርም ይቀጥላል የሚል ግምት አለ፡፡

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከፌዴራል መንግሥቱ እውቅና ማግኘት ሳያስፈልጋቸው በመረጡት ክልል ሊሠሩ እንደሚችሉ ህጉ ይፈቅዳል፡፡ ይህ ህግ ክልሎች ካላቸው ስልጣንና ነፃነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው፣ በመላ አገሪቱ በትምህርት ሥራ ላይ ከ1000 በላይ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተሳታፊ ሲሆኑ ስለድርጅቶቹ በማዕከል ያለው መረጃ ውሱን መሆኑን ነው፡፡ በቀጣይ አምስት ዓመታት የሲቪል ማህበራት፣ እንደዚሁም ብሄራዊና አለማቀፋዊ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሥራዎቻቸውን በተቀናጀ መልክ እንዲያከናውኑና አላማዎቻቸውን ከአምስተኛው የትምህርት ሴክተር እቅድ ጋር እንዲያስተባብሩ መንግሥት ጥረት ያደርጋል፡፡ ይህ የተባበረ አካሄድ የፋይናንስ ክፍተቱን በመሙላት ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

## የማህበረሰብ አስተዋጽኦ

ሁሉም በነፃ የመማር እድል ይኑረው የሚል መርህ እያካሄድን ማህበረሰቡ በትምህርት ፈንድ ላይ ከፍተኛ የሆነ አስተዋጽኦ እንዲኖረው መጠበቅ ትክክል አይሆንም። በኢትዮጵያ፣ ማህበረሰቡ የመማርያ ክፍሎችን በመስራት ፣ እንደዚሁም በትምህርት አመራርና ውሣኔ ሰጭነትና በመሳሰሉት ትምህርት ነክ ጉዳዩች የመሳተፍ የቆዩ ባህል አለው። በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር ወቅት በሺዎች የሚቆጠሩ የመማርያ ክፍሎችና ትምህርት ቤቶች እንዲገነቡ መደረጋቸው በትምህርት ወጭዎች ዳሰሳ (Education public expenditure review) የተገለፀ ሲሆን፣ እነዚህ ግንባታዎች የተከናወኑት በመንግሥት ካፒታል ወጭ ብቻ አይደለም። አብዛኛዎቹ የአካባቢ ግንባታዎች የተካሄዱት በማህበረሰቡ ግንባር ቀደምትነትና በወረዳና ክልል ቢሮ ሠራተኞች ትብብር ነው። እንደ አራተኛው የትምህርት መርሃግብሩ ሁሉ፣ በአምስተኛው መርሃግብሩ ማህበረሰቡ በጉልበት በቁሳቁስና በተለያዩ የአይነት እገዛዎች ተሳታፊ እንደሚሆን ይጠበቃል።

በ2007ዓ.ም በወጣው የትምህርት ወጭዎች ዳሰሳ እንደተገለፀው፣ እያንዳንዱ ቤተሰብ ባማካይ ከአጠቃላይ ወጭው 7% ለትምህርት ያውላል ለትምህርት የሚደረገው ወጪ 1.6 በመቶ ከደመወዝተኛ ቤተሰብ፣ 0.7 ከመደበኛ ካልሆነ ዘርፍ፣ 0.2 በመቶ ደግሞ ከግብርና ሴክተር የተውጣጣ ነው። ይህ ሲደመር በአመት 2 ቢሊዮን ብር ያክላል፣ ይህ ደግሞ በዚህ እቅድ ከታየው ጠቅላላ የፋይናንስ ክፍተት ከ13 እስከ 16 በመቶ ይሆናል።

በአምስተኛው የትምህርት መርሃግብር ማህበረሰቡ ከገንዘብ ከቁሰቁስና ከጉልበት አስተዋጽኦ በተጨማሪ በትምህርት ቤት አመራርና አስተዳደር በባለቤትነት እንዲሳተፍ ይጠበቃል። በተጨማሪ፣ በተለይ መለስተኛ የመማሪያ ክፍሎችን ለመስራት ማህበረሰቡ በማቴሪያልና በጉልበት በማገዝ ለፋይናንሱ አስተዋጽኦ ያደርጋል፤ አቅም በፈቀደ መጠንም ከደሞዝ ነፃ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል። የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና የከፍተኛ ትምህርት ለመከታተል በሚደረጉት ክፍያዎች ተማሪዎችና ወላጆች አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል። እነዚህ ሁሉ የፋይናንሱን ክፍተት ለመሙላት አስተዋጽኦ አላቸው። ይህ

እንዳለ ሆኖ፣ ለምሣሌ በከፍተኛ ትምህርት በሥራ ላይ ያለው የወጭ መጋራት (cost sharing) ስርዓትን በማሻሻል በተማሪ በነፍስ ወከፍ የሚወጣውን ወጪ ለመሸፈን ይቻላል፡፡